ዐውደ ዕለት
ሀገረ ስብከት
ወጎችና
ሥርዓቶች

t.me/OLDBOOKSPDF
Scanned by CamScanner



ሚኻኤል፡ ሌርሞንቶቭ።

የዘመናችን፡ሰው።

ሞስኮ ።
የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

t.me/OLDBOOKSPDF

ተርጓሚው ፡ ደስታ ፡ ታደሰ ።

ሠዓሊው ፡ ኮንስታንቲኖቭ ።

የሌርሞንቶቭ ፡ የገጽ ፡ ሥዕል ፡ ሠዓሊው ፡

አስታፍዬቭ ።

(፲፰፻፻፹፫ ዓ. ም. እ. ኤ. አ.)

ЛЕРМОНТОВ

ГЕРОЙ НАШЕГО ВРЕМЕНИ

На амхарском языке

© የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ የአማርኛ ፡ ትርጉም ፡
እ. ኤ. አ. ፲፱፻፸፯ ዓ. ም. ።

በሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ታተመ ።

П 70301—399
014(01)—77 548—76

t.me/OLDBOOKSPDF

ማውጫ ።

የመጀመሪያው ፡ ክፍል ።

ገጽ ፤

ኧ ቤላ . . . . . ፲፩

ፔ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች . . . . ፶፯

የፔቾሪን ፡ ማስታወሻዎች ።

ኧ ታማን . . . . . ፩፳፬

ሁለተኛው ፡ ክፍል ።

የፔቾሪን ፡ ማስታወሻዎች ፡ መዝጊያ ።

ፔ ልዕልት ፡ ሜሪ . . . . . ፩፵፪

ፔ ባለዕጣ ፡ ሰው . . . . . ፪፻፳፩

መዝጊያ . . . . . ፪፻፵፯

የማንኛውም ፡ መጽሐፍ ፡ መግቢያ ፡ የመጀ
መሪያና ፡ በኋላም ፡ የመጨረሻ ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡
እሙን ፡ ነው ። ይህ ፡ መግቢያ ፡ የድርሰቱን ፡
ዓላማና ፡ ይዘት ፡ ይገልፃል ፤ ካለዚያም ፡ ለሒስ ፡
አቅራቢዎች ፡ ማስተባበያና ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ።
አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተራ ፡ አንባቢዎች ፡ የድ
ርሰቱን ፡ ይዘት ፡ የሚመለከቱት ፡ ከግብረ ፡
ገብና ፡ ከጋዜጣ ፡ አንፃር ፡ ስላልሆነ ፤ መግቢያ
ውን ፡ አያነቡትም ። በአገራችንም ፡ ያለው ፡
አቋም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስለሆነ ፡ ያሳዝናል ።
የአገራችን ፡ አንባቢ ፡ ገና ፡ ያልበሰለና ፡ የዋህ ፡
ሲሆን ፤ በድርሰቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ግብረ ፡
ገብ ፡ ካላየበት ፡ የተረት ፡ ድርሰት ፡ ፈጽሞ ፡
አይቀበልም ። ቀልዱ ፡ አይጥመውም ። ምፀቱም ፡
አይገባውም ። አንባቢያችን ፡ በጨዋ ፡
ሕብረተሰብና ፡ በደህና ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡
ግልጽ ፡ ዘለፋ ፡ ቦታ ፡ እንደሌለው ፡ ገና ፡ አያው
ቅም ። ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፤ በቅልምድና ፡
ጨርቅ ፡ የተሸፈነው ፤ በዓይን ፡ የማይታየው ፤
ከዘለፋ ፡ የተሳለ ፡ ስለት ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ገዳይ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ትም ፡ የተማለ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ያግማችሁ ፡ «የሰው ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ያክማ ፡ እያሆንም» ፡ ትሉኝ ፡ ይሆናል ። መልሴም ፡ በእርግጥ ፡ እና ንተ ፡ በሐዘንና ፡ በሕልማዊ ፡ ኑሮ ፡ የምታምኑ ፡ ከመሆናችሁ ፡ ለምን ፡ በፔቾሪን ፡ አታምኑም? የበለጠ ፡ አሰቃቂና ፡ አስቀያሚ ፡ ነገር ፡ በሐሳባችሁ ፡ ለማሰላሰል ፡ ከቻላችሁ ፡ ፔቾሪንን ፡ የመሰለ ፡ ባሕርይ ፡ በሐሳብ ፡ ደረጃ ፡ ለምን ፡ ሊኖር ፡ እይቻልም ፡ ትላላችሁ? ከምትፈልጉትና ፡ ከምትመኙት ፡ የበለጠ ፡ እውነት ፡ ይዞ ፡ ስለቀረበ ፡ አይደለምን? እላችኋላሁ ።

ግብረ ፡ ገብነት ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ የለውም ፡ ብላችኋል ። ይቅርታ ። ጣፋጭ ፡ መብላት ፡ ሕዝቡን ፡ እጅ ፡ እጅ ፡ ብሎታል ። ሆዱም ፡ ታሟል ። በእሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሆምጣጣ ፡ መድሐኒት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እውነት ... ይህም ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ደራሲ ፡ የሰው ፡ ልጅችን ፡ ጉድለት ፡ ለማረም ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ እትገምቱ ። ፈጣሪ ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ድንቁርና ፡ አድነው! ደራሲው ፡ የዘመኑን ፡ ሰው ፡ ለመኮሰል ፡ ስለፈለገ ፡ እነሆ ፡ ሥሎ ፡ አቀረበው ። ሥዕሉም ፡ እራሱ ፡ እንደሚገባውና ፡ እንዳየው ፡ ሲሆን ፡ በራሱ ፡ አዘውትሮ ፡ የደረሰበትን ፡ ሐዘን ፡ ያጠቃልላል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በሽታው ፡ ታይቷል ። እንዴት ፡ ለማዳን ፡ እንደሚቻል ፡ ግን ፡ ፈጣሪ ፡ ይወቀው ።

መሣሪያ ፡ እንደፈጠረ ፡ እያውቅም ። የአገራችን ፡ አንባቢ ፡ ከሁለት ፡ ጠበኛ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመጡ ፡ ዲፕሎማቶችን ፡ ውይይት ፡ የሚሰማ ፡ ከገጠር ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ ይመስላል ። ሁለቱ ፡ ዲፕሎማቶች ፡ የራሳቸውን ፡ ወዳጅነት ፡ ለማጠንከር ፡ ሲሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ መንግሥታቸውን ፡ የሚያታልሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ያምናል ።

ይህች ፡ መጽሐፍ ፡ አንዳንድ ፡ አንባቢዎች ፡ እንዲሁም ፡ ያንዳንድ ፡ መጽሔቶች ፡ ሐሰ ፡ አቅራቢዎች ፡ በድርሰቱ ፡ የተጸፈው ፡ ቃል ፡ ቢቃል ፡ እንደሚገባቸው ፡ በቅርቡ ፡ አሳይታለች ። አንዳንዶች ፡ ይህ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ የጐደለው ፡ ተዋናይ ፡ የዘመናችን ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ ክፉኛ ፡ ሲቀየሙ ፤ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፤ ደራሲው ፡ የራሱንና ፡ የጓደኞቹን ፡ ሥዕል ፡ ነው ፡ ቀርጾ ፡ ያቀረበው ፡ ብለዋል ። የቆየና ፡ አሳዛኝ ፡ ቀልድ ፡ ነው! ሆኖም ፡ በሩሲያ ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ቀልድ ፡ ሌላ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ በአዲስ ፡ መለወጡ ፡ አይቀርም ። በኛ ፡ ዘንድ ፡ የተረት ፡ ተረት ፡ ሆኖ ፡ ሊነገር ፡ የሚገባው ፡ ከግለሰብ ፡ ሐሰ ፡ ያመለጥን ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የተከበራችሁ ፡ ጌቶች! «የዘመናችን ፡ ሰው» ፡ በእርግጥም ፡ ሥዕል ፡ ነው ። የአንድ ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ አይደለም ። ይህም ፡ ከመላው ፡ የዘመናችን ፡ ትውልድ ፡ ጉድለቶች ፡ ተጠራ

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያው ክፍል።

t.me/OLDBOOKSPDF

፫

በላ።

ከብፍሊስ ፡ የተዘረጋውን ፡ ጥርጊያ ፡ መን
ገድ ፡ ያገኙ ፡ ጉዞዉን ፡ ጀመርኩ ። ይገርው ፡
የምንዘውም ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ ሻንጣ ፡
ግማሹን ፡ የሞላው ፡ ስለጂዎርጂያ ፡ የሚያስረዱ ፡
የጉዞ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ነበሩ ። ከዚያ ፡ ሁሉ ፡
መዘከር ፡ ሁሉም ፡ ጠፍቶ ፡ ለእኔ ፡ የተረፈኝ ፡
ሻንጣውና ፡ አንዳንድ ፡ መታሰቢያዎች ፡ ብቻ ፡
ናቸው ። ለእናንተ ፡ ግን ፡ ታሪኩ ፡ እንዳይቸ
ካችሁ ፡ መጥፉቱ ፡ ሳይበጃችሁም ፡ አይቀር ።
መደኩይሻኡር ፡ ሸለቆ ፡ ስጠጋ ፡ ፀሐይዋ ፡
በረዶ ፡ ባለበሰው ፡ ኮረብታ ፡ ስር ፡ ተሸሽጋለች ።
ሳይመሽ ፡ ኮይሻኡር ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡
እንድንደርስ ፡ የሠረገላ ፡ ነጂው ፡ አሴቲያን ፡
ጮኽ ፡ ብሎ ፡ በማንኮረኮር ፡ ፈረሱን ፡ ሱ!
ሱ! እያለ ፡ ያጣድፈው ፡ እንደነበር ፡ ትዝ ፡ ይለ
ኛል ። መቼም ፡ በእውነቱ ፡ የዚያን ፡ የሸለቆ ፡
የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ ለመግለጽ ፡ ቃላት ፡ ያጥሩ
ኛል ። አካባቢው ፡ በሙሉ ፡ በተዋቡ ፡ ተራራ
ዎች ፡ ተከቧል ። በተራራዎቹ ፡ ደረት ፡ የቆሙት ፡
ቋጥኝ ፡ ድንጋዮች ፡ በጋና ፡ ክረምት ፡ ቅጠላቸው
ን ፡ በማይጥሉ ፡ በአረንጓዴ ፡ የልደት ፡ ዛፎችና ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ከኋላችን ፡ በአራት ፡ በሬዎች ፡ የሚጐተት ፡ ሠረገላ ፡ ብዙ ፡ እቃዎችን ፡ ተጭኖ ፡ ያለምንም ፡ ችግር ፡ ከች ፡ አለ ። በዚህ ፡ ተገርሜ ፡ ገልመጥ ፡ ስል ፡ ባለቤቱ ፡ በብር ፡ በተሰራው ፡ የካባርዲያን ፡ ፒፓው ፡ እያጨሰ ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ከኋላ ፡ ኋላ ፡ ሲራመድ ፡ አየሁት ። የለበሰው ፡ የመኰንን ፡ ኮት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ማዕረጉ ፡ ተነስቷል ። በእናቱ ፡ ላይ ፡ የጠጉራም ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጓል ። ከሩቁ ፡ ሲመለከቱት ፡ ሐምሳ ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። የካውካሰስ ፡ ፀሐይ ፡ ለእሱ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ እንዳልሆነ ፡ ጠይም ፡ ፊቱ ፡ ይመሰክራል ። ያለጊዜው ፡ የሸበተው ፡ ሪዙ ፡ ነቃ ፡ ካለው ፡ ሰውነቱ ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ አይጣጣምም ። ጠጋ ፡ ብዬ ፡ እጅ ፡ ነሳሁት ። በእንደበቱ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠኝ ፡ የሰላምታዬን ፡ እጸፋ ፡ በእንገቱ ፡ መልሶ ፡ ፒፓውን ፡ ማጤስ ፡ ቀጠለ ።

«አ፡ስዎም ፡ እንደኔው ፡ መንገደኛ ፡ መሆንዎ ፡ ነው፡» ብለው ፡

«አዎን» ፡ ለማለት ፡ ራሱን ፡ ደፋ ፡ አደረገው ።

«ወደስታቭሮፖል ፡ ነው ፡ የሚያመሩት፡»

«አዎን ፡ ጌታዬ ... የመንግሥት ፡ እቃ ፡ ይገር ፡ ነው ፡ የምጓዘው ፡» ሲል ፡ መለሰልኝ ።

«አረ ፡ እባክዎን ፡ ግራ ፡ የገባኝ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ እቃዎን ፡ አራት ፡ በሬዎች ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ተሸክመው ፡ ሲወጡ ፡

ቁጥቋጦች ፡ ተለብጠው ፡ ይታያሉ ። በጕርፍ ፡ የተቦረቦሩት ፡ ድንጋዮች ፡ ፈሰሳቸው ፡ በቢጫ ፡ ቀለም ፡ ተለድሏል ። ከበላያቸው ፡ የበረዶ ፡ ክምችት ፡ ይታያል ። ከበታቹ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ የለሽ ፡ ወንዝ ፡ ከሸለቆው ፡ እየደነፋ ፡ ወጥቶ ፡ ከአራግቫ ፡ ወንዝ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ይፈላል ። ከሩቁም ፡ ሁኖ ፡ ሲታይ ፡ የወንዙ ፡ ቀለም ፡ ወርቀ-ዘቦ ፡ ሆኖ ፡ ላዩ ፡ ግን ፡ የአባብ ፡ ጀርባ ፡ ይመስላል ።

ኰይሻኡር ፡ ተራራ ፡ ስር ፡ ስንደርስ ፡ አንዲት ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ መሳይ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ አግኝተን ፡ ቆም ፡ አልን ። አንድ ፡ ሐያ ፡ የሚሆኑ ፡ የጂዎርጂያ ፡ ተወላጆችና ፡ ተራራ ፡ ወጪዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ያውካካሉ ። አለፍ ፡ ሲሉ ፡ ግመል ፡ የጫኑ ፡ መንገደኞች ፡ ሰፍረዋል ። ፀደይ ፡ ገብቶ ፡ መራቱን ፡ በረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ ስለነበረ ፡ ሰረገላውን ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ለማድረስ ፡ በሬ ፡ መከራየት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። ርቀቱ ፡ ግን ፡ ከሁለት ፡ ቨርስታ ፡ አይበልጥም ።

ስድስት ፡ በሬዎችና ፡ ብዙ ፡ የአሴቲያን ፡ ተወላጆች ፡ ከመከራየት ፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ አልነበረኝም ። አንደኛው ፡ የሐገሬው ፡ ተወላጅ ፡ ሻንጣውን ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ፊጥ ፡ አድርጐ ፡ ሲሄድ ፡ ሌሎቹ ፡ በሬዎችን ፡ መርዳት ፡ ጀመሩ ። ይሁንና ፡ ከሥራቸው ፡ ጫጫታቸው ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መቼም ፡ አውቴአቸዋለሁ ። ሊያታለሉኝም ፡ አይችሉም!»

«በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሲያገለግሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆነዎታል?» ብዬ ፡ ብጠይቅ ፡ ቀና ፡ እንደ ማለት ፡ ብሎ ፡

«አዎን ። አሌክሴይ ፡ ፔትሮቪች* ፡ እዚህ ፡ ከንበሩበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ አለሁ ። እሳቸው ፡ ወደጠረፉ ፡ ተሹመው ፡ ሲመጡ ፡ ምክትል ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነበርኩኝ ። በተራራው ፡ አድመኞች ፡ ላይ ፡ በመዝመቴ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ አግኝቻለሁ ።»

«አሁንስ?»

«አሁንማ ፡ በሶስተኛው ፡ ባታሊዮኑ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የማገለግለው ። እርስዎስ?»

እኔም ፡ በተራዬ ፡ ማንነቴን ፡ አጫወትኩት ።

ንግግሬን ፡ እንደጨረስኩ ፡ በዝምታ ፡ ጉን ፡ ለጉን ፡ ሁነን ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጠልን ። ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ስንደርስ ፡ የበረዶው ፡ ብዛት ፡ ከገመትነው ፡ በላይ ፡ ሁኖ ፡ አገኘነው ። በደቡብ ፡ አካባቢ ፡ ልማድ ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ የቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ወዲያውኑ ፡ በጨለማ ፡ ተተካ ። በበረዶ

---

*የርሞሎቭ ፡ ጄኔራል ፡ የጆርጂያ ፡ አገረ ፡ ገዢና ፡ የካውካሰስ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዋናው ፡ አዛዥ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፯፻፸፱—፲፰፻፷፭ ዓ. ም.) ።

እኔ ፡ ስድስት ፡ በራዎች ፡ አስጭኜ ፡ በወዲህ ፡ ደግሞ ፡ እነዚህ ፡ አሴቲያኖች ፡ እየረዱኝ ፡ አንድ ፡ ሻንጣ ፡ ብቻ ፡ ተሸክመው ፡ መጠጣት ፡ እንዴት ፡ አቅታቸው?» ብዬ ፡ ጭንቀቴን ፡ ባጥየው ፡ ደህና ፡ አድርጉ ፡ ተመልከቶኝ ፡ የብልጠት ፡ ፈገግታውን ፡ አሳየኝ ።

«ካውካሰስ ፡ ከመጡ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ መሰል?» አለኝ ።

«አይ ፡ መቼም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሁኖኛል ፡» አልኩት ።

«አሁንም ፡ ያቺኑ ፡ ፈገግታውን ፡ አመጣ ።

«ምነው ፡ ጠየቁኝሳ?»

«አይ! ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ኑሮኝ ፡ እንኳ ፡ አይደለም ፡ ጊታዬ ። እኒህን ፡ የእስያ ፡ ተወላጆች ፡ ልግመኞች ፡ አያውቋቸውም! ይሄ ፡ ጫጫታቸው ፡ ብዙ ፡ የሚረዳ ፡ ይመስልዎታል? ምን ፡ እንደሚሉ ፡ እንኳ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም ። ሆኖም ፡ በራዎቹ ፡ ንግግሩ ፡ በደምብ ፡ ይገባቸዋል ። ሐያ ፡ በራም ፡ ለመጫን ፡ ይቻላል ። ግን ፡ እኒህ ፡ ሸረኞች ፡ አንዴ ፡ ያን ፡ ምላሳቸውን ፡ ከዘረጉ ፡ ንትንት ፡ አይሉም ። እንዴት ፡ ያሉ ፡ አታላዮች ፡ መሰለዎት! ምንም ፡ አያደርጓቸው ፡ ደግሞ ፡ አይችሉም ። አዲስ ፡ መንገደኛ ፡ ሲያገኙ ፡ ማራቡት ፡ ይወዳሉ ። ለመበላሸታቸው ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ የለውም ። ግና ፡ ምኑን ፡ አይተውት! ገንዘብ ፡ ያስጨምሩዎታል ። እኔማ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ው ም ፡ ብርሃን ፡ መንገዳችንን ፡ ለመቀጠል ፡ ቻልን ። የቀረን ፡ መንገድ ፡ አቀበት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ እንደበፊቱ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ዳገት ፡ አልነበረም ። ሻንጣዬን ፡ በሠረገላው ፡ ውስጥ ፡ እንዲያደርጉትና ፡ በሬዎቹ ፡ በፈረሶች ፡ እንዲተኩ ፡ እዝዤ ፤ የወጣነውን ፡ አቀበትና ፡ ሸለቆ ፡ ቁልቁል ፡ ብመለከት ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ደመና ፡ ሸፍኖት ፡ አልታይህ ፡ አለኝ ። በደረስንበት ፡ ቦታ ፡ እንዳችም ፡ ድምፅ ፡ አይሰማም ። ያጀቡኝ ፡ የእሴትያን ፡ ተወላጆች ፡ የቮድካ ፡ መግዣ ፡ እንድሰጣቸው ፡ ውጥር ፡ አድርገው ፡ ቢይዙኝ ፡ ሻምበሉ ፡ እንደለመደው ፡ አንዴ ፡ ቢጮህባቸው ፡ ብትንትናቸው ፡ ወጣ ።

«አዩአቸው ፡ እነዚህን ፡ ፍጡሮች ። ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ ለመጠየቂያ ፡ የሩሲያኛ ፡ ቋንቋ ፡ መናገሩ ፡ ይሳናቸዋል ። 'የኔ ፡ መኩንን ፡ ለቮድካ ፡ መግዣ ፡ ሳንቲም ፡ ስጠን!' ማለቱን ፡ ሞን ፡ ያውቁበታል ። እንዴ ፡ እኔ ፡ ከሆነ ፡ ታታሮቹ ፡ ይሻላሉ ። ባይሆን ፡ እነሱ ፡ ከመጠጡ ፡ ይቆጠባሉ ...» ሲል ፡ ሻምበሉ ፡ አጉረመረመ ።

እጣቢያው ፡ ለመድረስ ፡ የቀረን ፡ አንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ያህል ፡ ነው ። አካባቢው ፡ ጸጥ ፡ ብሏል ። የጸጥታውም ፡ ብዛት ፡ ትንኝን ፡ በድምጽዋ ፡ ብቻ ፡ የት ፡ እንዳለች ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ከቆምንበት ፡ በስተግራ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ከሚገኘው ፡ ሸለቆ ፡ በስተግዶ ፡ ባሉት ፡ ተራራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዎች ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የተኛው ፡ በረዶ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ሰጥቷቸዋል ። መሸት ፡ ቢልም ፡ ቅሉ ፤ የተወሰነ ፡ ብርሃን ፡ አቅፈው ፡ ማንፀባረቃቸው ፡ አልቀረም ። ጨለማ ፡ ባዳፈነው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ከዋክብት ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ ጀመሩ ። ከፍ ፡ ብለን ፡ አንጋጠን ፡ ስናይ ፡ ከዋክብቶቹ ፡ በፊት ፡ ከነበርንበት ፡ ቦታ ፡ የባሰውን ፡ ራቅ ፡ ያሉ ፡ መስለው ፡ ታዩን ። በመንገዱ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ያሉት ፡ ጠቋቁር ፡ ድንጋዮች ፡ ሆን ፡ ብለው ፡ የተተከሉ ፡ ይመስላሉ ። አልፎ ፡ አልፎም ፡ በየቦታው ፡ በበረዶው ፡ መሐከል ፡ ጉች ፡ ጉች ፡ ብለው ፡ የሚታዩ ፡ ቁጥቋጦች ፡ ነበሩ ። በአጠቃላይ ፡ ግን ፡ በአካባቢው ፡ እንዲት ፡ ቅጠል ፡ ስትንቃነቅ ፡ አትታይም ። በዚያ ፡ በፀጥታ ፤ በዚያ ፡ የሙት ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የደከሙትን ፡ ፈረሶች ፡ ትንፋሽና ፡ የሩስያን ፡ የሠረገላ ፡ ቃጭል ፡ መሰማቱ ፡ ደስ ፡ ይል ፡ ነበር ።

«መቼም ፡ ነገ ፡ ቀኑ ፡ ውብ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ፡» ብዬ ፡ ብል ፤ ሻምበሉ ፡ ሰምቶ ፡ እንዳልሰማ ፡ አስተያየቴን ፡ ንቆ ፡ ከፊት ፡ ፊታችን ፡ የተጉተረውን ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ በጣቱ ፡ እመለከተኝ ።

«ምንድነው?» አልኩት ።

«የጉድ ፡ ተራራ ፡ ይባላል ።»

«እውነት?»

«እንዴት ፡ እንደሚጨስ ፡ አዩት?»

በውነትም ፡ ጉድ ፡ ሲጨስ ፡ ይታያል ። ዙሪያውን ፡ ያለው ፡ ደመና ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ሲያን ዣብብ ፡ ሜፋ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የደመና ፡ ጥቁ ረት ፡ ከጨለመው ፡ ሰማይ ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር ፡ እንደ ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ ለብቻው ፡ ጐልቶ ፡ ይታ ያል ።

ትንሽ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የነበረው ፡ የፖስታ ፡ ቤቱና ፡ በዙሪያው ፡ የነበሩት ፡ ክዳን ፡ ጐጆዎች ፡ ይታዩናል ። የአካባቢው ፡ መብራቶችም ፡ «እን ኳን ፡ ደህና ፡ መጣችሁ ፡» እያሉ ፡ የሚያሸበሽቡ ፡ ይመስላሉ ። ቀዝቀዝ ፡ ያለው ፡ የማታ ፡ ነፋስ ፡ በዱብዳ ፡ ሸለቆዎቹን ፡ ሰንጣጥቆ ፡ እያፏጨ ፡ ኮች ፡ አለ ። ካፊያ ፡ ብጤም ፡ ተከተለ ። የያዝ ኳትን ፡ ካባ ፡ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ ከማድ ረጌ ፡፡ ካፊያውን ፡ የተከተለ ፡ በረዶ ፡ ወረደ ብን ። በአከብሮት ፡ ዓይን ፡ ሻምበሉን ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ ተመለከትኩት ...

«ለዛሬ ፡ እዚሁ ፡ ማደር ፡ ይኖርብናል ። በእንዲህ ፡ ያለ ፡ የአየር ፡ ሁኔታ ፡ መጓዙ ፡ አይበ ጅም ፡» ብሎ ፡ በቅሬታ ፡ ድምፅ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወደሠረገላው ፡ ነጂ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፤ «ከሬስቶቫያ ፡ ላይ ፡ የበረዶ ፡ ናዳ ፡ አይተሃል ፡ ወይ?» ሲል ፡ ጠየቀው ።

«የለም ፡ ጌታዬ ፡ አላየሁም ። ጊዚውን ፡ ጠ ብቆ ፡ የሚንከባለል ፡ ናዳ ፡ ግን ፡ በየቦታው ፡ ልብ ፡ ብያለሁ ፡» ሲል ፡ አሴቲያኑ ፡ መለሰለት ።

በፖስታ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመንገደኞች ፡ የሚ ሆን ፡ ክፍል ፡ ባለመኖሩ ፡ አንዲት ፡ ጠቀርሻ ፡ የወረራት ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ እንድናድር ፡ ሆነ ። ካውካሰስን ፡ ሰዞር ፡ የማትለየኝ ፡ አንዲት ፡ የሻይ ፡ ጀበና ፡ ስለነበረችኝ ፤ የመንገድ ፡ ወዳጇ ፡ አብሮኝ ፡ ሻይ ፡ እንዲጠጣ ፡ ጋበዝኩት ።

ተራራውን ፡ ተጠግታ ፡ የተሠራችውን ፡ ያረ ፍንባትን ፡ ጐጆ ፡ በራፍ ፡ ለመድረስ ፤ ሦስት ፡ የሚያዳልጡ ፡ እርምጃዎችን ፡ ማለፍ ፡ ነበረብን ። ወደጐጆዋ ፡ እያተመተምሁ ፡ ገባ ፡ ከማለቴ ፡ ከአንዲት ፡ ላም ፡ ጋራ ፡ ተጋጨሁ ። (ነዋሪዎቹ ፡ እልፍኙን ፡ ከእሽከር ፡ ቤት ፡ የሚለይ ፡ በረት ፡ አላቸው) ። ወዬት ፡ እንደምሄድ ፡ ማራ ፡ ገባኝ ። በአንድ ፡ ወገን ፡ በጐቹ ፡ ያመነዥካሉ ። በወዲህ ፡ ያደፈጠው ፡ ውሻ ፡ ያጉረመርማል ። እንደምንም ፡ በነበረው ፡ ብርሃን ፡ ተመርቼ ፡ የበር ፡ ጭላንጭል ፡ ወዳየሁበት ፡ አመራሁ ። በጢስ ፡ በጠቆሩ ፡ ሁለት ፡ ወጋግራዎች ፡ ተገድፋ ፡ በቆመችው ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሰፍረውባታል ። ጢሱ ፡ ወደውጭ ፡ እንዳይወጣ ፡ በጣራው ፡ ቀዳዳ ፡ የሚገባው ፡ ነፋስ ፡ ስለሚመለሰው ፡ ጐጆዋ ፡ በጢስ ፡ ታፍናለች ። ስለሆነም ፤ በዙሪ ያዬ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ ለመለየት ፡ አቃተኝ ። ዓይኔ ፡ ከተለማመደ ፡ በኋላ ፡ የተቦጫጨቀ ፡ ድራቶ ፡ የደረቡ ፡ ሁለት ፡ አሮጊት ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሕፃናት ፤ አንድ ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ የጂዎር

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዬ! ጌታዬ ፡ እነዚያ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮች ፡ እን
ዴት ፡ አስቸግረውን ፡ ነበር ፡ መሰለዎ? እግ
ዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ አሁን ፡ ትንሽ ፡ ታገስ ፡
ብለዋል ። ድሮማ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርምጃ ፡
እንኳን ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ሊሔዱ ፡ አይችሉም ፡
ነበር ። እንቅልፍማ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ ማን ፡
አልሞ? ትንሽ ፡ ሽለብ ፡ ካደረጉት ፡ የሰፈሩ ፡
ሰይጣን ፡ ከየት ፡ መጣ ፡ ሳይባል ፡ ደርሶ ፤
እንገትዎን ፡ በካራ ፡ ሊቆርጥ ፡ ወይም ፡ ከጀር
ባዎ ፡ በጥይት ፡ ሊገድለዎት ፡ ዘወትር ፡ ዝግጁ ፡
ነው ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ለጉብዝናቸው ፡ ምንም ፡
አይወጣላቸውም ።»

«መቼም ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ ሳያጋጥመዎት ፡
አልቀረም?»

«እንዴታ! እንዴታ ... »

ይህን ፡ እንዳለ ፡ የሪዙን ፡ የግራ ፡ ጫፍ ፡
እያፍተለተለ ፡ እንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጉ ፡ በት
ካዜ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። እየተዘዋወረ ፡
ስለጉብኝቱ ፡ ማስታወሻ ፡ የሚይዝ ፡ ማንኛ
ውም ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ ለማወቅ ፡ ጉጉት ፡ እንዳ
ለው ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ እንዳንድ ፡
ዝርዝር ፡ ሁኔታዎችን ፡ ለመረዳት ፡ ጓጓሁ ።
የተጣደውም ፡ ሻይ ፡ ፈላ ። ከሻንጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ሁ
ለት ፡ የመንገድ ፡ ብርጭቆዎች ፡ አውጥቼ ፡ ሻ
ዩን ፡ ቀድቼ ፡ እፊቱ ፡ አስቀመጥኩለት ። እንዴ ፡
ፉት ፡ እንዳለ ፡ አሁንም ፡ በትከዛ ፡ ተመስጦ ፡

ጂያ ፡ ተወላጅ ፡ እሳቱን ፡ ከበው ፡ ተቀምጠው ፡
እየሁ ። ሌላ ፡ ምርጫ ፡ ስላልነበረን ፡ እኛም ፡
ከእሳቱ ፡ ዳር ፡ ተመቻችተን ፡ ተቀምጠን ፡
ፒፓችንን ፡ ለኩስን ። ትንሽ ፡ እንደቆየን ፡
የሻይ ፡ ጀበናችንን ፡ ዘፈን ፡ እያዳመጥን ፡ ተሟ
ሟቅን ።

እንዳች ፡ መቅሰፍት ፡ የወረደባቸው ፡ ይመ
ስል ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ ያዩን ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡
እያመለከትሁ ፤ «ምስኪኖች ፡ ናቸው ፡» ብዬ ፡
ለሻምበሉ ፡ አስተዛዝኜ ፡ ነገርሁት ።

«ደደቦች ፡ ናቸው ። ምንም ፡ ነገር ፡ መሥ
ራት ፡ አይችሉም ። ይመኑኝ ፤ ቢያሳዩዋቸው ፤
ቢያስተምሯቸውም ፤ አይገባቸውም ። የኛ ፡
ካባርዲያንና ፡ ቼቼኖች ፡ ወረበሎች ፡ ይሁኑ ፡
እንጂ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ጥሩ ፡ ተዋጊዎች ፡ ናቸ
ው ። እነዚህ ፡ ግን ፡ ለመሣሪያም ፡ ቢሆን ፡ እ
ንኳ ፡ ግድ ፡ የላቸውም ። ከመሐከላቸው ፡ አንድ ፡
ደህና ፡ ተዋጊ ፡ ተፈልጐ ፡ አይገኝም ። ዳሩ ፡
ከአሲቲያኖች ፡ ምን ፡ ይጠብቃል?» ብሎ ፡ ምሬ
ቱን ፡ ነገረኝ ።

«እዚህ ፡ ከመጡ ፡ ቆይተዋል?»

«አዎ ፡ ከረምኩ ፡ እንጂ ፡ በካሚኒ ፡ አውራ ፡
ጐዳና ፡ ባለው ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ አሥር ፡
ዓመታት ፡ አገለግዬአለሁ ። ቦታውን ፡ ያው
ቁታል?»

«በዝና ፡ ብቻ ፡ ነው ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ተምትመን ፡ ስለነበር ፡ ሰልፉ ፡ ላይ ፡ መንገድግድ ፡ መግላፈጥ ፡ ጀመርን ። ምን ፡ ልበልዎት ፤ አሌክሲይ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይህን ፡ ሲያውቁ ፡ ጊዜ ፡ መሬት ፡ ብትውጠን ፡ ተሻለን ። እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የንዴት ፡ ፊት ፡ ፈጣሪ ፡ እንደገና ፡ እንዳያሳየኝ ፡ እለምነዋለሁ ። ወታደራዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልንገባ ፡ ለጥቂት ፡ አመለጥን ። እዩት ፤ የአጋጣሚን ፡ ነገር! ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ምንም ፡ ሳያዩ ፡ ይከርሙና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እርሜን ፡ ልውጣ ፡ ሲሉ ፡ መጥፎ ፡ እድል ፡ ያጋጥመዎታል ።»

ይህንን ፡ ስሰማ ፡ ተስፋ ፡ እቆርጥ ፡ ጀመር ።

«ቼርከሶችን ፡ ይውሰዱ ፤ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በሠርግ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በቀብር ፡ ላይ ፡ ያን ፡ የገብስ ፡ ጠላቸውን ፡ ይለጉና ፡ ድብድባቸውን ፡ ይቀጥላሉ ። እንዴማ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የአንድ ፡ የሠላማዊ ፡ ልውል ፡ እንግዳ ፡ ብሆንም ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ ለጥቂት ፡ አመለጥሁ ።»

«እንዴት ፡ እባክዎ?»

ፒፓውን ፡ ትንባሆ ፡ ሞልቶ ፡ ሲያበቃ ፡ ታሪኩን ፡ በሰፈው ፡ ጀመረልኝ ። «አንድ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ኩቱሬክ ፡ ማዶ ፡ በእንድ ፡ ጣቢያ ፡ ውስጥ ፡ ተመድቤ ፡ እገለግል ፡ ነበር ። ከእለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ምግብ ፡ ከያዘልን ፡ ጓዝ ፡ ጋር ፡ በግምት ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ መኩንን ፡ አብሮ ፡ መጣ ። ሙሉ ፡ የማዕረግ ፡ ልብሱን ፡

«እንዴታ! .. እንዴታ!» ይል ፡ ጀመር ። የካውካሰስ ፡ ነዋሪዎች ፡ ታሪካቸውን ፡ ማውራት ፡ እንደሚወዱ ፡ ስለማውቅ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ያወራኛል ፡ እየልኩ ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅሁ ። በአንድ ፡ ገጠር ፡ ውስጥ ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ሲያገለግሉ ፤ «እንደምን ፡ ዋልክ ፡» የሚላቸው ፡ ስለማይኖር ፤ ሰው ፡ ሲያገኙ ፡ ያላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ማውራት ፡ ይወዳሉ ። (በነገራችን ፡ ላይ ፡ ሻምበሉም ፡ ቢሆን ፡ እንደምን ፡ ዋላችሁ ፡ አይሉም ።) አካባቢው ፡ የሚነገርለት ፡ ነገር ፡ ሞልቷታል ። ስለዚያ ፡ አውሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሊያመጣ ፡ ስለሚችለው ፡ አደጋ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታሪክ ፡ ሲታሰብ ፡ በወረቀት ፡ የመዘገብነው ፡ ትንሽ ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ።

«ትንሽ ፡ ሩም ፡ መጨመር ፡ አይፈልጉም? ከቲፍሊስ ፡ ያመጣሁት ፡ ነጭ ፡ ሩም ፡ አለኝ ። ለዚህ ፡ ለብርድ ፡ ዋና ፡ መድኃኒት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡» ብዬ ፡ ጋበዝኩት ።

«የለም ፤ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፤ አልጠጣም ።»

«ለምን?»

«ሁለተኛ ፡ እንዳልጠጣ ፡ ምዬአለሁ ። አንዴ ፡ ገና ፡ የአምሳ ፡ አለቃ ፡ ሳለሁ ፡ አርገነው ፡ የማናውቀውን ፡ ለሽርሽር ፡ ብለን ፡ ወጣ ፡ አልን ። የከፋቱ ፡ ደግሞ ፡ የዘያኑ ፡ ሌሊት ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ጥሪ ፡ ጡራንባ ፡ ተነፋ ። ከዘያ ፡ በኋላማ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደለበሰ ፡ ወደእኔ ፡ መጥቶ ፡ ለአገልግሎት ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ እንደተመደበ ፡ ገለጸልኝ ። በቅጥ ነቴና ፡ በግርጣቱ ፡ በወዲህ ፡ ደግሞ ፡ በልብሱ ፡ አዲስነት ፡ ወደካውካሰስ ፡ ሲመጣ ፡ የመጀ መሪያው ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ። 'ወዲህ ፡ የተዘዋወሩት ፡ ከሩስያ ፡ ነው?' ብዬ ፡ ጠየቅ ኩት ። 'አዎን ፡ ጌታዬ' ። የእጅ ፡ ሠላምታ ፡ ከሰጠሁት ፡ በኋላ ፤ 'እንኳን ፡ ደህና ፡ መጡ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሊያገለግሉ ፡ በመምጣትዎ ፡ በ ጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። ብቻ ፡ ትንሽ ፡ እገሩ ፡ ሳይሰለቸዎት ፡ እይቀርም ። ቢሆንም ፡ በሁሉ ም ፡ ነገር ፡ እንደምንተባበር ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። እኔስ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሚች ፡ እባላለሁ ። ሙሉ ፡ የማዕረግ ፡ ልብስዎንም ፡ በማዬታ ፡ ለዘወትር ፡ መልበስ ፡ የለበዎትም ፤ ባርኔጣዎን ፡ ብቻ ፡ አድርገው ፡ ሊሄዱ ፡ ይችላሉ ።'»

«ስሙ ፡ ማን ፡ ይባላል?» ስል ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሚችን ፡ ጠየቅኩት ።

«ግሪጉሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ፔቾሪን ፡ ይባል ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያልተለመደ ፡ ጠባይ ፡ ያሳይ ፡ እንጂ ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ግሩም ፡ ወጣት ፡ ነበር ፡ መሰለዎት! ለምሳሌ ፤ አንዳ ንዴ ፡ ሲያሰኘው ፡ ዝናብና ፡ ብርድ ፡ ሳይል ፤ ሰ ሙሉ ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ ያን ፡ ገብቶ ፡ አ ውሬ ፡ ያድናል ። አብሮት ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ብርድ ፡ ሲይዘውና ፡ ሲያክም ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ሩንክች ፡ አይልም ፡ ነበር ። አንዳንዴ ፡ ደግሞ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ በተላላፊ ፡ ነፋስ ፡ ጉንፋን ፡ ይይዘዋል ። በድንገተኛም ፡ ድምፅ ፡ ሊደናገጥና ፡ ሊረበሽ ፡ ይችላል ። እኔ ፡ ግን ፡ በባዶ ፡ እጁ ፡ በፈት ፡ ለፈት ፡ ኃይለኛ ፡ አውሬ ፡ ሲገጥም ፡ አይቻለሁ ። ኧረ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ፤ የሱ ፡ ነገር ፡ አንዳንዴ ፡ ስንት ፡ ሰዓት ፡ በሙሉ ፡ ተዘግቶ ፡ ቁጭ ፡ ሲል ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ለማናገር ፡ አይ ቻልም ። ያሰኘው ፡ ለት ፡ ደግሞ ፡ በሳቅ ፡ ያንከ ተክተናል ... አዎን ፡ ጌታዬ ፤ እሱስ ፡ ትንሽ ፡ ግር ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ነው ። የነበሩት ፡ ውድ ፡ እቃዎች ፡ ብዛት ፡ ሲታይ ፡ ጌታ ፡ ለመሆኑ ፡ አያጠራጥርም ።»

«ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ አገለግለ?»

«አንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ አብረን ፡ አገ ለግልን ። ያች ፡ ዓመት ፡ ለእኔ ፡ የማትረሳኝ ፡ ዓመት ፡ ናት ። እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበለው ና ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ጨምሮኛል ። አንዳ ንዴ ፡ እኮ ፡ ለችግር ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ የሚባለው ፡ ሐሰት ፡ እይደለም ።»

«እንዴት ፡ ያሉ ፡ ችግሮች?» ብዬ ፡ ጠይቄው ፡ ሻዩን ፡ በድጋሚ ፡ ቀዳሁለት ።

«ታሪኩን ፡ እነግረዎታለሁ ። ከነበርንበት ፡ ሠፈር ፡ አንድ ፡ ስድስት ፡ ቨርስታ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰላማዊ ፡ ልዑል ፡ ይኖር ፡ ነበር ። የአስራ ፡ አምስት ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ወጣት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ረን ። ሴቶቹም ፣ ልክ ፣ እኛን ፣ ሲያዩን ፣ እየ
ሮጡ ፣ ያሸሽጋሉ ። ያየናቸው ፣ ሴቶች ፣ መልክ ፣
ቆንጆ ፣ የሚያሰኛቸው ፣ አይደለም ። 'የቼርኬስ ፣
ሴቶች ፣ መልክ ፣ መልካም ፣ ይመስሉኝ ፣ ነበር' ፣
ቢል ፣ ግሪጐሪይ ፣ አሌክሳንድሮቪች ፣ ቅር ፣ አለ
ው ። የያዝኩትን ፣ በልቤ ፣ ይገር ፣ 'እስቲ ፣
ትንሽ ፣ ታገስ ፣ ወዳጅ' አልሁት ።

ልዑሉ ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ የተሰበሰበው ፣
ሰው ፣ ብዛት ፣ መጠን ፣ የለውም ። አስያኖች ፣
በሠርጋቸው ፣ ሌላው ፣ ቀርቶ ፣ በመንገድ ፣ ሲያ
ልፉ ፣ የተዋወቁትን ፣ ሳይቀር ፣ መጋበዝ ፣ የቆየ ፣
ልምዳቸው ፣ ነው ። እንደደረስንም ፣ በክብር ፣
ተቀብለውን ፣ ከሁሉ ፣ በተሻለው ፣ ክፍል ፣
ውስጥ ፣ አስተናገዱን ። እቤት ፣ ውስጥ ፣ ከመግባ
ታችን ፣ በፊት ፤ እንዲያ ፣ ለምናልባቱ ፤ የሚሆ
ነው ፣ አይታወቅም ፣ በማለት ፣ ፈረሶቻችንን ፣
ያሰሩበትን ፣ ቦታ ፣ ሔጀ ፣ ተመለከትኩ ።

ሠርግ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ የሚያከብሩት?
ስል ፣ ሻምበሉን ፣ ጠየቅሁት ።

«እከባበራቸው ፣ እንኳ ፣ ያው ፣ እንደ
ተለመደው ፣ ነው ። መጀመሪያ ፣ ይማሙ ፣
ከቱራን ፣ ውስጥ ፣ ምዕራፍ ፣ ገልጦ ፣
ያነብላቸዋል ። ቀጥሎም ፣ ለሙሽሮቹና ፣
ለዘመዶቻቸው ፣ በሙሉ ፣ ስጦታው ፣
ይጐርፋል ። ከዚያማ ፣ ምን ፣ እለ! ያ! የገብስ ፣
ጠላቸው ፣ ይንቆረቆራል ። ጨዋታው ፣ ሲደራ ፣

ልጁ ፣ እንደልማድ ፣ ሆኖበት ፣ ጋልቦ ፣ መጥቶ ፣
እኛ ፣ ሰፈር ፣ ሳይደርስ ፣ ውሎ ፣ አያውቅም ።
ግሪጐሪይ ፣ አሌክሳንድሮቪችና ፣ እኔ ፣ ያን ፣
ወጣት ፣ በእውነቱ ፣ አበላሽነው ፣ ለማለት ፣
ይቻላል ። እንዴት ፣ ያለ ፣ ተዋጊ ፣ ነበር ።
የሚሳነው ፣ ምንም ፣ ነገር ፣ አልነበረም ። እየ
ጋለበ ፣ ከመሬት ፣ ላይ ፣ ባርኔጣ ፣ በማንሳትም ፣
ሆነ ፣ በመተኪስ ፣ ማንም ፣ የሚወዳደረው ፣ የለ
ም ። ገና ፣ ምን ፣ ያደርጋል ፤ ታላቅ ፣ የገንዘብ ፣
ፍቅር ፣ ነበረበት ። አንድ ፣ ቀን ፣ ግሪጐሪይ ፣ አሌ
ክሳንድሮቪች ፣ ለቀልድ ፣ ያህል ፣ 'ከአባትህ ፣ መ
ንጋ ፣ ከሁሉ ፣ የተሻለውን ፣ ፍየል ፣ ሰርቀህ ፣ ካ
መጣህ ፣ ወርቅ ፣ እሰጥሃለሁ' ፣ ቢለው ፣ በማ
ግስቱ ፣ አንዲት ፣ ፍየል ፣ ቀንዷን ፣ እየጐተተ ፣
ከተፍ ፣ አለ ። አልፎ ፣ አልፎም ፣ እንደዚሁ ፣
ልንቀልደበት ፣ ስንፈልግ ፣ በንዴት ፣ ተቃጥሎ ፣
ጐራዴውን ፣ ለመምዘዝ ፣ ይከጅላል ። 'አዛ
ግት ፣ ቶሎ ፣ ቲማ ፣ ቲማ ፣ ትላለህ ። ይኸ ፣ ጠባይህ ፣
አይበጅም ፣' እለዋለሁ ።

አንድ ፣ ቀን ፣ ሽማግሌው ፣ ልዑል ፣ ታላቅ ፣
ሴት ፣ ልጁን ፣ ሲድር ፣ ለሠርግ ፣ ሊጋብዘን ፣
ሰፈራችን ፣ ድረስ ፣ መጣ ። ምንም ፣ እንኳ ፣ ታ
ታር ፣ ቢሆን ፣ ወዳጅ ፣ እንደመሆናችን ፣ መጠን ፣
ግብግቡን ፣ እምቢ ፣ ለማለት ፣ በፍጹም ፣ አል
ቻልንም ። ወደደግሱም ፣ አመራን ። መንደር ፣
ውስጥ ፣ ስንገባ ፣ የውሻው ፣ ጩኸት ፣ አደነቆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይታያል ። ሆኖም ፣ በእኛ ፣ አትክልት ፣ ውስጥ ፣ አይናርም ፡» እያለች ፣ ነው ፣ ያቀነቀነችው ። ፔቾሪን ፣ ከወንበሩ ፣ ተነስቶ ፣ እጅን ፣ ልቡ ፣ ላይ ና ፣ እግንባሩ ፣ ላይ ፣ አድርጉ ፣ እጅ ፣ ነስቷት ፣ መልስ ፣ እንዲሰጣት ፣ ጠየቀኝ ። ቋንቋቸውን ፣ አቀ ላጥፎ ፣ ስለማያውቅ ፣ መልሱን ፣ በሚገባ ፣ ተረጉምኩለት ።

ዘፈኗን ፣ ጨርሳ ፣ ስትመለስ ፤ «ታዲያስ ፤ ቁን ጅናዋ ፣ እንዴት ፣ ነው?» ስል ፣ ግሪጉሪይ ፣ አሌክ ሳንድሮቪችን ፣ በሹክሹክታ ፣ ጠየቅኩት ። «ድን ቅ ፣ ናት! ውብ ፣ ናት! ስሚ ፣ ማን ፣ ይባላል?» ሲል ፣ ጠየቀኝ ፤ «ቤላ ፣ ነቻ!»

በውነቱም ፣ ውብ ፣ ነበረች ። የአረዛዘሚ ፤ የሰውነቷ ፣ ቅርጽ ፤ ጥቁር ፣ ዓይኖቿ ፤ የደም ፣ ግባቷ ፣ ያፈዛሉ ። ፔቾሪንም ፣ በዚሁ ፣ ውበቷ ፣ ተነድፎ ፣ ዓይኖቹ ፣ ከላይዋ ፣ አልናቀል ፣ አሉ ። እሷም ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ እየሰረቀች ፣ ስታየው ፣ አመሸች ። ለዚች ፣ ለውብ ፣ ወጣት ፣ ልዕልት ፣ የተማረከው ፣ ፔቾሪን ፣ ብቻ ፣ አልነበረም ። ከከፍሉ ፣ ጥግም ፣ እንደዚሁ ፣ ሁለት ፣ ዓይናች ፣ ቤላ ፣ ላይ ፣ ተተክለው ፣ አየሁ ። ደህና ፣ አድርጌ ፣ ስመለከተው ፤ ሁለተኛው ፣ የቤላ ፣ አፍቃሪ ፣ የቆየ ፣ ወዳጇ ፣ ካዝቢች ፣ መሆኑን ፣ ተረዳሁ ። ካዝቢች ፣ መቼም ፣ ጥሩ ፣ ወዳጃችን ፣ ነው ፣ ለማ ለት ፣ ባይቻልም ፤ በእኛ ፣ ላይ ፣ ግልጽ ፣ የሆነ ፣ ጥላቻ ፣ አልነበረውም ። ብዙ ፣ ጥርጣሬ ፣ በእሱ ፣

የፈረስ ፣ ጉግስ ፣ ይጀመራል ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የፈረስ ፣ ጨዋታ ፣ ይታያል ። እንድ ፣ አስቀያሚ ፣ ፍጡር ፣ በሸንካላ ፣ ፈረስ ፣ ተቀምጦ ፣ እየጋለበ ፣ ሕዝ ቡን ፣ ማሳቁ ፣ ዘወትር ፣ በእንዲህ ፣ ያለ ፣ ሁኔታ ፣ ላይ ፣ የማይቀር ፣ ትርኢት ፣ ነው ። ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ በኋላ ፣ መሸትሸት ፣ ሲል ፣ ዘፈኑና ፣ እስክስታው ፣ ይቀልጣል ። እንድ ፣ ምስኪን ፣ ሽማግሌ ፣ ሰባት ፣ ክር ፣ ያለው ፣ መሣሪያ ፣ ይዞ ፣ ይጫወታል ። ምን ፣ እንደሚሉት ፣ ረሳሁት ፤ የእኛን ፣ ባላላ ይካ ፣ ይመስላል ። ወጣት ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ ተሰድረው ፣ እያጨበጨቡ ፣ ይዘ ፍናሉ ። ቀጥሎም ፣ አንዲት ፣ ወጣት ፣ ሴትና ፣ ጉልማሳ ፣ ከመሐል ፣ ገብተው ፣ ዘፈኑን ፣ እየተቀባበሉ ፣ ሲያወርዱ ፣ ሌሎች ፣ ያጀባ ሉ ። ፔቾሪንና ፣ እኔ ፣ የከብር ፣ ቦታ ፣ ተሰጥቶን ፣ ተቀምጠናል ። የጋባዣችን ፣ ትንሿ ፣ ሴት ፣ ልጅ ፤ የአሥራ ፣ ስድስት ፣ ዓመት ፣ ኮረዳ ፣ ሳትሆን ፣ አትቀርም ፣ ወደፔቾሪን ፣ ጠጋ ፣ ብላ ፣ የሙገሳ ፣ ዘፈኗን ፣ ያረያረችለት ።»

«ምን ፣ እያለች ፣ እንያዘፈነችለት ፣ አሁን ፣ ትዝ ፣ አይለዎትም?»

«ትዝ ፣ ይለኛል ። ወጣት ፣ ፈረሰኞቻችን ፣ ንቁ ፣ ናቸው ። ኮታቸውም ፣ በሐር ፣ የተጠለፈ ፣ ነው ። ግን ፣ የኛ ፣ የሩሲያ ፣ መኮንን ፣ ከነሱም ፣ ያማረ ፤ የትከሻውም ፣ ጌጥ ፣ ከወርቅ ፣ የተሠራ ፣ ነው ፤ ከሌሎችም ፣ መካከል ፣ ሲቆም ፣ ጉልቶ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ፡ አለን ። ሆኖም ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ የፈጸመው ፡ ሸር ፡ አንድም ፡ የለም ። እንዳንደ ፡ ወደሰፈራችን ፡ ጠቦት ፡ እያመጣ ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጥልናል ። በዋጋ ፡ መከራክርን ፡ ፍጹም ፡ አይወድም ፡ የጠየቀውን ፡ ወዲያው ፡ ካልከፈሉት ፡ ይቆጣል ። እንዴ ፡ የተናገራትን ፡ ዋጋ ፡ ቢሞት ፡ አይቀንስም ። ኩባኝ ፡ አልፎ ፡ እሩቅ ፡ እየሄደ ፡ በካውካሰስ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለሩሲያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይረዳ ፡ ነበር ፡ እየተባለ ፡ ይነገርለታል ። በእውነቱም ፡ ደግሞ ፡ ሲያዩት ፡ ሁለንተናው ፡ ሸፍታ ፡ ይመስላል ። አጠር ፡ ብሎ ፡ ትከሻ ፡ ሰፋፊ ፡ ነው ። ታዲያ ፡ ብልጠቱን ፡ ደግሞ ፡ የሚደርስበት ፡ አልነበረም ። የሚለብሰው ፡ የሐገር ፡ ልብስ ፡ ዘወትር ፡ የቆሸሸና ፡ የተቦጫጨቀ ፡ ቢሆንም ፡ መሣሪያዎች ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ። ፈረሱ ፡ ሻንቆ ፡ መቼስ ፡ በመላው ፡ ካባርዳ ፡ የታወቀ ፡ ነበር ። የሱን ፡ ፈረስ ፡ ዓይነት ፡ የትም ፡ ታይቶ ፡ አይታወቅም ። የመንደሩ ፡ ፋረሰኞች ፡ በሙሉ ፡ ስለሚቀኑበት ፡ አይወዱትም ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሊሠርቁት ፡ ሞክረው ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ቀርታል ። ያ ፡ ሻንቆ ፡ ፈረሱ ፡ ትዛ ፡ ሲለኝ ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ እፈቱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ። ሻንቆ ፡ እንደከሰል ፡ የጠቆረው ፡ ሲሆን ፡ እግሩ ፡ የቫዮሊን ፡ ገመድ ፡ ይመስላል ። የዓይኖቹም ፡ ውበት ፡ ከቢላ ፡ ዓይኖች ፡ ሁሉ ፡ አስንሰም ። ጥንካሬውም ፡ ወደር ፡ የለውም ። አምሳ ፡ ቨርስታ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይጋልባል ። ጌታው ፡ በሐይበትም ፡ እንደሠለጠነ ፡ ውሻ ፡ ኋላ ፡ ኋላውን ፡ ይከተላል ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ የጌታውን ፡ ድምፅ ፡ እንኳ ፡ ይለያል ። ካዝቢች ፡ ፈረሱን ፡ የማሰር ፡ ልማድ ፡ አልነበረውም ። የእውነተኛ ፡ ወንበዴ ፡ ፈረስ ፡ ነበር ።

በዚያን ፡ ምሽት ፡ ካዝቢች ፡ ከሌላው ፡ ጊዜ ፡ በይበልጥ ፡ ያዘነ ፡ ሆኖ ፡ ታየኝ ። ከካባው ፡ ስር ፡ የብረት ፡ ኮት ፡ እንደለበስ ፡ አስተዋልኩኝ ። እንዲህ ፡ የለበሰበት ፡ ምክንያት ፡ ሳይናር ፡ እይቀርም ። አንድ ፡ የወጠነው ፡ ተንኮል ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ገመትኩ ።

ቤቱ ፡ ሞቅ ፡ ስላለ ፤ ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡ ወደ ደጅ ፡ ወጣሁ ። ተራራዎች ፡ በሙሉ ፡ ጨልመዋል ። ደመናውም ፡ ዝግ ፡ እያለ ፡ በየሸለቆው ፡ ይንሸረሸራል ። ፈረሶቹ ፡ ሳር ፡ ተሰጥቷቸው ፡ እንደሆነ ፡ ለማየትና ፡ ዘወር ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ አካባቢውን ፡ ለመፈተሽ ፡ ፈረሶች ፡ ታስረው ፡ ወደነበሩበት ፡ ቦታ ፡ ዘው ፡ አልሁ ። ጥሩ ፡ ፈረስ ፡ ስለነበረኝ ፡ ብዙዎች ፡ ካባርዲያኖች ፡ ዓይናቸውን ፡ ጥለውበታል ፡ በጣሙን ፡ እየተመኙት ፡ በቋንቋቸው ፤ t.me/OLDBOOKSPDF ይሉታል ።

---

*ጥሩ ፡ ፈረስ ፤ በጣም ፡ ጥሩ ፡ (በቱርክ ፡ ቋንቋ ።)

ቀስ ፡ እያልሁ ፡ በእጥሩ ፡ ጥግ ፡ ለጥግ ፡ ሳጠ
ቅስ ፡ የሚነጋገሩ ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ። ።
አንደኛውን ፡ ተነጋጋሪ ፡ ወዲያውኑ ፡ አወቅሁት ። ።
የጋባዣችን ፡ ልጅ ፡ ያ ፡ ቀኘርቃኣር ፡ አዛማት ፡
ነው ። ሁለተኛው ፡ ተናጋሪ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ በዝግታ ፡
ይመለስለታል ። «ደግሞ ፡ ምን ፡ ሊሠሩ ፡
ይሆን! መቼም ፡ ምክሩ ፡ የእኔን ፡ ፈረስ ፡ ለመን
ጠቅ ፡ እንዳልሆነ ፡ ነው ፡» እያልሁ ፡ ሳወጣ ፡
ሳወርድ ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ቆየሁ ። ወደ
እነሱም ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ጆሮዬን ፡ ከእጥሩ ፡ ለጥ
ፌ ፡ የሚነጋገሩትን ፡ ሁሉ ፡ ለማዳመጥ ፡ ሞከ
ርኩ ። በአጠገባችን ፡ ጉጆ ፡ ውስጥ ፡ ይዘፈን ፡
ስለነበር ፡ የሚነጋገሩትን ፡ በሙሉ ፡ ለማዳመጥ ፡
አልቻልሁም ። ስለምን ፡ እንደሚነጋገሩ ፡ ለማ
ወቅ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ጓጓሁ ። ።

«ካዝቢች ፤ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ፈረስ ፡ አለህ ፤
የቤቴ ፡ ባለቤት ፡ እኔ ፡ ብሆን ፡ ኑሮና ፡ ሶስት ፡
መቶም ፡ ያህል ፡ ፈረሶች ፡ ቢኖሩኝ ፡ ገሚሱን ፡
ለአንተ ፡ እሰጥህ ፡ ነበር ፡» እያለ ፡ አዛማት ፡ ሲና
ገር ፡ ሰማሁት ። ።

የለበሰውን ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ አስታውሼ ፡
ካዝቢች ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ። ።

ካዝቢች ፡ ለአዛማት ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይ
ሰጠው ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ «አምን ፤
አልተሳሳትክም ። እግርህ ፡ እስኪላጥ ፡ ካባርዳ
ንን ፡ በሙሉ ፡ ብትዞር ፡ የእኔን ፡ ፈረስ ፡ የመሰለ ፡
በፍጹም ፡ አታገኝም ። አንደ ፡ የራሺያኖችን ፡
ፈረሶች ፡ ለመስረት ፡ ከአብራኮች ፡ ጋር ፡ ከቱሬክ ፡
ማያ ፡ ተሻግረን ፡ ሄድን ። የሄድንበት ፡ ሳይቀናን ፡
ተርፍ ፡ ተበታትነን ፡ በተራችን ፡ ሽሽት ፡ ገባን ። ።
አራት ፡ ካዛኮች ፡ እኔን ፡ ያሳድዱ ፡ ገቡ ። እኒያ ፡
አረመኔዎች ፡ ከኋላዬ ፡ እየተከተሉ ፡ ሲጮኹ ፡
መትረባቸው ፡ ተሰማኝ ። ከፊት ፡ ለፊቴ ፡ ጢቅ ፡
ያለ ፡ ደን ፡ ተደንቅሮ ፡ ይጠብቀኛል ። ኮርቻዬ ፡
ላይ ፡ ጐንበስ ፡ ብዬ ፡ በደረቴ ፡ ተኝቼ ፡ ነፍሴን ፡
ለአላህ ፡ ሰጥቼ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ፈረሴን ፡
ገርፌ ፡ አስቀየምኩት ። ምን ፡ ልበልህ ፤ ከዚያማ ፡
ልክ ፡ ከንፍ ፡ እንዳላት ፡ ወፍ ፡ በዚያ ፡ በዱር ፡
ውስጥ ፡ ይዞኝ ፡ ይበር ፡ ጀመር ። እሾሁ ፤ ጭራ
ሮው ፡ ልብሴን ፡ ቦጫጭቆ ፡ ጣለው ። ፈቴንም ፡
ሞጫጨረው ። ፈረሱ ፡ እየዘለለ ፡ ደኑን ፡ በደ
ረቱ ፡ እየጣሰ ፡ ግልቢያውን ፡ ቀጠለ ። ፈረ
ሱን ፡ ትቼ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ብደበቅ ፡ ይሻላል ፡
ብዬ ፡ አሰብኩ ፡ ግን ፡ ከፈረሴ ፡ መለየት ፡ ደ
ግሞ ፡ አታተኝ ። ለካስ ፤ አላህ ፡ አትሙት ፡ ብ
ሎኝ ፡ ኑሮ ፡ ይህንኑ ፡ ሳስብ ፡ ከኋላዬ ፡ የተ
ተኮሱት ፡ ጥይቶች ፡ በእናቴ ፡ ላይ ፡ ተከታ
ትለው ፡ እያፏጩ ፡ አለፉ ። አዳኞቼም ፡ ከፈ
ረሳቸው ፡ ወርደው ፡ የእኔን ፡ ዱካ ፡ እየተከ
ተሉ ፡ ሲመጡ ፡ ተሰማኝ ... ድንገት ፡
ከፈታችን ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ ገደል ፡ አጋጠ
መን ። ፈረሴ ፡ ትንሽ ፡ ከአመነታ ፡ በኋላ ፡ እመር ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

አንገቱን ፡ ቀና ፡ አድርጐ ፡ ተፈተለከ ። አዳኞቹም ፡ ከደከሙት ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደኋላ ፡ ቀሩ ። አላህ ፡ ምስክሬ ፡ ነው ፤ ከምንግርህ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ ውሸት ፡ የለበትም ። በነበር ዙበት ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እስኪመሽ ፡ ድረስ ፡ እድፍጨ ፡ ቆየሁ ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ መሰለህ ፤ አዛማት? በዚያ ፡ በጨለማ ፡ የገደሉን ፡ ጫፍ ፡ እያነፈነፈ ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ በደንገላሳ ፡ እየጋለበ ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ። የሻንቆ ፡ ድምፅ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያው ፡ ለየሁት ። ሌላ ፡ ማን ፡ ወዳጅ ፡ አለኝ? በችግር ፡ ጊዜ ፡ ደረሰልኝ ። ከዚያም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ተለያይተን ፡ አናውቅም ።»

የፈረሱ ፡ ጌታ ፡ ያን ፡ ለስላሳ ፡ የፈረስ ፡ አንገት ፡ በቁልምጫ ፡ እየዳሰሰ ፡ ሲያሞካክሸው ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

«አንድ ፡ ሺህ ፡ የፈረስ ፡ መንጋ ፡ ቢኖረኝ ፡ ኖሮ ፤ ያለምንም ፡ ማመንታት ፡ በሻንቆ ፡ በለወጥሁህ ፡ ነበር ።» እያለ ፡ አዛማት ፡ ሲያወራው ፡ ሰማሁ ።

«የለም ፤ ምንም ፡ አልፈልግም ።» ብሎ ፡ ካዝቢች ፡ በግድየለሽነት ፡ ስሜት ፡ መለሰለት ።

«ካዝቢች ፤ አዳምጠኝ ፤ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነህ ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ዝነኛ ፡ ጀግና ፡ እንደሆንህ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። እንደምታውቀው ፡ አባቴ ፡ ካዛኩችን ፡ ስለሚፈራ ፡ ራቅ ፡ ወዳለ ፡ ቦታ ፡ አምኖ ፡ አይለቀኝም ። ግን ፡ አንተ ፡ ፈረስህን ፡

ብሎ ፡ ዘለላት ። ግን ፡ የኋላ ፡ እግሮቹ ፡ በገደሉ ፡ ውስጥ ፡ ስለገቡበት ፡ በፊት ፡ እግሮቹ ፡ ብቻ ፡ ተን ጠልጥሎ ፡ ቀረ ። ዘልዬ ፡ ወርጄ ፡ በገደሉ ፡ ገብቼ ፡ ረዳሁት ። በኋላም ፡ የኋላ ፡ ሁለት ፡ እግሮቹን ፡ ጉትቶ ፡ ሊያወጣቸው ፡ ቻለ ። ካዛኮቹ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እያዩን ፤ የእኔን ፡ መጨረሻ ፡ ለማወቅ ፡ አልፈለጉም ። ወደወደቅሁበትም ፡ ጉድጓድ ፡ አልመጡም ። ሞቷል ፡ ብለው ፡ ተውኝ ። ሆኖም ፡ ባለቤት ፡ የሌለው ፡ ፈረስ ፡ እግኝተው ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፈረሴን ፡ ለመያዝ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ጠምደው ፡ ያሳድዱት ፡ ጀመር ። በደረቴ ፡ በዚያ ፡ በሣርና ፡ እሾህ ፡ ላይ ፡ እየተሳብኩ ፡ ከደኑ ፡ እስክወጣ ፡ ድረስ ፡ የፈረሴን ፡ የማጣቱ ፡ ሐዘን ፡ አንገበገበኝ ። ጥቂት ፡ ካዛኮች ፡ ከደኑ ፡ ሲወጡ ፡ አየሁ ። የኔም ፡ ሻንቄ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወደእነሱ ፡ እየጋለበ ፡ መጣላቸው ። አገኘን ፡ ብለው ፡ እየተጫጫሁ ፡ ወደእሱ ፡ አመሩ ። እጅሬ ፡ መች ፡ እንዲህ ፡ በዋዛ! ለረጅም ፡ ሰዓት ፡ ሲያባርሩት ፡ ቆዩ ። አንዱ ፡ ገመዱን ፡ ልክ ፡ አንገቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊያጠልቅበት ፡ ሲቃረብ ፡ አያቹ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ደነገጥሁ ። ፈቲንም ፡ አዙሬ ፡ ጸሎቴን ፡ ጀመርኩ ። ከጥቂት ፡ ያቂታዎች ፡ በኋላ ፡ ዘወር ፡ ስል ፡ የእኔ ፡ ሻንቆ ፡ እንኳን ፡ ለያዝ ፡ ቀርቶ ፡ በሚያዩ ፡ ላይ ፡ ሲሯሯጥ ፡ ላየው ፡ አዲስ ፡ ጉልበት ፡ ያገኘ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ሜዳውን ፡ እያርገበገበ ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

ብትሰጠኝ ፡ የፈለግኸውን ፡ ሁሉ ፡ ከማድረግ ፡ ወደኋላ ፡ አልልም ። ቢሻህ ፡ የአባቴን ፡ ተወዳጅ ፡ የእጅ ፡ ብረት ፡ ወይም ፡ ጐራዴ ፡ ሠርቼ ፡ እሰ ጥሃለሁ ። የጐራዴው ፡ ስለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባ ልም ፤ ግና ፡ ከከንድህ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ ከማድ ረግህ ፡ ጐማምዶ ፡ ገብቶ ፡ ታገኝዋለህ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ እንኳ ፡ አይበግረውም ።» ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ካዝቢች ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠውም ።

«ሻንቆን ፡ በሁለት ፡ የአፍንጫ ፡ ቀዳዳዎቹ አረፋ ፡ እያስጐፈጥህ ፡ ስትጋልብ ፡ በመጀመሪያ ፡ ያየሁህ ፡ እለት ፡ በዓለም ፡ ያለው ፡ የሌለው ፡ ስሜቴ ፡ ሁሉ ፡ ተገፎ ፡ መንፈሴ ፡ ለእሱ ፡ ብቻ ፡ ገበረ ። አሁንማ ፡ በአባቴም ፡ ምርጥ ፡ ፈረሶች ፡ መጋለቡ ፡ እንኳ ፡ ውርደትና ፡ እፍረት ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ። በሕልሜም ፡ ሆነ ፡ በእውኔ ፡ በሐ ዘን ፡ እጐንብሼ ፡ ለዘወትር ፡ ፍክ ፡ የሚለኝ ፡ የሻንቆ ፤ ያ ፡ ኩሩ ፡ አረማመዱ ፤ እንደቀስት ፡ የተወጠረው ፡ ጀርባው ፤ ሲሆን ፡ እነዚያም ፡ ኩል ፡ የመሰሉ ፡ ዓይኖቹ ፡ ፍጥጥ ፡ ብለው ፡ ሲያ ዩኝ ፡ ሲያወያዩኝ ፡ የሚፈልጉ ፡ ይመስለኛል ። ካዝቢች ፤ ይሀን ፡ ፈረስህን ፡ ካልሸጥህልኝ ፡ የሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ።» እያለ ፡ እንባ ፡ ባሻ ከረው ፡ ድምጽ ፡ ይለምነው ፡ ነበር ። በእርግጥም ፡ እዛማት ፡ ያለቅሳል ። የሚገርመው ፡ ግን ፡ እሳ ቸውን ፡ ጥሎ ፡ የሚያለቅስ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ እንደሌለ ፡ አውቅ ፡ ነበር ። ለልቅሶው ፡ አበፈጁ ፡ ሁኖ ፡ የሰማሁት ፡ ሳቅ ፡ ነበር ።

«ስማኝ ፡ ለሻንቆ ፡ ስል ፡ የፈለግከውን ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ ወደኋላ ፡ እንደማልል ፡ ገል ጨልሃለሁ ። ብትፈልግ ፡ እህቴን ፡ ሠርቂ ፡ ላምጣልህ ። በዘፈንዋ ፤ በውዝዋዜዋ ፤ ይህ ፡ ቀረሽ ፡ የማትባል ፡ ናት ። የወርቅ ፡ ጥልፍ ፡ እ ጇ-ሥራዋ ፡ እጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ። የቱርኩ ፡ ሡልጣን ፡ እንኳ ፡ ይችን ፡ የመሰለች ፡ ሚስት ፡ አላገቡም ። ከፈለግክ ፡ ነገ ፡ ማታ ፡ ከወን ዙ ፡ ዳር ፡ ጠብቀን ፡ ይኖት ፡ ዱብ ፡ ልበል ፤ ወንዙን ፡ አሻግሬ ፡ እስክሚቀጥለው ፡ መንደር ፡ ድረስ ፡ ሸኝቼአት ፡ እመጣለሁ!.. አሁን ፡ ቤላ ፡ ለሻንቆ ፡ ታንሳለች?»

ካዝቢች ፡ እውንም ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ጀሮ ፡ ዳባ ፡ ብሎ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፤ ለመ ልስ ፡ ያህል ፡ እንድ ፡ ጥንታዊ ፡ ዘፈን ፡ ማንጐራ ጉርን ፡ ጀመረ ።

የእኛ ፡ እገር ፡ ወይዛዝርት ፡ ወደርም ፡ የላቸው ፤
እንደ ፡ ጥዋት ፡ ኮከብ ፡ ያበራል ፡ ዓይናቸው ፤
ከእንደ ፡ ወይዘሪት ፡ ጋር ፡ ከጀመርህ ፡ ጨዋታ ፡
ሳይታወቅ ፡ ቀኑ ፡ ያልፋል ፡ በደስታ ።
የልጅነት ፡ ዘመን ፤ ሆኖም ፡ ነፃነቱ ፤
ከሁሉ ፡ ያማረ ፤ ጣፋጭ ፡ ነው ፡ ስሜቱ ።
በመርቅ ፡ ደርዘን ፡ ሴት ፡ ቢሹ ፡ ይገዛሉ ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

ቶያ ፡ በዚያች ፡ ጕጆ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ ተነሳ ። ሁኔታውም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነበር ። አሣማት ፡ ቡሞትዴቂ ፡ ልብሱን ፡ አንጠል ጥሎ ፡ በሩጫ ፡ ትንፋሽ ፡ ቤት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፤ «ካገበቺ ፡ ሊገድለኝ ፡ ነበር!» አለ ። የተሰበሰበ ውም ፡ ሁሉ ፡ ከያለበት ፡ ጠበንጃውን ፡ መጮተት ፡ ጀመረ ። ከዚያ ፡ በኋላማ ፡ ምን ፡ ይወራል ... በጩኸቱ ፤ በውካታው ፤ በጠበንጃው ፡ ተኩስ ፡ ምድር ፡ ቁና ፡ ሆነች ። ካገበቺ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ እንደፍላፃ ፡ ተወርውሮ ፡ በሻንቆ ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ተኩሱን ፡ በጋሻው ፡ እየመከተ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ በሁለት ፡ በርግዶ ፡ ሽምጥ ፡ ጋለበ ።

እኔም ፡ የግሪጕሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪችን ፡ እጅ ፡ ጨብጨ ፤ «እዚህ ፡ ጉድ ፡ ውስጥ ፡ እጃችንን ፡ ሳንገባ ፡ ቶሎ ፡ ማምለጡ ፡ ይሻላል ፡» ብለው ፤

«እስቲ ፤ ፍፃሜውን ፡ እንየው ፡» ሲል ፡ መለሰልኝ ። «መጨረሻው ፡ እንደማያምር ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። እነዚህ ፡ አሴትያኖች ፡ ሲሳከሩ ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ መተራረዳቸው ፡ አይቀርም ፡» ካልሁት ፡ በኋላ ፡ በፈረሶቻችን ፡ ጉብ ፡ ብለን ፡ ወደቢታችን ፡ ዘወር ፡ አልን ።

«እና ፡ ካገበቺስ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ሆነ?» ብዬ ፡ በጉጉት ፡ ጠየቅሁት ።

የተቀዳለትን ፡ ሻይ ፡ ጨልጦ ፤ «እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ይሆናሉ? እመለጣ!»

ደፋር ፡ ፈረስ ፡ በሐብት ፡ ኧረ ፡ ከየት ፡ ሊያገኙ ፡ ሚዳ ፡ የሚሞላ ፡ የነፋስ ፡ ቁራኛ ፤ መቼም ፡ መች ፡ የማይክድ ፤ ታማኝ ፤ እውነተኛ ፤ እንደፈረስ ፡ ያለ ፡ የት ፡ አለ ፡ ጓደኛ?

አሣማት ፡ ሻንቆን ፡ ለማግኘት ፡ ያልገባበት ፡ ቀዳዳ ፡ የለም ። በልቅሶ ፤ በሙገሳ ፤ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፤ ለመያለል ፡ ሞከረ ። ሁኖም ፡ ካገበቺ ፡ ትዕግስቱ ፡ ሁሉ ፡ ስላለቀበት ፤

«አንተ ፡ ልጅ ፤ እባክህ ፡ ከፊቱ ፡ ሒድልኝ ፤ አብደሃል ፡ ልባል? በሻንቆ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ መቼም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ልትወጣ ፡ አትችልም ። ከሶስት ፡ እርምጃ ፡ ሳትሔድ ፡ በቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ይከስከስሀና ፡ ጭንቅላትህ ፡ ይፈጠፈጣል ።»

አሣማት ፡ ይህንን ፡ ሲሰማ ፡ የጉርምስና ፡ ወኔ ፡ ባንቀው ፡ ድምፁ ፤ «እኔ!» ብሎ ፡ ከመትጽበት ፡ አሣማት ፡ ጕራዴውን ፡ መዞ ፡ ካገበቺ ፡ ከለበሰው ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ ጋር ፡ የተጋጨ ፡ የጕራዴ ፡ ድምጽ ፡ በጆሮ ፡ ግንዱ ፡ ባረቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኃይለኛ ፡ ጡንቻ ፡ ያረፈበት ፡ ምት ፡ ተሰማኝ ። ወዲያውም ፡ አሣማት ፡ ተሽቀንጥሮ ፡ ከመሬት ፡ ተዘረረ ። «አሁን ፡ ጉድ ፡ ፈላ» ብዬ ፡ አስቢ ፤ ፈረሶቻችንን ፡ ከታሠሩበት ፡ ፈትቼ ፡ ወደጓሮ ፡ ወሰድኋቸው ። ያልሁት ፡ አልቀረም ፤ ትንሽ ፡ ሳይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘው ፡ አለ ። እኔም ፡ እንደአጋጣሚ ፡ እዚያም ፡ ነበርሁ ። ጨዋታው ፡ ስለፈረሶች ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። ፔኞሪንም ፡ የሻንቆን ፡ ኩሩነት ፤ ውበት ፤ ያፋርነት ፤ እያኳሸ ፡ ካሞጋገሰለት ፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ያለ ፡ ፈረስ ፡ እንደሌለ ፡ አረጋገጠለት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የታታሩ ፡ ወጣት ፡ ዓይናች ፡ በጉጉት ፡ ተቁለጨለጩ ። ፔኞሪን ፡ አይቶ ፡ እን ዳላየ ፡ ሆኖ ፡ ወሬውን ፡ ቀጠለ ። እኔም ፡ በፊናዬ ፡ አርዕስቱን ፡ ለመቀየር ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ ተፍጨረጨርኩ ። ሆኖም ፡ አዚዙሮ ፡ የሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ መግቻ ፡ የሚያደርገው ፡ የካዝቢችን ፡ ፈረስ ፡ ነው ። ወሬው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳያ ቆም ፡ አዛማት ፡ በመጣ ፡ ቁጥር ፡ የተለመደ ፡ ሆነ ። ከሶስት ፡ ሳምንታት ፡ በኋላም ፡ አዛማት ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ የፍቅርን ፡ ሚና ፡ እንደሚጫወት ፡ ተዋናይ ፡ እየገረጣ ፡ እየመነመነ ፡ እየሰለለ ፡ ሔደ ። ምን ፡ ሆኖ ፡ ይሆን?

የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳይ ፡ ፍንትው ፡ ብሎ ፡ የታየኝ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ግሪጐሪይ ፡ እሌክሳንድ ሮቪች ፡ ያንን ፡ ወጣት ፡ ወትውቶና ፡ ጐትጉቶ ፡ የመንፈስ ፡ እረፍት ፡ አሳጣው ። በመጨረሻም ፡ ጉዳዩን ፡ በግልጽ ፡ አወራው ።

«አዛማት ፤ ያህን ፡ ፈረስ ፡ ለማግኘት ፡ [illegible] ጉጉት ፡ ይሰማኛል ። ሆኖም ፡ ተስፋህን ፡ [illegible]

«ሌላው ፡ ቢቀር ፡ አልቈሰለም?»

«እሱን ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ይወቅ ። ሆኖም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እኮ ፡ የዋዛም ፡ አይደሉ ። ሲደ ባደቡ ፡ በዓይኔ ፡ አይቻለሁ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በላ ንጃ ፡ እንኳ ፡ ተዘልዝሎ ፡ ቶሎ ፡ አይወድቅም ። የመጨረሻ ፡ እስትንፋሱ ፡ እስክትከዳው ፡ ድረስ ፡ ቆሞ ፡ ይመክታል ።» ሻምበሉ ፡ ይህንን ፡ አውርቶ ፡ ለአንድ ፡ አፍታ ፡ ፀጥ ፡ አለ ። በኋ ላም ፡ በእግሩ ፡ ኮቴ ፡ ምድሩን ፡ ድው ፡ አድ ርጐ ፤

«መቼም ፡ መች ፡ ቢሆን ፡ የማይረሳ ፡ አንድ ፡ ጥፋት ፡ አድርጌያለሁ ። ወደሠፈራችን ፡ እንደተ መለስን ፡ አጥር ፡ ለብሼ ፡ የሰማሁትን ፡ ወሬ ፡ ሰግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ንገረው ፡ የሚል ፡ ሰይጣን ፡ በጆሮ ፡ ግንዴ ፡ ተጠግቶ ፡ አስወሸ ከተኝ ። ነገሩን ፡ ሲሰማ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ። ሳቀ ፡ ግን ፡ ለሸር ፡ መሆኑ ፡ በኋላ ፡ ገባኝ ።

«ውጥኑ ፡ ምን ፡ ኖሯል?»

«መቼም ፡ አንዴ ፡ ታሪኩን ፡ ከጀመርኩት ፡ አይቀር ፤ እሰከመጨረሻው ፡ ያዳምጡኝ ፤ ልጨር ስልዎት ።»

«ያህ ፡ በሆነ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ አዛማት ፡ ሳይታሰብ ፡ ከት ፡ አለ ። እንደተለመደው ፡ አ ንድ ፡ አንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ነገሮች ፡ መያሚሰጠው ፡ ወደ ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ዘንድ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ህን ፡ ደንደስ ፡ ዙሮ ፡ እንደማየት ፡ ያህል ፡ ነው ።
ለመሆኑ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ፈረስ ፡ ቢሸል
ም ፡ ምን ፡ ታደርግለታለህ?»

«የጠየቀኝን ፡ ሁሉ ፡ እፈጽምለታለሁ ።»

«ይህ ፡ ከሆነ ፤ እኔ ፡ ፈረሱን ፡ አገኝልሃለሁ ።
ይኸውም ፡ በስምምነት ፡ ነው ። የስምምነታችንን
ም ፡ ቃል ፡ ልትሞላ ፡ ማልልኝ ።»

«እኔ ፡ እምላለሁ ፤ አንተም ፡ በቃል ፡ ልት
ቆም ፡ ማል ።»

«ጥሩ ። እኔ ፡ ፈረሱን ፡ ላመጣልህ ፡ እምልል
ሃለሁ ። አንተ ፡ ግን ፡ በአፀፋው ፡ እህትህን ፡ ቤላ
ን ፡ ትሰጠኛለህ ። ሻንቆም ፡ የጋብቻ ፡ ስጦታዋ ፡
ይሆናል ። ውሉ ፡ ጠቃሚ ፡ እንደሚሆን ፡ ተ
ስፋ ፡ አደርጋለሁ ።»

አዛማት ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ በዝምታ ፡ አሳ
ለፈው ።

«አትፈልግም ፡ እንዴ? ካልፈለግህ ፡ ተወው ።
እኔ ፡ እንኳ ፡ ምራትህን ፡ የዋጥህ ፡ ሰው ፡ መስለ
ኸኝ ፡ ነበር ። ግና ፡ ከሕፃንነት ፡ ያልተላቀቅህ ፤
ለኮርቻ ፡ ያልደረሰህ ፡ ገብል ፡ ነህ ።»

አዛማት ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ብው ፡ ብሎ ፤
«አባቴስ?» ሲል ፡ ጠየቀው ።

«ምነው ፡ አባትህ ፡ እቤት ፡ ተቀምጠ ፡
ነው ፡ የሚውል ...? ወያውሎም ፡ አያወጣ ...?»

«አዎን ፤ ያወጣል ።»

«ታዲያ ፡ ትሰማማለኻ?»

አዛማት ፡ በሹክሹክታ ፡ ልክ ፡ እንደሞት ፡
ግርጥት ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«አዎን ፤ እስማማለሁ ። እኮ ፡ መቼ ፡ ይሁን?»

«ካገባቺ ፡ ከሰሞኑ ፡ አንድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
በጐች ፡ ይዞ ፡ ወደእኔ ፡ ብቅ ፡ ይላል ፤ እና ፡ ከዚያ ፡
በኋላ ፡ ያለውን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተወው ። ግን ፡
በአንተ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መሐላ ፡ እንዳይ
ጓደል ፡ አስብበት ።»

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተዋውለው ፡ ቃል ፡ አስረው ፡
ተለያዩ ። ሆኖም ፡ ውሉ ፡ ተገቢ ፡ እንዳልነበረ ፡
እሙን ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በመመልከት ፡ ለፔ
ቾሪን ፡ ምክር ፡ አዘል ፡ የሆነ ፡ አስተያየቴን ፡
ሰንዝሬለት ፡ ነበር ። ግን ፡ እሱ ፤ «ያች ፡ የቸር
ከስ ፡ ባላገር ፡ ልጅ ፡ እኔን ፡ የመሰለ ፡ ባል ፡
ከተገኘ ፡ ጠልታ ፡ ነው? (ወጣም ፡ ወረደ ፡ በአ
ገሩ ፡ ባሕል ፡ መሠረት ፡ ባሏ ፡ መሆኔ ፡ አልቀ
ረም ፡) ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ካገቢች ፡ መቀጣት ፡
ያለበት ፡ ወሮ ፡ በላ ፡ ነው ፡» ሲል ፡ መለሰልኝ ።
እስቲ ፡ እንግዲህ ፡ እርስዎ ፡ ይፍረዱና ፡ ለዚህ ፡
ዓይነቱ ፡ አንጋገር ፡ ምን ፡ መልስ ፡ ይሰጠዋል?
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ስምምነታቸውን ፡ እንዴት ፡
ሊያሚሉት ፡ እንደሚችሉ ፡ ምንም ፡ የማውቀው ፡
ነገር ፡ አልነበረም ። አንድ ፡ ቀን ፡ ካገቢች ፡
ወደእኛ ፡ ሠፈር ፡ ጐራ ፡ ብሎ ፡ በግና ፡ ማር ፡
ያስፈለገን ፡ እንደሆነ ፡ ጠየቀን ። እኔም ፡ የምንሻ ፡
መሆናችንን ፡ ገለጽሁለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዛማት ፡» ሲል ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ወጣቱን ፡ ተጣራና ፤ «ነገ ፡ ሻንቆ ፡ በእጇ ፡ ይገባል ። ዛሬ ፡ ማታ ፡ ቤላ ፡ እዚህ ፡ መጥታ ፡ ካላደረች ፡ የሻንቆን ፡ ዓይን ፡ አታየውም ።»

«ጥሩ ፡» ብሎ ፡ አዛማት ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብሎ ፡ ወደሰፈሩ ፡ ጋለበ ።

መሸትሸት ፡ ሲል ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ መሣሪያውን ፡ እንግቶ ፡ ከሰፈራችን ፡ ወጣ ፡ አለ ። እንዴት ፡ ሆኖ ፡ እንደተሳካላቸው ፡ ዝርዝሩ ፡ እኔንም ፡ አልገባኝም ። ሆኖም ፡ ማታ ፡ ከአዛማት ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ እጅ ፡ ለግር ፡ ታሥራ ፡ ፊቷ ፡ በሻሽ ፡ የተሸፈነ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በአዛማት ፡ ኮርቻ ፡ ላይ ፡ ይዘው ፡ እንደተመለሱ ፡ ዘበኛው ፡ አይቶ ፡ ነገረኝ ።

«ፈረሱስ?» ስል ፡ የሻምበሉን ፡ ጠየቅሁት ።

«ያቱቱን ፡ ንክ ፡ በማግሥቱ ፡ ካዝቢች ፡ የሚሸጣቸውን ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በጐች ፡ እየነዳ ፡ በማለዳው ፡ ብት ፡ አለ ። ረረሱንም ፡ ከአጥሩ ፡ አጠገብ ፡ ትቶ ፡ ወደእኔ ፡ መጣ ። እኔም ፡ ሻይ ፡ አፍልቼ ፡ ጋበዝሁት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በጠባዩ ፡ ዱርዬ ፡ ቢሆንም ፡ ትሉ ፡ እጠሩሂያ ፡ አለንና፤ ከዚያም ፡ ሻያችንን ፡ እየጠጣን ፡ ያጣጥ ፡ ያቶጠጉን ፡ ስንቀባጥር ፡ ቆየን ። በድንገትም ፡ የካዝቢች ፡ መንፈስ ፡ ተረብሾ ፡ አየሁት ። መዴያውም ፡ ግንባሩ ፡ በንዴት ፡ ተኮማትሮ ፡ ወደመስኩቱ ፡ ተወረወረ ። ክፉቱ ፡ መስኩቱ ፡ የሚያሳየው ፡ የፊት ፡ ለፊቱን ፡ በር ፡ ሳይሆን ፡ የጓሮውን ፡ ነበረ ።

«ምን ፡ ሆንክ?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

መላ ፡ ሰውነቱ ፡ እየተንዘፈዘፈ ፤ «ፈረሴ ... ሻንቆ ... ፈረሴ!» እያለ ፡ ተቅበዘበዘ ። በእርግጥም ፡ የፈረሱ ፡ ኮቴ ፡ ተሰማኝ ።

«አንድ ፡ ካዛክ ፡ ይሆናል ፡ የመጣው ፡» አልኩኝ ።

«አይደለም ። Urus yaman, yaman* ብሎ ፡ ጮኸ ፡ ልክ ፡ እንደአዳኝ ፡ ነበር ፡ ዘሎ ፡ ፈት ለክ ፡ ያለው ። ሁለቴም ፡ ተወርውሮ ፡ እዋናው ፡ በር ፡ ደረሰ ። በሩ ፡ በዘበኛው ፡ ጠመንጃ ፡ ተጋርዶ ፡ ቢቆየውም ፡ ከመቅጽበት ፡ ዘሎ ፡ አልፎ ፡ ከፊት ፡ ለፊቱ ፡ የተለጠለጠውን ፡ ሜዳ ፡ በሩጫ ፡ ተያያዘው ። አዛማት ፡ ሻንቆን ፡ እየጋለበ ፡ የሄደበት ፡ መንገድ ፡ አቧራ ፡ ተነስቶ ፡ ከሩቁ ፡ ይታያል ። ካዝቢች ፡ ጠመንጃውን ፡ አቀባብሎ ፡ እየሮጠ ፡ ተኩሰ ። አላማው ፡ መምታት ፡ አላመምታቱን ፡ ለማወቅ ፡ በመጀመሪያ ፡ ባለበት ፡ ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ይመለከት ፡ ገባ ። በኋላ ፡ ግን ፡ መሳቱን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ እያጕራ ፤ ጠመንጃውን ፡

---

*ሩሲያዊያን ፡ አይረቡም ፡ መጥፎዎች ፡ ናቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተገኘ ፡ አንገቱን ፡ በቢላዋ ፡ እንደሚጨል
ፋት ፡ ያውቃል ። ስለዚህም ፡ ነው ፡ ፈረሱን ፡
ከሰረቀ ፡ በኋላ ፡ ዱካው ፡ የጠፋው ። እንደምገም
ተው ፡ ከአብራኮች ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ያን ፡
የሚወደውን ፡ ግልቢያ ፡ ሲያሳድድ ፡ ቴሪክ ፡
ወይም ፡ ኩባን ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ የቀረ ፡ ይመስለ
ኛል ። ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ሕይወት ፡ ሊኖረው ፡
እንደማይችል ፡ ግን ፡ እሙን ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ ታላቅ ፡ ሽክም ፡ ነበር ።
የቼርከሷ ፡ ልጃገረድ ፡ በግሪጐሪይ ፡ አሌክሳን
ድሮቪች ፡ ቤት ፡ መኖሯን ፡ እንደሰማሁ ፤ የማ
ዕረግ ፡ ልብሴን ፡ ለብሼ ፡ ጎራዴዬን ፡ ታጥቄ ፡
ጐራ ፡ አልኩ ። ስገባ ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳን
ድሮቪች ፡ ከመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ጭንቅ
ላቱን ፡ በእንድ ፡ እጅ ፡ አስደግፎ ፡ በሁለተኛው ፡
እጅ ፡ ትንባሆ ፡ የሌለው ፡ ፒፓ ፡ ለጉም ፡ ተጋድ
ሞ ፡ አገኘሁት ። እንደገባሁ ፡ የሚቀጥለው ፡
ክፍል ፡ ተዘግቶ ፡ ቁልፉ ፡ ከእላዩ ፡ ላይ ፡ አለመ
ኖሩን ፡ አስተዋልኩ ። መግባቴንም ፡ ለማብ
ሰር ፡ ወለሉን ፡ በተረከዜ ፡ ከደበደብሁ ፡ በኋላ ፡
በሳል ፡ ምልክት ፡ ገለጽሁ ። ሆኖም ፡ እሱ ፡
ሰምቶ ፡ እንዳልሰማ ፡ ጭጭ ፡ አለኝ ። ድም
ዤን ፡ ጐርነን ፡ አድርጌም ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፤

«የመቶ ፡ አለቃ ፤ ምነው ፡ ዝም ፡ አሉኝ?
አመጣጤ ፡ ወደእርስዎ ፡ እኮ ፡ ነበር?»

«አ! ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ ጤና ፡ ይስጥ

ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቀለጣጥሞ ፡ በመራት ፡ ላይ ፡
እየተንከባለለ ፡ ልክ ፡ እንደሕፃን ፡ ልጅ ፡ ተንሰ
ቀሰቀ ። በሠፈሩ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ወጥ
ተው ፡ ሁኔታውን ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ። እሱ ፡
ግን ፡ ማንንም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አላየም ። ሰዎቹም ፡
ትንሽ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡
ወደሠፈራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ። እኔም ፡
የበጐቹን ፡ ሒሳብ ፡ ከተኛበት ፡ ድረስ ፡ ሄጀ ፡
ከጐኑ ፡ አስቀምጬለት ፡ ተመለስኩ ። ገንዘቡ
ንም ፡ ሳያነሳው ፡ በዚያው ፡ እንደተጋደመ ፡
ቀረ ። የሚገርመው ፡ ከተኛበት ፡ ሳይነሳ ፡ ሌሊ
ቱን ፡ በዚያው ፡ አነጋው ። በጥዋቱ ፡ ተነስቶ ፡
የፈረሱን ፡ ሌባ ፡ ለማወቅ ፡ ወደሠፈራችን ፡ መጣ ።
የበር ፡ ዘበኛውም ፡ ሻንቆን ፡ በያፋ ፡ የወሰደው ፡
አዛማት ፡ መሆኑን ፡ ስላየ ፡ ምስጢርነቱ ፡ አልታ
የውም ። ካዝቢች ፡ የአዛማትን ፡ ስም ፡ እንደ
ሰማ ፡ ዓይኑ ፡ በንዴት ፡ ደም ፡ ለብሶ ፡ ለመማ
ጠን ፡ ወደአዛማት ፡ አባት ፡ ቤት ፡ አመራ ።»

«ታዲያ ፡ አባትየው ፡ ምን ፡ አለ?»

«አባትየው ፡ ቤት ፡ አልነበረም ። ወይውጭ ፡
ከወጣ ፡ ስድስት ፡ ቀናት ፡ ሆኖታል ። አዛማትም ፡
እህቱን ፡ ለመስረቅ ፡ የቻለው ፡ ይህን ፡ አጋጣሚ ፡
አግኝቶ ፡ ነው ።

አባትየው ፡ ከሄደበት ፡ ሲመለስ ፡ ሁለቱ ፡
ልጆቹ ፡ የውኃ ፡ ሽታ ፡ ሆነው ፡ ቆዩት ። አዛማት ፡
በብልጠቱ ፡ ቆቅ ፡ ነው ። ያህን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ፡ በአልጋው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ እንዲህ ፡ አልኩት ፤

«ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ይስሙኝ ። የፈጸሙት ፡ ተግባር ፡ ግፍ ፡ ወንጀል ፡ እንደሆነ ፡ ማመን ፡ ይገባዎታል ።»

«ጥፋቱ ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው?»

«ጥፋቱማ ፡ ቢላን ፡ መጥለፍዎ ፡ ነዋ! ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ አዛማት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ጉድ ፡ ኑሯል? እንደእኔስ ፡ ከሆነ ፡ ጥፋትዎን ፡ ማመን ፡ አለበ ዎት ፡ አላለሁ ።»

«ለምን ፡ ብዬ?! ደስ ፡ አለችኝ ...»

ለእንዲህ ፡ ላለው ፡ አነጋገር ፡ ምን ፡ መል ስ ፡ ይሰጠዋል? እኔም ፡ የምለው ፡ ቅጡ ፡ ጠ ፋኝ ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በዝምታ ፡ ከደበንሁ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ልጅቷን ፡ ለአባቷ ፡ መመ ለስ ፡ እንዳለበት ፡ አጥብቄ ፡ ወተወትሁት ።

«መልሼ ፡ የምሰጥበት ፡ ምክንያት ፡ አይታየ ኝም ፡» አለኝ ።

«እዚህ ፡ መኖሯን ፡ ያወቀ ፡ አለትስ?..»

«እንዴት ፡ አድርጐ ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል?»

ለዚህም ፡ ቢሆን ፡ የምሰጠው ፡ መልስ ፡ አጣሁ ።

ይሄኔ ፡ ፔቮሪን ፡ ከተጋደመበት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

«ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ በእውነት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነዎት ። ይህች ፡ ጮርቃ ፡ ኮረዳ ፡

ልኝ ። ፒፓ ፡ ማጤስ ፡ ይፈልጋሉ?» በማለት ፡ ከተኛበት ፡ ቀና ፡ ሳይል ፡ መለሰልኝ ።

«የሻምበልዎ ፡ መሆኑን ፡ እያውቁም ፤ ማክ ሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ሊሉኝ ፡ እንዴት ፡ ደፈሩ?»

«ምን ፡ ልዩነት ፡ ያመጣል ፤ ይልቅስ ፡ አረፍ ፡ ብለው ፡ ሻይ ፡ መጠጣት ፡ አይፈልጉም? በው ስጤ ፡ ያለውን ፡ ጥቦትና ፡ ጭንቀት ፡ ቢያ ውቁ ...»

ወደአልጋው ፡ እያመራሁ ፤ «ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ አውቃለሁ ፡» ብዬ ፡ ባጭሩ ፡ መለስ ኩለት ።

«ካወቁም ፡ መልካም ። ሆኖም ፡ ሁሉን ፡ ለመዘከዘክ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ።»

«የመቶ ፡ አለቃ ፡ የሠሩት ፡ ወንጀል ፡ እኔ ንም ፡ እንደሚያስጠይቀኝ ፡ ያውቃሉ?»

«ለምን ፡ አላውቅም? ታዲያ ፡ ምን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ተፈጠረ? እስካሁንስ ፡ ማንኛውንም ፡ ችግርም ፡ ሆነ ፡ ያስታ ፡ ባንድ ፡ ስንካፈል ፡ ቆይተን ፡ የለም?!»

«ጊዜው ፡ የዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ። ቀልዱን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ያቁሙና ፡ ጉራዴውን ፡ ያስረክቡኝ ።»

«ሚትካ ፡ ጉራዴዬን ፡ አምጣልኝ ፡» ብሎ ፡ ተጣራ ። ሚትካም ፡ እንደታዘዘው ፡ ጉራዴ ውን ፡ አመጣ ። የወታደር ፡ ግዳጁን ፡ ከፈጸመሁ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

«የመንደሯ ፡ ናፍቆት ፡ እንኳ ፡ እስከዚህም ፡ አልጐዳትም ። ከሠፈሯ ፡ ሆና ፡ የምታየው ፡ ጋራ ፡ ሸለቆ ፡ ከዚህም ፡ ሆና ፡ ታየዋለች ። ለእን ደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የመንደር ፡ ፍቅራቸው ፡ ከዚህ ፡ የሚያልፍ ፡ አይደለም ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ በየእለቱ ፡ የሚሰጣት ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የለውም ። በመጀመሪያ ፡ የሚሰጣትን ፡ ስጦታ ፡ ሁሉ ፡ በንቀት ፡ ትገፈትረው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ስጦታው ፡ ወደደንገጡሯ ፡ እጅ ፡ ሲገባ ፡ ስታይ ፡ ቅናት ፡ አደረባት ። አይ ፡ ስጦታ! ሴት ፡ ለእንዲት ፡ ቡጫቂ ፡ ብልጭልጭ ፡ ጨር ቅ ፡ ብላ ፡ ምን ፡ የማታደርገው ፡ ነገር ፡ ይገኛል! ብቻ ፡ አሁን ፡ ይኸ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ... እና ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ይህችን ፡ ሴት ፡ ለመማረክ ፡ ሲል ፡ ያልሆነው ፡ ነገር ፡ የለም ። በመሀሉም ፡ የታታርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተማረ ። እሷም ፡ የእኛው ፡ ቋንቋ ፡ ይገባት ፡ ጀመር ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ስትፈራ ፡ ስትችር ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ማየት ፡ ጀመረች ። ይህም ፡ ሆና ፡ ሐዘኗ ፡ ገና ፡ አልለቀቃትም ፡ ነበር ። ከወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ የሐገሯን ፡ ዘፈን ፡ በዝማታ ፡ ስታዜም ፡ ስሰማት ፡ ሆዴ ፡ መንቦጫቦጨን ፡ እቋርጠ ፡ እያውቅም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመስኮቷ ፡ በኩል ፡ ሳልፍ ፡ ያየሁት ፡ ትርኢት ፡ ለምንጊዜም ፡ አይረሳኝ ። ቤላ ፡

በዚያ ፡ አረመኔ ፡ እጅ ፡ ከገባች ፡ ወይ ፡ ይገላ ታል ፡ ወይም ፡ ይሸጣታል ። ከእንግዲህ ፡ የፈለበ ውኃ ፡ አይታፈስም ፡ ነውና ፡ ባለፈ ፡ ነገር ፡ መራቀቁን ፡ እንተወው ። ከፈለጉ ፡ ጐራዴዬን ፡ ይ ውሰዱ ። እሷን ፡ ግን ፡ አይንኩብኝ ።»

«እንዳያትስ ፡ ሊፈቅዱልኝ ፡ ይችላሉ?»

«እዚያ ፡ እበሩ ፡ ጥግ ፡ ተሸጉጣለች ። እኔም ፡ እንኳ ፡ ለማየት ፡ ሞክሬ ፡ ሳይሳካልኝ ፡ ቀርቷል ። በሻሿ ፡ ፊቷን ፡ ሸፍና ፡ ከሚደግፋው ፡ ግዕዘን ፡ ተሸንጉራ ፡ እትናገር ፡ እትጋገር ፡ ሰውን ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አታይ ፡ ልክ ፡ እንደዱር ፡ ሚዳቋ ፡ አድፍጣ ለች ፡» ብሎ ፡ ጠረጴዛውን ፡ በንዴት ፡ በቡጢ ፡ ወገረው ። ከዚያም ፡ ቀጠል ፡ አድርጉ ፣ «የኋላ ፡ ኋላ ፡ ባሏ ፡ እኔ ፡ እንደምሆን ፡ እንድትነግራትና ፡ እንድታለማምዳት ፡ ብዬ ፡ የታታር ፡ ቋንቋ ፡ የምትችለውን ፡ የቡና ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ በደንገ ጡርነት ፡ ቀጥሬላታለሁ ።»

«እንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ የሚመለከቱትም ፡ ሆነ ፡ የሚሠሩት ፡ በራ ሳቸው ፡ መንገድ ፡ ስለሆነ ፣ የነበረኝ ፡ ምርጫ ፡ ተስማምቶ ፡ መለያየት ፡ ብቻ ፡ ነበረ ።»

«በመጨረሻስ ፡ ምን ፡ ሆነ? ልጅቷን ፡ ለያለማምዳት ፡ ቻለ? ወይስ ፡ መንደሯንና ፡ ቤተ ሰቦቿን ፡ ስትናፍቅ ፡ ከንጉጉቷ ፡ ተዘግቶባት ፡ ቀረች?» ሰል ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪችን ፡ ጠየቅሁት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚነበበው ፡ «ምነው ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ በሆነ?» የሚል ፡ ነበር ። አቤት ፡ ዓይኖቿ! ልክ ፡ እንደሚነድ ፡ የምድጃ ፡ ከሰል ፡ ያበራሉ ። ፒዮሪን ፡ ንግግሩን ፡ ቀጥሎ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፡ «ስሚኝ ፡ የእኔ ፡ ቆንጆ ፡ የእኔ ፡ እሩጎሩሳ ፡ በላዩ! እንዴት ፡ እንደምወድሽ ፡ ይገባሻል? ለአንቺም ፡ ይስታ ፡ ስል ፡ ምንም ፡ ከማድረግ ፡ ወደኋላ ፡ አልልም ። ግን ፡ ለሁልጊዜውም ፡ በዚሁ ፡ የምትቀጥይ ፡ ከሆነ ፡ ሞቲን ፡ እመር ጣለሁ ። ሙሉ ፡ ይስተኛ ፡ እሆናለሁ ፡ ስትይ ፡ ቃል ፡ ግቢልኝ ።»

በዚህ ፡ ወቅት ፡ ለይቂቃ ፡ ያህል ፡ የትካዜ ፡ መልክ ፡ አሳየች ። እኒያ ፡ ጠቋቁር ፡ ዓይኖቿ ፡ የእሱን ፡ ገጽ ፡ አሳደው ፡ ካገኙት ፡ በኋላ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ፡ መስማማቷን ፡ በአንገቷ ፡ ወዝውዛ ፡ ነገረችው ። እጅዋንም ፡ ጨብጠ ፡ ሊስማት ፡ ይታገላት ፡ ገባ ። እሷም ፡ በደከመ ፡ እንደበት ፡ ደግማ ፡ ደጋግማ ፡ «አባከዎን ፡ ይተውኝ ፤ ይተውኝ ፡» ስትል ፡ ለመነችው ። ሆኖም ፡ እሱ ፡ ትግሉን ፡ አልተወውም ። ቤላ ፡ እንባ ፡ በእንባ ፡ ሆና ፡ እየተንዘፈዘፈች ፤

«እም! ምርኮኛ ፤ ባሪያህ ፡ ስለሆንኩ ፡ በጉልበትህ ፡ ተመክተህ ፡ የፈለግኸውን ፡ ልታደርግ ፡ መብት ፡ አለህ ፡» ብላ ፡ ለቅሶዋን ፡ ቀጠለች ።

ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ይሄኔ ፡ ግን ባሩን ፡ በቡጢው ፡ መቶ ፡ ወደሚቀጥለው ፡

እንገቷን ፡ ደፍታ ፡ በቦርጭማ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ። ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ከፊቷ ፡ ቁሞ ፡ እንዲህ ፡ ይላታል ፤

«ስሚኝ ፡ የእኔ ፡ ቆንጆ! ወጣም ፡ ወረደ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የእኔ ፡ ሚስት ፡ እንደምትሆኝ ፡ አታውቂም? ከሆነስ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ ታሰቃይ ኛለሽ! ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንድ ፡ የምትወጅው ፡ ያገርሽ ፡ ልጅ ፡ አለ? እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ እትጨነን ፡ ንገሪኝና ፡ አሁኑኑ ፡ ልልቀትሽ ።» በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቤላ ፡ ጫንቃዋን ፡ አራግባ ፡ «የለኝም ፡» ለማለት ፡ ጭንቅላቷን ፡ ነቀነቀች ። እሱም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጥሎ ፤ «ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ፈጽሞ ፡ ቀፈፍሁሽ ፡ ልበል!» ሲል ፡ ቢጠይቃት ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳትሰጠው ፡ በከባዱ ፡ ተንፍሳ ፡ ዝም ፡ አለችው ። ውትወታውን ፡ በመቀጠል ፤ «ሃይ ማኖትሽ ፡ እኔን ፡ እንድትወጂ ፡ አይፈቅድል ሽም?» ይላታል ። አሁንም ፡ ከቤላ ፡ አንደበት ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ አልተሰነዘረም ። ሆኖም ፡ ፊቷ ፡ እየረገጣ ፡ ሄደ ። «ለመኝኝ ፡ በዓለም ፡ ያለው ፡ አላህ ፡ ለሁላችንም ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ነው ። እኔ ፡ አንቺን ፡ እንድወድ ፡ ከፈተደ ፡ አንቺ ፡ እኔን ፡ እንዳትወጂ ፡ የሚያደርግበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ የለውም ።» ይሀን ፡ ሲል ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ በአዕምሮዋ ፡ እንደተሠረፀ ፡ ሁሉ ፡ ዓይኖቿን ፡ በጓደኖቹ ፡ ላይ ፡ ተክላ ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ ተመለከተችው ። ከጓደኖቹ ፡ ብሌን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የእራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ እስተዳደግና ፡ ጠባይ ፡ አላቸው ።» በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንደሮቪች ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ የማርሽ ፡ ዜማ ፡ ያሏሟ ፡ ገባ ።

ያልሁት ፡ አልቀረም ። የተገዛው ፡ ስጦታ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የታሰበውን ፡ ያህል ፡ አልሠራም ። ከዚህ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በኋላ ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፤ ቤላ ፡ ትንሽ ፡ ለስላሳ ፡ ከመሆኗም ፡ ሌላ ፡ በእሱ ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ እምነት ፡ እደረባት ። አንድ ፡ ቀን ፡ ጥዋት ፡ ፈረሱ ፡ እንዲጫን ፡ አዝዞ ፤ የቸርኬስ ፡ የአገር ፡ ባሕል ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፤ መሣሪያውን ፡ ታጥቆ ፤ እሷ ፡ ወደአለችበት ፡ ክፍል ፡ ገብቶ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

«ቢላዬ! እንደምወድሽ ፡ ይገባሻል ። ማንነቴን ፡ ስታውቂ ፡ ትወጂኛለሽ ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ ጠለፍሁሽ ። ሆኖም ፡ እንደተሳሳትሁ ፡ ገባኝ ። በይ ፡ እንግዲህ ፤ በደህና ፡ ሁኚ ። በዓለም ፡ ያለሽ ፡ የስሜቴ ፡ ጣዖት ፡ እንቺ ፡ ብቻ ፡ ነሽ ። ከእሁን ፡ ወዲያ ፡ ከፈለግሽ ፡ ወደአባትሽ ፡ ቤት ፡ ለመመለስ ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ አለሽ ። እኔ ፡ ግን ፡ በጥፋቴ ፡ መቀጣት ፡ አለብኝ ። በይ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ። ወደየት ፡ እንደምሄድ ፡ ግን ፡ አላውቅም ። ምናልባትም ፡ የጥይት ፡ ወይንም ፡ የጐራዴ ፡ ራት ፡ ሆኜ ፡ የምቀርበት ፡ ጊዜው ፡ ተቃርቦ ፡ ይሆናል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እባክሽን ፡ እስታ

ክፍል ፡ ገባ ። እኔም ፡ ተከታትየው ፡ ዘው ፡ አልሁ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ እጅቹን ፡ አጣምሮ ፡ በንዴት ፡ እሳት ፡ ጐርሶ ፡ በነፍሱ ፡ ወለል ፡ ውስጥ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይንጐራደዳል ።

«ታዲያስ ፡ ጐበዝ!» ብለው ፤

«ምን ፤ ይች ፡ ሴት ፡ አይደለችም! ሰይጣን ፡ ናት! ሆኖም ፡ ይታዘቡኛል ፤ የኋላ ፡ ኋላ ፡ የእኔ ፡ ናት ...» ሲል ፡ መለሰልኝ ።

እኔም ፡ እራሴን ፡ ወዘወዝሁ ።

«ይበሉ ፤ እንወዳደር ፤ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ።»

«መልካም ።»

ለዚህም ፡ ውርርድ ፡ አጋና ፡ ተማተን ፡ ተለያየን ።

በማግሥቱ ፡ ወደኪዝላር ፡ ገበያ ፡ መልከተኛ ፡ ልኮ ፡ የፐርሺያን ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ በገፍ ፡ አስገዝቶ ፡ አስመጣላት ። የገዛላትንም ፡ ስጦታ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እያሳየኝ ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀኝ ፤

«ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ ይች ፡ የእዚያ ፡ እንቡጥ ፡ አበባ ፡ ይህን ፡ ስጦታ ፡ አሻፈረኝ ፡ የምትል ፡ ይመስለዎታል?»

«የቸርኬሺን ፡ ሴቶች ፡ አያውቋቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ። ከጂዎርጂያና ፡ ከትራንስካው ካዝ ፡ የታታር ፡ ሴቶች ፡ በጣም ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ያህ ፡ ያስታቸው ፡ እስከምን ፡ ጊዜ ፡ ሊቆይ ፡ ቻለ?» ብዬ ፡ ጠየቅሁ ።

«አዎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ፔቾሪንን ፡ ከየችበት ፡ ወቅት ፡ ጀምሮ ፤ በሕልሟም ፡ ሆነ ፡ በእውኗ ፡ ደጋግማ ፡ የምታየው ፡ እሱን ፡ መሆኑ ንና ፡ ማንም ፡ ወንድ ፡ እንደሱ ፡ ያልማረካት ፡ መሆኑን ፡ በኋላ ፡ ነገረችን ። ከዚያ ፡ በኋላማ ፡ ምኑ ፡ ይወራል ፤ የደስታ ፡ ኑሮአቸውን ፡ ቀጠሉ!»

«ይኸው ፡ ነው?» የሚሉ ፡ ቃላት ፡ ሳላስበው ፡ ከአፌ ፡ አመለጠ ። እንደእውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የታሪኩ ፡ ፍጻሜ ፡ አሳዛኝ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ስጠ ባበቅ ፡ ባጭሩ ፡ ስለተቀጨ ፡ አዘንኩ ። «ለመሆኑ ፡ አባቷ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ልጁ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ መሆኗን ፡ አልጠረጠረም?»

«መጠርጠሩን ፡ እንኳ ፡ ሳይጠረጥር ፡ የቀረ ፡ አይመስለኝም ። ግን ፡ ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ የሽማግሌውን ፡ መገደል ፡ ሰማን ። ታሪኩም ፡ እንዲህ ፡ ነበር ።»

ለታሪኩ ፡ የነበረኝ ፡ ጉጉት ፡ እንደገና ፡ እንሰራ ራብኝ ።

«ማረጋገጫም ፡ ባይኖረኝም ፡ ካዝቢች ፡ አባ ማት ፡ ፈረሱን ፡ የሰረቀው ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ ተመካክሮ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሳይገምት ፡ የቀረ ፡ አይመስለኝም ። እንድ ፡ ጊዜ ፡ አባትየው ፡ ልጁ ን ፡ ፍለጋ ፡ ውሎ ፡ ሲመለስ ፡ ካዝቢች ፡ ከመን ደሩ ፡ አጠገብ ፡ ሶስት ፡ ቬርስታ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡

ውሽኝ ። ላደረግኩትም ፡ ጥፋት ፡ ይቅር፡ሽኝ ፡ አትንፈጊኝ ፡» ካላት ፡ በኋላ ፡ ገጹን ፡ አዙሮ ፡ ለስንብት ፡ እጁን ፡ ወደአሷ ፡ ሰነዘረላት ። እሷ ፡ ግን ፡ የእጅ ፡ ሰላምታም ፡ ሆነ ፡ የታል ፡ መልስ ፡ ሳትሰጠው ፡ ጉልት ፡ ብላ ፡ ቀረች ። ገርበብ ፡ ባለው ፡ በር ፡ ቀዳዳ ፡ አጮልቂ ፡ ስመለ ከታት ፡ ሁኔታዋ ፡ አሳዘነኝ ። ያ ፡ ውብ ፡ ትንንሽ ፡ ፊቷ ፡ በሐዘን ፡ ተጨማዶ ፡ ታየኝ ። ፔቾሪን ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ስላላገኘ ፡ ወደበሩ ፡ ማምራት ፡ ጀመረ ። መላ ፡ ሰውነቱ ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር ። ይገርምዎታል ። ያን ፡ የዘረዘረውን ፡ ሁሉ ፡ ዛቻ ፡ በድርጊት ፡ ያውለዋል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አደረብኝ ። እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ፡ ይሁን ፤ ይህን ፡ ከማድረግ ፡ የሚያፈገፍግ ፡ ሰው ፡ አይደ ለም ። ለመውጣት ፡ ከበራፉ ፡ ሲደርስ ፤ ቤላ ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ዘላ ፡ እያለቀሰች ፡ በአንገቱ ፡ ላይ ፡ ተጠመጠመችበት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ ከመገዛያው ፡ ኋላ ፡ ቁሚ ፡ ሳላስበው ፡ አብሪ ያት ፡ አለቀስሁ ። ብቻ ፡ ማልቀስ ፡ ስልም ... ብቻ ፡ ቂልነት ፡ ነው ...»

ሻምበሉ ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ዝም ፡ አለ ። ቀጥሎም ፡ በእጁ ፡ ሪዙን ፡ እያፍተለተለ ፤ «የእውነት ፡ ለመናገር ፡ ከተፈለገ ፤ ቤላ ፡ ትመ ያው ፡ እንደነበረ ፤ እንደእሷም ፡ የወደድችኝ ፡ ሴት ፡ በሕይወቱ ፡ በሙሉ ፡ አላጋጠመኝም ። ይህን ፡ ሳስበው ፡ በጣም ፡ ያፈንትኛል ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

እድፍጦ ፡ ቆየው ። ጊዜው ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ሽማግሌው ፡ ከአጃቢዎቹ ፡ ተለይቶ ፡ በሐዘን ፡ ተውጦ ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ጉልም ፡ ጉልም ፡ ሲል ፡ ካገዚች ፡ ከተደበቀበት ፡ ቁጥ ቋጦ ፡ እንደድመት ፡ ዘሎ ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ገብ ፡ ብሎ ፡ በጉራዴ ፡ ባንድ ፡ ምት ፡ ወግቶ ፡ ከጣለው ፡ በኋላ ፡ ሽመጠጠ ። እንዳንዶቹ ፡ የሽማግሌው ፡ ተከታዮች ፡ ሁኔታውን ፡ ከሩቁ ፡ ሆነው ፡ አይ ተው ፡ ኑሮ ፡ ካገዚችን ፡ ለመያዝ ፡ ቢሞክሩም ፡ ሊደርሱበት ፡ አልቻሉም ።»

«ታዲያ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ካገዚች ፡ የሻን ቆንም ፡ ዋጋ ፡ አገኘ ፤ ቂም ፡ በቀሉንም ፡ ተወጣ ፡ ማለት ፡ ነዋ!» ስል ፡ የተራኪዬን ፡ አስተሳሰብ ፡ ለማወቅ ፡ ፈለግሁ ።

«እምን ፤ ባህላቸው ፡ ይህን ፡ እንዳይሠሩ ፡ አይከላከልም ።»

ሩሲያዊ ፡ ሁሉ ፡ ከሚኖርበት ፡ አካባቢ ፡ ባሕ ልና ፡ ወግ ፡ ጋር ፡ ለመለማመድ ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ አስገረመኝ ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ችሎታ ፡ መጥፎ ፡ ይሁን ፡ ጥሩ ፡ አላውቅም ። ሆኖም ፡ እንድ ፡ ለ. ታረም ፡ የማይችል ፡ ጥፋት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በረጋ ፡ መንፈስ ፡ ተስማምቶ ፡ ለመኖር ፡ መር ዳቱ ፡ አያጠረጠርም ።

ሻያውን ፡ ጠጥተን ፡ ጨረስን ። ከውጭ ፡ የተሰሩት ፡ ፈረሶች ፡ በበረዶ ፡ ውርጭ ፡ ይን ቀጠቀጣሉ ። ከወደምዕራብ ፡ ብት ፡ ያለችዋ ፡ ደብዛዛ ፡ ጨረቃ ፡ ራት ፡ ካሉት ፡ ከተራራዎች ፡ በሚበተነው ፡ በጥቁር ፡ ደመና ፡ መጋረጃ ፡ እንደምትሸፈን ፡ ያስታውቅ ፡ ነበር ። ወዲያ ውም ፡ ብት ፡ አልን ። የመንገድ ፡ ጓዴ ፡ እንደ ተነበየው ፡ ሳይሆን ፡ ደመናዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተገል ጠው ፡ በነጋታው ፡ ብሩሕ ፡ ቀን ፡ እንደሚውል ፡ ተረዳን ። በጠራው ፡ ጠሊቅ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ከዋክብት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጠላልፈው ፡ ሲያብረቀርቁ ፡ ይቆዩና ፤ ከምሥራቅ ፡ የሚመ ጣው ፡ ብርሃን ፡ እየዋጣቸው ፡ ይጠፉሉ ። ቀስ ፡ በቀስም ፡ በበረዶ ፡ የተለበጡት ፡ ተራራ ዎች ፡ ቁንጮአቸው ፡ እያበራ ፡ ሄደ ። በግራና ፡ በቀኝ ፡ ያሉትን ፡ እጹብ ፡ ድንቅ ፡ ሸለቆዎች ፡ ጉሙ ፡ እንደእባብ ፡ እየተሽለከለከ ፡ አልፎ ፡ ባሻገር ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ በሆኑት ፡ ኮረብታዎች ፡ ላይ ፡ ሲድህ ፡ ማየቱ ፡ የሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ብሩህ ፡ መሆኑን ፡ ያበስራል ።

በእካባቢው ፡ የሠፈነው ፡ ሰላም ፤ በጥዋት ፡ ፀሎት ፡ መንፈሳቸውን ፡ እንዳረኩ ፡ ሰዎች ፡ የረጋ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ የፈረሶችን ፡ ጋማ ፡ ከሚያንቀጠቀጠው ፡ ከወደምስራቅ ፡ ከሚመጣው ፡ ነፋስ ፡ በቀር ፡ በእካባቢው ፡ ፀጥ ፡ ብሏል ። በአምስት ፡ ከሳሳ ፡ ፈረሶቻችን ፡ አቃዎቻችንን ፡ ጠፍረን ፡ ያንን ፡ ጠመዝማዛ ፡ የጉድ ፡ ተራራ ፡ ተገተርነው ። የጋሪውን ፡ ማሽከ ርከሪያ ፡ ከሥር ፡ ሥሩ ፡ እየተከተልን ፡ ውሻል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እያነጣን ፡ ወደተራራው ፡ ደረት ፡ አመራን ። ተራራው ፡ ላይ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የተዘረጋው ፡ መንገድ ፡ ዱካው ፡ በዓይን ፡ እያታያም ። ከቁንጮው ፡ ላይ ፡ እራሳ ፡ እንደሚያያዝ ፡ ጥንብ ፡ አንሺ ፡ ያደሩ ፡ ጉሞች ፡ ገብ ፡ ብለዋል ። ከተራራው ፡ ሥር ፡ በረዶው ፡ እንደተከመረ ፡ ነው ። በእየር ፡ እጠት ፡ እንደልብ ፡ መተንፈሱ ፡ አስቸገረን ። ደሜም ፡ ወደጭንቅላቱ ፡ የወጣ ፡ መሰለኝ ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡ ስለሆንሁ ፡ ደስ ፡ አለኝ ። የሕፃንነት ፡ ስሜት ፡ መሆኑ ፡ ይገባኛል ። ሆኖም ፡ ከሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ተለይተን ፡ ወደተፈጥሮ ፡ እየተጠጋን ፡ በሄድን ፡ ቁጥር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ወደሕፃንነቱ ፡ ዓለም ፡ ይመለሳል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ሲወለድ ፡ እንደነበረውና ፡ በኋላም ፡ በፍጻሜው ፡ እንደሚሆነው ፡ የተጫነበትን ፡ ከባድ ፡ ሐዘንም ፡ ሆነ ፡ ችግር ፡ ያራግፋል ። እንደእኔ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞት ፡ በነዚህ ፡ የሰው ፡ እግር ፡ ዞር ፡ ባላለባቸው ፡ እጹብ ፡ ድንቅ ፡ ቅርጽ ፡ ባላቸው ፡ ተራራዎች ፡ ሽንሽን ፡ ብለው ፡ በወረዱ ፡ ሸለቆዎች ፡ የተጓዘ ፡ ሁሉ ፡ ለምን ፡ እኔ ፡ እንድሥላቸው ፡ እንድጽፋቸውና ፡ እንድተርክላቸው ፡ እንዳሰኘ ዱኝ ፡ ለረዳኝ ፡ ይችላል ። በመጨረሻም ፡ በጉዟ ፡ ተራራ ፡ ሜዳ ፡ ደርሰን ፡ አካባቢያችንን ፡ ለማድነት ፡ አረፍ ፡ አልን ። ከተራራ ፡ ቁንሥ ፡ አልሮ ፡ አልሮ ፡ ከተኰሰቱት ፡ ግራጫ ፡

ያመናዎች ፡ የሚነፍሰው ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፤ በትርቡ ፡ የበረዶ ፡ ውሽንፍር ፡ እንደሚመጣ ፡ ያበስራል ። ያህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ወርቃማ ፡ ብርሃን ፡ በእንከሮ ፡ እየተመለከትን ፡ እኛ ፤ እኛ ፡ ማለት ፡ እኔና ፡ የሻምበሉ ፡ ስለማንኛውም ፡ ነገር ፡ እረስተን ፡ ተገናንተን ፡ ቁሜ ፡ አልን ... አዎን ፤ በአፈ ታሪክም ፡ ሆነ ፡ በጽሑፍ ፡ ከተነገሩ ፡ ታሪኮች ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ መንፈስንና ፡ ስሜትን ፡ የሚያረካው ፡ ይህ ፡ የምናየው ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ የሻምበሉን ፡ ልብ ፡ ሳይቀር ፡ አዘነጋው ።

«ይህን ፡ የመሰለ ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ ለእርስዎ ፡ መቼም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም?» ስል ፡ የሻምበሉን ፡ ጠየቅሁት ።

«አዎን ፤ እንኳንስ ፡ ይኽ ፡ ይቅርና ፡ የጠበንጃም ፡ ተኩስ ፡ ይለመዳል ። በተኩሱ ፡ ድምጽ ፡ ተለምዶ ፡ የልብን ፡ ትርታ ፡ ለመግታት ፡ ይቻላል ፡ ማለቴ ፡ ነው ።»

«እረ ፡ ካሉስ ፡ የሰማሁት ፡ ለእንድ ፡ እንድ ፡ ወታደሮች ፡ የተኩሱ ፡ ጩኸት ፡ የሙዚቃ ፡ ዜማ ፡ ነው ፡ ይባላል ።»

«ከፈለጉ ፡ እንደዚያም ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፡ የሙዚቃ ፡ ዜማነቱ ፡ የልብን ፡ ትርታ ፡ ማፋጠኑ ፡ ነው ።» ካለ ፡ በኋላ ፡ ወደምሥራቅ ፡ እያመለከተ ፡ «እንዴት ፡ የተዋበ ፡ እገር ፡ ነው!» አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የጋራው ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ እንዳያዳልጡ ፡ በሐብል ፡ ለብጠናቸው ፡ የፈረሶችንም ፡ ልጓም ፡ ጨብጠን ፡ ወደቁልቁለቱ ፡ አመራን ። በስተቀኝ ፡ እንድ ፡ ኮረብታ ፡ ተጉልቶ ፡ ይታያል ። በስተግራ ፡ ካለው ፡ ጥልቅ ፡ ሸለቆ ፡ ሥር ፡ ያሉት ፡ የአሴትያን ፡ መንደር ፡ ከላይ ፡ ሆነው ፡ ሲታይ ፡ የወፍ ፡ ጐጆ ፡ ይመስላል ። ሁለት ፡ ጋሪ ፡ ብቻ ፡ የሚያስተላልፈው ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ በዓመት ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ በጨለማ ፡ የሚመላለሰው ፡ ፖስተኛ ፡ ትዝ ፡ ብሎኝ ፡ ተከዝሁ ። ከጋሪ ፡ ነጂዎቻችን ፡ እንዱ ፡ ከያሮስላቭል ፡ የመጣ ፡ ሩሲያዊ ፡ ባላገር ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ አሴቲያዊ ፡ ነበር ። አሴቲያዊው ፡ የጓለኛቹን ፡ ፈረሶች ፡ አላቆ ፡ የፊት ፡ መሪውን ፡ ፈረስ ፡ ልጓም ፡ ጨብጠ ፡ በጥንቃቄ ፡ እየመራ ፡ ሲወርድ ፡ ግድ የለሹ ፡ ሩሲያዊ ፡ ግን ፡ ከጋሪው ፡ እንኳ ፡ አልወረደም ። እንዲያውም ፡ «ሻንጣዎች ፡ ተን ከባለው ፡ እንዳይወድቁ ፡ ተጠንቀቅ ፡» ብለው ፡ «ግድየለም ፡ አያስቡ ፡ ጌታዬ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያችን ፡ አያደለም ። እነሱ ፡ ከደረሱበት ፡ እንዲሁ ፡ ሳንደርስ ፡ አንቀርም ፡» አለኝ ። እውነትም ፡ እንዳለው ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ አደገኛ ፡ መንገድ ፡ አልፈን ፡ በሰላም ፡ ደረስን ። እር ግጥ ፡ ሰዎች ፡ በይበልጥ ፡ ከተመራመሩበት ፡ ለሕይወት ፡ እስከዚህ ፡ መጠበቡ ፡ ፋይዳ ፡ እንደ ሌለው ፡ በታዮቻቸው ፡ ነበር ...

በእውነትም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ ዳግመኛ ፡ በሕይወቱ ፡ የሚያጋጥመኝ ፡ አልመሰለኝም ። ከበታቻችን ፡ ባለው ፡ በኩይ ሻአር ፡ ሸለቆ ፡ አራግቪና ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ እንደሐር ፡ ከር ፡ ተዘርግተው ፡ ከሩቁ ፡ ይታ ያሉ ። ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ የለበሰው ፡ ጉም ፡ ከኩ ይሻአር ፡ ሸለቆ ፡ አልፎ ፡ ከጥሞታ ፡ የፀሐይ ፡ ጨረር ፡ ሸሽቶ ፡ ካጠገቡ ፡ ካለው ፡ ዋሻ ፡ እየሄደ ፡ ይሸሸጋል ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ በበረዶ ፡ የተለበጡ ፡ እንደሰንሰለት ፡ የተያያዙት ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ተራሮች ፡ ይታያሉ ። የዓይን ፡ ብሌን ፡ ተወርውሮ ፡ የሚያርፍባቸው ፡ የተራራ ፡ ቁንጮዎች ፡ በሙሉ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። የለበሱት ፡ ደማቅ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ልዩ ፡ ውበትን ፡ አጐናጽፏቸው ፡ ሲታይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አትለዩኝ ፡ ያሰኛል ። ከደመና ፡ ውሽንፍር ፡ ለመለየት ፡ ከማ ይቻለው ፡ ከጥቁሩ ፡ ሰማያዊ ፡ ጉም ፡ ከሸፈነው ፡ ተራራ ፡ ሥር ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ የጀመረችዋን ፡ ፀሐይ ፡ ለማየት ፡ በታን ። ከፀሐይዋ ፡ በላይ ፡ የተዘረጋውን ፡ ቀዩ ፡ ደመና ፡ በእጁ ፡ እየጠቆመ ፡ «ውብ ፡ ቀን ፡ ይውላል ፡ አላልሁም ትም? ከሬስቶቫያ ፡ ሳንደርስ ፡ ከያዝን ፡ አጓጉል ፡ ነው ፡» ካለኝ ፡ በኋላ ፡ ወደጋሪ ፡ ነጂው ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ «ነታ ፡ በል!» ብሎ ፡ ማነሰሲም ፡ ማነሰሲሞቪች ፡ ሬሜኽበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሉ ፡ ላይ ፡ በጉልህ ፡ ታላት ፡ የተጻፈው ፡ ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. እ. ኤ. አ. በጀኔራል ፡ የር ሞሎቭ ፡ ትዕዛዝ ፡ ተተከለ ፡» የሚል ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ በመስቀሉ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ መረጃ ፡ ቢኖርም ፡ ሕገቡ ፡ የሚከተለው ፡ አፈ ፡ ታሪኩን ፡ ስለሆነ ፡ የትኛውን ፡ እንደምናምን ፡ ግራ ፡ ገባን ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ የጽሑፍ ፡ መረጃ ፡ የማመንና ፡ የመከተል ፡ ልምድ ፡ የለም ።

ኮቢ ፡ ጣቢያ ፡ ለመድረስ ፡ በለስላሳ ፡ በረዶ ፡ የተሸፈኑ ፡ ኮረብቶች ፡ መንገድ ፡ ወርደን ፡ አምስት ፡ ቬርስታ ፡ አቆልቁለን ፡ መጓዝ ፡ ነበረብን ። ፈረሶቻችን ፡ የድካም ፡ አረፋ ፡ ያጓፍጣሉ ። በኃይሉም ፡ ሆነ ፡ በግርፊያው ፡ አገራችንን ፡ የሰሜኑን ፡ የመሰለ ፡ በጨፍጋጋነቱ ፡ ብቻ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የበረዶ ፡ ውሽንፍር ፡ እኛንም ፡ በብርድ ፡ እንዘፈዘፈን ። «አይ ፡ የእኔ ፡ ግዙተኛ! አገርህ ፡ እንደልብህ ፡ የምትንከባለልበት ፡ የበረዶ ፡ ክንፎችህንም ፡ የምታራግብበት ፡ ሜዳና ፡ ሸርተቴ ፡ እንደሌለህ ፡ ሆነ ፡ በሽቦ ፡ እጥር ፡ ተዘግታ ፡ መውጫ ፡ ቀዳዳ ፡ ለመፈለግ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እንደምትጋጭ ፡ አሞራ ፡ ሆንህ ፡» እያልሁ ፡ በሐሳቤ ፡ እውጠነጥን ፡ ጀመር ።

«መጥፎ ፡ ቀን ፡ ነው ። ከሞጋግና ፡ ከደመና ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ የለም ። ከበረዶ ፡ ንቃታት ፡ ወይም ፡ ከጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እን

የተፈራረቁበት ፡ የበረዶ ፡ ግግር ፡ ከፈታችን ፡ ተነጥፎ ፡ ለጉዞአችንን ፡ የበለጠ ፡ ችግር ፡ ፈጠረብን ። በግራ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ የሸለቆ ፡ ሰንጣቂዎች ፡ ሥር ፡ የሚወርደው ፡ ፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ በበረዶ ፡ ድብቶችና ፡ ጠቋቁር ፡ ቋጥኞች ፡ ስለሚከለል ፡ ከውልብታው ፡ በቀር ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ አይታይም ። ሁለት ፡ ቬርስታ ፡ እርዝመት ፡ ያለውን ፡ የክሬስቶቫያን ፡ ተራራ ፡ ለመውጣት ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀብን ። ወዲያውም ፡ ደመናው ፡ ከበድበድ ፡ ብሎ ፡ በረዶ ፡ መጣል ፡ ጀመረ ። ነፋሱ ፡ ልክ ፡ እንደሶሎቪይ-ወንበዴ* ፡ በፉጨት ፡ እያጓራ ፡ ወደሸለቆው ፡ አመራ ። በዚህ ፡ ወቅት ፡ ከምሥራቅ ፡ በሚመጣው ፡ ነፋስ ፡ ያ ፡ ድንጋይ ፡ መስቀል ፡ ተመንቅሎ ፡ ወደቀ ። በነፈሰም ፡ ቁጥር ፡ ኃይሉ ፡ እየበረረና ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። በነገራችን ፡ ላይ ፡ ስለመስቀሉ ፡ አንድ ፡ ሊታመን ፡ የማይችል ፡ ሆኖም ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ ይነገርለታል ። አፈ ፡ ታሪኩ ፡ የሚለው ፡ ቀዳማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጴጥሮስ ፡ በካውካሰስ ፡ ሲያልፉ ፡ የተከሉት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ቀዳማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከዳጌስታን ፡ አላለፉም ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ በመስ

---

*የሩሲያ ፡ የአፈ ፡ ታሪክ ፡ ጀግና ፡ በአንድ ፡ ፉጨት ፡ እስትንፋስ ፡ ኃይሉ ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ገፍትሮ ፡ ይጥላል ፡ ይባላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳይገቡ ፤ ከበታቻችን ፡ ያለው ፡ የባይዳሩ ፡ ወንዝ ፡ ስለሞላ ፡ ለማቋረጥ ፡ የምንችል ፡ አይመስለ ኝም ። እሺያ ፡ ይልዎታል ፡ ይኸ ፡ ነው ። ወንዙ ቹም ፡ ልክ ፡ እንደሰዎቻቸው ፡ የሚያስተማምኑ ፡ አይደሉም ፡» አለ ፡ የሻምበል ።

በድካም ፡ የተጐሳቆሉትን ፡ ፈረሶች ፡ የሰ ዎቹ ፡ ጩኸትም ፡ ሆነ ፡ የአለንጋ ፡ ግርፊያቸው ፡ ችክለው ፡ ከቆሙበት ፡ እንዲት ፡ እርምጃ ፡ እን ኳን ፡ ሊያነቃንቃቸው ፡ አልቻለም ። በመጨ ረሻም ፡ ከጋሪ ፡ ነጂዎቹ ፡ አንዱ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ «ከቡርነትዎ ፤ ዛሬ ፡ ኮቢ ፡ ገብተን ፡ ለማደር ፡ የምንችል ፡ አይመስለኝም ። ሳይመሽ ፡ ወደግራ ፡ ተጠምዝዘን ፤ መንገደኞች ፡ መጥፎ ፡ አየር ፡ ሲያጋጥማቸው ፡ የሚያርፉባቸው ፡ ከወዲያ ፡ ማዶ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ ጐጆዎች ፡ ሳይኖሩ ፡ አይቀሩምና ፡ ብንሄድ ፡ የተሻለ ፡ ይመስለኛል ፡» ለሻምበሉ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ወደአሴቲያኖቹ ፡ እየጠቆመ ፤ «ለቮይካ ፡ መግጥ ፡ ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ ካገኙ ፡ ወደጐጆዎች ፡ ሊመሩን ፡ ተስማምተዋል ።»

«አውቃለሁ ፡ ወንድም! እነዚህ ፡ ዱርዬዎች ፡ ለገንዘብ ፡ ሲሉ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ከመ ስራት ፡ እንደማያመለሱ ፡ አንተም ፡ ባትነግረኝ ፡ አውቃለሁ ፡» ሲል ፡ የሻምበሉ ፡ መለሰለት ።

«ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ያለእነሱ ፡ እርዳታ ፡ የትም ፡ ልንደርስ ፡ እንደማንችል ፡ ማመን ፡ አለብ

ዎት ፡» ብዬ ፡ የእራሴን ፡ አስተያየት ፡ አቀረ ብሁ ።

«ምናልባት ፤ አዎ ፡ ምናልባት ፤ ግን ፡ የእ ነሱን ፡ ማንነት ፡ አውቃለሁ ። መቼ ፡ ሊያሞ ኙና ፡ ሊያታልሉ ፡ እንደሚችሉ ፡ የተፈጥሮ ፡ ንቃት ፡ አላቸው ። ያለእነሱ ፡ እርዳታ ፡ መንገድ ፡ የማይገፉ ፡ ይመስላቸዋል ።»

ወደግራ ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ ይዘን ፡ ተጓ ዝን ። ከብዙም ፡ ችግር ፡ በኋላ ፡ በእንጨትና ፡ በድንጊያ ፡ ከተሠሩ ፡ ሁለት ፡ ጐጆዎች ፡ ደረ ስን ። እነሱም ፡ በአጥርና ፡ በድንጋይ ፡ ታጥረ ዋል ። የተበጣጠሰ ፡ ቡትቶ ፡ የለበሱ ፡ ባለቤ ቶች ፡ ወጥተው ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉን ። በኋላ ፡ ግን ፡ እንደተረዳሁት ፤ እነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ደመ ወዝ ፡ ከፍሎ ፡ ያስቀመጣቸው ፡ መንግሥት ፤ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የተቸገሩትን ፡ ሰዎች ፡ እንዲ ያስተናግዱ ፡ ኑሯል ።

የምድጃውን ፡ እሳት ፡ ከበን ፡ ቁጭ ፡ ካልን ፡ በኋላ ፤ «የጀመሩልኝን ፡ የቤላን ፡ ታሪክ ፡ እን ዲቀጥሉልኝ ፡ ጥሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ያገኘን ፡ መሰለ ኝ ። ታሪኩ ፡ መቼም ፡ እንዳላለቀ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡» ስል ፡ ጠየቅሁት ።

«ላለማለቁ ፡ ምነው ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኑ» በማለት ፡ የሻምበሉ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ በዓይኑ ፡ ጥቅሻ ፡ ገረፈኝ ።

«በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ እያልቅም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ነሳንድሮቪች ፡ እንዴሕፃናት ፡ መጫወቻ ፡ አሻንጉሊት ፡ ተጠንቅቆ ፡ በልብስ ፤ በጌጥ ፡ አንዘብክቦ ፡ ስለያዛት ፡ ከቀን ፡ ወደቀን ፡ እያማረችና ፡ እየተዋበች ፡ ሄደች ። በፀሐይ ፡ ሐሩር ፡ የጠየመው ፡ ፊቷና ፡ አካላቷ ፡ ተመለሰ ። ጉንጮቿም ፡ እንደጽጌ ፡ ረዳ ፡ አበባ ፡ ፈነደቁ ... ግሩም ፡ ተጨዋች ፡ ነበረች ... በእኔ ፡ ላይማ ፡ ስታሾፍ ፤ አይ! ያች ፡ ተንኮለኛ ፡ ፈጣሪ ፡ ይቅር ፡ ይበላት!..»

«የአባቷን ፡ ሞት ፡ ስትሰማ ፡ ምን ፡ አለች?»

«ለጊዜው ፡ አዲሱን ፡ ትዳሯን ፡ እስክትለማመድ ፡ ድረስ ፡ የአባቷን ፡ ሞት ፡ ደበቅናት ። በኋላም ፡ ስትሰማ ፡ ሁለት ፡ ቀናት ፡ አለቃቅሳ ፡ ረሳችው ።

በጠቅላላው ፡ እራቱ ፡ ወራት ፡ የፍቅር ፡ ዓለም ፡ የሚቀጭበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደነገርኩዎት ፤ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ለእደን ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ። ከርከሮና ፡ አጋዘን ፡ ለእደን ፡ የሚገፋፋ ፡ እንዳች ፡ ኃይል ፡ ነበረው ። ሆኖም ፡ አሁን ፡ አጥሩን ፡ ሳይወጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ታል ። የኋላ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ የእደኑ ፡ ፍቅር ፡ ሲመለ ስበት ፡ ታየኝ ። ሁለት ፡ እጅጉን ፡ አጣምሮ ፡ በክፉሉ ፡ ውስጥ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይንጐራ ደድ ፡ ገባ ። እንድ ፡ ቀን ፡ ለማንም ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ ጠመንጃውን ፡ እንግቶ ፡ እንደወጣ ፡

ብዬ ፡ ነዋ! እጅግመሩ ፡ ያልተለመደ ፡ ስለ ሆነ ፡ ፍጻሜውም ፡ ከመነሻው ፡ የማይለይ ፡ መስሎኝ ፡ ነው ።»

«መልካም ፡ ገምተዋል ።»

«ይህን ፡ ይበሉኝ ።»

«ለእርስዎ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ይሰጥዎ ፡ ይሆ ናል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ታሪኩን ፡ ሳስታውሰው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ሐዘን ፡ ይሰማኛል ። ቤላ ፡ እንዴታ ፡ ያለች ፡ ግሩም ፡ ልጅ ፡ ነበረች! በመጨረሻማ ፡ ልክ ፡ ከአብራኬ ፡ እንደወጣች ፡ ልጄ ፡ አድርጌ ፡ ወደድኋት ። እርሷም ፡ እኔን ፡ እንደወላጅ ፡ አባቷ ፡ ትወደኝ ፡ ነበር ። በበኩሌ ፡ በሕይወቴ ፡ ቤተሰብ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አላውቅም ። የአ ባቴንም ፡ ሆነ ፡ የእናቴን ፡ ወሬ ፡ ከሰማሁ ፡ አ ንድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ አልፎኛል ። በጊዜው ፡ ሚስት ፡ ሳላገባ ፡ ቀረሁ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሴት ፡ አትፈልገኝም ። ግልጽ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከቤላ ፡ ጋር ፡ ማውራቱ ፡ ለእኔ ፡ ልዩ ፡ ደስታ ፡ ይሰጠኝ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ እየ ዘፈነች ፡ የሌዝጊንካን ፡ ውዝዋዜ ፡ ታሳየኝ ፡ ነበር ። አቤት ፡ ውዝዋዜዋ! የእሷን ፡ የሴት ፡ ወይዛዝርትም ፡ ቢሆን ፡ አያቸአቸዋለሁ ። ከሃያ ፡ አመታት ፡ በፊት ፡ ሞስኮ ፡ በሚገኘው ፡ በመሳፍንት ፡ ክበብ ፡ ተገኝቼ ፡ ነበር ። የቤላና ፡ የእነሱ ፡ ውዝዋዜ ፡ ሲወዳደር ፡ ምንና ፡ ምን! ከእግሯም ፡ ጫፍ ፡ አይያደርሱ! ግሪጐሪይ ፡ አለ.

t.me/OLDBOOKSPDF

ማርከውት ፡ ወደተራራ ፡ ወስደውታል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ይመላለስብኛል ... እንዲያውም ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ባይወደኝ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ አድሮብኛል ።»

«አይ ፡ የኔ ፡ ልጅ! ከዚህ ፡ የከፋ ፡ ነገር ፡ ላስብስ ፡ ብትይ ፡ የት ፡ ታገኛለሽ?» በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ትክንክን ፡ ብላ ፡ ካለቃቀሰች ፡ በኋላ ፡ እንባዎ ቿን ፡ አድርቃ ፡ በኩራት ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ እንዲህ ፡ አለችኝ ፤

«ካልወደደኝ ፡ ለምን ፡ ወደቤቴ ፡ እይልከኝም? በግድ ፡ ውደደኝ ፡ አላልሁት ። ሁኔታው ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ከቀጠለ ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ ትቸው ፡ እሄዳለሁ ። የገዛኝ ፡ ባሪያው ፡ አይደለሁም ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ የልዑል ፡ ልጅ ፡ እኮ ፡ ነኝ!..»

እንድ ፡ እንድ ፡ ነገሮችን ፡ በሐሳቧ ፡ እንድታብላላቸው ፡ በማለት ፡ በአጠገቧ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ እንዲህ ፡ አልኋት ፤

«ቢላዬ ፡ ስሚኝ ፤ እሱ ፡ እኮ ፡ ከቀሚስሽ ፡ ጋር ፡ እንደተሰፋ ፡ ጥለት ፡ ለዘወትር ፡ አብሮሽ ፡ ጉልት ፡ ሊል ፡ አይችልም ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወጣት ፡ ነው ፤ እደን ፡ ይወዳል ። ዙሮ ፡ ዙሮ ፡ ግን ፡ መመለሱ ፡ አይቀርም ። እንዲያውም ፡ ለወትሮው ፡ የሐዘን ፡ ፊት ፡ ካሳየሽው ፡ ቶሎ ፡ ይሰለችሻል ።»

«እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ደስተኛ ፡ እሆናለሁ ፡» ብላ ፡ የእጅ ፡ ከበሮዋን ፡ እየመታች ፡ በዚያ ፡ በድምጿም ፡ እያንቀነቀች ፡ ውዝዋዜ

እስከቀትር ፡ ሳይመለስ ፡ በዚያው ፡ ዋለ ። ይህም ፡ ድርጊት ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ እያለ ፡ በመጨረሻ ፡ ግን ፡ የዘወትር ፡ ልምዱ ፡ ሆነ ... ሁኔታው ፡ ደስ ፡ ስላላለኝ ፡ በመካከላቸው ፡ የገባ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ አሰብኩ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ ለማለት ፡ ወደቢታቸው ፡ ገባ ፡ አልሁ ። ቢላም ፡ የጥቁር ፡ ሐር ፡ ቀሚሷን ፡ ለብሳ ፡ በአልጋው ፡ ላይ ፡ ተቀምጣለች ። ፊቷ ፡ በሐዘን ፡ ተሰብሮ ፡ ስላየኋት ፡ ደነገጥሁ ።»

«ፔቾሪን ፡ ወዴት ፡ ሄደ?» ብዬ ፡ ጠየቅኋት ። «አደን ።»

«መቼ ፡ ነው ፡ የሄደው? ዛሬ?» ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠችኝም ፤ መልስም ፡ ለመስጠት ፡ የተሳናት ፡ መሰለኝ ። በመጨረሻም ፤

«የለም ፤ ትናንትና ፡ ነው ፡» ብላ ፡ በሐዘን ፡ መንፈስ ፡ መለሰችልኝ ።

«ከፋ ፡ ነገር ፡ እንዳልደረሰበት ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።»

በእንባ ፡ ያቀረራት ፡ ዓይኖቿን ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ እንዲህ ፡ አለችኝ ፤

«ትናንትና ፡ ቀኑን ፡ በሙሉ ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ የዋልሁት ፡ ያህንኑ ፡ ነው ። የማታየኝ ፡ ሁሉ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ አያደለም ። በአንድ ፡ በኩል ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ አቁሰሎት ፡ ወድቋል ፡ ብዬ ፡ አሰባለሁ ። በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ምናልባት ፡ ቸቸኛ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ፡ ታቀልጠው ፡ ገባች ። በኋላም ፡ ተምዘግ
ዝን ፡ ሄዳ ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተወርውራ ፡ ስታበታ ፡
በሁለት ፡ እጇቿ ፡ ፊቷን ፡ ሸፍና ፡ በልትሶ ፡
ተንሰቀሰቀች ።

የማደርገት ፡ ጠፋኝ ፡ እንደሚያውቁት ፡
እኔ ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ ያለኝ ፡ እግቦ ፡ እስከዚህም ፡
አይደለም ። እሷን ፡ ለማጽናናት ፡ ያልሞከር
ኩት ፡ ነገር ፡ የለም ። ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሁለታች
ንም ፡ ዝም ፡ ስላልን ፡ ቤቱ ፡ በፀጥታ ፡ ተወረረ ።
በእውነት ፡ እልዎታለሁ ፤ የነበርንበት ፡ ሁኔታ ፡
እጅግ ፡ ከባድ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ «ከእኔ ፡ ጋር ፡ ነፋስ ፡ ለመቀ
በል ፡ ብቅ ፡ ለማለት ፡ አትፈልጊም? አየሩ ፡
ግሩም ፡ ነው!» ብዬ ፡ ጠየቅኋት ። ጊዜው ፡ የመስ
ከረም ፡ ወራት ፡ ነበር ። ቀኑ ፡ ፀሐያማ ፡ ቢሆንም ፡
አይወብቅም ። ተራሮቹ ፡ ባውድማ ፡ ላይ ፡ እን
ዳለች ፡ ጥሬ ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።
ከቢቱም ፡ ወጣ ፡ ብለን ፡ የሰፈራችንን ፡ አጥር ፡
ቁልቁልና ፡ ላይ ፡ እየተመላለስን ፡ መንሸራሸር ፡
ጀመርን ። ጥቂት ፡ ከተሃሃርን ፡ በኋላ ፡ ከአን
ዲት ፡ ሳር ፡ በአለችበት ፡ ገብታ ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡
አለች ። እኔም ፡ አጠገቧ ፡ ሄጀ ፡ ቁጠጥ ፡
አልኩኝ ። እንደደንገጡር ፡ ኋላ ፡ ኋላዋ ፡ እየተ
ከተለው ፡ አጽናናት ፡ የነበረው ፡ ትዝ ፡ ሲለኝ ፡
ያስቀኛል ። ሠፈራችን ፡ የሚገኘው ፡ በዘጭ
ተኛ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ከምሽጋችን ፡ ሚሚ ፡

ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ የአካባቢው ፡ ውበቱ ፡
ልብ ፡ ያማርካል ።

በአንድ ፡ በኩል ፡ ሰፊ ፡ የተለጠለጠ ፡ መስክ ፡
በሸለቆዎች ፡ ተሸንሽኖ ፡ ይታያል ። ከሚዳው ፡
ጋር ፡ ኩታ ፡ ገጠም ፡ ሆኖ ፡ የወጣው ፡ ጫካ ፡
ከተራራ ፡ ተጋጥሞ ፡ እስከቁንጮው ፡ ተያ
ይዞ ፡ መጪል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከጉጆዎች ፡
ቡልቅ ፡ የሚሉ ፡ ጭሶችና ፡ አጐንብሰው ፡ ሳር ፡
የሚግጡ ፡ ፈረሶች ፡ በሩቁ ፡ ይታያሉ ። በሌ
ላው ፡ በኩል ፡ የታየ ፡ እንደሆነ ፡ አንድ ፡ ትን
ሽ ፡ ወንዝ ፡ ጋማቶቿ ፡ በቁጥቋጦ ፡ ችርችም ፡ ብ
ለው ፡ ወጥተው ፡ የተራራ ፡ ቋጥኞችን ፡ አዳ
ፍነው ፡ ከካውካስ ፡ ጋር ፡ ገጥመዋል ። እቀማመ
ጣችን ፡ በሰፈራችን ፡ ኮረብታ ፡ ማዕዘን ፡ ላይ ፡
ስለነበረ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ያለው ፡ ቁልጭ ፡
ብሎ ፡ ይታየናል ። እዚያው ፡ ቁጭ ፡ እንዳልን ፡
በድንገት ፡ በአንድ ፡ ግራጫ ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ የተ
ቀመጠ ፡ ሰው ፡ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ካለው ፡ ጫካ ፡
ፈትለክ ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ ወደእኛ ፡ እየጋለበ ፡
መቶ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ከተጠጋን ፡ በኋላ ፡
በወንዙ ፡ አካባቢ ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲቁ
ነጠነጥ ፡ አየሁት ። ደግሞ ፡ ይኸ ፡ ምን ፡ ዱብዳ ፡
ነው ፡ ብዬ ፡ ተገረምኩ ።

«ቢላ ፡ ከእኔ ፡ የተሻሉ ፡ የጠሩ ፡ ዓይኖች ፡ አሉ
ኽና ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ እይው? ማንን ፡ ሊጐበኝ ፡
ይሆን ፡ የመጣው?»

t.me/OLDBOOKSPDF

ትክር ፡ ብላ ፡ ካየች ፡ በኋላ ፡

«ካገዘቢች ፡ ነው!» ብላ ፡ ባረቀች ።

«ይህ ፡ ወንበዴ ፡ ሊያሾፍብን ፡ ነው ፡ ወደ ዚህ ፡ የወጣው?» ካልሁ ፡ በኋላ ፡ ካገዘቢች ፡ መሆኑን ፡ ለየሁት ። ምንም ፡ ለውጥ ፡ አይታይ በትም ፤ እንዳለ ፡ ነው ። እንደወትሮው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የተቦጫጨቀ ፡ ቡትቶ ፡ ለብሷል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቤላ ፡ ነፋስ ፡ እንዳረፈባት ፡ ቅጠል ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ ዓይኖቿን ፡ አር ገብግባ ፣

«ፈረሱ ፡ የአባቴ ፡ ነው ፡» ብላ ፡ ተቁነጠ ነጠች ።

«አይ ፡ ተፈጥሮ ፤ ይህ ፡ ውንብድና ፡ ደም ፡ ባንቺም ፡ ውስጥ ፡ አለ?» ብዙ ፡ በልቤ ፡ አሰ ብኩ ።

አጠገቤ ፡ የነበረውን ፡ አንዱን ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቼ ፤

«ያንን ፡ ሰው ፡ አነጣጥረህ ፡ ተኩሰህ ፤ ከፈረሱ ፡ ብታወርደው ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ሩብል ፡ እሸልምሃለሁ ፡» አልሁት ።

«አሽ ፡ ጌታዬ ፡ ግን ፡ እኮ ፡ እንዲት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ አይቆምም ።»

«ታዲያ ፡ እንዴረጋ ፡ ንገረዋ!» ስል ፡ እየሳ ቅሁ ፡ አሾፍሁበት ።

«ስማ ፡ ሰውዬ ፡ ከዚያ ፡ ግዶ ፡ እሰቲ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እርጋ ፡ ጃል ፡ ምን ፡ እንደእንዝርት ፡

ያሽከረክርሃል!» እያለ ፡ እጁን ፡ ያርገበግብ ፡ ጀመር ።

ካገዘቢች ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለመወያየት ፡ የፈለ ግን ፡ መስሎት ፡ ጀሮውን ፡ ወደእኛ ፡ ጣል ፡ አድርጉ ፡ ለማዳመጥ ፡ አለ ። ዘበኛዬም ፡ አነጣ ጥሮ ፡ ተኩሰና ፡ ሳተው ። ካገዘቢች ፡ ገና ፡ የተኩስ ፡ ድምጽ ፡ ሲሰማ ፡ ከነፈረሱ ፡ ተስፈንጥሮ ፡ ወደ ጉን ፡ ዘወር ፡ አለ ። ከዚያም ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ እየተቅበጠበጠ ፡ ጉራዬውን ፡ መዞ ፡ በራሱ ፡ ቋ ንቋ ፡ ደንፍቶ ፡ ጋለበ ።

እኔም ፡ ወደዘበኛው ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፤

«በሠራኸው ፡ ግፈር ፡ አለብህ ፡» አልሁት ።

«አዬ ፡ ጌታዬ! የሔደው ፡ እኮ ፡ ለሞት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በእንድ ፡ ጥይት ፡ ተመ ትተው ፡ መቼ ፡ ይወድቃሉ ።»

ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ እንድ ፡ እሩብ ፡ ሰዓት ፡ አልፎ ፡ ፔቾሪን ፡ ለአደን ፡ ከሄደበት ፡ ተመለሰ ። ቤላ ፡ ገና ፡ ስታየው ፡ ሩጣ ፡ ሄዳ ፡ ተጠመጠ መችበት ። ተሰይቶ ፡ ስለቆየ ፡ የነበራትን ፡ ቅሬታ ፡ አላሳየችውም ... አልነዘነዘችው ም ። የእሱ ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ እንኳ ፡ ተናደድኩ በት ።

«ሰሙ ፡ ጌታዬ! ካገዘቢች ፡ አውን ፡ እዚህ ፡ ነበረ ። ተኩሰን ፡ አባረርነው ። ምናልባትም ፡ መንገድ ፡ ልትገናኙ ፡ ትችሉ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ቂም ፡ ከያዙ ፡ ላይበቀሉ ፡ የሚቀሩ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፔቾሪን ፡ ጋር ፡ ለመወያየት ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረግሁ ። ሆኖም ፡ ያገኘሁት ፡ መልስ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ። «ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ያዳምጡኝ ። አንድ ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ጠባይ ፡ አለኝ ። የወረስሁት ፡ ካስተዳደጌ ፡ ይሁን ፡ ከተፈጥሮ ፡ አላውቅም ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ከማሳዝናቸው ፡ ሰዎች ፡ ያላነሰ ፡ የማገነው ፡ እራሴ ፡ ነኝ ። ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ለእነሱ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ማጽናኛ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ያለው ፡ እውነት ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ነው ። ከወላጆች ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ከወጣሁ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ሊገዛው ፡ የሚችለው ፡ ደስታ ፡ በሙሉ ፡ አላመለጠኝም ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ ጨርሶ ፡ እጅ ፡ እጅ ፡ አለኝ ። ከዚያም ፡ በጨዋ ፡ ሰዎች ፡ አካባቢ ፡ እራሴን ፡ ወስጄ ፡ ቀላቀልሁ ። ይኸም ፡ እንደዚያኛው ፡ ጨርሶ ፡ አስጠላኝ ። ሁሉንም ፡ ትቼ ፡ ከመልከ ፡ መልካም ፡ ወይዛዝርት ፡ ጋር ፡ ሽርጉዴን ፡ ቀጠልሁ ። ከእነርሱ ፡ የሚፈልቀው ፡ የፍቅር ፡ ለዛ ፡ ይበልጡን ፡ አጨፈገገኝ ። ከዚያም ፡ ወጥቼ ፡ ጊዜዬን ፡ በማንበብና ፡ በምርምር ፡ ለማዋል ፡ ቆረጥሁ ። አልገፋሁበትም ። ምክንያቱም ፡ ዝና ፡ ሆነ ፡ ደስታ ፡ የሚገኘው ፡ በምርምር ፡ እንዳልሆነ ፡ ተረዳሁ ። በግልጽ ፡ እንደማየው ፡ ከሆነ ፡ የእውነተኛ ፡ ደስታ ፡ ባለጸጐች ፡ መሀይማን ፡

ዋዘኞች ፡ አይደሉም ። አዛማትን ፡ እንደረዱት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሳይጠረጥር ፡ የሚቀር ፡ ይመስል ዎታል? ቤላንም ፡ አሁን ፡ እንዳያት ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ እንደሚወዳት ፡ አውቃለሁ ። እራሱ ፡ ነግሮኛል ። በቂ ፡ ሀብት ፡ ቢያጠራቅም ፡ ኖሮ ፡ እርሷን ፡ ለጋብቻ ፡ መጠየቁ ፡ የማይቀር ፡ ነበር ።»

ፔቾሪን ፡ ጥቂት ፡ ከተከዘ ፡ በኋላ ፤ «አዎ ፤ መጠንቀቅ ፡ አለብን ... ቤላ ፤ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ከአጥር ፡ ውጭ ፡ እንዳትወጪ ፡» በማለት ፡ አስጠነቀቃት ።

ያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከፔቾሪን ፡ ጋር ፡ በሰፊው ፡ ተወያየን ። በልጅቷም ፡ ላይ ፡ ያሳየው ፡ ለውጥ ፡ አሳዘነኝ ። ግማሹን ፡ ጊዜውን ፡ የሚውለው ፡ ውጭ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፤ እንደድሮ ፡ አያንከባከባትም ። በአጠቃላይም ፡ በእሷ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ቀዝቃዛ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ። የእርሷም ፡ ፊት ፡ እየገረጣ ፡ ሄደ ። እኚያም ፡ የሚያንፀባርቁ ፡ ዓይኖቿ ፡ ደበዘዙ ። ለብዙ ፡ ቀናት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ለማቀርብላት ፡ ጥያቄዎች ፡ የምትመልሰው ፡ «አዎን ፡» ወይም ፡ «የለም ፡» የሚል ፡ ብቻ ፡ ሆነ ።

«ቤላ ፤ ምን ፡ ሆነሻል? አዘንሽሳ?» «የለም ።» «የምትፈልጊው ፡ ነገር ፡ አለ?» «የለም ።» «ዘመዶችሽ ፡ ናፈቱሽ?» «ምን ፡ ዘመድ ፡ አለኝ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው ። ዝናም ፡ ቢሆን ፡ አመጣጡ ፡ በብልጠ
ትና ፡ በአጋጣሚ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ። ከዚያም ፡
ወደካውካሱስ ፡ ስዛወር ፡ በሕይወቱ ፡ ሙሉ ፡
ያላገኘሁትን ፡ ደስታ ፡ ተጐናጸፍሁ ። በጅሮ ፡
ግንዴ ፡ የሚያፏጨው ፡ የቸቸን ፡ ጥይትና ፡
ከሞት ፡ አፋፍ ፡ እየደረሰ ፡ የሚመለሰው ፡ ሕይ
ወታቸው ፡ መቼም ፡ መች ፡ የማይሰለቸኝ ፡ መስ
ሎኝ ፡ ነበር ። ገና ፡ ወርም ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡
ውስጥ ፡ ሕቅ ፡ አለኝ ። እንዲያውም ፡ የጥይቶች ፡
ፉጨት ፡ እንደትንኞች ፡ ጩኸት ፡ መቁጠር ፡
ገባሁ ። በዚህም ፡ ወቅት ፡ የመጨረሻ ፡ የተ
ስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ስላጣሁ ፡ ከምንጊዜውም ፡
የበለጠ ፡ ሕይወት ፡ መርገም ፡ መስላ ፡ ታየ
ችኝ ። በመጀመሪያ ፡ ቤላን ፡ አግብቼ ፡ በጭ
ኖቼ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ አድርጌ ፤ በዚያ ፡ ጥቁር ፡
አላላ ፡ ፀጉሯ ፡ ውስጥ ፡ ስድፍነፍን ፡ ሞኞ ፡
ሆዬ! ጭሩን ፡ ላለው ፡ እድሉ ፡ በር ፡ ከፋች ፡
ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ከፈጣሪ ፡ የተላከች ፡ መልዓክ ፡
መስላኝ ፡ ነበር ... ይህም ፡ ቢሆን ፡ እንደበፊቱ ፡
ስህተት ፡ ሆነ ። ሥልጣኔ ፡ ያልጸሰሰው ፡ የንጠር ፡
ፍቅሯ ፡ ከከተሚ ፡ መያዛዝርት ፡ ትዝታ ፡ ቢበ
ልጥ ፡ እንጂ ፡ ባላነሰም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ መሐይ
ምነታ ፡ ከከተሚ ፡ አሽታባሪዎች ፡ አነሁል ፡ ይሰ
ለቻል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ እመጻታለሁ ። አብ
ረን ፡ ላሳለፍናቸው ፡ የደበታ ፡ ደቂታዎች ፡ ምስ
ጋናዬ ፡ የወና ፡ ነው ። ለእሷም ፡ ሰል ፡ ሕይወ

ቱን ፡ ከማሳለፍ ፡ ወደኋላ ፡ አላፈገፍግም ። ግን ፡
ስለቸችኝ ... ቂል ፡ ልሁን ፡ ወይንም ፡ ክፉ ፤
አላውትም ። ሆኖም ፡ ከእርሷ ፡ ይበልጥ ፡
ለታዘንልኝ ፡ የሚገባው ፡ ለእኔ ፡ ነው ። መን
ፈሴ ፡ ያለመጠን ፡ ተረበሸ ። አእምሮዬ ፡ እረፍት ፡
አጣ ፤ ልቤንም ፡ የሚያረካ ፡ ነገር ፡ ጠፋ ። በዓ
ለም ፡ ውስጥ ፡ የሚያስደስተኝ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡
አጣሁ ። ሐዘንንም ፡ ሆነ ፡ ደስታን ፡ ለመለማ
መድ ፡ ለእኔ ፡ ያው ፡ ሆነ ። ሕይወቴ ፡ ከቀን ፡
ወደቀን ፡ ባዶ ፡ ቀፎ ፡ ሆና ፡ ታየችኝ ። የቀረ
ኝ ፡ እንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡
ጉዞ ... ወደኤውሮፓ ፡ ሳይሆን ፡ (ከዚህ ፡
ፈጣሪ ፡ ቢያወጣኝ ።) ወደአሜሪካ ፤ ወደአረብ ፡
አገር ፤ ወደሕንድ ፡ ለመጓዝ ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡
ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ እደረግሁ ። ምናልባትም ፡ የሕ
ይወቴ ፡ ፍጻሜ ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።
ይህም ፡ ምኞት ፡ በማዕበል ፡ ወይም ፡ በኮሮ
ኮንች ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ በሚደርሰው ፡ አደጋ ፡
ሰበብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደሚውል ፡ ተስፋ ፡
አለኝ ...» በዚህ ፡ መልክ ፡ ብዙ ፡ እወራኝ ።
ከሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጐልማሳ ፡ አንደበት ፡
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ ስሰማ ፡ የመጀመሪያ ፡
ጊዜ ፡ ነው ። የመጨረሻም ፡ እንዲያደርግልኝ ፡
ፈጣሪዬን ፡ እለምነዋለሁ ... ስለሆነም ፡ የተናገራ
ቸው ፡ ታላት ፡ በሙሉ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡
በጅሮ ፡ ግንዴ ፡ ያስተጋባሉ ። ፈመቼም ፡ እርስዎ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በእንዲሁ ፡ ሳይሆን ፡ አንድ ፡ ተንኮል ፡ አስቦ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ሐሳብ ፡ በአእምሮዬ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

እንድ ፡ ተን ፡ ፔቾሪን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ለአደን ፡ እንድንሄድ ፡ ጋበዘኝ ። የአደን ፡ ፍላጐት ፡ ስላልነበረኝም ፡ ላለመሄድ ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ አደረግሁ ። ሆኖም ፡ በመጨረሻ ፡ ወትውቶ ፡ ገፋፍቶ ፡ ይዞኝ ፡ ሄደ ። አምስት ፡ ወታደሮች ፡ አስከትለን ፡ ወፍ ፡ ሲንጫጫ ፡ ለአደን ፡ ሄድን ። አራት ፡ ሰዓት ፡ በሙሉ ፡ ጫካውን ፡ ስናስስ ፡ አንድም ፡ አውሬ ፡ ስላላ ገኘን ፤ «ዛሬስ ፡ አልቀናንምና ፡ ችክ ፡ ከምንል ፡ ወደሠፈራችን ፡ እንመለስ ፡» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። በፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ተቃጥለን ፡ ብንጠወልግም ፡ ቅሉ ፤ ግሪጐሪይ ፡ አሉከሳንድሮቪች ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ለመመለስ ፡ አልፈለገም ። ተፈጥሮው ፡ ነው ። አንድ ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ የግዴታ ፡ ግድ ረግ ፡ አለበት ። እናቱ ፡ በልጅነቱ ፡ እሞላቃ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ያሳደገችው ። በመጨረሻም ፡ ቀ ትር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተረገመ ፡ ከርከሮ ፡ አጋጠ መን ። ተኩስ ... አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ተኩስ ... ሁኖም ፡ አውሬው ፡ ሳይመታ ፡ ተሸሎክ ሉኩ ፡ ጫካ ፡ ገብቶ ፡ አመለጠ ። በእውነትም ፡ ጠማማ ፡ ቀን ፡ ናሮ ፡ ትንሽ ፡ በጥላ ፡ ሥር ፡ ከአረፍን ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ላይቀናን ፡ ባዶ ፡ እጃችንን ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ተመለስን ።

ከዋናው ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ የመጡት ፡ በዚያስ ፡ ያሉ ፡ ወጣቶች ፡ ሁሉም ፡ እንደዚህ ፡ ናቸው?» ሲል ፡ የሻምበሉ ፡ ጠየቀኝ ።

እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ እንዳሉና ፡ ንግ ግራቸውም ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ የተመረኮዘ ፡ መሆኑን ፡ ገለጽሁለት ። የመንፈስ ፡ ውድቀት ፡ የደረሰባቸው ፡ ወጣቶች ፡ ይህን ፡ ውድቀታ ቸውን ፡ እንደኃጢአት ፡ በመቁጠር ፡ ሸሽገው ፡ ይዘውታል ። ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የከተማ ፡ አነጋገር ፡ የሻምበሉ ፡ ሊያጤነው ፡ አልቻ ለም ። በደፈናው ፡ ግን ፡ አንገቱን ፡ ነቅንቆ ፤

«የመንፈስ ፡ መረበሽ ፡ ፈሊጥን ፡ ያመጡት ፡ ፈረንሳዮች ፡ ሳይሆኑ ፡ ይቀራሉ?» ቢለኝ ፤

«የለም ፤ እንግሊዞች ፡ ናቸው ።»

«አ! እንዲያ ፡ ነው? እነሱም ፡ የታወቁ ፡ ጠጪ ዎች ፡ ናቸው ።»

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሞስኮ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የማውቃት ፡ የሴት ፡ ወይዘሮ ፡ «ባያሮን ፡ እኮ ፡ አንድ ፡ ሰካራም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡» ብላ ፡ ያለችኝ ፡ ትዝ ፡ አለኝ ። የሻምበሉ ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ የሚያረግለት ፡ ነው ። እራሱን ፡ ከመጠጥ ፡ ለማግለል ፡ ሲል ፡ የመጠጥን ፡ አደ ገኛነት ፡ መናገር ፡ የዘወትር ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

«ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ካገለሏት ፡ ተመልሶ ፡ አልመ ጣም ፡» በማለት ፡ ሻምበሉ ፡ ታሪኩን ፡ ቀጠለ ። «አንዱ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ የጠፋ ፡ ጊዜ ፤ አመጣጡ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም ፡ ካገቢችን ፡ በጥይት ፡ ለመምታት ፡ ከሚቻልበት ፡ እርቀት ፡ ያረስን ። ካገቢች ፡ ፈረሱ ፡ ያደከምበት ፡ ወይም ፡ ከኛዎቹ ፡ ይባስበት ፡ አይታወትም ፣ በግልቢያ ፡ የእኛ ፡ ፈረሶች ፡ አጣደፉት ። በዚህ ፡ ወቅት ፡ ካገቢች ፡ ያ ፡ ሻንቆ ፡ ፈረሱ ፡ ትዝ ፡ እንደሚለው ፡ እርግጠኛ ፡ ነበርሁ ፡

ቀናም ፡ ስል ፡ ፔኞሪን ፡ በካገቢች ፡ ላይ ፡ ሲያነጣጥር ፡ አየሁት ። «አይተኩሱ ፤ ጥይትዎን ፡ በከንቱ ፡ አያጥፉ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እንደርስበታለን ፡» አልሁት ። መቼም ፡ ወጣት ፡ ነት ፡ የሰው ፡ ምክር ፡ ስለማይሰማ ፡ ፔኞሪን ፡ በፈታዱ ፡ ተኩሶ ፡ የካገቢችን ፡ ፈረስ ፡ የኋላ ፡ እግር ፡ አቆሰለው ። ፈረሱም ፡ አንድ ፡ አስር ፡ እርምጃዎች ፡ ከተራመደ ፡ በኋላ ፡ ተንደፍድፎ ፡ በጉልበቱ ፡ ተደፋ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካገቢች ፡ ከኮርቻው ፡ ዘሎ ፡ ሲወርድ ፡ በእቅፉ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አየን ። እርቧም ፡ ቤላ ፡ ኑራለች ፤ ምስኪኗ ፡ ቤላ! በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ከተንጨረጨረብን ፡ በኋላ ፡ ጉራዴውን ፡ መዞ ፡ በቤላ ፡ ላይ ፡ ሲሰነዝር ፡ ስላየሁት ፤ ጊዜ ፡ ሳልሰጠው ፡ ሽጉጤን ፡ አውጥቼ ፡ እንዳገኘሁ ፡ ተኮስኩ ። ከንዱን ፡ አግኝቼው ፡ ናሮ! እጁ ፡ ዘንጠፍ ፡ ብሎ ፡ ተዘረጋ ። የሽጉጡ ፡ ባሩድ ፡ ጢስ ፡ እንዳለፈ ፡ የቆሰለው ፡ ፈረስና ፡ ቤላ ፡ ተዘርግተው ፡ ሲታዩ ፤ መሳሪያውን ፡ ወርውሮ ፡ የሄደው ፡ ካገቢች ፡ ግን ፡ የተራራውን ፡ ቋጥኝ ፡ እንደድመት ፡

የፈረሶቻችንን ፡ ልጓሞች ፡ ለቀቅ ፡ አድርገን ፡ በቀስታ ፡ ጉዞ ፡ ጉን ፡ ለጉን ፡ ሆነን ፡ በዐጥታ ፡ መንገድ ፡ ጀመርን ። በጫካ ፡ ከተዋጠው ፡ ሠፈራችን ፡ ስንደርስ ፡ እንድ ፡ የጥይት ፡ ተኩስ ፡ ሰማን ። ዓይኖቻችን ፡ ወዲያውኑ ፡ ሲገናኙ ፡ ሁለታችንም ፡ በእንድ ፡ ጊዜ ፡ እንድ ፡ ሐሳብ ፡ ጭንቅ ላታችንን ፡ እንደመታው ፡ ተረዳሁ ። የጥይት ፡ ድምጽ ፡ ወደሰማንበት ፡ ጋልበን ፡ ስንደርስ ፡ ወታደሮች ፡ ተሰብስበው ፡ ወደሚዳው ፡ ይመለከታሉ ፤ በዚያ ፡ አቅጣጫም ፡ በእቅፎ ፡ ነጭ ፡ ነገር ፡ ያጋደመ ፡ እንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሽምጥ ፡ ሲጋልብ ፡ አየን ። ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ከማንም ፡ ቸቸን ፡ ፈረሰኛ ፡ ባላነሰ ፡ ቅልጥፍና ፡ ሽጉጡን ፡ መዞ ፡ ጋለበ ። እኔም ፡ ከኋላው ፡ ተከተልኩት ።

ደግነቱ ፡ አደኑ ፡ ፈረሶቻችንን ፡ ስላላደከማቸው ፡ የግልቢያ ፡ ፍጥነታቸውን ፡ አልቀነሱም ። በእየደቂቃውም ፡ ከፈታችን ፡ ያለውን ፡ ጠላታችንን ፡ እየተጠጋነው ፡ ስለሄድን ፡ ካገቢች ፡ መሆኑን ፡ ለመለየት ፡ ቻልሁ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከፊቱ ፡ ያጋደመው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻልሁም ። ግልቢያችንን ፡ በመቀጠል ፡ ፔኞሪንን ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ «ካገቢች ፡ እኮ ፡ ነው ፡» ብዬ ፡ ነገርሁት ። ፔኞሪንም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አይቶት ፡ ሚንትላቱን ፡ በመነትነት ፡ ፈረሱን ፡ ሽንቁጦ ፡ ግልቢያውን ፡ ቀጠለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ፡ቅዱሳን ፡ በት ፡ ካስገባናት ፡ በኋላ ፡ ሐኪም ፡ በፍጥነት ፡ እንዲመጣ ፡ መልክተኛ ፡ ላክን ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የስካር ፡ ሞቅታ ፡ ቢታይበትም ፡ መልክቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ደረሰልን ። ቁስሏንም ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ሕይወት ፡ ብቻ ፡ እንዳላት ፡ አስታወቀን ። ግን ፡ ተሳስቷል ...

ከደስታ ፡ በፈለቀ ፡ ስሜት ፡ ተገፋፍቼ ፡ የሻምበሉን ፡ እጅ ፡ ጨበጥ ፡ አድርጌ ፤ «ዳነች?» ብዬ ፡ ጠየቅሁ ።

«የለም ፤ ስህተቱ ፡ እሱ ፡ ከወሰነው ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ መጨመሩ ፡ ነው ።»

«ካዝቢች ፡ እንዴት ፡ ሊሠርቃት ፡ እንደቻለ ፡ እስቲ ፡ ያውሩኝ ።»

«ታሪኩ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ፔቾሪን ፡ የነገራትን ፡ ቃል ፡ በመጣስ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወጥታ ፡ ወደ ወንዙ ፡ ወርዳ ፡ ሔዳ ፡ ነበር ። ጊዜው ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ስለነበረ ፡ ከአንድ ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ እግሯን ፡ ከውሃው ፡ ዘፍዝፋ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ። ካዝቢች ፡ ተሽሎክሉኩ ፡ ሄዶ ፡ እፍኖ ፡ ወደቱጥቋጦው ፡ ካስገባት ፡ በኋላ ፤ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ እጋድሞ ፡ ግልቢያውን ፡ ጀመረ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቤላ ፡ የጩኸት ፡ ድምጽ ፡ ስላሰማች ፡ ዘበኞቹ ፡ ስምተው ፡ ተኩሰው ፡ ላቱት ፤ ይሄኔ ፡ እኛ ፡ ደረስን ።»

«ካዝቢች ፡ እሷን ፡ ለመውሰድ ፡ የፈለገው ፡ ለምን ፡ ይሆን?»

እየቧጠጠ ፡ ሲወጣ ፡ እየሁት ። በጥይት ፡ ልቀ ልበው ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ። ግን ፡ ሽጉጤ ፡ አለሞላ ረሱ ፡ አዳነው ። ከፈረሶቻችንም ፡ በፍጥነት ፡ ወርደን ፡ ወደቤላ ፡ ተሯሩጠን ፡ ሔድን ። ምስ ኪኗ ፡ ቤላ ፡ ግን ፡ በቁስሏ ፡ ደም ፡ እርሳ ፤ ከወደ ቀኙበት ፡ ሳትንቀሳቀስ ፡ ብድን ፡ ሁና ፡ አገኘ ናት ። ይህ ፡ ወሮበላ ፡ ልቧን ፡ አግኝቷት ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ አክትማ ፡ ነበር ። ከወደኋላዋ ፡ ስለተወ ጋች ፡ ተጐድታለች ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ በድን ፡ ሁና ፡ እራሷን ፡ ስታለች ። ፊቱን ፡ የተሸፈነችበትን ፡ ጉባር ፡ ቀዳደን ፡ ቁስሏን ፡ ጠፍረን ፡ አሰርንበት ። ፔቾሪን ፡ ያለማቋረጥ ፡ የጠወለጉ ፡ ከንፈሮቿን ፡ ቢስማቸውም ፡ ነፍስ ፡ ሊዘራባቸው ፡ አልቻለም ።

ወዲያው ፡ ፔቾሪን ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ቤላን ፡ ከመሬት ፡ ታቅፌ ፡ አንስቼ ፡ አቀበልኩት ። እሱም ፡ ታቅፏት ፡ ጉዞአችንን ፡ ወደቤታችን ፡ ቀጠልን ። ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻም ፡ «ይሰሙ! ማነሰም ፡ ማነሰሞቪች ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የዘግታ ፡ ጉዞ ፡ ከአንሕይወቷ ፡ ቤት ፡ መድረሷን ፡ አጠራጠራለሁ» አለኝ ። «አውነትዎን ፡ ነው ፡» በማለት ፡ በሐሳቡ ፡ ተስማምቼ ፤ ግልቢያችንን ፡ ተያያዝነው ። ሠራራችንም ፡ ሰንደርሰ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብሰበው ፡ ሲጠብቁን ፡ አገኘናቸው ። ቤላን ፡ በዝግታ ፡ ተሸነሠን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመታገሥታም ፡ በላይ ፡ ወደአደገችበት ፡ መንደር ፡ ለመመለስ ፡ መፈለጓን ፡ ገለጸች ። ከዚያም ፡ ፔቶሪንን ፡ አንዴ ፡ በቁልምጫ ፡ ስታሞጋግሰው ፡ መልሳም ፤ «ፍቅሬ ፡ ሰለቸህ» እያለች ፡ ስትወ ትሰው ፡ ቆየች ...

ፔቶሪን ፡ አገጩን ፡ በሁለቱ ፡ እጆቹ ፡ ላይ ፡ ደግፎ ፡ ተክዞ ፡ ሲሰማት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እንዲት ፡ ዘለላ ፡ እንባ ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ ስላላየሁበት ፡ ታዘብሁት ። ሰውየው ፡ የማልቀስ ፡ ልምድ ፡ እይኑረው ፡ ወይም ፡ እም ባውን ፡ ገትቶ ፡ ይያዘው ፡ አላውቅም ፤ ሆኖም ፡ በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ እንዲህ ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ አላጋጠመኝም ።

ጥዋት ፡ ትኩሳቱ ፡ በርዶላት ፡ ነበር ። ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ደክማ ፤ ገርጥታ ፡ ከላይ ፡ ከላዩ ፡ እየተነፈሰች ፡ ተኝታ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ትንሽ ፡ መለስ ፡ ሲልላት ፡ እንደገና ፡ መናገር ፡ ጀመረች ። ንግግሯ ፡ ስለምን ፡ እንደሆነ ፡ መቼም ፡ ሳይ ገምቱ ፡ እይቀሩም ... ይህን ፡ መሳይም ፡ ሐሳብ ፡ ሊወጣ ፡ የሚችለው ፡ በሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ... እስከዛሬም ፡ ክርስ ትና ፡ ባለመኑሳቷ ፡ ተፀፀተች ። ነፍሲም ፡ በመንግ ሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከግሪጉሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ጋር ፡ የማትገናኝ ፡ መሆኗን ፡ እስታውሳ ፡ እዘ ነች ። በእሷም ፡ ፈንታም ፡ ከግሪጉሪይ ፡ አሌክሳ ንድሮቪች ፡ ነፍስ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ በምትቆጪዋ ፡

«አይ ፡ የእርስዎ ፡ ነገር! እነዚህ ፡ የቸርከስ ፡ ሰዎች ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ ሌቦች ፡ ናቸው ፡ እኮ ፤ ጠባቂ ፡ ያጣ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ካገኙ ፤ ከመስረቅ ፡ አይመለሱም ። እቃው ፡ አስፈ ለገም ፡ አላስፈለገም ፡ ልምድ ፡ ሆኖባቸው ፡ ይሰ ርቁታል ፤ በተለይ ፡ ካዝቢች ፡ ግን ፡ በቤላ ፡ ላይ ፡ ዓይኑን ፡ ከጣለ ፡ ጊዜ ፡ የለውም ።

«ታዲያ ፡ ሞተች?»

«እዎን ፤ ከመሞቷ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ተሰቃየች ። እኛም ፡ እሷን ፡ በማስታመም ፡ ተጉሳቆልን ። ከምሽቱ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ እዚያው ፡ አልጋዋ ፡ ሥር ፡ እንዳለን ፡ ትንሽ ፡ ነፍስ ፡ ዘራች ። ወዲያውም ፡ ዓይኗን ፡ እንደከ ፈተች ፡ «ፔቶሪን ፡ የት ፡ አለ?» ብላ ፡ ጠየቀች ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፔቶሪን ፡ እጅዋን ፡ ጨበጥ ፡ አድ ርጉ ፤

«እዚህ ፡ አጠገብሽ ፡ ነው ፤ የእኔ ፡ ጄኒችካ» (የእኔ ፡ ቆንጆ ፡ ለማለት ፡ ነው) አላት ።

«እንግዲህ ፡ መሞቴ ፡ ነው» ብትለን ፡ ሐኪሙ ፡ ሊያድናት ፡ ቃል ፡ እንደገባልን ፡ ነገርናት ። ሆኖም ፡ እንገታን ፡ ነቅንቃ ፡ ፊቷን ፡ መልሳ ፡ ዳው ፡ መልሳ ፡ ተኛች ። መሞት ፡ እንዳልፈለገች ፡ ግልጽ ፡ ነበር!.. ሌሊቱን ፡ ሕመሟ ፡ ጠናባት ። ትኩሳቷ ፡ ልክ ፡ እንደረመጥ ፡ ከማቃጠሉም ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደጠፋ ፡ ያንዘፈዝፋት ፡ ገባ ። የእብታን ፡ የወንድሟን ፡ ሰም ፡ እየጠራች ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላዋ ፡ ሴት ፡ ነፍስ ፡ ቅናት ፡ እደረባት ። ከመሞቷ ፡ በፊት ፡ ብትጠመቅ ፡ ይሻላታል ፡ በሚል ፡ አስቤ ፡ ሐሳቡን ፡ ባቀርብላት ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ አየችኝ ። በመጨረሻም ፡ በተወለደችበት ፡ ኃይማኖት ፡ ወንታ ፡ ለመሞት ፡ መፈለጓን ፡ ነገረችኝ ። በዚህ ፡ መልክ ፡ እንደኛው ፡ ቀን ፡ አለፈ ። በዚህ ፡ ወቅት ፡ መላ ፡ አካላቷ ፡ እንዴት ፡ እንደተለዋወጠ ፡ ለመግለጽ ፡ ቃላት ፡ ያጥሩኛል ። እኒያ ፡ የገረጡ ፡ ጉንጮቹ ፡ እንደተመጠጠ ፡ ሎሚ ፡ ለተለቱ ። ዓይኖቿ ፡ እየፈጠጡ ፡ ከንፈሮቿ ፡ እሳት ፡ ሆኑ ። በውስጥ ፡ ደረቱ ፡ የጋለ ፡ ብረት ፡ እንደተቀመጠ ፡ ሁሉ ፡ ትኩሳቱ ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ ።

በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ በአልጋዋ ፡ ሥር ፡ ጉልት ፡ ብለን ፡ ዓይናችንን ፡ አፍጥጠን ፡ ነጋ ። ሥቃዩ ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ አልነበረም ። ታቃስታለች ፤ ትንሽ ፡ መለስ ፡ ሲልላትም ፡ የተሻላት ፡ በማስመሰል ፡ ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳን ድሮቪች ፡ ሄዶ ፡ እንዲያርፍ ፡ ትጠይቀውና ፤ ከዚያም ፡ እጇን ፡ ስማ ፡ በእጆቿ ፡ ጨብጣ ፡ ትይዘዋለች ። ሊነጋጋም ፡ ሲል ፡ ጣዕረ ፡ ሞቷ ፡ ተናነቃት ። በአልጋዋ ፡ ላይ ፡ እየተገለባበጠች ፡ ቱስልዋ ፡ የታሰረባትን ፡ ሻሽ ፡ በጣጥሳ ፡ ስትጥለው ፡ ያም ፡ መሩሰለ ፡ ጀመረ ። ቱስታ ፡ እንደገና ፡ ከታሠረላት ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ አረፍ ፡ ብላ ፡ ተኛች ። ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ እን

ደስማት ፡ ጠየቀችው ፡ እሱም ፡ ከአልጋዋ ፡ አጠገብ ፡ ተንበርክኮ ፡ እስከነትራሷ ፡ ቀና ፡ እድርጎት ፡ የተዘበዘብትን ፡ ከንፈሮቿን ፡ ይስማቸው ፡ ጀመር ። በዚያም ፡ በሚንዘፈዘፉ ፡ እጆቿ ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ ተጠምጥማ ፡ ስትታይ ፡ በዚህች ፡ ደቂቃ ፡ ነፍሷንም ፡ ለእርሱ ፡ ለመስጠት ፡ የፈለገች ፡ ትመስል ፡ ነበር ። አዎን! መሞቷ ፡ ጥሩ ፡ ሆነ! ግሪጐሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ቢተዋት ፡ ኖሮስ ፡ ምን ፡ ይውጣት ፡ ነበር? ወጣም ፡ ወረደ ፡ አይቀርላትም ፡ ነበር ...

በማግስቱ ፡ እስከእኩል ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሐኪሙ ፡ በመድኃኒት ፡ ቢያዋክባትም ፤ ምንም ፡ ሳትተነፍስ ፡ በአልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተጋድማ ፡ ቆየች ። ከዚያም ፡ ወደሐኪሙ ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፤

«በሕይወቷ ፡ የምትቆየው ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ እራስዋ ፡ ተናግረዋል ። ታዲያ ፡ ለምን ፡ በመድኃኒት ፡ ያሲቃዩአታል?» ስል ፡ ጠየቅሁት ።

«ሕሊናዬ ፡ እንዳይወቅሰኝ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ በተቻለኝ ፡ ሁሉ ፡ መርዳት ፡ አለብኝ» ብሎ ፡ መለሰልኝ ። እንዲህ ፡ እርጉ ፡ ሕሊና ፡ የለም!

ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ተቃጠለች ። መስኩቱንም ፡ ብንከፍት ፡ የውጩ ፡ ሙቀት ፡ ከቤቱ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ። በረዶ ፡ በአጠገቧ ፡ ብናስ

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ፡ እሱን ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ በሐዘን ፡ ነድጄ ፡ በምትሁ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ከጥግ ፡ ሥር ፡ አረፍ ፡ ብሎ ፡ በእንጨት ፡ ከአሸዋው ፡ ላይ ፡ ያቦጫጭር ፡ ጀመር ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሐዘን ፡ ቅስሙን ፡ ባይሰብረውም ፡ የተፈጥሮ ፡ ልምድ ፡ ሆኖ ፡ ላጽናናው ፡ ገና ፡ ስጀምር ፡ አንገቱን ፡ ወደሰማይ ፡ አንጋጠ ፡ በሳቅ ፡ ይንከተከት ፡ ገባ ... በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሰራ ፡ አካላቴ ፡ ተጨፈገገ ፤ ወዲያውም ፡ ጥዬው ፡ የሬሳ ፡ ሳጥን ፡ ለማዘዝ ፡ ሄድኩ ።

ይህንንም ፡ ለመስራት ፡ የወሰንኩት ፡ ከእሱ ፡ ለመላቀቅ ፡ ብዬ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ግሪጉሪይ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በገዛላት ፡ የቸር ከስ ፡ የብር ፡ ጌጦች ፤ በሐር ፡ ጨርቅ ፡ የሳጥኑን ፡ ዙሪያ ፡ አስዋብሁት ። በማግስቱም ፡ ማለዳ ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ በነበረችበት ፡ የወንዝ ፡ ጋማት ፡ ላይ ፡ ወስደን ፡ ቀበርናት ። ያኔ ፡ ገላጣ ፡ የነበረው ፡ መቃብሯ ፡ ዛሬ ፡ ዙሪያው ፡ በዛፍና ፡ በአበባ ፡ ችምችም ፡ ብሏል ። እንዲያው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ መስቀል ፡ በመቃብሯ ፡ ላይ ፡ ልተክልላት ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ስላልተጠመቀች ፡ ተውሁት ።

«ፔቾሪን ፡ እንዴት ፡ ሆነ?» ስል ፡ ጠየቅሁት ።

«ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ታመመ ፤ አይ ፡ ምስኪን! ያለመጠን ፡ ከስቶ ፡ መነመነ ፤ ይህም ፡ ሆኖ ፡ ስለቤላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አውርቶን ፡

ቀምጥም ፡ አልረዳትም ። ይህም ፡ የውሃ ፡ ጥም ፡ የሞቷ ፡ መቃረብ ፡ ምልክት ፡ መሆኑ ፡ ገባኝ ። ይህንንም ፡ ለፔቾሪን ፡ ነገርኩት ። ቤላ ፡ እንግቷን ፡ ከአልጋዋ ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፤ «ውሃ! ውሃ» እያለች ፡ ትወተውት ፡ ነበር ።

ፔቾሪን ፡ ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱ ፡ አንዴ ፡ እንደ ፡ አንሶላ ፡ ገረጣ ። ፊቴን ፡ በእጁ ፡ ከልዬ ፡ እፀልይ ፡ ገባሁ ። የትኛውን ፡ ግን ፡ እንደፀለየሁ ፡ አውን ፡ ትዝ ፡ አይለኝም ... በሕይወቴ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡ ሜዳም ፡ ሆነ ፡ በሆስፒታል ፡ ሲሞቱ ፡ አይቻለሁ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳዛኝ ፡ አሟሟት ፡ ግን ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ። እንዲያ ፡ እንደልጅ ፡ ስወዳት ፡ ከመሞቷ ፡ በፊት ፡ አንዴም ፡ እንኳን ፡ ስሜን ፡ ባለማንሳቷ ፡ በጣም ፡ አዘንሁ ... ሆኖም ፡ ፈጣሪ ፡ ይቅር ፡ ይበላት!.. ለነገሩስ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ሆንሁና ፡ ነው ፡ የሚሞት ፡ ሰው ፡ በጣሪዕሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የሚያነሳኝ?..

ውሃውን ፡ ከጠጣች ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ ተሻላት። ከአንድ ፡ ከሶስት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ሞተች ። ከከንፈሯ ፡ ላይም ፡ የተደረገለት ፡ መስተዋት ፡ የመተንፈሷን ፡ ምልክት ፡ ሳያሳይ ፡ ቀረ!.. ከዚያም ፡ ፔቾሪንን ፡ ከቤት ፡ ይዣው ፡ ወጥቼ ፤ በሠፈራችን ፡ አጥር ፡ ጥግ ፡ እጃችንን ፡ ወደኋላ ፡ አድርገን ፡ በዝምታ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንጉራደድ ፡ ጀመር ። ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሐዘን ፡ ምልክት ፡ ባለማየቴ ፡ በጣም ፡ ገረመኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እናውቅም ። ነገሩን ፡ ካነሳሁት ፡ በጣም ፡ እንደሚ
ያሳዝነው ፡ ስለማውቅ ፡ እኔም ፡ ዝም ፡ ማለቱን ፡
መረጥሁ ። ከአንድ ፡ ከሶስት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡
ወደጅርጂያ ፡ ተቀያሮ ፡ ሄደ ። እነሆ ፡ ከዚያን ፡
ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ተገናኝተን ፡
እናውቅም ... በማዛጋው ፡ ውስጥ ፡ ስሙ ፡
ያልሰፈረ ፡ ቢሆንም ፡ በቅርቡ ፡ ወደሩሲያ ፡ እንደ
ተመለሰ ፡ ሰምቼአለሁ ። መቼም ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡
ወሬ ፡ የሚደርሰው ፡ እርፍዶ ፡ ነው ።»

ይህን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ የጥንት ፡ ብስጭ
ቱን ፡ እስታውሶ ፡ ነው ፡ መሰል ፡ አመት ፡ ያለ
ፈው ፡ የወሬ ፡ ቋንጣ ፡ መስማቱ ፡ ምንኛ ፡ መጥፎ ፡
መሆኑን ፡ በሰፈው ፡ አወራልኝ ።

እኔም ፡ ወሬውን ፡ አላቋርጠው ፡ እንጂ ፡
በሃሳቤ ፡ ከእሱ ፡ ጋር ፡ አልነበርኩም ።

ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ የበረዶው ፡ ወጨ
ፎ ፡ ቆም ፡ ያመናውም ፡ ገለጥሰጥ ፡ ሲል ፡ መንገ
ዳችንን ፡ ጀመርን ። መንገድ ፡ ላይ ፡ ወሬው ፡
ሁሉ ፡ ስለቤላና ፡ ስለፔቾሪን ፡ ብቻ ፡ ሆነ ።

«ካዝቢች ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የት ፡ ደረሰ?»

«ካዝቢች?.. ስለእሱስ ፡ በእውነቱ ፡ ምንም ፡
የማውቀው ፡ ነገር ፡ የለም ። ከወንዙ ፡ ማዶ ፡
በሚጥሩት ፡ ሻፕሰግስ ፡ ጐሣ ፡ መሀል ፡ ቀይ ፡
ቢሽሚት ፡ የሚለብስ ፡ ጥያት ፡ በጆሮ ፡ ግንዱ ፡ ሰ
ያልፍ ፡ ጉንበስ ፡ እያለ ፡ የሚያሳልፍ ፡ በእኛ ፡
ተኩስ ፡ የማይበረግግ ፡ አንድ ፡ ደፋር ፡ ካዝቢች ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚባል ፡ አለ ፡ እየተባለ ፡ ሲነገርለት ፡ አሰማ
ለሁ ፡ ግን ፡ ያ ፡ የምናውቀው ፡ ካዝቢች ፡ መሆ
ኑን ፡ በጣም ፡ እጠራጠራለሁ!..»

ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ እና ፡ እኔ ፡ ኮቢ ፡
ላይ ፡ ተለያየን ። እኔ ፡ በፖስታ ፡ አመላላሽ ፡
ፈረሶች ፡ መንገዴን ፡ ቀጠልሁ ። እሱ ፡ ግን ፡
ዝሙ ፡ ስለበዛበት ፡ ከእኔ ፡ እኩል ፡ በመቀጠል ፡
አልቻለም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ እንገናኛ
ለን ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አልነበረንም ። ይሁንና ፡
አጋጣሚ ፡ ሁኖ ፡ እንደገና ፡ ተገናኘን ። ከፈለ
ጉ ፡ ስለእሱም ፡ አወጋዎታለሁ ። ግን ፡ ይህ ፡
እራሱን ፡ የቻለ ፡ አንዴ ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ነው ...
ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ የሚከበር ፡ ሰው ፡
ለመሆኑ ፡ ማመን ፡ ይኖርባችኋል ። ይህንንም ፡
ካመናችሁ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ታሪኩ ፡ ረጅም ፡
ቢሆንም ፡ የማክሲም ፡ ማክሲሞቪችን ፡ ታላቅ
ነት ፡ ካላመንኋችሁ ፡ ተጋቢ ፡ ሽልማቴን ፡ እግ
ኝቼአለሁ ፡ ለማለት ፡ እደፍራለሁ ።

፪

ማክሲም ማክሲሞቪች ።

ከማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ጋር ፡ ከተለያየን ፡ በኋላ ፡ በቴሬክና ፡ በዳርያል ፡ ሸለቆዎች ፡ ውስጥ ፡ መዝናናት ፡ ጀመርሁ ። ካዝቤክ ፡ ቁርሴን ፡ አደርግና ፡ ላርስ ፡ ሻዬን ፡ ፉት ፡ ብዬ ፤ ቭላዲካቭካዝ ፡ ለራት ፡ ደረስሁ ። ስለተራሮቹ ፡ ሽንተረር ፡ አገላለጽ ፤ ስለእካባቢው ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፤ ይህን ፡ እካባቢ ፡ ለማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ ይሰማቸዋል ፡ ብዬ ፡ ስለማልገምትና ፡ ጠቅላላውንም ፡ ሁኔታ ፡ በስታቲስቲክስ ፡ መልክ ፡ ባቀርበው ፡ አንባቢ ፡ ስለማይኖረኝ ፡ ትቼዋለሁ ።

ያረፍሁበት ፡ ሆቴል ፡ የመንገደኞች ፡ መስፈሪያ ፡ ናት ። ቤት ፡ ያፈራውን ፡ ጠባብሶም ፡ ሆነ ፡ የጐመን ፡ ሹርባ ፡ ማቅረብ ፡ ሲቻል ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የተመደቡት ፡ ሶስት ፡ ድኩማኖች ፡ ሰክረው ፡ ይሁን ፤ ያደቦች ፡ ይሁኑ ፡ አላውቅም ፤ የሚታዘዙትን ፡ አያሰሙም ።

ከየካቴሪኖግራድ ፡ የሚመጣው ፡ አጀቢ ፡ ሠራዊት ፡ ስላልደረሰ ፡ እነሱ ፡ እሰኪመጡ ፡ ድረስ ፡

ሶስት ፡ ቀናት ፡ መጠበቅ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ፡ ይህም ፡ ለእኔ ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነበር ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የታላት ፡ ድርድር ፡ ለእንድ ፡ ሩሲያዊ ፡ ምንም ፡ ጉት ፡ ስለማይሰጠው ፡ የነበረውን ፡ አጋጣሚ ፡ በዚህ ፡ እንሚታው ። ሥራ ፡ ከምፈታ ፡ ብዬ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ስለቤላ ፡ ያወራኝን ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ ተከታይ ፡ እንደሚኖረው ፡ ሳላውቅ ፡ መጻፍ ፡ ጀመርሁ ። ታሪኩ ፡ እንድ ፡ እንዴ ፡ እንደዋዛ ፡ የተጀመረ ፡ ነገር ፡ ፍጻሜው ፡ አሳዛኝ ፡ ይሆናል ። አጋጣሚ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ያውቃሉ? በቭላዲካቭካዝና ፡ በየካቴሪኖግራድ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ካባርዳን ፡ የተባለውን ፡ ቦታ ፡ አጅበው ፡ የሚያሽጋግሩ ፡ ወታደሮች ፡ አጋጣሚ ፡ ነው ፡ ይባላል ። የመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ለእኔ ፡ ስልቹ ፡ ነበር ። በማግስቱ ፡ ማለዳ ፡ እንድ ፡ ሠረገላ ፡ ደረሰ ። ተሳፋሪውም ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ኑረዋል ። እንደ ነባር ፡ ወዳጅች ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጠን ። እኔ ፡ የያዝሁት ፡ ክፍል ፡ ውሰጥ ፡ እብሮኝ ፡ እንዲያርፍ ፡ ጋበዝሁት ። ሳይግደረደር ፡ ግብግቦን ፡ ተቀበለው ። እንዲያውም ፡ ትክሻዬን ፡ መታ ፡ ብሎ ፤ የእንግት ፡ በላይ ፡ ፈገግታ ፡ አሳይቶኝ ፡ ዘወር ፡ አለ ። የማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ እንዳንድ ፡ ጠባዮቹ ፡ ያልተለመዱ ፡ ናቸው ።

ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ የምግብ ፡ ሥራ ፡ ይዋጣለታል ። ጥብሱና ፡ መረቁ ፡ ሲጣፍጥ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ንም ፡ የተሳፈረ ፡ ሰው ፡ አልነበረበትም ። ከዚህ ፡ ሠረገላ ፡ በኋላ ፡ ጉጭ ፡ ያለ ፡ ሪዝ ፡ ያለው ፤ የሐ ንጋሪ ፡ መኰንን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቅ ፡ አለ ። በአለባበሱ ፡ ቢሆንም ፡ እሽከር ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። የፒፓውን ፡ እመድ ፡ ሲያራግፍና ፡ በሠረገላው ፡ ጎጅ ፡ ሲጮ ህበት ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ማንኑቱን ፡ ወዲያውኑ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ቻልሁ ። የአንድ ፡ የሩሲያ ፡ መኮ ንን ፡ አሽከር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብዬ ፡ ገመ ትሁ ።

በመስኮቱም ፡ አንገቴን ፡ ብቅ ፡ አድርጌ ፤ «ወንድም ፡ ማን ፡ ነው ፡ ወደዚህ ፡ የመጣው?» ስል ፡ ጠየቅሁት ።

በግልምጫ ፡ ከተመለከተኝ ፡ በኋላ ፡ ሻሽ ፡ የመ ለሰችውን ፡ ክራቫቱን ፡ አስተካክሎ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠኝ ፡ ጥሎኝ ፡ ሔደ ። እብሮት ፡ የነበረው ፡ አርሜኒያዊ ፡ ግን ፡ የመጣው ፡ የወታደ ር ፡ ጓዝ ፡ መሆኑን ፤ በማግስቱም ፡ ከዚህ ፡ እን ደሚነሳ ፡ በፈገግታ ፡ ገለፀልኝ ።

በዚህ ፡ ወቅት ፡ ወደመስኮቱ ፡ ተጠግቶ ፡ የነበረ ው ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ «የእግዚአብ ሔር ፡ ክብሩ ፡ ይስፋ!» ካለ ፡ በኋላ ፡ «ግሩም ፡ ሠረገላ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ቲፍሊስ ፡ ለሥራ ፡ የሚሔድ ፡ ባለስልጣን ፡ ይሆናል ። የእገሩን ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፡ ገብነት ፡ ያወቀ ፡ አልመሰለኝም ። አይ ፤ ለእንደናንተ ፡ ያለ ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ መች ፡

እንዲህ ፡ አልነበረም ። እሱ ፡ ባይመጣ ፡ ኖሮ ፡ የቀዝቃዛ ፡ ምግብ ፡ ስበላ ፡ መክረሜ ፡ ነበር ። የያዝነው ፡ የካኬቲየን ፡ መጠጥ ፡ የገበታችንን ፡ ገመና ፡ ሸፈነልን ። ከዚያም ፡ ፒፓችንን ፡ ለኩሰን ፡ እኔ ፡ ከመስኮቱ ፡ ጥግ ፡ ቁጭ ፡ ስል ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ቀኑ ፡ ብርዳማ ፡ ስለነበር ፡ ከምድጃው ፡ አጠገብ ፡ አረፍ ፡ አለ ። ሁለታችንም ፡ ለጊዜው ፡ ዝም ፡ አልን ። ምን ፡ ልናወራ ፡ እንችላለን? እሱ ፡ ስለራሱ ፡ በሙሉ ፡ አውርቶኛል ። እኔ ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ የማወራው ፡ ነገር ፡ ስለሌለኝ ፤ በመስኮቱ ፡ መመልከቴን ፡ ቀጠልሁ ። በሩቁም ፡ እየሰፋ ፡ በሚፈሰው ፡ በቴሬክ ፡ ወንዝ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ የተሠሩትን ፡ ጕጆዎች ፡ በዛፎች ፡ መካከል ፡ አቧልኬ ፡ ተመለከትሁ ። ባሻገሩ ፡ የበረዶ ፡ ቆብ ፡ የደፋው ፡ የካዝቤክ ፡ ተራራ ፡ ተገትሯል ። በሐሳቤም ፡ «ደህና ፡ ሁኑ» አልኋቸው ። ከዚህም ፡ ቦታ ፡ ተለይቼ ፡ በመሔዴ ፡ ቅር ፡ አለኝ ...

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆየን ። ፀሐይ ፡ በተራራዎች ፡ ጫና ፡ ትያፋላች ። ሸለቆውም ፡ በደመናዎች ፡ ተከባ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሠ ረገላ ፡ ታሚሎችና ፡ የሰዎች ፡ ጫጫታ ፡ አስ ተጋባ ። በርከት ፡ ባሉ ፡ ሠረገሎች ፡ ላይ ፡ የተቦ ጫጨቀ ፡ ቡትቶ ፡ የለበሱ ፡ አርመኖች ፡ ተሳፍረ ውበት ፡ ወደአጥር ፡ ግቢው ፡ ገቡ ። በመጨረሻ ፡ በደረሰው ፡ ንፀሕና ፡ ውብ ፡ ሠረገላ ፡ ግን ፡ ም

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆናል? የእንግሊዝ ፡ ሠረገላም ፡ እንኳ ፡ ችሎ ፡ አይዘልቀውም ።»

«ለመሆኑ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ የመጣው? እስቲ ፡ ጮራ ፡ ብለን ፡ እንጠይቅ?..» ብሎኝ ፡ ከክፍላችን ፡ ወጣ ፡ ስንል ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ እቃ ፡ እየተሸከመ ፡ በራፉ ፡ ወደተከፈተው ፡ ክፍል ፡ ሲያስገባ ፡ አየን ።

«ስማ ፡ ወዳጄ!» ብሎ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ አሽከሩን ፡ ጠርቶ ፡ «ይህ ፡ ግሩም ፡ ሠረገላ ፡ የማነው?» ሲል ፡ ጠየቀው ።

አሽከሩ ፡ ግን ፡ በቀጥታ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ እያጉረመረመ ፡ ሻንጣ ፡ መፍታቱን ፡ ቀጠለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ሣንፍል ፡ ብሎ ፡ የአሽከሩን ፡ ትከሻ ፡ ጨብጦ ፡ በንዴት ፡

«አንተን ፡ እኮ ፡ ነው ፡ የምጠይቅህ ፡» አለው ።

«የማነው ፡ ብሎ ፡ ነገር? የጌታዬ ፡ ነዋ!»

«እኮ ፡ ጌታህ ፡ ማነው?»

«ፔቾሪን ...»

«ማን ፡ አልኸኝ? ፔቾሪን ፡ የፈጣሪ ፡ ያለህ! ለመሆኑ ፡ ለሥራ ፡ ካውካሰስ ፡ ተመድቦ ፡ ያውቃልን?» በማለት ፡ እጅጌዬን ፡ እየጐተተ ፡ በያስታ ፡ ፈነደቀ ።

«ይመስለኛል... ግን ፡ እኔ ፡ ማገልገል ፡ ከጀመርሁ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜዬ ፡ ነው»

«ይኸውልሃ! ስሙ ፡ ማሪጐሪያ ፡ አሌክሳንድሮቪች ፡ አይደለም?.. ጌታህና ፡ እኔ ፡ የጥንት ፡

ጓደኞች ፡ ነን ...» ካለው ፡ በኋላ ፡ አሽከሩን ፡ በፍትር ፡ መልክ ፡ ጀርባውን ፡ ቸብ ፡ ቢያደርገው ፡ ወደአንድ ፡ ወገን ፡ አጋደለ ።

«ያትርታምንና ፡ ጌታዬ ፡ ሥራዬን ፡ እያስፈቱኝ ፡» ብሎ ፡ አሽከሩ ፡ አጉረመረመ ።

«እሱን ፡ ተወው! ግን ፡ የጌታህ ፡ የድሮ ፡ ጓደኛው ፡ መሆኔን ፡ አታውቅም ፡ አብረንም ፡ እኮ ፡ ኑረናል ... አሁን ፡ ይልቅ ፡ የት ፡ ነው ፡ ያለው?»

ፔቾሪን ፡ ከኮሎኔል ፡ ኤን ፡ ጋር ፡ ራት ፡ በልቶ ፡ በዚያው ፡ እንደሚያድር ፡ አሽከሩ ፡ ነገረው ።

«ዛሬ ፡ ማታ ፡ አይመጣም ፡ ማለት ፡ ነዋ! ወንድም ፡ ምናልባት ፡ ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ወደእሱ ፡ ከሔድህ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ እዚህ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ንገረው ። እንዲሁ ፡ ብቻ ፡ በለው ፡ ለቮድካ ፡ መግዣ ፡ ሳንቲም ፡ እስጥሃለሁ ...»

አሽከሩ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የመደለያዋን ፡ ዋጋ ፡ ቢንቃትም ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ የጠየቀውን ፡ መልክት ፡ እንደሚያደርስለት ፡ ቃል ፡ ገባለት ።

«እንደስማ ፡ ወዲያው ፡ ነው ፡ የሚመጣው!.. ውጭ ፡ ወጥቼ ፡ እቀበለዋለሁ ... እኚህን ፡ ኮሎኔል ፡ አለማወቂ ፡ አሳዘነኝ ።» በማለት ፡ በፔቾሪን ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ አረጋገጠልኝ ።

ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ከአጥሩ ፡ ውጪ ፡ ካለው ፡ አግድም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በሹ ፡ በሁኔታው ፡ ያስታውታል ። ሽማግሌው ፡ በፒዮሪን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ ያዘን ፡ እንደነበር ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ተደም ፡ ሲል ፡ ስለ ነበራቸው ፡ ወዳጅነትና ፡ አሁንም ፤ «ስሜን ፡ እንደሰማ ፡ በሮ ፡ ይመጣል ፡» ብሎ ፡ ስለፔ ትሪን ፡ ያወራኝ ፡ ትገ ፡ ሲለው ፡ ብሽቀቱ ፡ እንደ ሚበዛበት ፡ እሙን ፡ ነው ። የመኝታ ፡ ጊዜ ፡ መድረሱን ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪችን ፡ ለማስ ታወስ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ መስኮቴን ፡ ብከፍት ፡ ጊዜው ፡ ጨለምለም ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ወደቤት ፡ እንደገባ ፡ ለጠየቅሁት ፡ በማጉረምረም ፡ መል ሶልኝ ፤ በመጨረሻም ፡ እስከነአካቴው ፡ አልመለ ሰልኝም ።

ከአግዳሚ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ የበራ ፡ ሻማ ፡ እስቀምጪ ፤ የወታደር ፡ ካፖርቴን ፡ ደረብ ፡ አድርጌ ፡ በፎተዩ ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ እንዳልሁ ፡ እንቅልፍ ፡ ይዞኝ ፡ ሔደ ። ማክሲም ፡ ማክሲሞ ቪች ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ መጥቶ ፡ ባይቀሰቅሰኝ ፡ ኑሮ ፡ የሰላም ፡ እንቅልፍ ፡ ስለጥጥ ፡ ባደርሁ ፡ ነበር ። ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ፒፓውን ፡ ወደጠረጴዛው ፡ ወርውሮ ፡ በክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ ይን ጐራደድ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ የምድጃውን ፡ እን ጨት ፡ ቆስቁሶ ፡ ጋደም ፡ ብሎ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሲስል ፡ ሲተፋና ፡ ሲገላበጥ ፡ ቆየ ።

«ትኋኖች ፡ አላስተኙዎት ፡ አሉ?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

ይጠብቅ ፡ ገባ ። እኔ ፡ ግን ፡ ወደነፍሴ ፡ ተመ ለስሁ ። የፔቾሪንን ፡ መምጣት ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እኔም ፡ በጉጉት ፡ እጠባበቅ ፡ እንደነበረ ፡ መግለጽ ፡ ግዴታ ፡ አለብኝ ። ሻምበሉ ፡ እንዳወራልኝ ፡ የፔቾሪን ፡ ተፈጥሮ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚስብ ፡ ባይሆንም ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ጠባይ ፡ አለው ። ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ከድኩማኖች ፡ አንዱ ፡ የሻይ ፡ መፍያ ፡ ሳሞቫርና ፡ የሻይ ፡ ጀበና ፡ ይዞ ልኝ ፡ መጣ ። በመስኮት ፡ ተጣርቼ ፤ «ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ ሻይ ፡ አይጠጡም?» ስል ፡ ጠየቅሁት ።

«አልጠጣም ፤ እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ።»

«ፋት ፡ ቢሉ ፡ ይሻሉታል ፤ አየሩ ፡ እየቀዘ ቀዘ ፡ ነው ።»

«የለም ፤ አልፈልግም ።»

«እንደፈለጉ ፡» ብዬ ፡ ሻዩን ፡ መጠጣት ፡ ጀመርሁ ። ከአንድ ፡ ከአስር ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ሽሚው ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፤

«እውነትዎን ፡ ነው ፡ ወንድሚ ፤ ሻይ ፡ መጠ ጣቱ ፡ ይሻላል ። እኔማ ፡ ወዳጄን ፡ እየጠበቅሁ ፡ ነበር ... አሽከሩ ፡ ከፈጴ ፡ ጊዜ ፡ የለውም ፤ አ ንድ ፡ አጋጣሚ ፡ ገጥሞት ፡ ነው ።»

ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ሲኒ ፡ ሻሂውን ፡ ከጠጣ ፡ በኋላ ፡ ድገም ፡ ቢባል ፡ እንኳ ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ወደውጭ ፡ ወጣ ። ያለመጠን ፡ መረ

t.me/OLDBOOKSPDF

«አምን ፡ እንቅልፍ ፡ ከለከሉኝ» ሲል ፡ በረድሙ ፡ ተንፍሶ ፡ መለሰልኝ ።

በማግስቱ ፡ ጠዋት ፡ እኔም ፡ የተነሳሁት ፡ በጥዋቱ ፡ ቢሆንም ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ከእኔ ፡ ቀድሞ ፡ ተነስቶ ፡ ውጭ ፡ ካለችዋ ፡ አማዳሚ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ጉልት ፡ ብሎ ፡ አገኘሁት ። «ወደኮማንዳንቱ ፡ ስለምሔድ ፡ ፔቾሪን ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ሰው ፡ ልከህ ፡ አስጠራኝ ፡» አለኝ ።

«እሺ» ብዬ ፡ ቃል ፡ ገባሁለት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ እንደሕፃንነት ፡ ዘመኑ ፡ ሩጫውን ፡ ተያያዘው ።

ጥዋቱ ፡ በንጹህ ፡ አየር ፡ የተሞላ ፡ ሲሆን ፡ ግሩም ፡ የውበት ፡ ፀጋ ፡ ተከናንቧል ። በጋራዎቹ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ጉልት ፡ ያለው ፡ ወርቃማ ፡ ደመና ፡ ለብቻው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ተራራ ፡ ይመስላል ። ከመግቢያው ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ ክብ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የአሁድ ፡ ገበያ ፡ ከዘወትሩ ፡ ይበልጥ ፡ ደርታል ። የማር ፡ ስልቻ ፡ በፈንታቸው ፡ ላይ ፡ የዋቀሩ ፡ በባዶ ፡ እግራቸው ፡ ያሉ ፡ አሴቲያዊያን ፡ ወጣት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ዙርያዬን ፡ ከበውኝ ፡ ቆሙ ። በሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ተውጠው ፡ ስለነበር ፡ ጊዜ ፡ አልሰጠኋቸውም ፡ አባረርኋቸው ፡ የሻምበሉ ፡ ሚንቶት ፡ ሳልወድ ፡ እንጉም ፡ የሐሳቡ ፡ ምርኮኛ ፡ አያረገኝ ።

አሰር ፡ ደቂቃ ፡ ሳያሞላ ፡ የምጠብቀው ፡ እንግዳ ፡ ከክቡ ፡ አደባባይ ፡ ባሻገር ፡ ብት ፡

ሲል ፡ ታየኝ ። ኮሎኔል ፡ ኤን ፡ እንግዳውን ፡ እስከ ሆቴሉ ፡ ይሸኙ ፡ ሽኝቶት ፡ ወደሠፈሩ ፡ ተመለሰ ። እኔም ፡ ከሆቴሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ድኩማን ፡ እንዴን ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪችን ፡ እንዲጠራ ፡ ላክሁት ።

የፔቾሪን ፡ አሽከር ፡ ወደጌታው ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ፈረሶቹ ፡ ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ እንዲዘጋጁ ፡ ነግሮ ፡ አዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ለጌታው ፡ ፓኪት ፡ ሲጋር ፡ ሰጥቶት ፡ ወደሥራው ፡ አመራ ። ፔቾሪን ፡ ሲጋሩን ፡ ከአቀጣጠለ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አዛግቶ ፡ ከአጥሩ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ካለችዋ ፡ አግድም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ አለ ። አስቲ ፡ ሥዕላዊ ፡ መልኩን ፡ ልግለፀው ።

መካከለኛ ፡ ቁመት ፡ አለው ፤ ቀጥ ፡ ካለው ፡ ቁመናው ፡ ጋር ፡ የተዋቀረው ፡ ሰፊው ፡ ደረቱ ፡ ከጠንካራ ፡ ሰውነት ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ የመንገድ ፡ ችግር ፡ የአየር ፡ መለዋወጥ ፤ የከተማ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ህይወትና ፡ ውስጣዊ ፡ የስሜት ፡ ትግል ፡ እንዳልበገረው ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ። ከታች ፡ ሁለት ፡ ቁልፎች ፡ ብቻ ፡ የያዙት ፡ ክፍት ፡ አቧራማ ፡ ኮት ፡ የውስጡን ፡ ነጭ ፡ ንጹህ ፡ የሐር ፡ ሸሚዙን ፡ ያሳያል ። ይህም ፡ ውጭ ፡ የመኳንንት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ቆሸሸ ፡ ያሉት ፡ የእጅ ፡ ሹራቦቹ ፡ በነዚያ ፡ በትናንሽ ፡ የመኳንንት ፡ ጣቶቹ ፡ ልክ ፡ የተሰፉ ፡ ይመስላሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆነው ፡ እንደሚወጡ ፡ በማለት ፡ ገመትሁ ። ከነዓው ፡ ወጉሩ ፡ ወረድ ፡ ብለው ፡ ጥቁር ፡ ሆነው ፡ የሚታዩት ፡ ትንድቦቹና ፡ ሪዙ ፡ በነጭ ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ጥቁር ፡ ጋማና ፡ ጭራ ፡ ይመስላሉ ። ሥዕላዊ ፡ ገጹን ፡ ለመያምደም ፡ ያህል ፤ የእፍ ንጫው ፡ ጫፍ ፡ ትንሽ ፡ ወደላይ ፡ ቀልበስ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ጥርሶቹ ፡ ነጫጭ ፡ ሲሆኑ ፤ ዓይኖቹ ፡ ያልተለመዱ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ዓይኖቹ ፡ በተለይ ፡ ሁለት ፡ ታላት ፡ ወርውሮ ፡ ማለፍ ፡ ግድ ፡ ይሆ ንብኛል ።

በመጀመሪያ ፡ ሲስቅ ፡ ዓይኖቹ ፡ ተደምመው ፡ አይፈኩም! እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ በሴ ሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ልብ ፡ አላላችሁም? ይህም ፡ ምልክት ፡ የሰውየውን ፡ ክፋት ፤ አለበለዚያም ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዘላለማዊ ፡ ጥልቅ ፡ ሐዘን ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ገርበብ ፡ ባሉት ፡ ሽፋሽፍቶች ፡ ውስጥ ፡ ለማለት ፡ ከተቻለ ፤ ዓይኖቹ ፡ እንደርስፋረስ ፡ ያበራሉ ። አስ ተያየቱ ፡ ከልብ ፡ ከፈለቀ ፡ ስሜት ፡ የወጣ ፡ አይደለም ። በሐሳብ ፡ ምጥቀት ፡ የተዋጠም ፡ አ ይመስልም ። ዓይኖቹ ፡ እንደብረት ፡ ተብረቅር ቱው ፡ ቢያበሩም ፡ ውስጣቸው ፡ የቀዘቀዘ ፡ ነው ። በእንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚያተኩሩት ፡ ዓይኖቹ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ በር ግደው ፡ ከመግባታቸውም ፡ ሌላ ፤ እግባብ ፡ ያል ሆኑ ፡ ጥያቄዎችን ፡ የሚሠንዝሩ ፡ ይመስላሉ ።

የእንዱን ፡ የእጅ ፡ ሹራብ ፡ ሲያወልቅ ፡ አለንጋ ፡ ጣቶቹን ፡ እያቹ ፡ ተደነቅሁ ። አረማመዱ ፡ የድ ካምና ፡ የግዴለሽነት ፡ ሲሆን ፡ እጆቹን ፡ እያነቃን ቃቸውም ። ይህም ፡ በለውየው ፡ ውስጥ ፡ እንድ ፡ የተደበቀ ፡ ጠባይ ፡ መኖሩን ፡ ያስረዳል ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። ሆኖም ፡ ከዚህ ፡ ውሳኔ ፡ የደረስሁት ፡ እኔ ፡ በአየሁት ፡ ላይ ፡ ተመስርቼ ፡ ስለሆነ ፤ ግምቴን ፡ በጭፍኑ ፡ ተቀብለህ ፡ እመንበት ፡ ብዬ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ አላስገድድም ። እወንበሯ ፡ ላይ ፡ ሔዶ ፡ ቁጭ ፡ ሲል ፡ እጥፍጥፍ ፡ ብሎ ፡ ላየ ው ፡ አካላቱ ፡ እጥንት ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡ አያ ስደፍርም ፡ ነበር ። መላ ፡ ቁመናው ፡ ሲታይ ፡ የሕዋሳት ፡ ድክመት ፡ ያጠቃው ፡ ይመስላል ። ከዳንስ ፡ በኋላ ፡ በፎተይ ፡ ወንበሯ ፡ ተዝለፍልፋ ፡ የተቀመጠችዋን ፡ በባልዛክ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የምናገኛትን ፡ የሠላሳ ፡ አመት ፡ ሴት ፡ የፔ ቾሪን ፡ ሁኔታ ፡ ያስታውሰናል ። በመጀመሪያ ፡ የሀያ ፡ ሶስት ፡ አመት ፡ እድሜ ፡ ሰጥቼው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ አትኩሬ ፡ ስመለከተው ፡ የሠላሳ ፡ አመት ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ገመትሁ ። የሕ ፃን ፡ ፈገግታ ፡ ይታይበታል ። የፈቱ ፡ ቆዳ ፡ እን ደሴት ፡ የለሰለሰ ፡ ነው ። በተፈጥሮው ፡ የተጠቀ ለለው ፡ ወጉሩ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ባረፈበት ፡ የግ ረማ ፡ ማንባሩ ፡ ቆዳ ፡ መለመሮች ፡ ተሰበጣጥ ረው ፡ ይታያሉ ። እነዚህም ፡ መስመሮች ፡ በንደትና ፡ በሳንቀት ፡ ጊዜ ፡ በይበልጥ ፡ ግልጽ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውየው ፡ ደመ ፡ በረድ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ሊያሳስቱ ፡ ይችላሉ ። ያህን ፡ ሁሉ ፡ ለማለት ፡ የቻልሁት ፡ ስለሰውየው ፡ ታሪክ ፡ አስቀድሚ ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ ስላለ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ምናልባትም ፡ ያህን ፡ ታሪክ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢጽፈው ፡ ኖሮ ፡ በልዩ ፡ መልክ ፡ ያቀርበው ፡ ነበር ፡ እላለሁ ። ሆኖም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ ታሪክ ፡ ልትሰሙት ፡ ስለማትችሉ ፡ ባቀረብ ኩላችሁ ፡ ልትደስቱ ፡ ይገባችኋል ። ስለሰውየው ፡ ለመደምደም ፡ ያህል ፤ መልክ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ውበቱ ፡ በተለይ ፡ ወይዛዝርትን ፡ የሚማርክ ፡ ነው ።

ፈረሶቹ ፡ ተጭነው ፡ የእንገታቸው ፡ ቃጭል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲወዛወዝ ፡ ቅጭል ፡ ቅጭል ፡ ይላል ። አሽከሩ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወደጌታው ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ የፈረሶቹን ፡ መዘጋጀት ፡ ነገረው ። እስካሁን ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ብቅ ፡ አላለም ። ደግነቱ ፡ ፔቾሪን ፡ በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ እንደሰንሰለት ፡ የተያያዙትን ፡ የካውካሱስ ፡ ተራራዎች ፡ ይመለከት ፡ ስለነበር ፡ የሚቸኩል ፡ አይመስልም ።

«ትንሽ ፡ ቆየት ፡ ቢሉ ፡ ከድሮው ፡ መዳጅዎ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ እድል ፡ ይኖረዎታል ፡» አልሁት ።

«እውነት ፡ ነው ፡ ትናንትና ፡ ሰምቼ ፡ ነበር» ብሎ ፡ መዲያው ፡ ከመለሰልኝ ፡ በኋላ ፡ «እኮ ፡

እሱን ፡ የት ፡ አሉ?» ሲል ፡ ጠየቀኝ ። ወደአደባባዩም ፡ ዘወር ፡ ስል ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ያለው ፡ ጎያሉን ፡ በሙሉ ፡ ተጠቅሞ ፡ በሩጫ ፡ ወደእኛ ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ። ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ ካለንበት ፡ ቦታ ፡ ደረሰ ። ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይላል ። ላቡም ፡ ያንቆረቆራል ። ከባርኔጣው ፡ ሾልከው ፡ የወጡት ፡ ሽበቶ ፡ ፀጉሮቹ ፡ እርሰው ፡ ከግንባሩ ፡ ጋር ፡ ተጣብቀዋል ። ጉልበቱም ፡ ይብረከረካል ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ በወዳጄ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ ለመጠምጠም ፡ ሲል ፡ ፔቾሪን ፡ ከሩቁ ፡ በቀዘቀዘ ፡ አቀባበል ፡ እጁን ፡ ዘረጋለት ። ሰላምታ ፡ የተሞላበት ፡ ፈገግታ ፡ ግን ፡ ነበረው ። የሻምበሉ ፡ በድንጋጤ ፡ ተርበትብቶ ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ቀረ ። ይሁንና ፡ ከፔቾሪን ፡ የተሰነዘረለት ፡ መዳፍ ፡ በሁለት ፡ እጆቹ ፡ ተስገብግቦ ፡ ጨበጣቸው ። እንድም ፡ ቃል ፡ ለመተንፈስ ፡ አልቻለም ።

«እንደምን ፡ አሉ ፤ ወዳጄ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች?! እርስዎን ፡ በማየቴ ፡ የተሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ እንደምን ፡ ነዎት?»

«እንተስ ፡ ...? አ ... እርስዎስ? ከተለያየን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖናል ፡ ... በጣም ፡ ብዙ ፡ ጊዜያችን ፡ ነው ። እንዴ ፡ ... ወዴት ፡ ነው ፡ የሚሄዱት ...?» ሲል ፡ ዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ እቅረው ፡ ጠየቀው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈያደርም ፡ በእኛ ፡ አካባቢ ፡ ካለው ፡ የተሻለውን ፡ አተርባለሁ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ እናወራለን ፡ ስለፔቴርቡርግ ፡ ኑሮዎስ ፡ እያወጉኝም?..»

«ወዳጄ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ በእውነቱ ፡ ምንም ፡ የማወራዎ ፡ ነገር ፡ የለኝም ... ስለ ምቾኩል ፡ ልሰናበትዎ ። እስከዛሬ ፡ ስላልረሱኝ ፡ ምስጋናዬ ፡ የበረታ ፡ ነው ...» ብሎ ፡ የሽማግሌውን ፡ እጅ ፡ ጨበጠው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሌው ፡ ይበልጥ ፡ በድንጋጤ ፡ ደረቀ ። የወረረውን ፡ ሐዘንና ፡ ንዴትም ፡ ላለማስታወቅ ፡ ከመጣር ፡ አልቆጠበም ።

«ስላልረሳኸኝ?..» ሲል ፡ በዝግታ ፡ ድምፅ ፡ ካጉረመረመ ፡ በኋላ ፤ «የለም ። ምንም ፡ የረሳሁት ፡ ነገር ፡ የለም ። ግን ፡ ግድየለም ... ብቻ ፡ ግንኙነታችን ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ አልገመትሁም ፡ ነበር ፡» አለው ።

«ይተዉት ... በቃ ...» በማለት ፡ ፔቾሪን ፡ ወዳጅነት ፡ በተሞላበት ፡ መንፈስ ፡ ሽማግሌውን ፡ ካቀፈው ፡ በኋላ ፤ «የተቀየርሁ ፡ እንኳ ፡ አይመስለኝም ... ከሆነም ፡ ምንም ፡ የምለውጠው ፡ ነገር ፡ የለም ። ሁላችንም ፡ የተፈጠርነው ፡ በእየፈናችን ፡ ለመኖር ፡ ነው ... ወደፊት ፡ መገናኘታችንን ፡ የሚያውቀው ፡ ፈጣሪ ፡ ብቻ ፡ ነው!..»

ፔቾሪን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፡ ወደሠረገላው ፡ እየወጣ ፡ ሲሆን ፤ የሠረገላው ፡ ነጅ ፡

«ወደፔርሺያ ፡ ከዚያም ፡ እርቱ ፡ እሄዳለሁ ።»

«አሁኑኑ ፡ እንደማይሆን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ አይቆዩም?.. ከተገናኘን ፡ ዘመን ፡ የለውም ...»

ከፔቾሪን ፡ የተገኘው ፡ መልስ ፡ ቢኖር ፤

«አሁኑኑ ፡ መሄድ ፡ አለብን ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች» የሚል ፡ ብቻ ፡ ነበረ ።

«ያንተ ፡ ያለህ ... የፈጣሪ ፡ ያለህ ... ችኮላው ፡ ወዴት ፡ ነው? ስንት ፡ ስንት ፡ የማወራዎት ፡ ጉዳይ ፡ ስንት ፡ የምጠይቅዎት ፡ ጥያቄ ፡ አለኝ ... ሥራዎ ፡ እንዴት ፡ ነው? ጡረታ ፡ ወጥተዋል? እስካሁንስ ፡ ምን ፡ ሲሰሩ ፡ ቆዩ?»

«ሁሉም ፡ ሰልችቶኛል ፡» ሲል ፡ ፔቾሪን ፡ በፈገግታ ፡ መለሰለት ።

«ባለፈው ፡ ሠፈራችን ፡ እንዴት ፡ እንደኖርን ፡ ትዝ ፡ ይልዎታል?.. አደን ፡ በጣም ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ለመሆኑ ፡ ቤላን ፡ ያስታውሷታል?..»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፔቾሪን ፡ ፊቱ ፡ ተቀያይሮ ፡ ዘወር ፡ አለ ። «አዎን ፡ አስታውሳለሁ» በሰለቸ ፡ ድምጽ ፡ ከመለሰ ፡ በኋላ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ አዛጋ ። ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንዲቆይ ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ።

«ጥሩ ፡ እራት ፡ አለኝ ፤ ሁለት ፡ ያማሩ ፡ ዶሮዎች ፡ አሉኝ ። የዚህ ፡ አገር ፡ ካኽቲያን ፡ ወይን ፡ ወያር ፡ የለውም ። ከጆርጂያው ፡ ባይወ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያውኑ ፡ የልጓሙን ፡ ጠፈር ፡ በእጆቹ ፡ ጨምድዶ ፡ ያዘ ።

«ይቆዩ ... ይቆዩ ... ፈጽሞ ፡ ረስቼው ፡ ነበር ... ወረቀቶችም ፡ እኮ ፡ እስካሁን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ናቸው ። በሄድሁበት ፡ ሁሉ ፡ ይዣቸው ፡ እዞራለሁ ። ጀርጂያ ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ፈጣሪ ፡ ያገናኘናል ፡ ብዬ ፡ አልሜም ፡ አላውቅ ። እና ፡ ወረቀቶችዎን ፡ ምን ፡ ላርጋቸው?» በማለት ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ በድንገት ፡ የሠረገላውን ፡ በር ፡ እንቆ ፡ በጩኸት ፡ ይጠይቀው ፡ ገባ ።

«የፈለጉትን ፡ ያርጉት ፤ ደህና ፡ ይሁኑ!..» ሲል ፡ ፔቾሪን ፡ መለሰለት ።

«ታዲያ ፤ ወደ ፡ ፔርሺያ ፡ መሄድዎ ፡ ነዋ! መቼ ፡ ለመመለስ ፡ ይፈልጋሉ?» የሚለው ፡ የማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ የጥያቄ ፡ ጩኸት ፡ የሠረገላውን ፡ ዱካ ፡ ተከትሎ ፡ አስተጋባ ...

በዚህ ፡ ወቅት ፡ ሠረገላው ፡ ከነበረበት ፡ ተንቀስቅሶ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ይገኛል ። ፔቾሪን ፡ ለመጨረሻው ፡ ጥያቄ ፡ በእጁ ፡ ውዝዋዜ ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ ትርጉሙ ፡ «መመለሴን ፡ እንጃ ... ደግሞስ ፡ ለምን?» የሚል ፡ ይመስላል ።

የፈረሱ ፡ ታሜልና ፡ የተሽከርካሪው ፡ ጩኸት ፡ መሰማቱ ፡ ካቆመ ፡ ገዚ ፡ የለውም ። ሆኖም ፡ ያ ፡ ምስኪን ፡ ሽማግሌ ፡ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ ተውጦ ፡ በቆመበት ፡ ተተክሎ ፡ ቀረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም ፡ ሽማግሌው ፡ ምንም ፡ እንዳልሆነ ፡ ለማሳየት ፡ ቢጥርም ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ችፍጥ ፡ ያሉት ፡ እንባዎቹ ፡ ያሰጡታል ።

«... አምን ፤ ወዳጆች ፡ ነበርን ። ግን ፡ የዘመኑ ፡ ወዳጅነት ፡ ምን ፡ ፋይዳ ፡ አለው? እኔ ፡ ለእሱ ፡ ምንድን ፡ ነኝ? ከሃሳብ ፡ ሐብት ፤ ከሹመት ፡ ሹመት ፡ የለኝ ። ከዚያም ፡ በላይ ፡ የጨረጨስኩ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ። የፔቲርቡርግ ፡ ኑሮው ፡ እንዴት ፡ ለወጠው? የሠረገላውን ፡ ውበት ፤ የጓዙን ፡ ብዛት ፡ ሠደርያውን ... ልብ ፡ አሉት?» ይህን ፡ ሲል ፡ ፈገግ ፡ የተሞላበት ፡ ፈገግታ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይነበብለት ፡ ነበር ። ወደእኔ ፡ ዘወር ፡ ብሎም ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡ «ስለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ያስባሉ? እስቲ ፡ ይንገሩኝ? ወደፔርሺያ ፡ እንዲሄድ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰይጣን ፡ ገፋፋው? በእውነት ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ። የማያስተማምን ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ድሮም ፡ አውቃለሁ ። ሁኖም ፡ ፍጻሜው ፡ ስለማያምር ፡ ያሳዝናል ። ግን ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ። የድሮ ፡ ወዳጆቹን ፡ የሚረሱ ፡ ሰዎች ፡ መጨረሻቸው ፡ መጥፎ ፡ እንደሚሆን ፡ ድሮ ፡ ጀምሬ ፡ የምለው ፡ ነው!..» ይህን ፡ ብሎ ፡ ሐዘኑን ፡ ለመሸፈን ፡ የቆመውን ፡ ሠረገላ ፡ ተሽከርካሪ ፡ የሚፈትሽ ፡ በመምሰል ፡ ሽትብ ፡ ቁልቁል ፡ ይል ፡ ገባ ።

የሻምበሉ ፡ ሃሳቡን ፡ ከመቀየሩ ፡ በፊት ፡ ማስታወሻዎቹን ፡ ሰብስቤ ፡ ወሰድሁ ። ወዲያውም ፡ የሽኘዎቹ ፡ ጓድ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚነሳ ፡ ተነገረን ። እኔም ፡ ፈረሶቹ ፡ እንዲጫኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠሁ ። ባርኔጣዬን ፡ ልክ ፡ ስደፋ ፡ ሻምበሉ ፡ ወደክፍሌ ፡ ዘው ፡ አለ ። ለመንገዱ ፡ የተዘጋጀ ፡ ግን ፡ አይመስልም ፤ ሁለመናውም ፡ ቀዝቅዟል ።

«እርስዎስ ፡ አይሄዱም ፡ እንዴ ፤ ማክሲም ፡ ማሲሞቪች?»

«አልሄድም ።»

«ለምን?»

«ኮማንዳንቱን ፡ አላገኘሁትም ። የመንግሥት ፡ እቃ ፡ ለሱ ፡ ማስረከብ ፡ አለብኝ ።»

«ቅድም ፡ ወደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ አልነበረም?»

«መሄዱንስ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ቤቱ ፡ አልነበረም ። እኔም ፡ አልጠበቅሁትም ፡ ፡ሲል ፡ ታትቶ ፡ መለሰልኝ ።

«ምን ፡ ለማለት ፡ እንደፈለገ ፡ ገብቶኛል ። በሕይወቱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ምስኪን ፡ ሰውዬ ፡ የወታደር ፡ ሕጋዊ ፡ ሥርዓቱን ፡ ጥሶ ፡ በጽሑፍ ፡ ቋንቋ ፡ እንናገርና ፡ ለግል ፡ ጉዳዩ ፡ ቢያውለው ፡ ያገኘው ፡ ሽልማት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሆነ!

«ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ በጣም ፡ አዝናለ

እንባ ፡ ያቀረሩ ፡ ዓይኖቹ ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ሐዘኑን ፡ አልሸፈኑትም ።

«ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፤ ፔቾሪን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ወረቀት ፡ ነው ፡ እርስዎ ፡ ዘንድ ፡ የተወው?» ስል ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

«ምን ፡ አውቃለሁ ፤ ማስታወሻ ፡ ብጤ ፡ ይመስለኛል ።»

«ምን ፡ ሊያደርጉት ፡ ያስባሉ?»

«እ ... ምን ፡ አደርገዋለሁ? አቃጥለዋለኋ!»

«ለእኔ ፡ ቢሰጡኝ ፡ አይሻልም?»

በመገረም ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ከተመለከተኝ ፡ በኋላ ፡ አጉረምርሞ ፡ ቦርሳውን ፡ ይፈትሽ ፡ ጀመር ። ቀጥሎም ፡ ብሽቀት ፡ በተሞላበት ፡ ሁኔታ ፡ በመጀመሪያ ፡ አንዱን ፡ ከዚያም ፡ ሁለተኛውን ... ሶስተኛውን ... አሥረኛውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ከቦርሳው ፡ እያወጣ ፡ በየተራ ፡ ወደመሬት ፡ ወረወራቸው ። የሽማግሌው ፡ ሕፃናዊ ፡ ድርጊት ፡ አሳቀኝም ፤ አሳዘነኝም ...

«ያለው ፡ ይኸው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ስላገኙ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አልዎ!»

«የፈለግሁትን ፡ ላያርገው ፡ እችላለሁ?»

«ቢፈልጉ ፡ በጋዚጣም ፡ ላይ ፡ ያትሙት ... እኔ ፡ ምን ፡ ችግረኝ ።

ዘመዱ ፡ አያያለሁ ፡ ወዲያ ... በእርግጥ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ ጣራ ፡ ሥር ፡ አብረን ፡ ኑረናል ። በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ኑሬአለሁ ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁ ። እንዲህ ፡ በቶሎ ፡ በመለያየታችን ፡ የተ
ሰማኝ ፡ ሐዘን ፡ ልክ ፡ የለውም ፡» አልሁት ።
«እኛ ፡ ያልተማርን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከ
እናንተ ፡ ከዘመናዊ ፡ ወጣቶች ፡ ምናችን ፡ ይደ
ርሳል !.. እናንተ ፡ ኩሩዎች ፡ ናችሁ ። እዚህ ፤
እዚህ ፡ እስካላችሁና ፡ የቼርኬስ ፡ ጥይት ፡ በእና
ታችሁ ፡ እስካኛጪ ፡ ድረስ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
በሞላ ፡ ጐደል ፡ አብራችሁን ፡ ናችሁ ...
አጋጣሚ ፡ ሁኖ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ስንገናኝ ፡ ግን ፡
እኛችንን ፡ ለመጨበጥ ፡ ትፀየፋላችሁ ።»
«ምን ፡ አጠፋሁ ፡ እና ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ወቀሳ ፡
ነሚደርስብኝ ፤ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች?»
«አይ ፡ እኔ ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ በአጠቃላይ ፡ ነው ፡
የተናገርሁት ። ለማንኛውም ፡ መልካም ፡ እድ
ልና ፡ ቀና ፡ ጉዞ ፡ እመኝልዎታለሁ ።»
በመጨረሻም ፡ በቀዝቃዛ ፡ ስሜት ፡ ተለያ
የን ። ያ ፡ ደጉ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪችም ፡
ይረቅና ፡ ኮስታራ ፡ የሻምበል ፡ ሆነ ። ለምን ፡
ቢባል ፡ ፔቾሪን ፡ አውቆም ፡ ሆነ ፡ ባያውቅ ፡
በእንገቱ ፡ ላይ ፡ ተጠምጥሞ ፡ ሰላም ፡ ሊለው ፡
ቢፈልግ ፡ ለማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ እጁን ፡
ብቻ ፡ ዘረጋለት ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሰው ፡
ልጅ ፡ ተስፋ ፡ አዲስና ፡ አላፊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜያዊ ፡
ምኞት ፡ ሊተካ ፡ ቢችልም ፡ የአንድ ፡ ወጣት ፡
ሰው ፡ የወደፊት ፡ ያማረ ፡ ተስፋና ፡ ሕልም ፡
ወይም ፡ ደማሞ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ተግባርና ፡
ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ የሚያይበት ፡ ብሩህ ፡ እም
ነት ፡ ባጭሩ ፡ ሲቀጭ ፡ ማየት ፡ ያሳዝናል ... ሆ
ኖም ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ እድሜ ፡ ውስጥ ፡
ምን ፡ የሚቀየር ፡ ነገር ፡ አለ? ስለዚህም ፡ ወደ
ደም ፡ ጠላ ፡ ልበ ፡ ደንዳና ፡ ከመሆን ፡ እያልፍም ...
ጉዞዬን ፡ ለብቻዬ ፡ ቀጠልሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የፔጆሪን
ማስታወሻዎች።

t.me/OLDBOOKSPDF

መግቢያ

ፔቾሪን ፡ ከፔርሺያ ፡ ሲመለስ ፡ መሞቱን ፡ በቅርቡ ፡ ሰማሁ ። በማስታወሻዎቹ ፡ ላይ ፡ የራሴን ፡ ስም ፡ ፈርሜ ፡ ለማውጣት ፡ እድል ፡ ስላጋጠመኝ ፡ የመሞቱ ፡ ዜና ፡ ይበልጥ ፡ አስደሰተኝ ። አንባቢ ፡ ግን ፡ በዚህች ፡ እምነት ፡ ጥፋቴ ፡ እንደማያወግዘኝ ፡ ተስፋ ፡ እደርጋለሁ ።

የአንድን ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ ውስጣዊ ፡ የግል ፡ ምስጢር ፡ ደፍሬ ፡ በእደባባይ ፡ ለማውጣት ፡ ያስገደደኝን ፡ ምክንያት ፡ ቁጥዬ ፡ መግለጽ ፡ ይኖርብኛል ። የግል ፡ ወዳጅ ፡ እንኳ ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ነገሩ ፡ እስከዚህ ፡ ግራ ፡ ሊያጋባም ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ እኔ ፡ ሰውዬውን ፡ በሕይወቱ ፡ ያየሁት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ እሱም ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወዳጅነት ፡ የያዛቸው ፡ የማይጣጠሙ ፡ ሰዎች ፡ የሐዘን ፡ የስድብ ፡ ጋጋታ ፡ የምክርና ፡ የሽሙጥ ፡ የጭቃ ፡ ጆራፋቸውን ፡ የሚለጥፉት ፡ እንዱ ፡ በሞት ፡ ሲነጣል ፡ ወይም ፡ እሳቸኝ ፡ ዕጣ ፡ ሲደርስበት ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ ቢሆን ፡ እኔን ፡ እይመለከተኝም ። ወዳጅ ፡ አልነበርንምና፤ እነዚህን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስታወሻዎች ፡ ሳነብ ፤ ደራሲው ፡ የራሱን ፡ ደካምነት ፡ መጥፎ ፡ ልምዶች ፤ ያለምንም ፡ እር ሀራጌ ፡ በቅንነት ፡ ማቅረቡን ፡ ተገነዘብሁ ። የአንድ ፡ ሰው ፡ ውስጣዊ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፤ በበሰለ ፡ አእምሮ ፡ ከተመዘገበና ፡ ሌሎችን ፡ ቀስቅሶ ፡ ለማሳመን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ካልተጻፈ ፡ ከአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ የማያንስበት ፡ ምክንያት ፡ የለውም ። የሩሶም ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ የአጻጻፍ ፡ ስልት ፡ ስሀተቱ ፡ ለባልንጀሮቹ ፡ በማቅረቡ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በእጄ ፡ ከገቡት ፡ ማስታወሻዎች ፡ አንዳንዶቹን ፡ በግልጽ ፡ ለማሳተም ፡ የተገደድሁት ፡ በቅን ፡ መንፈስ ፡ ተነሳስቼ ፡ ነው ። በማስታወሻው ፡ ውስጥ ፡ ደራሲው ፡ ያሰፈራቸውን ፡ ስሞች ፡ ብቀይርም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እውነተኛ ፡ ስማቸውን ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ፡ እንደሚያገኙት ፡ አርግጠኛ ፡ ነኝ ። በሚቹም ፡ ላይ ፡ ላቀረቡት ፡ ክስ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ መልስ ፡ እንደሚሆናቸው ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። አንድ ፡ ነገር ፡ ሲገባን ፡ ይቅርታ ፡ ማድረግ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የተለመደ ፡ ነውና!..

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሰፈርሁት ፡ ፒቶሪን ፡ በካውካሱስ ፡ በንበረበት ፡ ወቅት ፡ የጻፋቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ሙሉ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ያሠራረበት ፡ አንድ ፡ ወፍራም ፡ መጽሐፍ ፡ ይተረጎማል ።

ይህንንም ፡ መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ አቀርበዋለሁ ። ሆኖም ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ሐላፊነቱን ፡ ልሸከም ፡ አልችልም ።

ምናልባት ፡ አንባቢዎቼ ፡ ስለፔቾሪን ፡ ያለኝን ፡ አስተያየት ፡ ሊያውቁ ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል ። ለዚሁ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ያለው ፡ በመጽሐፉ ፡ አርእስት ፡ ነው ። አንዳንዶቹ ፤ ይህ ፡ ክፉ ፡ ፌዝ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። እኔ ፡ አላውቅም ፤ ይሆን ፡ ይሆናል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

፫

ታማን።

ታማን ፡ በሩሲያ ፡ ወደብ ፡ ካሉ ፡ ከተማዎች ፡ በሙሉ ፡ የመጨረሻው ፡ አስፀያፊ ፡ ከተማ ፡ ነው ። በረሀብ ፡ ለመሞት ፡ ምንም ፡ አልቀረኝ ። በውሃም ፡ ሊያሰምጡኝ ፡ ነበር ።

ትናንትና ፡ ማታ ፡ በእቃ ፡ መጐተቻ ፡ ጋሪ ፡ ተጭኜ ፡ ከተማው ፡ ገባሁ ። ጋሪ ፡ ነጂው ፡ እነዚያን ፡ የደከሙ ፡ ሦስት ፡ ፈረሶቹን ፡ ከከተማው ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ባለችው ፡ የመጀመሪያና ፡ የመጨረሻ ፡ ሽክላ ፡ ቤት ፡ ያጀፍ ፡ ወስዶ ፡ አቆማቸው ። የፈረሶቹ ፡ ቃጭል ፡ የቀሰቀሰው ፡ የጥቁር ፡ ባሕር ፡ ቀበሌ ፡ ተረኛ ፡ ዘብ ፡ ካዛክ ፡ «ማንህ?» ሲል ፡ ጮህ ፡ ብሎ ፡ ባረቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ካዛክ ፡ ፱ አለቃና ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ፖሊስ ፡ ከሕንፃዋ ፡ ብቅ ፡ አሉ ። እኔም ፡ ወደተመደብሁበት ፡ ቦታ ፡ የምሔድ ፡ መኾንን ፡ መሆኔንና ፡ የማደሪያም ፡ ቦታ ፡ የምፈልግ ፡ መሆኔን ፡ ገለጥሁላቸው ። የማደሪያ ፡ ቦታ ፡ ለማግኘት ፡ ከፖሊሱ ፡ ጋር ፡ ከተማውን ፡ ብናካልል ም ፡ ይኳማቸኝ ፡ ነገሩ ፡ ሆነ ። ሁለም ፡ የማደሪያ ፡ ቤቶች ፡ ተይዘው ፡ ነበር ። ሦስት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀናት ፡ እኪታትዬ ፡ ካለመተኛቴም ፡ ሌላ ፡ ብርድ ፡ ስለነበረ ፤ ትዕግስቴ ፡ ሁሉ ፡ ተሟጠጠ ። «እንተ ፡ ወስላታ! ከፈለግኸው ፡ ቦታ ፡ ውሰደኝ ። ከፈለግህ ፡ ገሃነም ፡ እሳትም ፡ ምራኝ ፤ ብቻ ፡ ጉኔ ፡ የሚያርፍበት ፡ ቦታ ፡ ፈልግልኝ» ብዬ ፡ በፖሊስ ፡ ላይ ፡ ጮህኩበት ። በዚህ ፡ ግን ፡ ፖሊሱ ፡ ማጅራቱን ፡ በጥፍሮቹ ፡ እያከከ ፤ «ያላየናት ፡ እንዲት ፡ ቦታ ፡ ቀርታለች ፤ ግን ፡ ቦታዋ ፡ ለእርስዎ ፡ የምትሆን ፡ አይደለችም ፡ ጌታዬ ፤ ጽዱ ፡ አይደለችም» አለኝ ። የፖሊስ ፡ የመጨረሻ ፡ አንጋገር ፡ ምን ፡ ለማለት ፡ እንደሆነ ፡ በግልጽ ፡ ባይገባኝም ፡ እንዲመራኝ ፡ ጠየቅሁት ። በተሰበጣጠሩ ፡ እጥሮች ፡ ዳርና ፡ ዳሩ ፡ በተከበበ ፡ ጠባብ ፡ ጭቃማ ፡ መንገድ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተጉዘን ፤ ከባሕሩ ፡ ወደብ ፡ ካለች ፡ አንድ ፡ ዳሰሳ ፡ ጉጅ ፡ ደረስን ።

ያች ፡ የወደፊት ፡ መኖሪያዬ ፡ የሆነችው ፡ የድንጋይ ፡ ክዳን ፡ ያላት ፡ ቤት ፡ በነጭ ፡ ግድግዳዋ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ እርፎባት ፡ ታበራለች ። በኮርኮንች ፡ የድንገዩ ፡ አጥር ፡ በተከበበው ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ከዚች ፡ ጉጅ ፡ ያነሰችና ፡ ያረጀች ፡ ሌላ ፡ ቀሳ ፡ ትገኛለች ። ከነጪ ፡ ግድግዳ ፡ ጋር ፡ የተያያዘው ፡ ጭው ፡ ያለው ፡ አዘትት ፡ ወርዶ ፡ ከባሕሩ ፡ ይገናኛል ። ጥቁር ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የባሕር ፡ ሞገድ ፡ እያጐራ ፡ ሙጥቱ ፡ ከመደቡ ፡ ጋር ፡

እየተጋጨ ፡ ይመለሳል ። ጨረቃዋ ፡ ከላይ ፡ ገብ ፡ ብላ ፡ ፀጥ ፡ ባለውና ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ በሚቁነጠነጠው ፡ የተሰጠለጠ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ታበራለች ፡ በብርሃኗም ፡ ሁለት ፡ መርከቦች ፡ ከወደቡ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ እንደቆሙ ፡ ለማየት ፡ ተቻለ ። ለመርከቦቹ ፡ መልህቅ ፡ ላይ ፡ ያረፈው ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ መስመር ፡ ጥሎ ፡ ሲታይ ፡ አድፍጦ ፡ የተኛ ፡ እፍኝት ፡ ይመስላል ። «በወደብ ፡ ውስጥ ፡ መርከብ ፡ አለ ፤ ነገ ፡ ወደ ፡ ጌሌንጂክ ፡ መሐድ ፡ እችላለሁ» ብዬ ፡ አሰብሁ ።

ከከተማው ፡ የተሰጠኝ ፡ አንድ ፡ የካዛክ ፡ ወታደር ፡ አብሮኝ ፡ አለ ። ሻንጣዬን ፡ አውርዶ ፡ ጋሪ ፡ ነጂውን ፡ እንዲሸኝ ፡ ከነገርሁት ፡ በኋላ ፡ የቤቱን ፡ ባለቤት ፡ መጣራት ፡ ጀመርሁ ። መልስ ፡ አልነበረም ፤ በሩንም ፡ ቀርቢ ፡ አንኳኩሁ ። አሁንም ፡ መልስ ፡ የለም ።

«ምን ፡ ሆኑ?» ብዬ ፡ ሳስብ ፡ አንድ ፡ የአሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ብት ፡ አለ ።

«ባለቤቱ ፡ የት ፡ አለ?» — «ባለቤቱ ፡ የሉም ።» «ምን? ከባለቤቶች ፡ ማንም ፡ የለም ፡ ማለትህ ፡ ነው?» — «አዎን ፡ ማንም ፡ የለም ።» — «ባለቤትዋስ?» — «ከተማ ፡ ሄደዋል ።» — «ታዲያ ፡ በሩን ፡ ማን ፡ ይከፍትልኛል?» ብዬ ፡ መዝጊያውን ፡ በእርግጫ ፡ ወገርሁት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡

በሩ ፡ ተከፍቶ ፡ ከቤቱ ፡ የወጣ ፡ መጥፎ ፡ ጠረን ፡ አወጀኝ ። ክብሪት ፡ ጭሬ ፡ ወደልጁ ፡ ፊት ፡ አስጠግቼ ፡ በብርሃኑ ፡ ስመለከት ፡ የልጁ ፡ ዓይኖች ፡ ከተወለደ ፡ ጀምሮ ፡ የታወሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ተረዳሁ ። ሳይንቀሳቀስ ፡ ከፊቴ ፡ የተገተረውን ፡ ልጅ ፡ እኔም ፡ ትኩር ፡ ብዬ ፡ እጨነው ፡ ጀመር ።

በእውሮች ፤ በሸውራሮች ፤ በደንቆሮች ፤ በዲዳዎች ፤ በእጅና ፡ በእግረ ፡ ቆራጦች ፤ በመጻጉዎች ፡ በመሳሰሉት ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ ያለመውደድ ፡ ስሜት ፡ ለመደበቅ ፡ አልሻም ። በሰው ፡ ልጅ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ የላይ ፡ ጉድለቱ ፡ በውስጡም ፡ እንዳለ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታዝቤአለሁ ። አንድ ፡ ሰው ፡ እግሩ ፡ ሲቆረጥ ፡ ከስሜቶቹ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ አብሮ ፡ የሚቆረጥ ፡ ይመስለኛል ።

የዚያን ፡ የእውር ፡ ልጅ ፡ ገጽ ፡ ትኩር ፡ ብዬ ፡ ሳጤነው ፡ ቆየሁ ። ግን ፡ ዓይን ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ምን ፡ እንብብ ፡ ትሉኛላችሁ? ሳልወድ ፡ በግድ ፡ በሐዘን ፡ ተሰብሬ ፡ የልጁን ፡ ገጽ ፡ ስመለከት ፡ በድንገት ፡ ፈገግ ፡ ሲል ፡ አየሁት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ልገልጸው ፡ የማልችለው ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ አካላቴን ፡ ወረረው ። ምናልባትም ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ እንደመልኩ ፡ እውር ፡ አይሆንም ፡ ብዬ ፡ ተጠራጠርሁ ። ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ዕውር ፡ ለመመስል ፡ እንደማይችል ፡ በማሰት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እራሴን ፡ በራሴ ፡ እጽናናሁ ። ደግሞስ ፡ ጥረቱ ፡ ለምን ፡ ነው? ይሁንና ፡ ያይ ፡ ይሆናል ፡ የሚለው ፡ ጥርጣሬ ፡ ከመንፈሴ ፡ አልጠፋም ። ምን ፡ ላድርግ ፡ በተፈጥሮዬ ፡ ተጠራጣሪ ፡ ነኝ ።

«የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ልጅ ፡ ነህ?» ስል ፡ በመጨረሻ ፡ ጠየቅሁት ። «አይደለሁም ።» «ታዲያ ፡ ማነህ?» «እናት ፡ አባት ፡ የሌለኝ ፡ ደሀ ፡ እደግ ፡ ነኝ ።» «የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ልጅ ፡ አሏት?» «የላቸውም ። የነበራቸው ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡ ከአንድ ፡ ታታር ፡ ጋር ፡ ኮብልላ ፡ ሄዳለች ።» «ምን ፡ ዓይነት ፡ ታታር?» «ማንነቱን ፡ ሰይጣን ፡ ይወቀው ። እኔ ፡ ግን ፡ የክሪሚያ ፡ ታታር ፤ የኬርች ፡ መርከበኛ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የማውቀው ።»

ወደጐጆዋ ፡ ስገባ ፤ ከምድጃዋ ፡ አጠገብ ፡ ያገኘሁት ፡ ዕቃ ፡ ሁለት ፡ አግድም ፡ ወንበሮች ፤ አንድ ፡ ጠረጴዛና ፡ ሳንቃ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አንድም ፡ የቅዱሳን ፡ ሥዕል ፡ በቤቱ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ አይታይም ። ይህም ፡ መጥፎ ፡ ምልክት ፡ ነው ። ከባሀሩ ፡ የሚመጣው ፡ ነፋስ ፡ በአንድ ፡ በተሠበረች ፡መስኮት ፡ በኩል ፡ ይነፍሳል ። ከሻንጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ሻማ ፡ አውጥቼ ፡ አቀጣጥዬ ፡ እቃዬን ፡ መደርደር ፡ ጀመርሁ ። ጐራያዬንና ፡ ጠበንጃዬን ፡ ከግድግዳው ፡ ጥግ ፡ አኖርሁ ። ሽጉጤን ፡ ግን ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስተመጥሁ ። ያልሰለቸ ፡ ልብሴን ፡ ጐዝጉዤ ፡ ከአንድም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

መንበር ፡ ተኛሁ ። በሁለተኛው ፡ አግድም ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ዘበኛዬ ፡ ጋደም ፡ ብሎ ፡ አሥር ፡ ደቂቃ ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያንኳርፍ ፡ ገባ ። እኔ ፡ ግን ፡ እንቅልፍ ፡ በዓይኔ ፡ አልዞር ፡ አለኝ ። በሃሳቤም ፡ ያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ከፊቴ ፡ እየመጣ ፡ ይደነቀር ፡ ጀመር ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ አለፈ ። በመስኮት ፡ የሚገባው ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ እርከን ፡ አበጅቶ ፡ ይታያል ። በድንገትም ፡ እንድ ፡ ጥላ ፡ ውልብ ፡ ሲል ፡ ታየኝ ። ከተኛሁበት ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ በመስኮት ፡ ስመለከት ፡ የሰው ፡ ጥላ ፡ አሁንም ፡ ሽው ፡ ብዬ ፡ ሲያልፍ ፡ አየሁት ። ወዴት ፡ እንደሄደ ፡ ግን ፡ ለማወቅ ፡ አልቻልሁም ። ጥላው ፡ የታየኝ ፡ ሰው ፡ ወደባሕር ፡ በሚያመራው ፡ አዘቅት ፡ አቆልቁሎ ፡ ወረደ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ሌላ ፡ መሄጃ ፡ ደግሞ ፡ አልነበረውም ። ወዲያውኑ ፡ ጐራዴዬን ፡ ታጥቂ ፡ በቀስታ ፡ ከጐጆዋ ፡ ወጣሁ ። ከዚያም ፡ እውሩ ፡ ወደእኔ ፡ ሲመጣ ፡ አየሁት ። በጥንቃቄ ፡ እርምጃ ፡ የሚያመራውንም ፡ እውር ፡ ወደአጥሩ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ አሳለፍሁት ። እንዳች ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ በብብቱ ፡ ይዟል ። መርከቦቹ ፡ በቆሙበት ፡ አትጣጫ ፡ ወደምትወስደው ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በጥንቃቄ ፡ አመራ ። ይህኔ ፡ «እውሮችም ፡ ያያሉ ፤ ደንቆሮችም ፡ ይሰማሉ ፡» ያለው ፡ ቅዱስ ፡ መንጌል ፡

«ታዲያስ ፡ እውሩ? የዛሬው ፡ ማዕበል ፡ ኃይ
ለኛ ፡ ነው ። ያንኮ ፡ አይመጣም ፡» የሚል ፡
የሴት ፡ ድምፅ ፡ ተሰማኝ ።

«ያንኮ ፡ እኮ ፡ ማዕበል ፡ አይፈራም ፡» ሲል ፡
እውሩ ፡ መለሰላት ።

«ቢሆንም ፡ ጭጋግ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ነው ፡»
አለችው ።

«ጭጋግ ፡ ከሆነ ፡ ጠባቂ ፡ መርከቦችን ፡ ተሽ
ሎክሉኮ ፡ ለማለፍ ፡ ይችላል ።»

«ቢሰምጥስ?»

«ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፤ እሁድ ፡ ለት ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለ ፡ አዲስ ፡ ሪባን ፡ መሔ
ድሽ ፡ ነዋ!»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፀጥታ ፡ ሆነ ። ሆኖም ፡ እንድ ፡
ነገር ፡ አስገረመኝ ። ያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ ባወራበት ፡ ወቅት ፡ የኡክርዮኖች ፡ የቃ
ላት ፡ አጣጣል ፡ ነበረው ፤ እሁን ፡ ግን ፡ ጥርት ፡
ያለ ፡ የሩሲያ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራል ።

እውሩ ፡ ልጅ ፡ እያጨበጨበ ፡ «ይኸውልሽ...
አላልሁሽም? ያንኮ ፡ ባሕርን ፤ ነፋስን ፤ ጭጋግን ፤
ወይም ፡ ደግሞ ፡ የጠረፍ ፡ ጠባቂዎችን ፡ አይፈ
ራም ። አዳምጭ ፤ ይህ ፡ የሚሰማው ፡ የማዕበል ፡
አይደለም ። ልታታልይኝ ፡ አትችይም ፤ የያን
ኮን ፡ ረጅም ፡ መቅዘፊያ ፡ ነው ፡» አላት ።

ሴትዮዋ ፡ በጉጉት ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ እሻግራ ፡ ትመ
ለከት ፡ ገባች ።

ትዝ ፡ አለኝ ። ከዓይኔም ፡ እንዳይሰወር ፡ በቅርቡ ፡
እከታተለው ፡ ገባሁ ።

በዚህ ፡ ወቅት ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ በደመ
ናዎች ፡ ተከበበች ። ባሕሩም ፡ በጭጋግ ፡ ስለተ
ሸፈነ ፡ ከወደቡ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ከቆሙት ፡ መር
ከቦች ፡ ቀረብ ፡ ያለው ፤ መብራቱ ፡ ለአመል ፡
ያህል ፡ ይታያል ። እንፋሎት ፡ እየተፋ ፡ የሚደ
ነፋው ፡ ማእበል ፡ ከአሁን ፡ አሁን ፡ ምድሩን ፡
የሚያጥለቀልቀው ፡ ይመስላል ። በችግር ፡
እየተመለከትሁ ፡ ልጁን ፡ ተከትዬ ፡ ቁልቁል ፡
ወረድሁ ። ያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡ ወደ
ቀኝ ፡ ከታጠፈ ፡ በኋላ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ስለተ
ጠጋ ፡ ማእበል ፡ አቅፎ ፡ ወስዶ ፡ ይደለዋል ፡
ብዬ ፡ ሠጋሁ ። ሆኖም ፡ ከጉድጓዱ ፡ ጉድባ ፡
ከድንጋይ ፡ ድንጋይ ፡ እየተራመደ ፡ ሲሸጋገር ፡
ሳየው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ሲመጣ ፡ የመጀመ
ሪያው ፡ ጊዜ ፡ እንዳልሆነ ፡ ተረዳሁ ። በመጨረ
ሻም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንደሰማ ፡ ቀጥ ፡ ካለ ፡
በኋላ ፡ ያን ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ ቁሜ ፡ አድርጉ ፡
ተቀመጠ ። ባንዲት ፡ ቋጥኝ ፡ ድንጋይ ፡ ተደብቄ ፡
የሚያደርገውን ፡ እመለከት ፡ ጀመር ። ከጥቂት ፡ ደ
ቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ ከወዲያ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡
ነገር ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ከእውሩ ፡ አጠገ
ብ ፡ ቁሜ ፡ አለ ። ወያኔ ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡
የሚነጋገሩትን ፡ ሁሉ ፡ እያመጣ ፡ በግልጽ ፡
ያሰማኝ ፡ ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዉትቃገፖለሀ ፡ እውሩ ። ምንም ፡ ነገር ፡ እይታ የኝም ።»

ምንም ፡ እንኳ ፡ ከሩቁ ፡ የማየት ፡ ልም ድ ፡ ከድሮው ፡ ቢኖረኝም ፡ ወደባሕሩ ፡ እት ኩራ ፡ ብመለከት ፡ ምንም ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ አጣሁ ። ከአንድ ፡ ከአሥር ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ባሻገር ፡ ካሉት ፡ ተራራዎች ፡ ሥር ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ መርከብ ፡ አየሁ ። ከማዕበሉም ፡ ፈረሰኛ ፡ ጋር ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያለ ፡ እኛ ፡ ወዳለንበት ፡ ተጠጋ ። እንዲህ ፡ ባለ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሌሊት ፡ ሀያ ፡ ቀዳ ፡ አቁርጦ ፡ እንዲመጣ ፡ ያደረገው ፤ አንድ ፡ አስ ቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ቢኖረው ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የልቤ ፡ ትርታ ፡ ሳልወድ ፡ በግድ ፡ ምቱን ፡ እየጨመረ ፡ ሔደ ። ከንፍ ፡ እንዳለው ፡ አሞራ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየቀዘፈ ፡ እንደዳከዬ ፡ ጭጋጉን ፡ እየበረጋገደ ፡ የሚንሳፈፈውን ፡ ጀልባ ፡ ፍጥነት ፡ ሳይ ፡ ከድንጋይ ፡ ጋር ፡ ተጋጭቶ ፡ ተሰበረ ፡ ብዬ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ከን ፍ ፡ እንዳለው ፡ አሞራ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየቀዘፈ ፡ በድንጋዮች ፡ መካከል ፡ ተሽሎክሉኩ ፡ በሰላም ፡ ከአንዲት ፡ ጠባብ ፡ ወደብ ፡ ደረሰ ። እንድ ፡ መኮክለኛ ፡ ቁመት ፡ ያለው ፡ ከታታር ፡ የበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ባርኔጣ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ከጀልባ ው ፡ ወጣ ። በእጁ ፡ ምልክት ፡ ሲሰጣቸው ፡ ሁሉ ም ፡ ከጀልባው ፡ እቃ ፡ ያራግፉ ፡ ገቡ ። ከጀል

t.me/OLDBOOKSPDF

ባው ፡ የወጣው ፡ የእቃ ፡ ብዛት ፡ ብዙ ፡ ሲሆን ፡ መርከቧ ፡ እንዲት ፡ ሳትሰጥም ፡ እንደቀረች ፡ ሳስበው ፡ እስከዛሬ ፡ ይገርመኛል ። እያንዳን ዳቸው ፡ ከወረደው ፡ እቃ ፡ ተሸከመው ፡ በባ ሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ ይዘው ፡ ከዓ ይኔ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ተጓዙ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደጐጇዬ ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። ይህም ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ስላስደነገጠኝ ፡ ሌሊቱ ፡ እስኪነጋ ፡ ተጨነቅሁ ።

ካዛኩ ፡ ሲነቃ ፡ ከነልብሴ ፡ ቢያየኝ ፡ መገረሙ ፡ ቢገባኝም ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ማብራሪያ ፡ አልሰ ጠሁትም ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በደመና ፡ የተለበ ጠውን ፡ ሰማያዊ ፡ ሰማይ ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ሔዶ ፡ ሔዶ ፡ የሚያርፍበትን ፡ ቋጥኝና ፡ ከዚያም ፡ የሚያቆ ምበትን ፡ ደበዝበዝ ፡ ያለች ፡ ቤት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ እያየሁ ፡ ሳደንቅ ፡ ከቆየሁ ፡ በኋላ ፡ ጌሴንጊክ ፡ ለመሔድ ፡ መቼ ፡ እንደምችል ፡ ኮማንዳንቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደፋናጐሪያ ፡ ሠፈር ፡ አመራሁ ።

ሆኖም ፡ ኮማንዳንቱ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሊነግረኝ ፡ አልቻለም ። በወደቡ ፡ አጠገብ ፡ የቆሙት ፡ መርከቦች ፡ ጠረፍ ፡ ጠባቂ ፡ ይሁኑ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ መርከብ ፡ እሳውቅም ፤ እስካ ሁን ፡ መጫን ፡ እንኳ ፡ አልጀመሩም ። ፀምናል ባት ፡ በሦስት ፡ ወይም ፡ በአራት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡

ፖስታ ፡ ጫኝ ፡ መርከብ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ፤ ያኔ ፡ እናያለን ፡» ሲል ፡ ኮማንዳንቱ ፡ መለሰ ልኝ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ ወደዚያች ፡ ደላላ ፡ ጐጆዬ ፡ ተናድጀና ፡ አገኘ ፡ ተመለስሁ ። ያ ፡ የካሳከ ፡ ዘበኛዬም ፡ ፍርኃት ፡ በተሞላበት ፡ ሁኔታ ፡ ከበሩ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበለኝ ።

«ሁኔታው ፡ አላማረም ፡ ጌታዬ!» «እሞን ፡ ወዳጄ ፤ ከዚህ ፡ ሐገር ፡ መቼ ፡ እንደምንሔድ ፡ አይታወቅም ።» እንዲህ ፡ ስለው ፡ የባሰውን ፡ ተጨነቀ ። ወደእኔም ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ በሹክሹክታ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ነገረኝ ።

«አካባቢው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አይልም ። በጥቁር ፡ ባሕር ፡ የሚያገለግሉትን ፡ የ ፱ አለቃ ፡ ዛሬ ፡ አግኝቻቸው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ አውቃቸዋለሁ ። አምና ፡ በአንድ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አብረን ፡ አገልግለናል ። የት ፡ እንዳረፍን ፡ ብነግራቸው ፡ እንዲህ ፡ አሉኝ ። «ወንድሜ ፡ ሆይ ፤ ቦታው ፡ ጽዳት ፡ የለውም ። ሰዎቹም ፡ ክፉ ፡ ናቸው» እውነቱን ፡ ነው ፡ የዚያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ነገርማ ፡ አይነሳ!! ብቻውን ፡ የት ም ፡ ደርሶ ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ። ገበያ ፡ ወጥቶ ፡ ለመግዛትም ፡ ሆነ ፡ ውሃ ፡ ለመቅዳት ፡ መሪ ፡ አያ ሻውም ። ይህን ፡ ተአምር ፡ አካባቢው ፡ ስለተለ ማመደው ፡ ከመጤሩ ፡ አይቆጥረውም ።»

«ታዲያ ፡ ምን ፡ አለበት? ይልቅስ ፡ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ መጥታ ፡ ነበር?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጥዋት ፡ እርስዎ ፡ በሌሉበት ፡ አንዲት ፡ ኦሮ ገ ት ፡ ሴትዮ ፡ ከሴት ፡ ልጅዋ ፡ ጋር ፡ መጥታ ፡ ነበር ።»

«ከየት ፡ የመጣች ፡ ሴት ፡ ልጅ? ሴት ፡ ልጅ ፡ የት ፡ አላት?»

«እንግዲያውስ ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፤ አምላክ ፡ ይወቅላት ። ለማንኛውም ፡ ኦሮጊቷ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ አለች ።»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደቤት ፡ ገባሁ ። የምድጃዋ ፡ እሳት ፡ ላይ ፡ ለድሃ ፡ ቤተሰብ ፡ ደረጃ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ምግብ ፡ ይቀቀላል ። ለማቀር ብላት ፡ ጥያቄ ፡ ሁሉ ፡ ሳትመልስ ፡ ደንቆሮ ፡ መሆኗን ፡ አበሰረችኝ ። የማደርገው ፡ ቢጨ ንቀኝ ፡ የፍልጥ ፡ እንጨት ፡ ይቆሰቁስ ፡ የነበረ ውን ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ለማነጋገር ፡ ተገደድሁ ። ጀሮውንም ፡ ጠምዝዦ ፡ ይገፍ ፡ እንዲህ ፡ አል ሁት ፤ «አንተ ፡ እውር ፡ ሰይጣን ... ለመሆኑ ፡ ትናንትና ፡ የት ፡ ነበርህ? ያንን ፡ ጥቅል ፡ ይዘህ ፡ የሔድኸው ፡ የት ፡ ነው?» ስለው ፡ እየጮኸ ፡ ያነባ ፡ ጀመር ። «የት ፡ ሔድሁኝ? የትም ፡ አል ሔድሁ ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጥቅል ፡ አላየሁም ።» በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሮጊቷ ፡ ሰምታ ፡ ማጉረምረም ፡ ገባች ። «አውን ፡ ይህ ፡ ምስኪን ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ አደረገዎት? ለምን ፡ እይተውትም?» ይህ ፡ እነ ጋገር ፡ የባሰውን ፡ እናዶኝ ፡ ከቤት ፡ ወጥቼ ፡ ሔድሁ ። ምስጢራቸውንም ፡ ለመፍታት ፡ ቁርጥ ፡ ውሳኔ ፡ አደረግሁ ።

ካፖርቴን ፡ ደረብ ፡ አድርጌ ፡ ከአጥሩ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ትክል ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ማዶ ፡ ማዶውን ፡ መመልከት ፡ ገባሁ ። ከፊት ፡ ለፊቴ ፡ የተለጠለጠው ፡ ከትናንት ፡ ጀምሮ ፡ በማዕበል ፡ የሚቁነጠነጠው ፡ የባሕር ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡የሚናዱ ፡ ከተማዎችን ፡ ይመስል ፡ ያለፉትን ፡ ዘመናት ፡ አስታወሰኝ ። ሐሳቤን ፡ ወደዋና ፡ ከተማችን ፡ ወደሰሜን ፡ ሸመጠጠ ። በትካዜ ፡ ዓለም ፡ ውስጥም ፡ ሰጥሜ ፡ ያለሁበትን ፡ አካባቢ ፡ ፈጽሞ ፡ ረሳሁ ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ ወይም ፡ ይበልጥ ፡ ሳልቆይ ፡ አልቀረሁም ። በድንገት ፡ አንድ ፡ ዘፈን ፡ ብጤ ፡ በጆሮዬ ፡ አስተጋባ ። በእርግጥም ፡ ዘፈን ፡ ነው ፡ የሚያዜመው ፡ ጥሩ ፡ የሴት ፡ ድምፅ ፡ ነው ። ግን ፡ ከየት ፡ ነው ፡ የሚመጣው? ለማንኛውንም ፡ ጆሮዬን ፡ ቀስሬ ፡ ማዳመጤን ፡ ቀጠልሁ ። ዜማ ፡ ግራ ፡ ያጋባል ፡ አንዴ ፡ ረዘም ፡ ያለና ፡ አሳዛኝ ፡ ነው ። ቆየት ፡ ያልና ፡ ደግሞ ፡ ፈጣንና ፡ ሕያውት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ዙሪያዬን ፡ ተገለማምጨ ፡ ተመለከትሁ ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ ባጠገቤ ፡ አልነበረም ። እንደገና ፡ ሳዳምጥ ፡ ዜማው ፡ ከላይ ፡ የሚመጣ ፡ ይመስላል ። ወደላይ ፡ አንጋጥጨ ፡ ተመለከትሁ ፡ ዝንጉርጉር ፡ ቀሚስ ፡ የለበሰች ፡ አንዲት ፡ ወጣ ፡ ሯን ፡ የለቀቀች ፡ ሴት ፡ ምስል ፡ ልጅ ፡ ከዘያች ፡ ይሳሳ ፡ ጉጅ ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ ቆማ ፡ ከዘሐይ ፡ ጨረር ፡ ዓይኗን ፡ በከንዲ ፡ ሸፍና ፡ ማዶውን ፡ እያየች ፡ አንዴ ፡ ስትስቅ ፡ ከራሷ ፡ ጋር ፡ ስትናገር ፡ መልሳ ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ ዘፈን ፡ ስታንጐራጉር ፡ ተመለከትሁ ። ዘፈኗን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አስታውሰዋለሁ ።

ጭው ፡ ያለ ፡ ሣራማ ፡ ሜዳ ፡ በመሰለው ፤
በሰማያዊው ፡ ባሕር ፡ ንጥት ፡ ፍንትው ፡ ባለው ፤
መርከቦች ፡ በላዩ ፡ ያው! ይንሳፈፋሉ ፤
ነጭ ፡ አውታር ፡ ዘርግተው ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ይላሉ ።

ይህንን ፡ ድምፅ ፡ ትናንት ፡ የሰማሁት ፡ መሰለኝ ። ለእንድ ፡ ደቂቃም ፡ ያህል ፡ እንደገና ፡ በሐሳብ ፡ ተውጨ ፡ ብዬ ፡ ከጣራ ፡ ሳያት ፡ አጣኋት ። ከየት ፡ መጣች ፡ ሳትባል ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ዜማ ፡ እያዜመች ፡ በጣቷ ፡ እየጨበጨበች ፡ በአጠገቤ ፡ አልፋ ፡ እየሮጠች ፡ ወደአሮጊቷ ፡ ገባች ። ወዲያውም ፡ ሲከራከሩ ፡ ድምፃቸው ፡ ተሰማኝ ። የአሮጊቷ ፡ መናደድ ፡ ያስታውቃል ፤ ልጅቷ ፡ ግን ፡ ከት ፡ ከት ፡ እያለች ፡ ትስቃለች ። ትንሽ ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ ይህችው ፡ የዛር ፡ ልጅ ፡ ተመልሳ ፡ ከቤት ፡ ወጣች ። ከተቀመጥሁበት ፡ ቦታ ፡ ስትደርስ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዳየችኝ ፡ ሁሉ ፡ ቆም ፡ ብላ ፡ በመገረም ፡ ሁለት ፡ ዓይኖቿን ፡ ትኩር ፡ አድርጋ ፡ እየችኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስምንት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እትመስልም ። ያ ፡ እጹብ ፡ ድንቅ ፡ እካላታ ፡ ልዩ ፡ የሆነው ፡ የአንገት ፡ አቀለባበት ፤ ያ ፡ ወርዶ ፡ በሽንጧ ፡ ላይ ፡ የተዝለፈለፈው ፡ ቡናማ ፡ ፀጉሯ ፤ ያ ፡ በመጠኑ ፡ በዐሐይ ፡ ብርሃን ፡ የጠየመው ፡ አንገቷና ፡ ትከሻዋ ፤ በተለይም ፡ ቅርጽ ፡ የሚመስለው ፡ እፍንጫዋ ፡ ደስ ፡ አለኝ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የጉን ፡ አስተያየቷ ፡ ያልተገራና ፡ ጠርጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ፈገግታዋን ፡ ለመግለጽ ፡ ቢያስቸግርም ፤ በአጠቃላይ ፡ ያሳደረችብኝ ፡ ስሜት ፡ የዋዛ ፡ አልነበረም ። ያ ፡ ቀጥ ፡ ያለው ፡ አፍንጫዋ ፡ አሳበደኝ ። ግዮቴ ፡ በመጽሐፉ ፡ ያቀረባትን ፡ ያችን ፡ የጀርመን ፡ ተዋናይ ፡ ሚኙን ፡ ያገኘኋት ፡ መስለኝ ። በእውነትም ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ቁንጥንጥ ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ ከመቅጽበት ፡ ድርቅ ፡ በማለቱ ፡ ግራ ፡ በሚያጋባው ፡ ንግግር ፤ በአዘላለሏ ፤ ባልተለመደው ፡ ዘፈኗ ፡ ... በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይመሳሰላሉ ።

መሸትሸት ፡ ሲል ፡ ከበሩ ፡ አጠገብ ፡ አቁሜ ፡ አናገርኋት ።

«የእኔ ፡ ቆንጆ ፤ እስቲ ፡ ንገሪኝ ፤ ዛሬ ፡ እጣራው ፡ ላይ ፡ የወጣሽው ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ ነው?»

«ነፋስ ፡ ከየት ፡ እንደሚነፍስ ፡ ለማየት ፡ ነው ።»

«ለምን?»

ከዚያም ፡ በግዴለሽነት ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ ወገግታ ፡ ወደመርከቦች ፡ የሚያመራውን ፡ መንገድ ፡ ይዛ ፡ ተጓዘች ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ አልሆነም ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እንዲት ፡ ደቂቃ ፡ ሳታርፍ ፡ ያችን ፡ ደላላ ፡ ጐጆ ፡ እየዞረች ፡ ስትዘፍንና ፡ ስትዘል ፡ ዋለች ። በእርግጥም ፤ የምትገርም ፡ ፍጡር ፡ ናት ። መላ ፡ ሁኔታዋ ፡ ሲታይ ፡ ደግሞ ፡ እብድ ፡ እትመስልም ። እንዲያውም ፡ እነዚያ ፡ ዓይኖቿ ፡ ሰውነቴን ፡ ሰንጥቀው ፡ ገብተዋል ። አንድ ፡ ዓይነት ፡ የመማረኪያ ፡ ኃይል ፡ አላቸው ። አንዳንድ ፡ አስተያየቷ ፡ ለጥያቄ ፡ የሚጋብዝ ፡ ይመስላል ። ሆኖም ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ገና ፡ አፌን ፡ ስከፍት ፡ በፈገግታዋ ፡ ሸንግላኝ ፡ እየሮጠች ፡ ጥላኝ ፡ ትሄዳለች ።

እንዲህ ፡ ያለች ፡ ሴት ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ አላጋጠመኝም ። ቆንጆ ፡ አይደለችም ። በቁንጅናም ፡ በኩል ፡ ቢሆን ፡ የራሴ ፡ ግምትና ፡ የራሴ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለኝ ። የጠራች ፡ ዘር ፡ ናት ... የሴቶችም ፡ የጠራ ፡ ዘርነት ፡ ለፊረሶች ፡ የሚፈለገውን ፡ ያህል ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በምርምር ፡ ጥናት ፡ ያገኘችው ፡ ወጣት ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ናት ። የዘሩ ፡ ጥራት ፡ የሚታወቀው ፡ በአረማመድ ፤ በእጅና ፡ በእግር ፡ በተለይም ፡ በአፍንጫ ፡ ነው ። በሩሲያ ፡ ውስጥ ፡ ሰንደዶ ፡ አፍንጫ ፡ ከማግኘት ፡ ይልቅ ፡ ትናንሽ ፡ እግሮች ፡ ማግኘት ፡ ይቀላል ። ያቺ ፡ የኔ ፡ ዘፋኝ ፡ ከአሥራ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

«ደስታ ፡ ያለው ፡ ነፋስ ፡ ከሚነፍስበት ፡ ቦታ ፡ ስለሆነ ፡ ነዋ!»

«በዜማሽ ፡ የምትጠሪው ፡ ደስታ ፡ ነበረ?»

«ዘፈን ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ደስታ ፡ አለ ።»

«በራስሽ ፡ የሐዘን ፡ ዘፈን ፡ ብትዘፍኚስ?»

«ታዲያ ፡ ምን ፡ አለበት? ሁኔታው ፡ ካልተሻሻለ ፡ ያው ፡ እየተባባሰ ፡ ይሔዳል ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ በመጥፎና ፡ በጥሩ ፡ ሕይወት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እስከዚህ ፡ ጉልቶ ፡ አይታይም ።»

«ያንን ፡ ዘፈን ፡ ማነው ፡ ያስተማረሽ?»

«ማንም ፡ አላስተማረኝም ፤ የመጣልኝን ፡ ሁሉ ፡ እዘፍናለሁ ። የማዜምለትም ፡ ሰው ፡ ይሰማኛል ። ሌሎች ፡ ግን ፡ አይገባቸውም ።»

«ስምሽ ፡ ማን ፡ ነው ፤ የእኔ ፡ ወፍ?»

«ያጠመቀኝ ፡ ያውቀዋል ።»

«ታዲያ ፡ ያጠመቀሽ ፡ ማነው?»

«ምኑን ፡ አውቂው?»

«ልበ ፡ ስውር ፡ ነሽ ፤ ግን ፡ እኔ ፡ ስላንቺ ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ አለ ።»

ይህንን ፡ ስላት ፡ በፊታ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ለውጥ ፡ አልታየበትም ። ጉዳዩ ፡ እሷን ፡ እንዳይ መለከት ፡ ሁሉ ፡ ከንፈሯ ፡ አልተንቀጠቀጠም ። «ትናንት ፡ ማታ ፡ ባሕሩ ፡ ዳር ፡ እንደነበርሽ ፡ አውቃለሁ» በማለት ፡ ለራሴ ፡ ታላት ፡ ነብር ፡ ሰጥቼ ፡ ላስፈራራት ፡ ያየሁትን ፡ በሙሉ ፡ ዘነ

ገዘሁ ፡ ነገርኳት ። ሆኖም ፡ መከራዬ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ። እንዲያውም ፡ በሳት ፡ ተን ከተከተች ።

«ብዙ ፡ አይተዋል ፡ የሚያውቁት ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ። ይህችንም ፡ የሚያውቋትን ፡ ለራስዎ ፡ ቢይዟት ፡ ይሻላል ።»

«ለኮማንዳንቱ ፡ ሄጂ ፡ ብነግርስ?» ስል ፡ ኮስተር ፡ ብዬ ፡ ጠየቅኋት ። ድንገትም ፡ እንጣጥ ፡ ብላ ፡ ትዘፍን ፡ ገባች ። ከዚያም ፡ እንደተባረረች ፡ ወፍ ፡ እልም ፡ ብላ ፡ ከአጠገቤ ፡ ጠፋች ። በመጨረሻ ፡ የሰነዘርሁት ፡ ሃሳብ ፡ ያለቦታው ፡ የገባ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ ሲገባኝ ፡ ምነው ፡ አፌን ፡ በቆረጠው ፡ አልሁ ።

ጊዜው ፡ ጨለምለም ፡ አለ ፤ ካዛኩ ፡ የሻሂ ፡ ጀበና ፡ እንዲጥድ ፡ አዝዤ ፤ ሻማ ፡ አብርቼ ፤ የመንገድ ፡ ፒፓዬን ፡ አቀጣጥዬ ፡ ጠረጴዛው ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ አጨስ ፡ ጀመር ። የሁለተኛውን ፡ ብርጭቆ ፡ ሻሂ ፡ ልጨርስ ፡ ስል ፡ በሩ ፡ በቱስታ ፡ ተከፍቶ ፡ ቀላል ፡ የሰው ፡ ኮቴ ፡ ተሰማኝ ። በድንጋጤ ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ብመለከት ፡ ያችው ፡ የዛር ፡ ልጅ ፡ ሆና ፡ አገኘኋት ። ምንም ፡ ትንፋሽ ፡ ሳትነፍስ ፡ ከፊት ፡ ለፊቴ ፡ ጉልት ፡ ብላ ፡ እፍጣ ፡ ትመለከተኝ ፡ ገባች ። እስተያየቷ ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የእኔን ፡ ልብ ፡ የማረኩትን ፡ የድሮ ፡ ትዝታ ፡ እስታወሰኝ ። እስከም ናገር ፡ ድረስ ፡ የምትጠብቀኝ ፡ ትመስላለች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆይቼ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከተኛ ፡ በኋላ ፡ ካዛኩን ፡ ቀስቅሼ ፤ «የሽጉጥ ፡ ድምፅ ፡ ስትሰማ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ እንድትመጣ» ብዬ ፡ አዘዝሁት ። እሱም ፡ በድን ጋጤ ፡ ፈዞ ፡ ካየኝ ፡ በኋላ ፤ «እሺ ፡ ጌታዬ» የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ ። እኔም ፡ ወዲያውኑ ፡ ሽጉጤን ፡ ታጥቄ ፡ ወጣሁ ። ያች ፡ የዛር ፡ ልጅም ፡ ከቁልቁለቱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ስትጠብቀኝ ፡ አገኘኋት ። ልብሷ ፡ ቀላልና ፡ ስስ ፡ ነበር ። የሻሽ ፡ መቀነት ፡ ቢጤም ፡ በወገቧ ፡ ላይ ፡ አስራለች ።

መጻፌን ፡ ጨበጥ ፡ አድርጋ ፤ «ይከተሉኝ» ብላኝ ፡ እጇን ፡ ይዛኝ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወረድን ። እንዴት ፡ ወድቄ ፡ እንዳልተሰበርሁ ፡ አላውቅም ። ከቁልቁለቱ ፡ ታች ፡ ስንደርስ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያንን ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ በተከተልሁበት ፡ መንገድ ፡ ወደቀኝ ፡ ዞረን ፡ አመራን ። ጨረቃዋ ፡ ገና ፡ አልወጣችም ። በጥቁሩ ፡ ሰማያዊ ፡ ደመና ፡ ላይ ፡ የሚያበሩት ፡ ሁለት ፡ ከዋክብት ፡ ከሩቅ ፡ የሚታዩ ፡ ቤቶች ፡ ይመስላሉ ።

በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚፎገለው ፡ ማዕበል ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ታሥራ ፡ የቆመችዋን ፡ እንድ ፡ ጀልባ ፡ ብድግ ፡ ዝቅ ፡ ያደርጋታል ። መሪዬ ፤ «በጀልባዋ ፡ ላይ ፡ እንቀመጥ» አለችኝ ። በተፈጥሮዬ ፡ የባሕር ፡ ሽርሽር ፡ አፍቃሪ ፡ ባለመሆኔ ፡ ሳመነታም ፡ የማፈግፈጊያው ፡ ጊዜ ፡ ስላ

ሆኖም ፡ እኔ ፡ የምናገረው ፡ ጠፍቶኝ ፡ ግራ ፡ ገባኝ ። በረጋ ፡ መንፈስ ፡ ቁጭ ፡ ያለውን ፡ ፊቷን ፡ ስመለከት ፡ ከውስጣዊው ፡ ቁንጥንጥ ፡ ባሕርዮ ፡ ጋር ፡ የማይጣጣም ፡ ሆኖ ፡ ተሰማኝ ። ጠረጴዛውን ፡ የሚጸስሱት ፡ እጆች ፡ ይርበደበዳሉ ። ጡቶቿ ፡ ወደላይ ፡ እየቆዩ ፡ ሲያብጡ ፡ ሳያቸው ፡ ትንፋሽዋን ፡ ሆን ፡ ብላ ፡ የያዘችው ፡ መሰለኝ ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሰፈነው ፡ ፀጥታ ፡ በጣም ፡ ሰለቸኝ ። የዚህን ፡ ከባድ ፡ የዝምታ ፡ አየር ፡ ያለምንም ፡ ጋጋታ ፡ ለመቀየር ፡ ስል ፡ ሻይ ፡ በብርጭቆ ፡ ልስጣት ፡ ስል ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ በእንገቴ ፡ ላይ ፡ ተጠምጥማ ፡ በዚያ ፡ ለስላሳ ፡ ከንፈሮቿ ፡ ከንፈሮቼን ፡ ስትጉርሳቸው ፡ የውስጣዊ ፡ ግለቷ ፡ ተሰማኝ ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ ጨለመብኝ ። ራሴም ፡ ዞረ ፤ የወጣትነት ፡ ስሜቴን ፡ ሳልሸመቅቅ ፡ በአለኝ ፡ ኃይል ፡ በሙሉ ፡ አቀፍኋት ። እሷ ፡ ግን ፡ ከአቅፌ ፡ ውስጥ ፡ እንደእባብ ፡ ተሽሎኩልካ ፡ አምልጣ ፡ «ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ሲተኛ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ እንገናኝ» ብላኝ ፡ እንደጦር ፡ ተወርውራ ፡ የሻይ ፡ ጀበናውን ፡ ይዛ ፡ ሻማውን ፡ ጥላ ፡ ከቤቱ ፡ እንደቀሰት ፡ ተወርውራ ፡ ወጣች ። በሳሩ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ከእኔ ፡ የተረፈውን ፡ ሻይ ፡ በመጠጣት ፡ ለመሞት ፡ ይጠብቅ ፡ የነበረው ፡ ካዛክ «ይህች ፡ ሰይጣን» ሲል ፡ ከነበርሁበት ፡ የሕልም ፡ ዓለም ፡ ባንኝ ፡ ነቃሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ልሆነ ፡ ተከትያት ፡ ገባሁ ። ቁጭ ፡ እንዳልንም ፡ ጀልባው ፡ መንቀሳቀስ ፡ ጀመረ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ተቆጥቼ ፤ «ይህ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው?» ብዬ ፡ ጠየቅኋት ። እንድቀመጥ ፡ በእጅዋ ፡ እየገ ፋችኝ ፤ «ይህ ፡ ማለት ፡ እውድሃለሁ ፡ ማለት ፡ ነው» ብላ ፡ አቀፈችኝ ። ጉንጭዋም ፡ ከጉን ጮቼ ፡ ጋር ፡ አጋጥማ ፡ ስትተነፍስ ፡ ሙቅ ፡ ትንፋሽ ፡ ተሰማኝ ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ወደውሃው ፡ ድምቡቅ ፡ አለ ። ሽጉ ጢን ፡ ብዳብስ ፡ ከማህደሩ ፡ አጣሁት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ መጠራጠር ፡ ጀመርሁ ። ደሜም ፡ ፈልቶ ፡ አካላቴን ፡ ወረረው ። ዘወር ፡ ብዬ ፡ ሳይ ፡ ጀልባችን ፡ ከወደቡ ፡ አንድ ፡ አምሳ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ እርቃ ፡ መሄዷን ፡ ተገነዘብሁ ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ዋና ፡ አልችልም ። ከእሷም ፡ ለመላቀቅ ፡ ልገፋት ፡ ብል ፡ እንደድመት ፡ ልብ ሴን ፡ ጨምድዳ ፡ ይዛ ፡ አልለቀኝ ፡ አለች ። ሳላስበውም ፡ በድንገት ፡ ብትገፈትረኝ ፡ ከጀል ባው ፡ ተፈንግሌ ፡ ከመውደቅ ፡ ለትንሽ ፡ አመ ለጥሁ ። በዚህ ፡ ወቅት ፡ ጀልባዋ ፡ ልትገለ በጥ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ትወዝወዝ ፡ ጀመር ። እኔም ፡ በስንት ፡ ችግር ፡ ሚዛኔን ፡ ጠብቁ ፡ ለመቆም ፡ ቻልሁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በእሷና ፡ በእኔ ፡ መካከል ፡ የሞትና ፡ የሽረት ፡ ትግል ፡ ተጀመረ ። ንደት ፡ ጉልበት ፡ ቢጨምርልኝ ም ፡ ጠላቴ ፡ ከእኔ ፡ የበለጠች ፡ ኃይለኛ ፡ ሆና ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

አገኘኋት ። እነዚያን ፡ ትናንሽ ፡ እጆቿን ፡ ጥርትም ፡ አድርጌ ፡ ይገር ፤ «ምንድነው ፡ የም ትፈልጊው?» ብዬ ፡ ጮህኩባት ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ጣቶቿ ፡ የመንቃቃት ፡ ጩኸት ፡ ቢያሰሙም ፡ ጩኸት ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አላሰ ማችም ። ያ ፡ እባብ ፡ ተፈጥሮዋ ፡ ሕመሙን ፡ ሁሉ ፡ በውስጧ ፡ እንድትችለው ፡ አደረጋት ። «ምስጢራችንን ፡ ስለአወቅህ ፡ ሄደህ ፡ ልትነ ግርብን ፡ ትችላለህ» ብላ ፡ በኃይል ፡ ከጀልባዋ ፡ ጠረዝ ፡ ላይ ፡ አጋደመችኝ ። በዚህን ፡ ወቅት ፡ የሁለታችንም ፡ አንገቶች ፡ ወደባሕሩ ፡ ሲዘቀዘ ቁ ፡ የእሷ ፡ ፀጉር ፡ ወርዶ ፡ ውሃው ፡ ተነከረ ። ያች ፡ ደቂቃ ፡ የሞትና ፡ የሽረት ፡ ደቂቃ ፡ ነበረች ። እንዳልወድቅ ፡ በጉልበቴ ፡ የጀልባውን ፡ ጠረዝ ፡ ተረግጬ ፤ በአንድ ፡ እጄ ፡ ፀጉሯን ፡ በሌለኛ ው ፡ ጉሮሮዋን ፡ ስይዛት ፡ ልብሴን ፡ ለቀቀችው ። ወዲያው ፡ አሽቀንጥራ ፡ ወደውሃው ፡ ወረወር ኋት ።

ጊዜው ፡ ጨልሟል ። አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በጭጋጉ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ስትል ፡ ካየኋት ፡ በኋላ ፡ ዱካዋ ፡ ጠፋ ።

በጀልባዋ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቆራጣ ፡ አሮጌ ፡ መቅዘፊያ ፡ አገኘሁ ። ከብዙ ፡ ችግር ፡ በኋላ ፡ እንደምንም ፡ እየቀዘፍሁ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ደረ ስሁ ። የባሕሩንም ፡ ዳርቻ ፡ ይገር ፡ ወደቤቴ ፡ ሳ መራ ፡ ትናንትና ፡ ማታ ፡ ያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡

ጀልባ ፡ ይጠብቅበት ፡ የነበረውን ፡ ቦታ ፡ ዘ
ወር ፡ ብዬ ፡ ተመለከትሁ ። ጨረቃዋ ፡ ብቅ ፡
ማለት ፡ ጀምራ ፡ ስለነበር ፡ በብርሃኗ ፡ አንድ ፡
ነጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡
ተጒልቶ ፡ ያየሁ ፡ መሰለኝ ። ማን ፡ እንደሆነም ፡
ለማወቅ ፡ ጉጉት ፡ ስላደረብኝ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡
ተጠግቼ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ ካለው ፡ ቋጥኝ ፡ ጀርባ ፡
ባለው ፡ ሣር ፡ ላይ ፡ አድፍጬ ፡ መመልከቴን ፡ ቀ
ጠልሁ ። ከነበርሁበት ፡ ቦታ ፡ እንኅቴን ፡ ትንሽ ፡
ቀና ፡ ሳደርግ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በጉልህ ፡ ይታየ
ኛል ። ያችን ፡ የዛር ፡ ልጅ ፡ እዚያ ፡ በማየቴ ፡
አልተደነቅሁም ። አላዘንሁምም ። ፀጕሯን ፡
እየጠመዘዘች ፡ የባሕሩን ፡ ውሃ ፡ ታራግፋለች ።
ከአካላቷ ፡ የተላጠቀው ፡ እርጥብ ፡ ልብሷ ፡
ቅርጿን ፡ በደንብ ፡ ያሳያል ። ወዲያውም ፡ ከሩ
ቁ ፡ የመጣ ፡ አንድ ፡ ጀልባ ፡ ወደባሕሩ ፡ ጥቅ ፡
በፍጥነት ፡ ሲገሰግስ ፡ አየሁ ። እንደትናንትናው ፡
ማታ ፡ አንድ ፡ የታታር ፡ የበግ ፡ ቆዳ ፡ ባርኔጣ ፡
የደፋ ፡ ሰው ፡ ከጀልባው ፡ ወረደ ። የወገሩ ፡
ጉንጉን ፡ የካዛኮችን ፡ ይመስላል ። ትልቅ ፡
ጩቤ ፡ ታጥቋል ። «ያንኑ!.. ሁሉ ፡ ነገር ፡
ከሸፈ ፡» አለችው ። ንግግራቸው ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡
ድምፅ ፡ ስለነበረ ፡ የቀረውን ፡ አልሰማሁትም ።
በመጨረሻም ፡ ያንኮ ፡ ድምፁን ፡ ጕርነን ፡
አድርጉ ፡ ፈያ ፡ እውርስ ፡ የት ፡ አለ» ሲል ፡
ጠየቃት ። እሷም ፡ «መልሺ ፡ ልኬዋለሁ ፡»

t.me/OLDBOOKSPDF

አለችው ። ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ እውሩ ፡
ቀረጢት ፡ ቢጤ ፡ በጀርባው ፡ ተሸክሞ ፡ መጣ ።
«ስማ ፡ እውሩ! ያንን ፡ ቦታ ፡ ተጠንቅቀ
ሀ ፡ ጠብት ። ምን ፡ ማለቴ ፡ እንደሆነ ፡ ይገባኻል?
እዚያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡
ነው ። ለ ... (ስሙን ፡ ልሰማ ፡ አልቻልሁም)
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ አሽከርህ ፡ አይደለሁም ፡
ብለህ ፡ ንገረው ። ሁኔታው ፡ እደግኖ ፡ ነው ።
ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሥራ ፡ እፈልጋለሁ ። እንደኔ ፡ ያለ ፡
ደፋር ፡ መቼም ፡ መች ፡ አያገኝም ። ለእገልግሎቴ ፡
«የተሻለ ፡ ዋጋ ፡ ብትከፍል ፡ ኑሮ ፡ ያንኮ ፡
አይከዳህም ፡ ነበር» ብለህ ፡ ንገረው ። ነፋሱ ፡
በነፈሰበት ፡ የባሕር ፡ ሞገድ ፡ ባፏጨበት ፡
ብሄድ ፡ ሥራ ፡ አላጣም ።» ያንኮ ፡ ጥቂት ፡
ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ንግግሩን ፡ ይቀጥላል ።
«እሷን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይዣት ፡ እሄዳለሁ ።
ካሁን ፡ በኋላ ፡ እዚህ ፡ ለመቅረት ፡ አትችልም ።
አሮጊቷንም ፡ «የመሞትሽ ፡ ጊዜ ፡ ተቃርቧል»
በላት ። ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ኑራለች ። በቃት ።
እኛን ፡ ከእንግዲህ ፡ ደግሞ ፡ አታየንም ።»
እውሩ ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምፅ ፤ «እኔስ?»
ሲል ፡ ጠየቀው ።
«እንተ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ታደርግልኛለህ?» ሲ
ል ፡ መለሰለት ።
በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ የዛር ፡ ልጅ ፡ በጀልባው ፡
ቁሞ ፡ ብላ ፡ እጅጉን ፡ እያሙለበለበች ፡ ኀደኛ

ዋን ፡ ትሰናበተው ፡ ገባች ። ያንኩም ፡ በእውሩ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ሳንቲም ፡ ቢጤ ፡ ጣል ፡ አድርጉ ፡ ሲያበቃ ፡ «እንካ ፤ በዚህች ፡ ብስኩት ፡ ግዛባት» አለው ።

«ይህችን ፡ ብቻ?» ሲል ፡ እውሩ ፡ ጠየቀው ።

«ደግ ፡ ይሁን ፤ ይህንንም ፡ ጨምረህ ፡ ውሰድ ፡» ብሎ ፡ የወረወረለት ፡ ሳንቲም ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ስትወድቅ ፡ ቅጭል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ አሰማች ። እውሩ ፡ ልጅ ፡ ሳንቲሟን ፡ ከመሬት ፡ አላነሳትም ። ያንኩም ፡ በጀልባው ፡ ገብቶ ፡ የጀልባ ፡ ሸራውን ፡ ሲበቅለው ፡ በነበረው ፡ የነፋስ ፡ ኃይል ፡ እየተገፋ ፡ በፍጥነት ፡ ከአጠገቤ ፡ ርቀው ፡ ሄዱ ። በዚያ ፡ በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ያ ፡ ነጭ ፡ የነፋስ ፡ ሸራ ፡ ከዓይን ፡ እስኪርቅ ፡ ድረስ ፡ በጥቁር ፡ ማዕበል ፡ ባሻገር ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እውሩ ፡ ልጅ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ጉልት ፡ እንዳለ ፡ ቀረ ። ወዲያው ፡ አንድ ፡ የስቅስቅታ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማኝ ። የሚያለቅሰው ፡ ይኸው ፡ እውሩ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሲያለቅስ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ቆየ ። ሁኔታው ፡ በጣም ፡ አሳዘነኝ ። እስቲ ፡ የእነዚህን ፡ ንጹህ ፡ ኮንትሮባንድ ፡ ሰላማዊ ፡ ሕይወት ፡ ለመረበሽ ፡ ምን ፡ እጣ ፡ አጋጠመኝ? በረጋ ፡ የውሃ ፡ ጉድጓድ ፡ ከረሩ ፡ ላይ ፡ እንደተወረወረች ፡ ድንጋይ ፡ የእነሱን ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ በጠበጥሁ ፡ እንደ ድንጋዩም ፡ እኔም ፡ ሰጥሜ ፡ ነበር ።

ወደማረፊያ ፡ ቤቴ ፡ ተመለስሁ ። በመግቢያው ፡ በር ፡ ላይ ፡ በእንድ ፡ በእንጨት ፡ ገበቴ ፡ ላይ ፡ ሻማ ፡ ይበራል ። ያ ፡ የእኔ ፡ ካዛክ ፡ ትዕዛዜን ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ ጠብመንጃውን ፡ እንደ ጨበጠ ፡ እንቅልፍ ፡ ይዞት ፡ አገኘሁት ። አልቀሰቀስሁትም ። ሻማዬን ፡ እንስቼ ፡ ወደክፍሌ ፡ ዘው ፡ አልሁ ። ግን ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ጉድ ፡ ፈልቶ ፡ ቆየኝ ። ሻንጣዬ ፤ የብር ፡ ቅብ ፡ ጉራዴዬ ፤ ወዳጆቼ ፡ ለማስታወሻ ፡ የሰጡኝ ፡ የዳግስ ታን ፡ ጩቤ ፡ ጠፍቶኝ ፡ ቆየኝ ። ያ ፡ የተረገመ ፡ እውር ፡ ቅድም ፡ ተሸክሞ ፡ ያመጣው ፡ እቃ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አውን ፡ ገባኝ ። ያንን ፡ ካዛክ ፡ ከተኛበት ፡ በንዴት ፡ ቀስቅሼ ፡ ሙልጭ ፡ አድርጌ ፡ ሰደብኩት ፡ ግን ፡ ያለፈ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ። ለአለቃዬ ፡ «እውሩ ፡ እቃዬን ፡ ሠረቀኝ! የአሥራ ፡ ስምንት ፡ እመት ፡ ልጅ ፡ ልታሰምጠኝ ፡ ነበር ፡» ብሎ ፡ መክሰሱ ፡ አስቂኝ ፡ አይሆንም?

የፈጣሪ ፡ ነብሩ ፡ ይስፋና ፡ በማግሥቱ ፡ ጥዋት ፡ የመንገዣ ፡ መርከብ ፡ ስለመጣ ፡ ታማኝን ፡ ለቅቴ ፡ ሔድሁ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያች ፡ እሮጊት ፡ ሲትና ፡ ያ ፡ እውር ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ አላውቅም ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ለሥራ ፡ ታዝዤ ፡ ለምሔደው ፡ ለእኔ ፡ ለከፍተኛው ፡ መኰንን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሐዘንም ፡ ሆነ ፡ ደስታ ፡ ምኔ ፡ ነው?

እንደኛው ፡ ክፍል ፡ ተፈፀመ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለተኛው ክፍል።

የፔጆሪን ማስታወሻዎች መዝጊያ።

t.me/OLDBOOKSPDF

፪

ልዕልተ ሜሪ።

ግንቦት ፡ ፲፭ ቀን ፡ ትናንት ፡ ፒቲኮርስክ ፡ ደርሼ ፡ ከከተማው ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ በማ ሹክ ፡ አጠገብ ፡ ቤት ፡ ተከራይቼ ፡ ገባሁ ። ቦታው ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከጠሮ ፡ ጋር ፡ የመጣ ፡ ደመና ፡ የቤ ቱን ፡ ጣራ ፡ ይሸፍነዋል ። ዛሬ ፡ ጥዋት ፡ በአ ሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መስኩቴን ፡ ስከፍት ፡ ከፊት ፡ ለፊቴ ፡ ያለው ፡ የአበባ ፡ ተክል ፡ ሽታ ፡ አወደኝ ። በአበባ ፡ ያሸበረቁት ፡ የቀጋ ፡ ዛፎች ፡ ቅርንጫፎች ፡ ወደመስኩቴ ፡ ብቅ ፡ እያሉ ፡ ይጐበ ኙኛል ። ነፋሱ ፡ ከአታክልቲ ፡ ዛፍ ፡ ቅጠላትን ፡ እያመጣ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ይበትነዋል ። በሦስ ቱም ፡ ማዕዘናት ፡ ግራም ፡ ትዕይንት ፡ ይታየ ኛል ። በስተምዕራብ ፡ ጕሽኪን «ከጠሮው ፡ የተረፉ ፡ የተበታተኑ ፡ ደመናዎች» ያላቸውን ፡ የሚመስሉ ፡ የቢሽቲ ፡ አምስት ፡ ኮረብታዎች ፡ በሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ አሸብርቀው ፡ ደብዘዝ ፡ ብለው ፡ ይታያሉ ። በስተሰሜን ፡ የማሹክ ፡ ተራራ ፡ የተጨማደደ ፡ የፔርሺያን ፡ ባርኔጣ ፡ የደፋ ፡ መስሎ ፡ አካባቢውን ፡ አሚልቶ ፡ ገብ ፡ ብሏል ። በስተምሥራቅ ፡ ያለው ፡ ትዕይንት ፡ ከሁሉም ፡ ደመቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። አቆልቁሎ ፡ ሲመለከቲ ፡ እንዲት ፡ ንጹሕ ፡ ከተማ ፡ ፍንትው ፡ ብላ ፡ ውብ ፡ ሁና ፡ ትታያለች ። በበልነት ፡ ያለው ፡ ምንጭና ፡ በተለያየ ፡ ቋንቋ ፡ የሚነጋገሩ ፡ ሕዝ ቦች ፡ ድምፅ ፡ ጫጫታ ፡ ይሰማል ። በአሻገር ፡ ያሉት ፡ ተራራዎች ፡ በሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ተውበው ፡ ደብዘዝ ፡ ብለው ፡ ይታያሉ ። በአድ ማሱ ፡ ላይ ፡ ከካዝቤክ ፡ ጀምሮ ፡ እስከመንትያ ው ፡ ኤልብሩስ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ተራራዎች ፡ በብር ፡ ሰንሰለት ፡ የተጠለፉ ፡ ሲመስሉ ፡ አናታቸው ፡ በበረዶ ፡ አሸብርቋል ። በእንዲህ ፡ ያለ ፡ አካባቢ ፡ መኖር ፡ ታላቅ ፡ ፀጋ ፡ ነው ። አካላቴ ፡ በደስታ ፡ ተወረረ ። እየሩ ፡ እንደሕ ፃን ፡ ልጅ ፡ አሳሳም ፡ ንጹሕና ፡ ትኩስ ፡ ነው ። ፀሐዩ ፡ ቦግ ፡ ብሏል ። ስማዩም ፡ ጠርቷል ። ለሰ ው ፡ ልጅ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ያስፈልገ ዋል? እዚህ ፡ ለሐዘን ፡ ለምኞት ፡ ለቁጭት ፡ ቦታ ፡ የላቸውም ። ሆኖም ፡ መሐድ ፡ እለብኝ ። የመሐኟዬን ፡ ጊዜ ፡ ተደርሷል ። ኤልሳቤጥ ፡ ፀበል ፡ በሽተኞች ፡ ጥዋት ፡ ጥዋት ፡ ይሰበሰባሉ ፡ ማለትን ፡ ስለሰማሁ ፡ ለመሐድ ፡ መሰንሁ ።

---

* «ጠሮ» ከተባለው ፡ ከአሌክሳንድር ፡ ጕሽኪን ፡ ግጥም ፡ የመጀመሪያ ፡ መሥመሮች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መሐል ፡ ከተማ ፡ ገብቼ ፡ ወደእደባባይ ፡ ዘወር ፡ ስል ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በረድፍ ፡ በረድፍ ፡ ዳገቱን ፡ ሲወጡ ፡ ተመለከትሁ ። ወንዶቹ ፡ የደረቡትን ፡ ጥንታዊ ፡ ኮት ፤ ሚስቶቻቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ የለበሱትን ፡ ቁንጠኛ ፡ ልብስ ፡ ስመለከት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የመጡት ፡ ከወደደጋው ፡ መሆኑን ፡ ለመገመት ፡ አስቸጋሪ ፡ አይሆንም ። አሉ ፡ የተባሉት ፡ የከተማው ፡ ወንዶች ፡ በሙሉ ፡ ወደፀበሉ ፡ ሔደዋል ፡ መሰል ፤ ሳልፍ ፡ ሰዎች ፡ በመገረም ፡ ይመለከቱኝ ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፡ የለበስሁት ፡ የፔቴርቡርግ ፡ የኮት ፡ ቅድ ፡ አይተው ፡ ተገረሙ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የወታደር ፡ ምልክት ፡ ሲያዩ ፡ በጥላቻ ፡ ይመለከቱኝ ፡ ጀመር ።

በእጅ ፡ የምትያዝ ፡ መነፅር ፡ የጨለጡት ፡ የከተማ ፡ መኳንንት ፡ እመቤቶች ፡ ይበልጥ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባዮች ፡ ነበሩ ። ወደካውካሱስ ፡ ተግዘው ፡ በሚመጡ ፡ ነጭ ፡ ባርኔጣ ፡ በደፉ ፡ መኮንኖች ፡ ሜንቅላት ፡ ውስጥ ፡ የበሰለ ፡ አስተሳሰብ ፡ ስላጤኑ ፤ የኮት ፡ ቁልፉም ፡ ባረፈበት ፡ ልብ ፡ ደግነት ፡ ስላዩ ፡ በወታደር ፡ አለባበስ ፡ አይሸበሩም ። እነዚህ ፡ ወይዛዝርት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ። በየዓመቱ ፡ አደናቂዎቻቸው ፡ ያፈራረቃሉ ። ምናልባትም ፡ የእነዚህ ፡ ወይዛዝርት ፡ ለሳ ፡ ያለመሰልቸት ፡ በፈገግታ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባዮች ፡ ስለሆኑ ፡ ይሆናል ።

ወደኤልሳበጥ ፡ ፀበል ፡ የሚያመራውን ፡ መንገድ ፡ ተከትዬ ፡ ስሔድ ፤ ሲቪሎች ፡ ወንዶችና ፡ ወታደሮች ፡ ተሰብስበው ፡ የቆሙበትን ፡ ቦታ ፡ አለፈ ። ሔድሁ ። በኋላ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ከሌላው ፡ ከፀበል ፡ ፈውስ ፡ ፈላጊ ፡ ወገን ፡ ተለይተው ፡ የቆሙ ፡ ልዩ ፡ መደቦች ፡ እንደሆኑ ፡ ተረዳሁ ። ይጠጣሉ ። ውሃ ፡ ግን ፡ አይደለም ። የሚንሸራሸሩትም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። የፍቅር ፡ ስሜታቸው ፡ በጊዜውና ፡ በአጋጣሚ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። ቁማርተኞችም ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ እጅ ፡ እጅ ፡ አለን ፡ ይላሉ ። ለልብሳቸውና ፡ ለወጋቸው ፡ ልዩ ፡ ቦታ ፡ ይሰጡታል ። በዚያ ፡ ብርጭቋቸው ፡ ያን ፡ ሳልፈር ፡ የሞላበት ፡ ፀበል ፡ ሲቀዱ ፡ እንኳ ፡ ጅንን ፡ ይላሉ ። ሲቪሎቹ ፡ ደማቃ ፡ ያልሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ከራቫት ፡ ሲያስሩ ፤ ወታደሮቹ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ክብና ፡ ሰፊ ፡ ከፈፍ ፡ ኮሌታ ፡ ያለው ፡ ሸሚዝ ፡ ለብሰዋል ። የክፍለ ፡ ሀገሩን ፡ ወይዛዝርት ፡ ይንቃሉ ። በዋና ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ለእነሱ ፡ ዝግ ፡ የሆነውን ፡ የመሳፍንት ፡ መስብሰቢያ ፡ ያልማሉ ።

በመጨረሻም ፡ ፀበሉ ፡ ጋ ፡ ደረስሁ ። ከፀበሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቀይ ፡ ጣራ ፡ ያላት ፡ ትንሽ ፡ ቤት ፡ ትታያለች ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ የተንጣለለ ፡ የዝናብ ፡ መከለያ ፡ የሚሆን ፡ ዛኒጋባ ፡ ተጥሏል ። ብዙም ፡ የቆሰሉ ፤ የገረጡ ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

አሳዛኝ ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በአግዳሚ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ምርኩዛቸውን ፡ ይዘው ፡ ቁጭ ፡ ብለዋል ። አብዛኛዎቹ ፡ ወይዛዝርት ፡ ፀበሉ ፡ ፈንድቶ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ በጉጉት ፡ ከወ ዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይመላለሳሉ ። ከነዚህ ፡ ወይዛዝ ርት ፡ መካከል ፡ ቆንጆ ፡ ሆነው ፡ የታዩኝ ፡ ገጾች ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ናቸው ። የማሹክን ፡ ተራራ ፡ በሚከልለው ፡ የወይን ፡ አትክልት ፡ ቁጭን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ኑሜጭ ፡ ባርኔጣ ፡ የደፉ ፡ ሴቶች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይታ ያሉ ። በነዚህም ፡ ሴቶች ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ የተጨ ማደደ ፡ ባርኔጣ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ መለዮ ፡ የደፉ ፡ ሰዎች ፡ ሲከተሏቸው ፡ ስላየሁ ፡ የብቸ ኝነት ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ ገመትሁ ። አየኦ ሊያን ፡ በሚል ፡ ስም ፡ በሚጠራው ፡ ኮረብታው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ዛኒጋባ ፡ ጥግ ፡ ቆመው ፡ ጐብኝዎቹ ፡ የኤልብሩስን ፡ ተራራ ፡ አቅርቦ ፡ በሚያሳየው ፡ መነጽራቸው ፡ ይመለከታሉ ። ከነዚህም ፡ መካከል ፡ ከቆዳ ፡ በሽታቸው ፡ ለመንፃት ፡ አስተማሪዎቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ የመጡ ፡ ልጆች ፡ ይገኛሉ ።

እያለከለኩ ፡ ዳገቱን ፡ ወጥቼ ፡ የቤቱን ፡ ጥግ ፡ ተያግፈ ፡ አካባቢውን ፡ ሳያንት ፡ በያንገት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የማውቀው ፡ ድምፅ ፡ ተሰማኝ ።

«ፒቾሪን! ከመጣህ ፡ ቆይተሃል?»

ዘወር ፡ ስል ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ አየሁት ።

ተሳሳምን ። የተዋወቅነው ፡ በአንድ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ አብረን ፡ ስናገለግል ፡ ነው ። የመጣው ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ተኩም ፡ ብሎ ፡ ሲሆን ፡ አመጣጡም ፡ በጥይት ፡ እግሩ ፡ ስለተመታ ፡ ነው ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ ነው ። ያገልግሎት ፡ ዘመኑ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ የለበሰው ፡ ወፍራም ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ ብርቱ ፡ ሁኗል ። የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የወታደር ፡ መስቀልም ፡ አድርጓል ። ሰውነቱ ፡ ደንዳና ፡ ሲሆን ፡ ፊቱ ፡ ጠይም ፡ ፀጉሩ ፡ ጥቁር ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እድሜው ፡ ሃያ ፡ አንድ ፡ ቢሆንም ፡ የሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ይመስላል ። ከሰው ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ራሱን ፡ እንጋሎ ፡ የማውራትና ፡ ወይም ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ጉንጮቹን ፡ አስደግፎ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ሪዙን ፡ የማፍተልተል ፡ ልምድ ፡ አለው ። እነጋገሩ ፡ ችኩል ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለዛ ፡ አለው ። ግሩሽኒ ትስኪይ ፡ በተፈለገው ፡ ሁኔታ ፡ የሚደረድሯ ቸውን ፡ ሐረጐች ፡ ከሸመደዱ ፡ ውበት ፡ ስሜታ ቸውን ፡ ከማይቀሰቅሳቸው ፡ ሆኖም ፡ የውበት ፡ አድናቂ ፡ ሆነው ፡ ከሚታዩ ፡ ፍቅርና ፡ ሐዘን ፡ ልባቸውን ፡ የሰበረው ፡ ከሚመስሉ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ እንዱ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ እንድ ፡ ስሜት ፡ ለማሳደር ፡ ይጥራሉ ። በነፍስ ፡ ሐኖሩ ፡ የሚኖሩም ፡ ሴቶች ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማሳመን ፣ ይሞክራል ። በዚያ ፣ ከባድ ፣ የወታደር ፣ ኑሮ ፣ የሚኮራውም ፣ ለዚህ ፣ ነው ። ሰርስሬ ፣ ውስጣዊ ፣ ስሜቱን ፣ እንደግውቅ ፣ ስለሚያምን ፣ ቢጠላኝም ፤ ላይ ፣ ላዩን ፣ ትልቅ ፣ ወዳጆች ፣ እንመስላለን ። ግሩሽኒትስኪይ ፣ በደ ፋርነቱ ፣ የተመሰከረለት ፣ ነው ። በጦር ፣ ሜዳም ፣ ላይ ፣ እራሴ ፣ አይቼዋለሁ ። ሁለት ፣ ዓይኖቹን ፣ ጨፍኖ ፣ እየፎከረ ፣ ጉራዬውን ፣ መዞ ፣ ወደፊት ፣ ይገሰግሳል ። የዚህ ፣ ዓይነቱ ፣ ጀግንነት ፣ ለሩሲ ያውያን ፣ የተለመደ ፣ አይደለም!

እኔም ፣ አልወደውም ። እንድ ፣ ቀን ፣ በ መጥፎ ፣ አጋጣሚ ፣ ተጋጭተን ፣ እንዳችን ፣ ከመጥፎ ፣ ነገር ፣ ላይ ፣ እንደርሳለን ፣ ብዬ ፣ እፈራለሁ ።

ወደካውካሱስ ፣ የመጣው ፣ ባለው ፣ ሕልማዊ ፣ ምኞት ፣ እምነቱ ፣ ተገፋፍቶ ፣ ሳይሆን ፣ አይቀ ርም ። ወደካውካሱስ ፣ ለመምጣት ፣ ከአባቱ ፣ አገር ፣ እንደነገ ፣ ሊነሣ ፣ ማታውኑ ፣ ለደጊቷ ፣ ጐረቤቱ ፣ «የምሔደው ፣ ለወታደርነት ፣ አይደ ለም ፣ ሞትን ፣ ፍለጋ ፣ እንጂ! ምክንያቱም ...» እንዳለ ፣ እርግጠኛ ፣ ነኝ ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ዓይኖ ቹን ፣ በመዳፎቹ ፣ ከድኖ ፣ «የለም ፣ እርስዎ ፣ (እንጂ) ምክንያቱን ፣ ማወቅ ፣ የለብዎትም ። ያ ፣ እሩሀሩህ ፣ ልብዎ ፣ ይጨነቃልና! ደግሞስ ፣ ለምንነ እኔ ፣ ለእርስዎ ፣ ምንድነኝ፣ ሁኔታዬ ፣ ይገባዎታልን፣ መዘተ ...» ሲል ፣ ይታየኛል ።

ይከንፋላቸዋል ። እነዚህ ፣ ሰዎች ፣ ሲያረጁ ፣ ወይም ፣ ለላማዊ ፣ ባላባት ፣ ይሆናሉ ፣ ካለዚ ያም ፣ ጠጪዎች ፣ ሆነው ፣ ያርፋሉ ። እንዳ ንዴም ፣ ሁለቱንም ፣ አጣምረው ፣ ይይዛሉ ። እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ ሰዎች ፣ ከፉ ፣ አይደሉም ። ሆኖም ፣ ውስጣቸው ፣ ባዶ ፣ ቀፎ ፣ ነው ። ግሩ ሽኒትስኪይ ፣ ጮሀ ፣ ብሎ ፣ መናገር ፣ ይወዳል ። በተለይ ፣ ውይይቱ ፣ ከዕለቱ ፣ ሁኔታ ፣ ውጭ ፣ ከሆነ ፣ የቃላት ፣ መዓት ፣ ይደረድራል ። እኔ ፣ መቼም ፣ ከእርሱ ፣ መከራከሩን ፣ አልወድም ። የሚቀርብለትን ፣ ተቃውሞ ፣ ካለመቀበሉም ፣ ሌላ ፣ መልስ ፣ አይሰጥም ። አይሰማማምም ። ንግግሩም ፣ ቆሞ ፣ ሲቀጥል ፣ በአጀማመሩ ፣ መልስ ፣ የሚሰጥ ፣ ይመስላል ። ሆኖም ፣ ላዳ መጠው ፣ ካለፈው ፣ የቀጠለ ፣ ነው ።

ብልጥ ፣ ነው ። ንግግሮቹ ፣ አስቂኝ ፣ ቢሆኑም ፤ ሰው ፣ የሚነኩ ፣ መጥፎ ፣ አይደሉም ። አንድን ፣ ሰው ፣ በአንድ ፣ ቃል ፣ የመግደል ፣ ልምድ ፣ የለውም ። በመላው ፣ ሕይወት ፣ ራሱን ፣ ብቻ ፣ ይወድ ፣ ስለነበር ፣ የሰዎችን ፣ ደካማ ፣ ቦታቸ ውን ፣ ጠንቅቆ ፣ አያውቅም ። የሕይወቱ ፣ የኑሮ ፣ ፍች ፣ የአንድ ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ታሪክ ፣ ዋና ፣ ባሕርይ ፣ ሆኖ ፣ ለመቅረብ ፣ ነው ። ለዚህ ፣ ዓለምም ፣ የተፈጠረ ፣ ሰው ፣ አለመሆኑን ፣ ይህ ፣ ሁሉም ፣ በደል ፣ የሚያርስበት ፣ ለዚህ ፣ መሆኑን ፣ አምኖበት ፣ ብዙዎችን ፣ ሰዎች ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

በ«ከ» ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የ፡መዘገ
በበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በእርሱና ፡ በፈጣሪው ፡
ብቻ ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ እንደሚቀር ፡ እራሱ ፡
ነግሮኛል ።

ይሁንና ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ይህን ፡ አሳዛኝ ፡
ጠባዩን ፡ ወደጐን ፡ ትቶ ፡ ሲያወራ ፡ አስቂኝና ፡
አስደላች ፡ ሰው ፡ ነው ። ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡
ግን ፡ ማየት ፡ እፈልጋለሁ ። ምክንያቱም ፡ ያለ ፡
የሌለ ፡ ጠባዩን ፡ የሚያሳየው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ነውና!

እንደጥንት ፡ ወዳጆች ፡ ሰላምታ ፡ ተለዋወ
ጥን ። በአካባቢው ፡ ስላለው ፡ ሕይወትና ፡ ሰ
ዎች ፡ ጠየቅሁት ።

በረጅሙ ፡ ተንፍሶ ፡ «ኑሮአችን ፡ የሰለቸ ፡
ነው ። የጥዋት ፡ ፀበል ፡ ጠዪዎች ፡ እንደበ
ዝተኞች ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ። የማታ ፡ ማታ ፡
ቪኖ ፡ ጠዪዎች ፡ ደግሞ ፡ እንደማንም ፡ ጤነኛ ፡
ጠባያቸው ፡ አይቻልም ። በአካባቢው ፡ ሴቶች ፡
አሉ ። ግን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አያጽናኑም ።
ካርታ ፡ ጨዋታ ፡ ያዘወትራሉ ። አለባበሳቸ
ውም ፡ ቆንጆ ፡ አይደለም ። የፈረንሳይ ፡ ድንቋ ፡
ችሎታቸው ፡ በጣም ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው ። በዚህ ፡
ዓመት ፡ ከምስኩ ፡ የመጡት ፡ ጉብኝ ፡ ልዕልት ፡
ሊጐቭስካያና ፡ ሴት ፡ ልጆቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።
እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አላገኘኋቸውም ። የለበሰሁት ፡
ከባድ ፡ የወታደር ፡ ኮት ፡ ከሕብረተሰቡ ፡

መባረሪያ ፡ ምልክቱ ፡ ሆኗል ። እሱን ፡ ለብሼ ፡
በተረብሁ ፡ ጊዜ ፡ ተፈላጊነቱ ፡ የለማኝ ፡ ያህል ፡
ነው ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ወይዛዝርት ፡ በአጠገ
ባችን ፡ አልፈው ፡ ወደፀበሉ ፡ አመሩ ። አንደ
ኛዋ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛዋ ፡ ወጣት ፤
አቋቋሙ ፡ መልካም ፡ ናት ። መልካቸው ፡ በባ
ርኔጣቸው ፡ ተከልሎ ፡ በደምብ ፡ ባይታይም ፡
አለባበሳቸው ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለበት ፡ ነው ።
ምንም ፡ ውሃ ፡ አይወጣላትም ። ወጣቷ ፡ ኮሌታ ፡
ረጅም ፡ ቀላል ፡ ግራጫ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሳለች ።
በዚያ ፡ ረዘም ፡ ባለ ፡ አንገቷ ፡ ላይ ፡ የሐር ፡
ሻሽ ፡ አስራበታለች ። እነዚያ ፡ ውብ ፡ እግሮቿ ፡
በቡናማ ፡ ጥቋቁር ፡ ጫማዎች ፡ እስከቁርጭም
ጭሚቶቻቸው ፡ ተደፍነዋል ። በእውነትም ፡
ቁንጅናቸው ፡ ውበት ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡
ቢያያቸው ፡ በአድናቆት ፡ ትንፋሹ ፡ ያጥራል ።
ረጋ ፡ ያለው ፡ ደርባባ ፡ አረማመዷ ፡ ገና ፡ ያልፈ
ነዳ ፡ እምቡጥ ፡ አበባ ፡ ቢያስመስላትም ፡
ሁለንተናዋን ፡ የሚገልጽ ፡ ተስማሚ ፡ ቃላት ፡
ለማግኘት ፡ ያስቸግራል ። ሆኖም ፡ ዓይንን ፡
ለመማረክ ፡ ችሎታ ፡ አላት ። በአጠገባችን ፡
ስታልፍ ፡ ያወደን ፡ መዓዛ ፡ እንዳንዴ ፡ ከምትወ
ደድ ፡ ሴት ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሽታ ፡
ይመስላል ።

«ልዕልት ፡ ሊጐቭስካያና ፡ በእንግሊዝኛ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሜሪ ፡ ብለው ፡ የሚጠሯት ፡ ልጃቸው ፡ እነ ዚህ ፡ ናቸው ። ከመጡ ፡ ሦስት ፡ ቀናቸው ፡ ነው ።» በማለት ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ አበሰ ረኝ ።

«ስሚንም ፡ ካሁኑ ፡ አውቀኸዋል?» ስለው ፡ ፊቱ ፡ ቀልቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰልኝ ።

«ስሚን ፡ የሰማሁት ፡ በድንገት ፡ ነው ። ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅ ፡ በእውነቱ ፡ ምንም ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ። ለእነዚህ ፡ ኩሩ ፡ ወይዛዝርት ፡ እኛ ፡ ወታደሮች ፡ አውሬዎች ፡ መስለን ፡ ነው ፡ የምንታያቸው ። ቁጥር ፡ ባለበት ፡ መለዮ ፡ ሥር ፡ አስተዋይ ፡ አእምሮና ፡ የወፍ ራም ፡ ኮት ፡ ቁልፎች ፡ ባረፉበት ፡ ደረት ፡ ሥር ፡ ሩህሩህ ፡ ልብ ፡ እንዳለም ፡ ቢያውቁ ፡ ደንታ ፡ የላቸውም ።»

«የፊረደበት ፡ የወታደር ፡ ኮት!» ብዬ ፡ ከሳቅሁ ፡ በኋላ ፡ «ትህትና ፡ በሞላበት ፡ መልክ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚያቀርብላቸው ፡ ያ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ማነው?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

«አሉማ ፡ የሞስኮው ፡ መኳንንት ፡ ራየቪች ፡ ነው ። ቁማርተኛ ፡ ነው ። በሰማያዊ ፡ ሠደርያው ፡ ላይ ፡ ያንጠለጠለው ፡ የወርቅ ፡ ሰዓቱ ፡ ቁማርተኛነቱን ፡ ያስታውቅበታል ። ያ ፡ የሮቢንሰን ፡ ክሩሶን ፡ የመሰለው ፡ ወሩራም ፡ ከዘራና ፡ ያ ፡ የባላገር ፡ ጺሙ ፡ ሁሉ ፡ የሰውየውን ፡ ማንነት ፡ ያመሰክራል ።»

«እንዲያው ፡ በመላው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ የያዝህ ፡ ትመስላለህ?»

«ለዚህ ፡ እኮ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለኝ ።»

«በእውነት?»

ይሄኔ ፡ ወይዛዝርቱ ፡ የፀበሉን ፡ ምንጭ ፡ ለቀው ፡ እኛን ፡ አልፈው ፡ ሔዱ ። ግሩሽኒት ስኪይ ፡ በምርኩዙ ፡ ተደግፎ ፡ አቋቋሙን ፡ ካሳመረ ፡ በኋላ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ጮህ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«Mon cher, je haïs les hommes pour ne pas les mépriser, car autrement la vie serait une farce trop dégoutante.»*

እነዚያም ፡ ወይዛዝርት ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ አጤኑት ። አስተያየታቸው ፡ ግራም ፡ ቢያጋባ ፡ ለማሾፍ ፡ እንዳልሆነ ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ድርጊቱ ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ አደነቅሁት ።

«ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ በጣም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ናት ። ዓይኗ ፡ እንደኩል ፡ የጠራ ፡ ነው ። አምን ፡ ልክ ፡ እንደኩል ፡ ነው ። ስለእሷ ፡ ስትናገር ፡ ይህን ፡ አገላለጽ ፡ ብትጠቀምበት ፡ መል

---

* ወዳጄ ፡ የዘመናችንን ፡ ሰዎች ፡ ላለመናቅ ፡ ስል ፡ በጥላቻ ፡ ዓይን ፡ አያቸዋለሁ ። ምክንያቱም ፡ ሕይወት ፡ ያለዚያ ፡ ቀልድ ፡ የተሞላበት ፡ አስቂያሚ ፡ ትያትር ፡ ይሆናል ። (በፈረንሳይኛ)

t.me/OLDBOOKSPDF

እግረ ፡ መንገዴን ፡ ወደትልቁ ፡ ዛኒጋባ ፡ ለማረ
ፍ ፡ ዘው ፡ ስል ፡ እንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ትርኢት ፡
እየሁ ። የተዋናዮች ፡ አቀማመጥ ፡ እንደዚህ ፡
ነበር ። እናታቷ ፡ ልዕልት ፡ ከዚያ ፡ ከሞስኮ ፡
ጨዋ ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ በዛኒጋባው ፡ እግዳሚ ፡
ወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡
ያለው ፡ ውይይት ፡ የያዙ ፡ ይመስላሉ ። ልዕ
ልት ፡ ሚሪ ፡ ግን ፡ የመጨረሻ ፡ ፀበሏን ፡ ጠጥታ ፡
በምንጩ ፡ እካባቢ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ በሐሳብ ፡
ተውጣ ፡ ትንሽራሽር ፡ ነበር ። ግሩሽኒትስኪይ ፡
ከፀበሉ ፡ አጠገብ ፡ ቆም ፡ ብሏል ። በአጠገቡ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

ከዛኒጋባው ፡ ተጠልዬ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ለማ
የት ፡ ቻልሁ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡
የፀበል ፡ መጠጫው ፡ ብርጭቆ ፡ ከእጁ ፡ እም
ልጦ ፡ በእሽዋው ፡ ላይ ፡ ወደቀበት ። የወደቀበ
ትን ፡ እቃ ፡ ለማንሳት ፡ ቢሞክር ፡ የቆሰለው ፡
እግሩ ፡ አስቸገረው ። በዚያ ፡ በምርኩዙ ፡ ላይ ፡
ተደግፎ ፡ ብርጭቆውን ፡ ለማንሳት ፡ ያለ ፡ የሌለ
ውን ፡ ኃይሉን ፡ ቢጠቀምም ፡ ሳይሳካለት ፡
ቀረ ። በዚያ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ ሥቃይ ፡ ተሥሎ ፡
ይታይበት ፡ ነበር ።

ከእኔ ፡ የተሻለ ፡ ልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ሁሉን ፡
እይታለች ።

ልክ ፡ እንደወፍ ፡ ስትበር ፡ ደርሳ ፡ ያን ፡
የወደቀበትን ፡ ብርጭቆ ፡ ወግ ፡ ባለው ፡ መልክ ፡

ካም ፡ ነው ። የሸፋሽፍቷ ፡ ፀጉር ፡ ከርዝመቱ ፡
የተነሳ ፡ የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የዓይኗን ፡ ብሌን ፡
ጉብኝቱት ፡ እያውቅም ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡
ዓይን ፡ እወዳለሁ ። እያበሩም ፡ ግን ፡ ለስላሳ ፡
ስለሆኑ ፡ የሚያብሱህ ፡ ይመስላሉ ። በነገራችን ፡
ላይ ፡ ከፈቷ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ውበት ፡ ዓይ
ኖቿ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ጥርሶቿስ ፡ ነጫጭ ፡
ናቸው? ይኼም ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።
ባነጋገርህ ፡ ላቅ ፡ ስትል ፡ ባለማየታችን ፡
ያሳዝናል ።»

«ስለሴቶች ፡ ስታወራ ፡ ስለእንግሊዝ ፡ የጥሩ ፡
ፈረስ ፡ ዘር ፡ የምታወራ ፡ ትመስላለህ ፡» ሲል ፡
ግሩሽኒትስኪይ ፡ መለሰልኝ ።

«Mon cher, je méprise les femmes pour ne pas les aimer, car autrement la vie serait un mélodrame trop ridicule»* ስል ፡ ቆጣ ፡ ብዬ ፡ ተናግ
ሬው ፡ ሄድሁ ።

ለግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በኮረብታው ፡ ባለው ፡
የወይን ፡ ተክል ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡
በቋጥኞች ፡ እየተዘዋወርሁ ፡ ፀሐዩ ፡ እስኪበረታ ፡
ስንሽራሸር ፡ ቆይቼ ፡ ወደቤቴ ፡ ተመለስሁ ።

---

* ወዳጄ ፡ ሆይ! ሴቶችን ፡ ሳለመውደድ ፡ ስል ፡
እጠላቸዋለሁ ። ምክንያቱም ፡ ሕይወት ፡ ያለዚያ ፡
ቁም ፡ ነገር ፡ የሌለበት ፡ ባዶ ፡ ትያትር ፡ ትሆና
ለች ። (በፈረንሳይኛ)

t.me/OLDBOOKSPDF

ር ፣ ጥሮ ፣ ለሳንቲም ፣ ብሎ ፣ ከዚህ ፣ በተቀለጠፈ ፣ ሁኔታ ፣ እንስቶ ፣ ይሰጥህ ፣ ነበር ። ከዚህም ፣ ሌላ ፣ ለእንተ ፣ በማዘኗ ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ የሚያስደንቅ ፣ ነገር ፣ ያለ ፣ እይመስለኝም ። በዚያ ፣ በቆሰለ ፣ እግርህ ፣ ለመቆም ፣ ስትሳቀቅ ፣ ስትታይ ፣ በጣም ፣ አሳዛኝ ፣ መልክ ፣ ነበረህ ።»

«መላ ፣ ስሚቷ ፣ በዚያ ፣ ዓይኖቿ ፣ ሲገለጽ ፣ ልብህን ፣ አላሸበረውም?»

«በጭራሽ ።»

ዋሸሁ ። ሆኖም ፣ ላበሽቀው ፣ ፈልጌ ፣ ነው ። ማንኛውንም ፣ ነገር ፣ ለመቃወም ፣ ከውስጥ ፣ የሚገፋፋኝ ፣ አንድ ፣ ጠባይ ፣ አለብኝ ። ሕይወቱ ፣ በሙሉ ፣ ልቤ ፣ የፈለገውን ፣ ደግ ፣ ነገር ፣ በመቃወም ፣ በአሳዛኝ ፣ ድርጊቶች ፣ የሞላ ፣ ነው ። ፍንክንክ ፣ ያለ ፣ ሁሉን ፣ ነገር ፣ እድናቂ ፣ ሰው ፣ ሲገኝ ፣ እንደክረምት ፣ እቀዘቅዛለሁ ። ስለሆነም ፣ በዝምተኛ ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ መገኘቱ ፣ ይበልጥ ፣ አላሚና ፣ አሳቢ ፣ ያደርገኛል ፣ ብዬ ፣ እምናለሁ ። ከዚህም ፣ ሌላ ፣ ደስ ፣ የማይል ፣ ከዚህ ፣ በፊት ፣ የማውቀው ፣ እንድ ፣ ዓይነት ፣ ስሜት ፣ እንደወረረኝ ፣ ለመናዘዝ ፣ እፈልጋለሁ ። ይህም ፣ ስሜት ፣ ጥላቻ ፣ ነው ። በድፍረት ፣ ጥላቻ ፣ ነው ፣ የምለውም ፣ ዘውትር ፣ ለራሴ ፣ እውነትን ፣ የመናገር ፣ ልምድ ፣ ስላለኝ ፣ ነው ። ማንም ፣ ወጣት ፣ ለው ፣ (በከፍተኛ ፣ ደረጃ ፣ የሚገኝና ፣ ፍላጐቱን ፣ ሁሉ ፣

እንስታ ፣ ለጠችው ። እፈር ፣ ብላ ፣ ወደዛኒጋ ባው ፣ ከተመለከተች ፣ በኋላ ፣ እናቷ ፣ እንዳላ ይዋት ፣ ስታውቅ ፣ መልሳ ፣ ተረጋጋች ። ግሩሽኒ ትስኪይ ፣ «አመሰግናለሁ ።» ለማለት ፣ ገና ፣ አፉን ፣ ሲከፍት ፣ ከአጠገቡ ፣ እርቃ ፣ ሔዳ ፣ ነበር ። ከጥቂት ፣ ጊዜም ፣ በኋላ ፣ ከእናቷና ፣ ከዚያ ፣ መኳንንት ፣ ጋር ፣ በእንድነት ፣ ዛኒጋባውን ፣ ለቀው ፣ ሔዱ ። ልዕልቷ ፣ የአደባባዩን ፣ ዛፎች ፣ አልፋ ፣ እስክትሔድ ፣ ድረስ ፣ የተከተሏትን ፣ የግሩሽኒትስኪይ ፣ ዓይኖች ፣ ዘወር ፣ ብላ ፣ እንኳ ፣ ሳታይ ፣ ኮስተር ፣ ብላ ፣ መንገዷን ፣ ቀጠለች ... በመጨረሻም ፣ ወደጐን ፣ ባለው ፣ መንገድ ፣ አልፋ ፣ በፒተርሆርስክ ፣ ካሉት ፣ ቆንጆ ፣ ቤቶች ፣ አጥር ፣ ግቢ ፣ ውስጥ ፣ ስትገባ ፣ ባርኔጣዋ ፣ ውልብ ፣ ሲል ፣ አየ ። ከዚያም ፣ እናቷ ፣ ልዕልት ፣ ራየቪችን ፣ ከአጥር ፣ ግቢው ፣ በር ፣ ላይ ፣ ተሰናብተው ፣ ተከትለዋት ፣ ገቡ ። የተጨነቀው ፣ እጨቱ ፣ መኰንን ፣ በእካባቢው ፣ የእኔን ፣ መኖር ፣ ያወቀው ፣ ያኔ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

እጇን ፣ ያዝ ፣ አድርጉ ፣ «የሆነውን ፣ ሁሉ ፣ አየህ? መቼም ፣ መልእክ ፣ ናት ።»

በቀዘቀዘ ፣ መንፈስ ፣ «ለምን?» ብዬ ፣ ጠየቅሁት ።

«እንጃ ፣ አላየሁም ፣ እንጃ?»

«ብርሳቱሀን ፣ እንስታ ፣ ስትሰጥህ ፣ አይታ ለሁ ። እንዲያውም ፣ የእትክልቱ ፣ ጠባቂ ፣ ቢኖ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማሚላት ፡ የሚችል ፡ ማለቱ ፡ ነው) የማረከ
ችው ፡ ሴት ፡ እንደሱው ፡ እንግዳ ፡ የሆነውን ፡
ሌላ ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ ስትወድ ፡ ማየቱ ፡ መጥፎ ፡
ስሜት ፡ እንደሚያላድርበት ፡ ጥርጥር ፡ የለ
ውም ።

ግሩሽኒትስኪይና ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ ሳንነጋገር ፡
በፀጥታ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወርደን ፡ ያች ፡ ቆንጆ ፡
ሴት ፡ በጣቧበት ፡ ቤት ፡ መስተዋት ፡ አልፈን ፡
ሄድን ። ልዕልቷም ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡
ብላ ፡ ነበር ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ እጅጌዬን ፡ ሳብ ፡
አድርጐ ፡ ሴቶችን ፡ በማይማርክ ፡ አስተያየት ፡
ተመለከታት ። እኔም ፡ ያን ፡ በእጅ ፡ የሚያዝ ፡
መነፅሬን ፡ ደንቅሬ ፡ ስለተመለከትኋት ፡ በግሩ
ሽኒትስኪይ ፡ ሁኔታ ፡ ፈገግ ፡ ስትል ፡ የእኔው ፡
ጨርሶ ፡ እበሽቃት ። በእውነትም ፡ ከሆነ ፤
እንዴት ፡ አንድ ፡ የካውካሱስ ፡ ወታደር ፡ ከሞስ
ኮ ፡ በመጣች ፡ ልዕልት ፡ ላይ ፡ መነፅሩን ፡ ለ
መደንቀር ፡ ይደፍራል?...

ግንቦት ፡ ፲፫ ቀን ።

ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሐኪሙ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።
ስሙ ፡ ቬርነር ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሩሲያዊ ፡
ነው ። ያህም ፡ ምንም ፡ እያስደንቅም ። ለም
ሳሌ ፡ እኔ ፡ ኢቫኖቭ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ጆር
መን ፡ ሰው ፡ አውቅ ፡ ነበር ።

ቬርነር ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ የሚ
ደንቅ ፡ ሰው ፡ ነው ። እንደብዙዎቹም ፡ ሐኪ

ሞች ፡ በአስተሳሰቡ ፡ ማቴሪያሊስትና ፡ ተጠራ
ጣሪ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በልቦናው ፡ ግን ፡ ገጣሚ ፡
ነው ። ገጣሚነቱም ፡ በነፍስ ፡ እንጂ ፡ በሕይ
ወቱ ፡ ሙሉ ፡ ሀሊት ፡ መስመር ፡ እንኳን ፡ ገጥሞ ፡
እያውቅም ። ሰዎች ፡ የእንድን ፡ አካል ፡ እንቀ
ሳቃሽ ፡ ኃይል ፡ እንደሚያጠኑት ፡ ሁሉ ፡ እሱም ፡
የሰውን ፡ ልብ ፡ ደህና ፡ እድርጐ ፡ ያውቃል ።
ይሁንና ም ፡ ትላልቅ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሊቃው
ንት ፡ ትኩሳት ፡ ለማብረድ ፡ እድል ፡ እንደሌ
ላቸው ፡ ሁሉ ፡ እሱም ፡ በዚህ ፡ እውቀቱ ፡ ተጠቅ
ሞበት ፡ እያውቅም ። ቬርነር ፡ ዘወትር ፡ በበሽ
ተኞች ፡ ላይ ፡ በድብቅ ፡ ያሾፍባቸዋል ። አንድ ፡
ጊዜ ፡ ግን ፡ ለአንድ ፡ ለሞተ ፡ ወታደር ፡ ሲያለ
ቅስ ፡ አይቼዋለሁ ። በይዞታው ፡ ደሃ ፡ ነው ።
ሐብታም ፡ ለመሆን ፡ ታላቅ ፡ ፍላጐት ፡ ቢኖረ
ውም ፡ ለመነገድ ፡ ሲል ፡ ከመስመሩ ፡ ነቅነቅ ፡
አይልም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለወዳጅ ፡ ጥሩ ፡ ከመ
ዋል ፡ ይልቅ ፡ ለጠላት ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ መሥ
ራትን ፡ እንደሚመርጥ ፡ እወራኝ ። ምክንያ
ቱም ፡ ወዳጅነት ፡ በልግስና ፡ የሚገኝ ፡ እይደለ
ምና! 'ለጠላትህ ፡ የምታደርገው ፡ ደግ ፡ ነገር ፡
እየበዛ ፡ በሔደ ፡ ቁጥር ፡ ግን ፡ ጥላቻውም ፡ የዚ
ያን ፡ ያህል ፡ እየከረረ ፡ ይሔዳል ።' ብሎኛል ።
አፉ ፡ እያጭልም ። ያም ፡ ነገረኛ ፡ ምላሱ ፡ በቃ
ላት ፡ የታጠቀ ፡ ነው ። በእንግሩ ፡ ብዙዎች ፡
ደግ ፡ ሰዎችን ፡ ይመንጅላቸዋል ፤ በፀበሉ ፡ እካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለመጠን ፡ ትልቅ ፡ ነው ። የወንሩ ፡ ቁርጥ ፡ አጭር ፡ ሲሆን ፤ በጉልሀ ፡ የሚታየው ፡ የሞን ቅላቱ ፡ ቅርጽ ፡ ግን ፡ ለናፊኖለጂስት ፡ ሐኪ ሞች ፡ ሳያስደንቃቸው ፡ አይቀርም ። እነዚያ ፡ ጠቋቁር ፤ ትንንሽ ፤ እረፍት ፡ የለሽ ፡ ዓይኖቹ ፡ የሰውን ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ጠልቀው ፡ ለማየት ፡ ዘወትር ፡ ይጥራሉ ። እለባበሱ ፡ ግሩም ፡ ነው ። ለስላሳ ፡ ትናንሽ ፡ ጣቶቹ ፡ በብጫማ ፡ የእጅ ፡ ሹራቦች ፡ ተሸፍነዋል ። ክራቫትና ፡ ሠደሪያው ፡ ደማቅ ፡ ጥቁር ፡ ነው ። ወጣቶቹ ፡ ሜፊስቶፌል* ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ሰጥተውታል ። በዚህ ፡ በቅጽል ስም ፡ ያልተደሰቱ ፡ ቢመስልም ፡ በልቡ ፡ ግን ፡ ሳይቀበለው ፡ እይቀርም ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባባት ፡ ችለናል ። እኔ ፡ በተፈጥሮዬ ፡ በቀላሉ ፡ ወዳጅ ፡ ለማበጀት ፡ አልችልም ። በሁለት ፡ ወዳጆች ፡ መካከል ፡ እንዱ ፡ ለእንዱ ፡ ባሪያ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ እይቀበሉትም ። የባርኑቱን ፡ ቦታ ፡ እኔ ፡ ለመ ያዝ ፡ አልፈልግም ። የበላይነቱንም ፡ ቢሆን ፡ አል ፈቅድም ። ምክንያቱም ፡ ለማዘዝ ፡ ሁልጊዜ ፡ ማታለል ፡ ይኖርብሃልና! ከዚህም ፡ ሌላ ፡ እሽ ከርም ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ! ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡

* ሜፊስቶፌል — ጊዮቴ ፡ በደረሰው ፡ ፀፋው ስት ፡» በተባለው ፡ ድራማ ፡ ውስጥ ፡ የሠይ ጣን ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።

ባቢ ፡ ያሉ ፡ ተቀናቃኝና ፡ ተለማማጅ ፡ ሐኪ ሞች ፡ በሽተኞችን ፡ በፈዝ ፡ ያንኳሸሻቸዋል ፡ እያሉ ፡ ያሙታል ። በሽተኞቹ ፡ በዚህ ፡ ወሬ ፡ ስለተናደዱ ፡ ደንበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ከዱት ። በካው ካሱስ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ጨዋ ፡ መኳንንት ፡ ወዳ ጆቹ ፡ ይህን ፡ የተበከለውን ፡ ስሙን ፡ ለማደስ ፡ ጥረት ፡ ቢያደርጉም ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ቀርቷል ።

መልኩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሲያዩት ፡ ደስ ፡ ባይልም ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ላጤነው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ውስጣዊ ፡ ልቡ ፡ የተፈተሸ ፡ ጠንቃራና ፡ እሩህሩህ ፡ ሆኖ ፡ መሆኑ ፡ ያስታውቃል ። እ ንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሴቶች ፡ እንዴ ፡ ከወደዱ ፡ በፍቅር ፡ ስለሚያብዱ ፡ በኤንዲሚ ዮን* ፡ እንኳ ፡ ቀይሩ ፡ ቢባሉ ፡ እሽ ፡ አይሉም ። ሴቶች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የውስጣዊ ፡ ውበትን ፡ የማወቅ ፡ ኃይል ፡ ስላላቸው ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባ ቸዋል ። ምናልባትም ፡ እንደቬርነር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሴቶችን ፡ ከልብ ፡ የሚያፈቅሩ ፡ ለዚህ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ቬርነር ፡ ቁመቱ ፡ ደርባባ ፤ ቁጭንና ፡ እንደ ሕፃን ፡ አቅመ ፡ ቢስ ፡ ነው ፤ እንደባይሮን ፡ አንዱ ፡ እግሩ ፡ ከአንዱ ፡ ያጥራል ። ጭንቅላቱ ፡

* ኤንዲሚዮን — በጥንት ፡ የግሪክ ፡ ተረት ፡ ዘላለማዊና ፡ የዘወትር ፡ ሰንጋት ፡ ያለው ፡ ወጣት ፡ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከቨርነር ፡ ጋር ፡ የተዋወቅነው ፡ እንዲህ ፡ ነው ።
ቬርነር ፡ ያገኘው ፡ በኤስ ... ውስጥ ፡ ተሰብስ
በው ፡ ከሚንጫፈቱት ፡ ወጣቶች ፡ መካከል ፡
ነው ። መሸትሸት ፡ ሲል ፡ ውይይቱ ፡ ወደሚታ
ፊዚክ ፡ ፍልስፍና ፡ አመራ ። ሁላችንም ፡ የተለ
ያየ ፡ እምነታችንን ፡ ገለጽን ።

«እኔ ፡ በበኩሌ ፡ የማምንበት ፡ ነገር ፡ አንድ ፡
ነው ፡» በማለት ፡ ዶክተሩ ፡ ሐሳቡን ፡ ሠነዘረ ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያልተናገረውን ፡ ሰው ፡
ሐሳብ ፡ ለመስማት ፡ ፈልጌ ፤

«ታዲያ ፡ እምነትዎ ፡ ምንድነው?» ስል ፡
ቀስ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅኩት ።

«ወጣም ፡ ወረደ ፡ በአንድ ፡ ብሩህ ፡ ጥዋት ፡
መሞቴን ፡ አውቃለሁ ።»

«እንግዲያውስ ፡ በእምነቴ ፡ እኔ ፡ ከእር
ስዎ ፡ እሻላለሁ ። ይኸው ፡ በአንድ ፡ በተረገመ ፡
ሌሊት ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ለመምጣት ፡ መጥፎ ፡
እድል ፡ ስላጋጠመኝ ፡ ነው ።»

ለተሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ ወሬአችን ፡ ፍሬከር
ሲኪ ፡ መስሎም ፡ ቢታያቸውም ፡ የእነርሱ ፡
ወሬ ፡ ከእኛ ፡ የተሻለ ፡ አልነበረም ። ከዚያን ፡
ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ ተመራ
ርጠን ፡ ለብቻቸን ፡ ተወዳጅን ። በየጊዜው ፡
እየተገናኘን ፡ ባልተፈቀጠ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በቁ
ም ፡ ነገር ፡ ስንወያይ ፡ ከቆየን ፡ በኋላ ፡ እርስ ፡
በርሳችን ፡ እንደምንፋተት ፡ ተዋወቅን ፡ ሲሠር ፡
የጥንት ፡ ሮማዊያን ፡ ሽማግሌነትን ፡ ሥሎ ፡ባቀ
ረበልን ፡ መልክ ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ እንጋጭና ፡
በሳቅ ፡ ተንከትክተን ፡ ለምሽቱ ፡ በቂ ፡ ደስታ ፡
ገብይተን ፡ እንለያየን ።

ቬርነር ፡ ወደክፍሌ ፡ ሲገባ ፡ በፎቴ ፡ ላይ ፡
ጋደም ፡ ብዬ ፤ ጭንቅላቴን ፡ በእጀቼ ፡ ተደግፌ ፡
ጣራ ፡ ጣራውን ፡ እመለከት ፡ነበር ። ከወንበሩ ፡
ላይ ፡ ቁጭ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ አዛግቶ ፡ ውጪ ፡
እንደሚሞቅ ፡ አበሰረኝ ። እኔም ፡ ዝንቦቹ ፡
እንዳስቸገሩኝ ፡ ካስረዳሁት ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ብ
ለን ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቁጭ ፡ አልን ።

«ውድ ፡ ዶክተር ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡
ቂሎች ፡ ባይኖሩ ፡ ኖሮ ፤ ኑሮ ፡ ስልቹ ፡ እንደሚ
ሆን ፡ አይስቱትም ። እነሆ ፡ ለምሳሌ ፤ እኛ ፡
ሁለት ፡ ምሁራን ፡ ነን ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡
ሊተችበትና ፡ ሊነገርበት ፡ እንደሚችል ፡ አስ
ቀድመን ፡ ስለምናውቅ ፡ እንከራከርም ። የኢያ
ንዳንዳችንም ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ከሞላ ፡
ጐደል ፡ እንተዋወቃለን ። አንድ ፡ ቃል ፡ ብቻ
ዋን ፡ ስትነገር ፡ ለእኛ ፡ ታሪክ ፡ ልትሆነን ፡ ትች
ላለች ። የላይ ፡ ቆዳችንን ፡ ሰርስረን ፡ ገብተን ፡
ውስጣዊ ፡ ስሜታችንን ፡ ለማየት ፡ እንችላለን ።
ለእኛ ፡ አሳዛኝ ፡ ነገር ፡ አስቂኝ ፡ ነው ። አስ
ቂኙ ፡ ደግሞ ፡ ያሳዝነናል ። በሌላም ፡ አንጋ
ገር ፡ እንደእውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ከራሳችን ፡ በስተቀር ፡
ለሌላው ፡ ደንታ ፡ የለንም ። ስለሆነም ፡ በመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ካከላችን ፡ የስሜት ፡ የሐሳብ ፡ ልውውጥ ፡ በፍጹም ፡ ሊኖር ፡ እይችልም ። ስለእያንዳንዳችን ፡ ማወቅ ፡ የምንፈልገውን ፡ ነገር ፡ በሞላ ፡ እውቀናል ። ሌላም ፡ ለማወቅ ፡ የምንፈልገው ፡ ነገር ፡ የለም ። እንድ ፡ የቀረን ፡ እርእስት ፡ ቢኖር ፡ የመጨረሻ ፡ ዜናዎች ፡ ናቸው ። ምንም ፡ የሚነግሩኝ ፡ ነገር ፡ የለም?»

በረጅሙ ፡ ንግግር ፡ ተሰላችቼ ፡ ዓይኔን ፡ ጨፍኜ ፡ አዛጋሁ ።

ዶክተሩ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ካሰላሰለ ፡ በኋላ፣ ወከተናገሩት ፡ ፍሬከርሲኪ ፡ ውስጥ ፡ እንድ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለ ፡» አለኝ ።

«ሁለት ፡» ብዬ ፡ መለስሁለት ።

«እንዱን ፡ ይንገሩኝ ፤ ሁለተኛውን ፡ እኔ ፡ አወራዎታለሁ ።»

ጣራ ፡ ጣራውን ፡ መመልከቴን ፡ ቀጥዬ ፡ በውስጤ ፡ እየሳቅሁ ፤ «ጥሩ ፤ ይጀምሩ ፡» አልሁት ።

«በቅርቡ ፡ ወይዚህ ፡ ጠበል ፡ ስለመጣ ፡ ሰው ፡ በዝርዝር ፡ ሁኔታዎችን ፡ ለማወቅ ፡ ይሻሉ ። ስለማን ፡ ለማወቅ ፡ እንደሚፈልጉ ፡ መጣመት ፡ ቀላል ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የሚፈልጉት ፡ ሰው ፡ ስለእርስዎ ፡ ሰጠይት ፡ ነበር ።»

«በእውነቱ ፡ ዶክተር ፤ ለርስዎና ፡ እኔ ፡ መነጋገር ፡ እያስፈልገንም ፡ ሁለታችንም ፡ ልብ ፡ ለልብ ፡ እንተዋወቃለን ።»

«ሁለተኛውስ ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ ነበር?»

«ሁለተኛው ፡ ሐሳብ ፡ እነሆ! እንድ ፡ ነገር ፡ እንዲነግሩኝ ፡ እፈልጋለሁ ። በመጀመሪያ ፡ ያረጀ ፡ መናገር ፡ ከመስማት ፡ የባሰ ፡ እድካሚ ፡ በመሆኑ ፤ ሁለተኛ ፡ እድማጭ ፡ ምንም ፡ የሚጐድሰው ፡ ነገር ፡ ስለሌለው ፤ ሦስተኛ ፤ በመስማት ፡ የሌላን ፡ ሰው ፡ ምስጢር ፡ ለማወቅ ፡ ስለሚቻል ፡ አራተኛ ፡ እንደእርስዎ ፡ ያለ ፡ ብልጥ ፡ ሰው ፡ ከተናጋሪ ፡ ይልቅ ፡ አድማጭን ፡ ስለሚመርጥ ... ይልቅ ፡ ወደቱም ፡ ነገሩ ፡ እንመለስና ፤ ልዕልት ፡ ሊጐቭስካያ ፡ ስለእኔ ፡ ምን ፡ አልዎት?»

«ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ላለመሆኗ ፡ እርግጠኛ ፡ ነዎት?»

«እዎን ፤ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም ፡ ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ የጠየቀችዋ ፡ ስለግሩሽኒትስኪይ ፡ ነው ።»

«በእውነቱ ፡ ጥሩ ፡ ግምት ፡ የመስጠት ፡ ተደናቂ ፡ ችሎታ ፡ አለዎት ። ወጣቷ ፡ ልዕልት ፡ ያ ፡ ወፍራም ፡ ኮት ፡ የለበሰው ፡ ወታደር ፡ ‘በጠብ ፡ ምክንያት ፡ ማዕረጉ ፡ የተነሳበት ፡ ሳይሆን ፡ እይቀርም’ ፡ ብላ ፡ ተናግራ ፡ ነበር ።

«ይህን ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ግምቷን ፡ እንዳላበላሽባት ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።»

«እዎን ... እንዴ ... »

«ታሪኩ ፡ እየተደያዘ ፡ መጣ ፤ ለዚህም ፡ እስቲኝ ፡ ድራማ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚኾለንን ፡ ያህል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እናደርጋለን ። ሕይወት ፡ ምንጊዜም ፡ በተሰለቸ ፡ ጉራጉር ፡ ውስጥ ፡ ጥላኝ ፡ እታውቅም ፡» እያልኩ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቅሁ ።

«ምስኪኑ ፡ ማሩሽኒትስኪይ ፡ በእርስዎ ፡ የጭንሳ ፡ ይሰቃያል ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ ።»

«ከዚያስ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ይከተር?»

«ልዕልት ፡ ሊጐቭስካያ ፡ የእርስዎን ፡ መልክ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በፔቴርቡርግ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እንዳዩዎት ፡ ይላሉ ። ስምዎን ፡ ጠርተው ፡ ነግሮውኛል ። ስለእርስዎ ፡ የሚያውቁት ፡ ነገር ፡ አለ ። እንደሚባለው ፡ ከሆነ ፡ ታሪክዎ ፡ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ ተደናቂ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ሴላ ፡ ልዕልቲቱ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ስለሚወራው ፡ ሐሜትና ፡ አሉባልታ ፡ እጥ ላልተው ፡ ስለሥራዎችዎ ፡ አውርተውኛል ። ልጅቷ ፡ ልክ ፡ በዘመናዊ ፡ ድርሰት ፡ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ዋና ፡ ባሕርይ ፡ ታሪክዎን ፡ በጉጉት ፡ እያየች ፡ ታዳምጥ ፡ ነበር ። ልዕልቲቷ ፡ የሚያወሩት ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የማይረባ ፡ ቢሆንም ፡ ወሬአቸውን ፡ ለማስተባበል ፡ አልፈለግሁም ።»

«ወዳጄ ፡ ግለት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡» ብዬ ፡ ልጨብጠው ፡ እጄን ፡ ዘረጋሁለት ።

ያከተራም ፡ ከሰሚት ፡ ጋራ ፡ ከጨበጠኝ ፡ በኋላ ፡ ወሬውን ፡ ቀጠለ ፡

«ከፈለጉ ፡ ላስተዋወቅዎት ፡ እችላለሁ ...»

«ወዳጄ ፡ ሆይ! የእንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋና ፡ ባህሪ ፡ በእስተዋዋቂ ፡ ሲገናኙ ፡ ሰውተው ፡ ያ ውታሉ? ከሚወዳት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ የሚተዋወቁው ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ካደናት ፡ በኋላ ፡ ነው ...» ስል ፡ እጆቼን ፡ ዘርግቼ ፡ መለስሁለት ።

«ከዚህች ፡ ልዕልት ፡ ጋር ፡ ለመወዳጀት ፡ ከልብ ፡ ይፈልጋሉ?»

«እረ ፡ አይደለም ። እንግዲያውስ ፡ ሐሳቤ ፡ ገና ፡ አልገባዎትም ። እንዲያውም ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ይበልጥ ፡ ያሳዝነኛል ፡» ብዬ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ካልሁ ፡ በኋላ ፡ ንግግሬን ፡ ቀጠልሁ ፤ «የውስጣዊ ፡ ስሜትን ፡ ላለመግለጽ ፡ የዘወትር ፡ ሕግ ፡ አለብኝ ። ሌሎች ፡ ይህንን ፡ ስሜቴን ፡ ራሳቸው ፡ ፈልፍለው ፡ ሲደርሱበት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። ምክንያቱም ፡ በእስፈላጊ ፡ ጊዜ ፡ ለመሸፈጥ ፡ ቦታ ፡ ስለሚተውልኝ ፡ ነው ። ብቻ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ስለእናቲቱና ፡ ስለልጅዋ ፡ በዝርዝር ፡ ያውሩኝ ። ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው?»

«በመጀመሪያ ፡ ልዕልቲቷ ፡ የሟች ፡ ዓመት ፡ ሴት ፡ ናቸው ። ደህና ፡ ይመገባሉ ፤ ሆኖም ፡ ደማቸው ፡ እንደቆሸሸ ፡ በጉንጫቸው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ በልዝ ፡ ያስታውቃል ። ግማሹን ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉት ፡ ሥራ ፡ ፈተው ፡ በሞስኒ ፡ ውስጥ ፡ በእረፍት ፡ ስለሆነ ፡ ውፍረት ፡ ጨምረዋል ። አንቱል ፡ ቀልዶችን ፡ ያፈቅራሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚወዳጁት ፡ ጠና ፡ ካሉ ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ አሳውንት ፡ ጋር ፡ ነው ።»

«ያከተር ፤ ሞስኮ ፡ ሄደው ፡ ያውቃሉ?»

«በሚገባ ፡ እንጂ ። አንዴ ፡ ለልምምድ ፡ ሐጂ ፡ ነበር ።»

«በጀ ...»

«በእውነቱ ፡ ያለኝን ፡ በሙሉ ፡ ሳልነግር ም ፡ የቀረሁ ፡ አይመስለኝም ። ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ላክልበት ። ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ስለፍቅር ፤ ስለውስጣዊ ፡ ስሜት ፤ ስለመሳሰሉ ፡ ሁሉ ፡ ማውራት ፡ ትወዳለች ። አንድ ፡ ከረምት ፡ በፔቴርቡርግ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ አሳልፋለች ። ሆኖም ፡ በከተማው ፤ በተለይም ፡ በሕዝቡ ፡ የተደሰተች ፡ አይመስለኝም ። የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አላደረጉላትም ፡ ይሆናል ።»

«ዛሬ ፡ ቤታቸው ፡ ሲሔዱ ፡ ሌሎች ፡ ሰ ዎች ፡ ነበሩ?»

«እዎን ፡ ነበሩ ። እንድ ፡ መኰንንና ፡ ከአ ዲስ ፡ ፀበልተኞች ፡ ውስጥ ፡ እንዲ ፡ በጣም ፡ የታመመች ፡ ቆንጆ ፡ የልዕልቷ ፡ ባል ፡ ዘመድ ፡ ትመስለኛለች ፤ ነበሩ ። ከፀበሉ ፡ እላይዋትምን ቱሙቷ ፡ መጠነኛ ፡ ነው ። ፀጉሯ ፡ ነጣ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ መልኳ ፡ የላምባ ፡ በሽተኛ ፡ ትመስላለች ። ከተኛ ፡ ጉንጯ ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ ስማታለች ። በአጠቃላይ ፡ ደሞ ፡ ከገጽሞ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ይነበባሉ ።»

ልጃቸውም ፡ ወጣ ፡ ስትል ፡ የማይገቡ ፡ ወሬዎ ችን ፡ ያወራሉ ። ሴት ፡ ልጃቸው ፡ ምንም ፡ የማ ታውቅ ፡ እንደእርግብ ፡ የዋህ ፡ ናት ፡ ይሏታል ። ይህ ፡ እነጋገር ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ግንኙነት ፡ እንዳለው ፡ አልገባኝም ። ለማጽናናት ፡ ስል ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አልናገርም ፡ ለማለት ፡ ቃቶኝ ፡ ነበር ። ልዕልቷ ፡ የመጡት ፡ ከቁርጥማት ፡ በሽታ ፡ ለመፈወስ ፡ ነው ። ልጃቸው ፡ ግን ፡ ከምን ፡ በሽ ታ ፡ ለመዳን ፡ እንደሆነ ፡ አምላክ ፡ ይወቀው ። ለ ማንኛውም ፡ ሁለቱም ፡ በየቀኑ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ብርጭቆ ፡ ፀበል ፡ እንዲጠጡና ፡ በሳምንት ፡ ሁለቴ ፡ በፀበሉ ፡ እንዲነከሩ ፡ መከርኳቸው ። ልዕልቷ ፡ ሰው ፡ የማዘዝ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ አይመስሉም ። ባይሮንን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ያነ በበችውንና ፡ የአልጀብራ ፡ እውቀት ፡ ያላትን ፡ የልጃቸውን ፡ አስተሳሰብ ፤ ብልህነት ፡ ያከብ ራሉ ። የሞስኮ ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ ትምህርቱን ፡ በሚገባ ፡ ተያይዘውታል ። በመሠረቱ ፡ የሚደ ገፍ ፡ ነው ። የእኛ ፡ ወንዶች ፡ ጠባይ ፡ ብልሹ ፡ ስለሆነ ፡ የተማሩ ፡ ሴቶች ፡ ለወዳጆዋቸው ፡ አይፈልጉም ። እናትየዋ ፡ ወጣት ፡ ወንዶችን ፡ ይወዳሉ ። ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ግን ፡ የምትመለ ከታቸው ፡ ጥርጣሬ ፡ በሞላበት ፡ መንፈስ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሞሰኮ ፡ ልምድ ፡ መሆኑ ፡ ነው። በሞሰኮ ፡ ውበተ ፡ ያሉ ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

«ማርያም ፡ የሳመቻት ፡ አሉኝ፣ በእውነት?...»

ዶክተሩ ፡ እጁን ፡ ከደረቴ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጐ ፡ «ያውቁአታል!» አለኝ ።

በእውነቱ ፡ የልቤ ፡ ትርታ ፡ ከሌላው ፡ ጊዜ ፡ በፈጠነ ፡ ይመታ ፡ ነበር ።

«እንግዲህ ፡ የመፈንጠዙ ፡ ተራ ፡ የእርስዎ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አሳልፈው ፡ እንደማይሰጡኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በዓይኔ ፡ አላየኋትም ። ግን ፡ መልኳን ፡ ሥለው ፡ እንዳቀረቡልኝ ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ የድሮ ፡ የወዳጅነት ፡ ሴት ፡ ታስታውሰኛለች ። ስለእኔ ፡ በፊቷ ፡ ምንም ፡ አያውሩ ። ከጠየቀችዎም ፡ መጥፎ ፡ መጥፎውን ፡ ይንገሩአት ።»

ቪርነር ፡ ትከሻውን ፡ ነቅንቆ ፣ «እንደፈለጉ ፡» አለኝ ።

እሱ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ሐዘን ፡ ሰውነቴን ፡ ወረረው ። ካውካሱስ ፡ ውስጥ ፡ ያገናኘን ፡ አጋጣሚ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከዚህ ፡ መኖሬን ፡ እውቃ ፡ ነው ፡ የመጣችው፣ ግንኙነታችን ፡ እንዴት ፡ ይሆን? ለመሆኑ ፡ እሷ ፡ ናት ፡ ወይ፣ ሰውነቴ ፡ ከጠረጠረ ፡ እውነት ፡ እሷ ፡ ናት ፡ ግለት ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ሕይወቴ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ትዝታና ፡ ተጽዕኖ ፡ ያሳደረብኝ ፡ ሰው ፡ ካለ ፡ እሷ ፡ ናት ። ያለፈውን ፡ ሁኔታችንን ፡ ሐዘንም ፡ ሆነ ፡ ያበታ ፡ ናፍ፣ ባለኝ ፡ ቁጥሬ ፡ ልቤ ፡ በሐዘን ፡ ጡንቻ ፡ ይወገራል ። አፈጣጠሬ ፡ አንጉል ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አልረሳም ... ምንም ፡ አልረሳም!

ከአራት ፡ በኋላ ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ወደአደባባዩ ፡ ብወርድ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ አገኘሁ ። በአንድ ፡ አግድም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ያሉትን ፡ ልዕልቲቷንና ፡ ልጆቸውን ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ከበው ፡ ያወራቸዋል ። እኔም ፡ በአጠገብ ፡ አንድ ፡ አግድም ፡ ወንበር ፡ ፈልጌ ፡ ቁጭ ፡ ካልሁ ፡ በኋላ ፡ የሚያልፉ ፡ ሁለት ፡ መኰንኖች ፡ እግኝቼ ፡ አወራ ፡ ጀመር ። ወሬዬ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ሁለቱ ፡ መኰንኖች ፡ እንደአብዮ ፡ በላቅ ፡ ይንከተከቱ ፡ ገቡ ። አንዳንድ ፡ ወጣቶችም ፡ የእኛ ፡ ላቅ ፡ ስቢቸው ፡ ከበው ፡ ቁጭ ፡ ካሉባት ፡ ቦታ ፡ ልዕልቲቷን ፡ ትተው ፡ ወደእኛ ፡ መጡ ። ቀስ ፡ በቀስም ፡ ልዕልቲቷን ፡ ያጀቧት ፡ ሳይቀሩ ፡ ትተዋት ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡ ተሰበሰቡ ። የባጥ ፡ የቆጡን ፡ ስቀባጥር ፡ በአላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ሳሾፍ ፣ ፀሐይ ፡ ጨርሳ ፡ እስክትገባ ፡ ድረስ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ በቀልድ ፡ ሳስደስተው ፡ አመሸሁ ። ልዕልቲቷና ፡ ልጆቸው ፡ ተያይዘው ፡ ከእንድ ፡ እንካሳ ፡ ሽማግሌ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ እኛ ፡ ስናወራ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይመላለሱ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወጣቷ ፡ ልዕልት ፡ እየተገላመጠች ፡ ስትመለከተኝ ፡ በሁኔታዋ ፡ የተናደደች ፡ ብትመስልም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ትርብ ፡ ወዳጅ ፡ የሆንሁ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ከእሷ ፡ ጋር ፡ በቅርብ ፡ ለመተዋወቅ ፡ እንደማልጥር ፡ ስታይ ፡ በኃይል ፡ ይገርማታል ። በየእለቱ ፡ በ ወበሉና ፡ በእደባባዩ ፡ እንገናኝ ፡ ጀመር ። እ ኔም ፡ የማረክቻቸውን ፡ የተሸቀረቀሩ ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ የገረጡትን ፡ የሞስኮ ፡ ነዋሪዎ ችንና ፡ ሌሎችንም ፡ ሳጫውት ፡ እውል ፡ ነበር ። በተፈጥሮዬ ፡ እንግዳ ፡ እቤቴ ፡ ሲመጣ ፡ ደስ ፡ አይለኝም ። አሁን ፡ ግን ፡ በየእለቱ ፡ ለምሳ ፤ ለእራት ፤ ለካርታ ፡ ጨዋታ ፡ ቤቴ ፡ በእንግዳ ፡ ተሞልቶ ፡ ይውላል ። እንደማግኔት ፡ ከሚስ በው ፡ ዓይኖቿ ፡ ይበልጥ ፡ ፊት ፡ ለፊቴ ፡ የተደረ ደረው ፡ ሻምፓኝ ፡ ለእካባቢው ፡ ልዩ ፡ ውበትን ፡ ያጐናጽፈዋል ።

ትናንትና ፡ እንድ ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ የፔር ሺያን ፡ ሥጋጃ ፡ ለመግዛት ፡ ቼላኽቭ ፡ ሱቅ ፡ ገብታ ፡ ዋጋ ፡ ስትደራደር ፡ አገኘኋት ። ልዕ ልቲቷ ፡ የሥጋጃው ፡ ውበት ፡ ለቤቷ ፡ ክፍል ፡ ተስማሚ ፡ ስለሆነ ፡ እናቷ ፡ ውድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እንዳይተውት ፡ ትለምናቸው ፡ ነበር ። እኔም ፡ ከተባለው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ እርባ ፡ ሩብል ፡ ጨምሬ ፡ ገዛሁት ። ለዚህም ፡ ሥራዬ ፡ ከባድ ፡ የጥላቻ ፡ ግልምጫ ፡ ተቀብዬ ፡ ዘወር ፡ እልሁ ። ከእራት ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ የቼርከስ ፡ ፈረሴን ፡ የገዛሁትን ፡ ሥጋጃ ፡ አልብሼ ፡ ሆን ፡ ብዬ ፡ በደጃፏ ፡ አለፍሁ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልዕልቲ

ንዴቷን ፡ በውስጧ ፡ ለመደበቅ ፡ ትጥራለች ።

የጨዋነት ፡ ይሉኝታ ፡ ይዞት ፡ ወደልዕልቷ ፡ የተመለሰውን ፡ ወጣት ፤ «ምንድነው ፡ የሚ ያወሩት? መቼም ፡ አስደሳች ፡ ሳይሆን ፡ አይ ቀርም? ምናልባት ፡ ስለጦር ፡ ሜዳ ፡ ጀብዳቸው ፡ ይሆናል?...» ብላ ፡ ጠየቀችው ። አነጋገሯ ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ ስለነበረ ፡ እኔን ፡ ለማና ደድ ፡ ሆን ፡ ብላ ፡ እንደሆነ ፡ ገባኝ ። «መል ካም ፡ ውዲቷ ፡ ልዕልት ፡ በሽቀዋል ። ገና ፡ ምን ፡ እይተው?» በማለት ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ እጉረመረምሁ ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ እንደአዳኝ ፡ ነበር ፤ ልዕ ልቲቷን ፡ ይከተላል ። ከዓይኑም ፡ እንድትለይ በት ፡ አይሻም ፤ ምናልባትም ፡ ነገ ፡ ልዕልት ፡ ሊጐብስኪያን ፡ አስተዋውቁኝ ፡ ብሎ ፡ ሳይጠ ይቅ ፡ አይቀርም ። እሳቸውም ፡ ብቸኝነት ፡ ስላጠቃ ቸው ፡ በደስታ ፡ ይተዋወቁታል ።

በእለፉት ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ነገ ሩ ፡ ሁሉ ፡ ተሩጠነ ። ልዕልት ፡ ሚሪ ፡ በጣ ሙን ፡ ጠላችኝ ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ አሽሙር ፡ ለበስ ፡ የሆነ ፡ የሙገሳ ፡ ቃላት ፡ ሠንዝራብኛለች ። እኔን ፡ የመሰሉ ፡ ከመኳንንትና ፡ ከመሳፍንት ፡ ጋራ ፡ የምውል ፡ በፔተርበርግ ፡ ካሉት ፡ ከአጐታ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ቷ ፡ ቤት ፡ የነበረው ፡ ቩርነር ፡ ሁኔታው ፡ የድራማ ፡ መሰል ፡ እንደነበረ ፡ አወራኝ ። ልዕልቲቷ ፡ ልትወነጅለኝ ፡ መፈለጓ ፡ ገባኝ ። እንዲያውም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ምሳና ፡ እራት ፡ የበሉ ፡ ሁለት ፡ መኰንኖች ፡ ከእሷ ፡ ጋራ ፡ ቁመው ፡ በተቆጣ ፡ መልክ ፡ ሰላም ፡ ሲሉኝ ፡ አይቼ ፡ ተገረምሁ ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ሰሞኑን ፡ ግራ ፡ የገባ ፡ ሁኔታ ፡ ይታይበታል ። ሁለት ፡ እጅቹን ፡ ወደ ኋላው ፡ አጣምሮ ፡ ማንንም ፡ ሳያናግር ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይንጐራደዳል ። እግሩም ፡ ከመዳኑም ፡ ሌላ ፡ የሚያንከሰው ፡ ለአመል ፡ ነው ። ከእናቷ ፡ ልዕልት ፡ ጋራ ፡ ለመተዋወቅና ፡ ለወጣቷ ፡ ልጃቸውም ፡ የሙገሳ ፡ ቃላት ፡ ለመደርደር ፡ አንድ ፡ አጋጣሚ ፡ አግኝቷል ። ልዕልት ፡ ሚሪ ፡ በሙገሳው ፡ የተቆጣች ፡ እትመስልም ። እንዲያውም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲገናኙ ፡ እጅ ፡ ሲነሳት ፡ አፃፋውን ፡ በፈገግታ ፡ ትመልስለታለች ።

ትናንትና ፡ ሰንገናኝ ፡ « እነሊጐቭስካያን ፡ ለመተዋወቅ ፡ በእርግጥ ፡ አትፈልግም?» ብሎ ፡ ጠየቀኝ ።

« በእርግጥ ፡ አልፈልግም ፡» አልሁት ።

« ከፀበሉ ፡ ካለው ፡ የተሻለው ፡ ቤተና ፡ የከተማዋ ፡ ፈዋ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰበሰቡት ፡ እዚያ ፡ ነው ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

« በእውነቱ ፡ ወዳጄ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ሰልችቶኛል ፤ የነዋሪዎችን ፡ አታንሳው ። እንተ ፡ ለመሆኑ ፡ እቤታቸው ፡ ትሔዳለህ?»

« እስካሁን ፡ አልሔድሁም ። አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ልዕልቲቷን ፡ እንጋግራአታለሁ ። ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ቤታችሁ ፡ ልምጣ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ያሳፍራል ። ትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ማዕረግ ፡ ቢጤ ፡ እንኳ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ ግድየለም ፡ ነበር ።»

« ውድ ፡ ወዳጄ ፤ እንዲሁ ፡ እንዳለህ ፡ ተፈላጊ ፡ ሰው ፡ ነህ ። ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ ልትጠቀምበት ፡ አልቻልህም ። የአንድ ፡ ወታደር ፡ ወፍራም ፡ ኮት ፡ በእንዲት ፡ ስሜት ፡ ንቁ ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ጀግና ፡ አድርጐ ፡ እንደሚያሳይ ፡ አታውቅም?»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በመሸኩርመም ፡ ስቆ ፡ « ምን ፡ ትቀልዳለህ?» አለኝ ።

« ልዕልቲቷ ፡ አንተን ፡ እንዳፈቀረችህ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡» ብዬ ፡ ከንፈሩ ፡ እስኪጀሮ ፡ ግንዱ ፡ ግልጥጥ ፡ እንደገና ፡ ኩርፍ ፡ አለ ።

እይ ፡ ራስ ፡ ወዳድነት! እርኪሜዲስ ፡ በራስ ፡ ወዳድነት ፡ ነበር ፡ ዓለምን ፡ በውሸል ፡ ከፍ ፡ አድርጐ ፡ ለማንሳት ፡ የፈለገው ።

የተናደደ ፡ መስሎ ፡ « እንተ ፡ ሁልጊዜ ፡ ታሾፋለህ ። እርሷ ፡ እንኳን ፡ እኔን ፡ ልትወደኝ ፡ ተርቱ ፡ በደምብም ፡ እታውቀኝም ።»

«ታዲያ ፡ ምኑ ፡ ያስገርማል? ሴቶች ፡ የሚወዱት ፡ ሁልጊዜ ፡ የማያውቁትን ፡ ሰው ፡ ነው ።»

«እኔ ፡ እኮ ፡ በእውነቱ ፡ እሷን ፡ ለማስደሰት ፡ ስል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጥሬ ፡ አላውቅም ። ፍላጐቴና ፡ ምኞቴ ፡ ከደህና ፡ ቤተሰብ ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅ ፡ ስለሆነ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተስፋ ፡ ያለቦታው ፡ ነው ... ለእናንተም ፡ የፔቴርቡርግ ፡ ሴት ፡ ማራኪዎች ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ ሌላ ፡ ነው ። ሴቶችን ፡ አትኩረው ፡ ስትመለከቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍቅር ፡ ይወድቃሉ ። በነገራችን ፡ ላይ ፡ ፔቾሪን ፤ ወጣቷ ፡ ልዕልት ፡ ስለአንተ ፡ ማንሳቷን ፡ ሰምተሃል?»

«እንዴት? ካሁኑ ፡ ስለእኔ ፡ አንስታ ፡ ላንተ ፡ አወራችህ?»

«ምንም ፡ የሚያስፈነጥዝ ፡ ነገር ፡ የለም ። አንድ ፡ ቀን ፡ ፀበሉ ፡ አጠገብ ፡ በድንገት ፡ ወሬ ፡ ጀመርን ። ሁለት ፡ ቃል ፡ ሰንዝራ ፡ ለሶስተኛው ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችኝ ፤ 'ያ ፡ ማነው ፡ አስተያየቱ ፡ ደስ ፡ የማይል ፤ ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ያን ፡ ቀን ...' ብላ ፡ የነበረው ፡ ሁኔታ ፡ ትዝ ፡ ብሏት ፡ ስትሽኮረመም ፤ 'ቀኑን ፡ መጥቀስ ፡ አያስፈልግም ። ያ ፡ ቀን ፡ እኔ ፡ ለዘላለም ፡ አልረሳውም' ፡ ብዬ ፡ ሐሳቧን ፡ ጨረስሁት ። ወዳጄ ፡ ፔቾሪን ፤ እንኳን ፡ ደስ ፡ አለህ ፡ አልልህም ። ስለአንተ ፡ ያላት ፡ አስተሳሰብ ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ ነው ። ሚሪ ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ሴት ፡ ስለሆነች ፡ ይህ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ።»

እንደግሩሽኒትስኪይ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ አንዲት ፡ ሰላ ፡ ትንሽ ፡ ደስ ፡ ካለቻቸው ፡ የእኔ ፡ ሚሪ ፡ የእኔ ፡ ሶፊያ ፡ እያሉ ፡ መናገር ፡ ይወዳሉ ።

ፊቴን ፡ ኮስተር ፡ አድርጌም ፡ የሚከተለውን ፡ መለስሁለት ፤

«እውነትም ፤ መልከ ፡ መልካም ፡ ናት ፤ ግን ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ተጠንቀቅ ። የሩሲያ ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚማረኩት ፡ ለመንፈስ ፡ ፍቅር ፡ እንጅ ፡ ለትዳር ፡ አይደለም ። መንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ ደግሞ ፡ ከሁሉ ፡ የከፋ ፡ አደገኛ ፡ ነው ። እንደምገምተው ፡ ልዕልቲቷም ፡ ለጊዜው ፡ ለመደሰት ፡ ከሚፈልጉ ፡ ሴቶች ፡ መካከል ፡ እንዷ ፡ ትመስለኛለች ። ከአንተ ፡ ጋር ፡ ሆና ፡ ለሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ከሰለቻት ፡ ያንተ ፡ ጉዳይ ፡ አከተመ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዝም ፡ ታህ ፡ ስለአንተ ፡ እንድታልም ፡ ሊያደርጋት ፡ ይገባል ። እነጋገርህ ፡ ደግሞ ፡ ዘወትር ፡ እንድትጓጓ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ። ዘወትር ፡ ከአንተ ፡ አንዳች ፡ የምትጠብቀው ፡ ነገር ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ ለእንተ ፡ ስትል ፡ የጎብረተሰብን ፡ አስተያየት ፡ አስር ፡ ጊዜ ፡ ታውግዘዋለች ። ማስዋዕትነትም ፡ ብላ ፡ ትቆጥረዋለች ። ለዚህም ፡ የምትሰጥህ ፡ እጸፋ ፡ መ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልስ ፡ እንተን ፡ አሰቃይታ ፡ ከነአካቴው ፡ ዓይ
ኑን ፡ አልይ ፡ ትልሃለች ። የበላይነቱን ፡ ሥል
ጣን ፡ ይዘህ ፡ በእሷ ፡ ላይ ፡ ተፅእኖ ፡ ካላሳ
ደርህ ፡ እንዴም ፡ ብትስምህ ፡ ለሁለተኛው ፡ እ
ድል ፡ አይኖርህም ። ለዓመት ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡
በፍቅር ፡ ልትከንፉ ፡ ትችላላችሁ ። በመጨረ
ሻም ፡ የእናቱን ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰምታ ፡ አስቀያሚ ፡
ፍጡር ፡ አግብታ ፡ ታርፍልሃለች ። ያኔ ፡ ግን ፡
በኑሮዋ ፡ እንዳልተደሰተችና ፡ በሕይወቷም ፡
ሙሉ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንዳልወ
ደደች ፡ ትነግርሃለች ። ያም ፡ ሰው ፤ አንተ ፡
ነህ ፤ ሆኖም ፡ ከዚያ ፡ ከወደደችው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡
አብራ ፡ ለመኖር ፡ የለበሰው ፡ የወታደር ፡ ከባድ ፡
ኮት ፡ አጥር ፡ ሆኖ ፡ ለየን ፡ ብትልም ፤ በዚያ ፡
ከባድ ፡ ኮት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ልብ ፡ ጨዋና ፡ ኩ
ራ ፡ መሆኑን ፡ አትክድም ።»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ጠረጴዛውን ፡ በጡጫዉ ፡ መግሮ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይንጐራደድ ፡ ገባ ።

በልቤ ፡ ውስጥ ፡ በሳት ፡ እየተንፈተፈትሁ ፤ እንድ ፡ ሁለቴ ፡ ፈገግ ፡ አልሁ ። ያሚኑቱ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ አላየኝም ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ በእውነት ፡ ሳትር ፡ እንደያዘው ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ በሚነገረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማመን ፡ ጀመረ ። እንዲያውም ፡ በአካባቢው ፡ እንጥረኛ ፡ የተሠራ ፡ የብር ፡ ተለበት ፡

እድርጐ ፡ ስላየሁ ፤ ጥርጣሬዬን ፡ ይበልጥ ፡ አጠነከረው ። ተለበቱን ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ስመለከት ፡ ሚሪ ፡ የሚል ፡ ስምና ፡ ዝነኛ ፡ የወበል ፡ ብርሞቆ ፡ ወድቆ ፡ አንስታ ፡ ያቀበለችበት ፡ ቀን ፡ ተቀርጸበት ፡ አየሁ ። ይህንንም ፡ ማየቴን ፡ አልገለጽሁለትም ። ምክንያቱም ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚያደርግልኝን ፡ ኑዛዜ ፡ ልቀንስበት ፡ አልፈለግሁም ። በራሱም ፡ ፈቃድ ፡ አምኖኝ ፡ ምስጢረኛው ፡ እንድሆን ፡ አፈልጋለሁ ። ያኔ ፡ ግን ፡ በእርግጥ ፡ ከልቤ ፡ መደሰት ፡ እጀምራለሁ ...

. . . . . .

ዛሬ ፡ የተነሣሁት ፡ እረፈድ ፡ ብዬ ፡ ነው ፤ በወበሉ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። ቀኑ ፡ ሞቃታማ ፡ ነበር ። ቁንጮዬቸው ፡ በበረዶው ፡ ከለበሱት ፡ ተራራዎች ፡ እያፈገፈገ ፡ የሚመጣው ፡ ደመና ፡ በቅርቡ ፡ ጠሮ ፡ እንደሚወርድ ፡ ያበስራል ። በማሹክ ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ጢስ ፡ ከጠፋ ፡ ትንታግ ፡ ላይ ፡ የወጣ ፡ ይመስላል ። የሚያንጃብቡት ፡ ጉሞች ፡ የተራራውን ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ እንደእባብ ፡ ይጥመዘግዛሉ ። የአካባቢው ፡ አየር ፡ በመብረቅ ፡ ብልጭልታ ፡ ተከበበ ። በመይን ፡ ተከል ፡ የተከበበችዉን ፡ መንገድ ፡ ያገኙ ፡ መደዋሻዋ ፡ እመራው ። ሰውነቴን ፡ ቀዝኖል ። ዶክተሩ ፡ ያወራኝ ፡ ከጉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንጪ ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ የሳመቻት ፡ ምልክት ፡ ያለባት ፡ ሴትዮ ፡ ትገ ፡ ብላኝ ፤ ስለእሷ ፡ ሳስብ ፡ ቆየሁ ። «ምንድነው ፡ ከዚህ ፡ የምትሠራው፣ ማናትስ? እሷስ ፡ ናት ፡ ብዬ ፡ ለምን ፡ እሰብሁ፣ ለምንስ ፡ እርግጠኛ ፡ ሆንሁ? ጉንጫቸው ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ የሳመቻቸው ፡ ሴቶች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ...» ይህን ፡ በሐሳቤ ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ዋሻዋ ፡ ጋ ፡ ደረስሁ ። በዚያም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ እግድም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ አገኘሁ ። ከሠሌን ፡ የተሠራ ፡ ባርኔጣ ፡ ደፍታለች ። ጥቁር ፡ ሻሽ ፡ በጫንቃዋ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጋለች ። አንገትዋን ፡ ጉንበስ ፡ አድርጋው ፡ ስለነበር ፤ ባርኔጣዋ ፡ ፊቷን ፡ ሸፍኗታል ። የተመስጦ ፡ ሐሳቧን ፡ ላለማቋረጥ ፡ ብዬ ፡ ዘወር ፡ ልል ፡ ስል ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አየችኝ ።

ሳላስበው ፡ በድንገት ፡ ከአፌ ፤ «ቬራ ፡» የሚል ፡ ቃል ፡ አፈተለከኝ ።

ተደናገጠች ። ፊቷም ፡ ገረጣ ።

«እዚህ ፡ እንደሆኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ነበርሁ ፡» አለችኝ ።

አጠገቧ ፡ ሔጀም ፡ እጆቿን ፡ ይገር ፡ ቁጭ ፡ አልሁ ። ያን ፡ ለሰላሳ ፡ ድምፅሞን ፡ እንደገና ፡ ስሰማ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የረሳሁት ፡ ስሚት ፡ አገረሸብኝ ። እነዘያም ፡ ጥልት ፡ ዓይኖችዋ ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ ዓይኔን ፡ ይመለከቱት ፡ ጀመር ።

አስተያየቷም ፡ ጥርጣሬ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ እኔንም ፡ ጥፋተኛ ፡ ለማድረግ ፡ የተሰነዘረ ፡ ይመስላል ።

«ከተገናኘን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆነን?» አልኋት ።

«እዎ ። ሁለታችንም ፡ በጣም ፡ ተቀይረናል ።»

«ከእንግዲህ ፡ አትወጂኝም ፡ ማለት ፡ ነው ።»

«ባለትዳር ፡ ነኝ ።»

«እንደገና? ከጥቂት ፡ ዓመታትም ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። ሆኖም ...»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እጅዋን ፡ መንችጋ ፡ ከእጅቼ ፡ አላቀቀችው ። ጉንጮቿም ፡ ፍም ፡ መሰሉ ።

«ከሁለተኛው ፡ ባልሽ ፡ ፍቅር ፡ ያዘሽ ፡ ልበል?»

ምንም ፡ ዓይነት ፡ መልስ ፡ ሳትሰጠኝ ፤ ፊቷን ፡ ከእኔ ፡ አዞረችው ።

«ወይስ ፡ ቀናተኛ ፡ ነው?»

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጭጭ ፡ አለችኝ ።

«እዲሱ ፡ ባልሽ ፡ መልከ ፡ መልካምና ፡ ከበርቴ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ ። የምትፈሪውም ...» መልኳን ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ ሳያት ፡ ተደናግጣለች ። ጥርጣሬ ፡ ከገጿ ይነበባል ። ዓይኖቿም ፡ በእንባ ፡ አቅረዋል ።

«እኔን ፡ በማለታየት ፡ የምታገኘውን ፡ ደስታ ፡ አስቲ ፡ ንገረኝ፣ በእውነት ፡ ልጠላህ ፡ ይገባል ። ከተገናኘንበት ፡ ጀምሮ ፡ እስከዛሬ ፡ ለእኔ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰጠኸኝ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ሥቃይ ፡ ብቻ ፡ ነው ...» ብላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተናገረች ። ስትናገር ፡ ድም ፅዋ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይላል ። ወዲያውም ፡ እንገ ቷን ፡ ዘንፈል ፡ አድርጋ ፡ ከደረቴ ፡ አስደገፈ ችው ።

«ምናልባትም ፡ የምትወጂኝ ፡ ለዚህ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ደስታ ፡ በቶሎ ፡ ይረሳል ። ሐዘን ፡ ግን ፡ አይረሳም ፡» ብዬ ፡ እገምታለሁ ።

ከደረቴ ፡ ጥብቅ ፡ አድርጌ ፡ አቅፌ ፡ ይዣት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ቆየን ። በኋላም ፡ ከንፈሮቻ ችን ፡ ተገናኙ ፤ አሳሳማችን ፡ ጉጉትና ፡ ስስት ፡ የሞላበት ፡ ነበር ። እጆቿ ፡ ልክ ፡ እንደበረዶ ፡ ሲቀዘቅዙ ፣ ጭንቅላቷ ፡ እንደእሳት ፡ ያቃጥላል ። ከዚያም ፡ በወረቀት ፡ ቢጻፍ ፡ ትርጉም ፡ የማ ይሰጥ ፡ የናፍቆት ፡ ውይይት ፡ ከፈትን ። እን ዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ውይይት ፡ መደገምም ፡ ሆነ ፡ ማስታወስ ፡ አይቻልም ። እንደኢጣልያ ፡ አሬራ ፡ የቃላት ፡ ትርጉም ፡ ፍችም ፡ በድምፅ ፡ ይሞላል ።

ከባሏ ፡ ጋር ፡ እንዳልተዋወቅ ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳቡ ፡ አደረገች ። ባሏም ፡ ያኔ ፡ በአደባባይ ፡ ያየሁት ፡ ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ያገባችው ም ፤ ለልጅዋ ፡ ብላ ፡ ነው ። ኩሽር ፡ ነው ። የቁርጥማት ፡ በሽታም ፡ አለበት ። በሰውየው ፡ ላይ ፡ ስላለኝ ፡ አበሳጋየት ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ለመሰንዘር ፡ አልፈለግሁም ። እንደአባት ፡ ፣ ታ ከብረዋለች ፤ እንደባል ፡ ግን ፡ ታታልለዋለች ...

የሰው ፡ ልብ ፡ የሚገርም ፡ ነገር ፡ ነው ። በተ ለያጣ ፡ የሴት!

የቪራ ፡ ባል ፡ ሴሚየን ፡ ቫሲልዬቪች ፡ የልዕ ልት ፡ ሊንቭስካያ ፡ የሩቅ ፡ ዘመድ ፡ ነው ። የሚኖሩበትም ፡ ጉን ፡ ለጉን ፡ ስለሆነ ፡ ቪራ ፡ በየጊዜው ፡ ወደልዕልት ፡ ቤት ፡ ጉራ ፡ ትላለች ። ወደእነሊንቭስካያም ፡ ቤት ፡ በየጊዜው ፡ ሄጂ ፡ ለመተዋወቅ ፡ ቃል ፡ ገባሁላት ። በሷ ፡ ላይ ፡ ሰዎቹ ፡ ጥርጣሬ ፡ እንዳያድርባቸው ፡ እዚያም ፡ ውይይቴ ፡ ሁሉ ፡ ከልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ጋር ፡ እንደ ሚሆን ፡ ተስማማን ። ይህን ፡ ከእኔ ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ የማይቀር ፡ ስለሆነ ፡ ጥሩ ፡ጊዜ ፡ አሳልፉ ለሁ ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ...

በእውነትም ፡ ጥሩ ፡ ጊዜ ፡ ይኖረኛል ። ሰዎች ፡ ደስታን ፡ ብቻ ፡ የሚሹበትና ፤ ከእንድ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ በመፋቀር ፡ ፍስሃ ፡ የሚያ ገኙ ፡ የሚመስላቸውን ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ አል ፈዋለሁ ። አሁን ፡ እኔ ፡ የምፈልገው ፡ መው ደድ ፡ ሳይሆን ፡ ለዛ ፡ ብሎ ፡ መወደድን ፡ ነው ። ከእነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ከእንዷ ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ቋሚ ፡ መጻጅነት ፡ እንዲኖረኝ ፡ እሻለሁ ። የሚ ያሳዝን ፡ ልባዊ ፡ ስሜት ፡ ነው!

ከሁሉ ፡ የሚገርመኝ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ የምወ ዳት ፡ ሴት ፡ ምርኩኛ ፡ ሁኔ ፡ አለማወቁ ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ የመውደድ ፡ ጥረት ፡ ሳላደርግ ፡ ማርኪያትሁ ፡ እግኛለሁ ። ለምን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሴት ፡ መውደድ ፡ አለመውደዴን ፡ አልጠየቀ
ችኝም ። ሆኖም ፡ እንደድሮው ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡
አመነችኝ ። እኔም ፡ እሷን ፡ ለማታለል ፡ ፈጽሞ ፡
አልፈልግም ። በዓለም ፡ ካሉት ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡
ለማታለል ፡ የማልደፍረው ፡ እሷን ፡ ብቻ ፡
ነው ። በቅርቡ ፡ እንደምንለያይ ፡ አውቃለሁ ።
ይህም ፡ መለያየት ፡ የዘለዓለም ፡ እንደሚሆን ፡
እገምታለሁ ። ሁለታችንም ፡ ወደመቃብራችን ፡
የምናዘግመው ፡ በተለያየ ፡ ጉዳና ፡ ነው ።
ይህም ፡ ሆኖ ፡ ስለእሷ ፡ ያለኝን ፡ ትዝታ ፡ ከልቤ ፡
አልፍቀውም ። ስለዚህም ፡ ሁልጊዜ ፡ እንግራ
ታለሁ ። በአጭ ፡ አምንሃለሁ ፡ ብላ ፡ እትቀበ
ለኝ ፡ እንጂ ፡ በልቧ ፡ እንደምታምነኝ ፡ እርግ
ጠኛ ፡ ነኝ ።

በመጨረሻ ፡ ተለያየን ። ከነበርንበት ፡ ቦታ ፡
ቁሚ ፡ ባርኔጣዋ ፡ በቁጥቋጦውና ፡ በቋጮ ፡
እየተሽለከለከ ፡ ሲሄድ ፡ በዓይናቼ ፡ ሸኘ
ኋት ። ልክ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ተገናኝተን ፡
ስንለያይ ፡ እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ አሁንም ፡ ልቤ ፡
በሐዘን ፡ ተነሣተረ ። ይህም ፡ ውኔታ ፡ ያረካኛል ።
ይህ ፡ ስሜት ፡ ወጣትነቴ ፡ እንደገና ፡ መመለሱን ፡
ሊያሳየኝ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ማለፍን ፡ ሊያበስ
ረኝ፣ ቁመናዬን ፡ አይቶ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
መገመቱ ፡ ያስቃል ፡ ፊቴ ፡ የገረጣ ፡ እንጅ ፡
ወዙ ፡ ገና ፡ አልጠፋም ። እጆቼና ፡ እግሮቼ ፡
ተንቀሳቅሶችና ፡ ጠንካሮች ፡ ናችው ። ውጉራ ፡

ይሆን? ምናልባትም ፡ ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡
ስለማልሰጠው ፡ ከእጆቻችን ፡ ያመልጠናል ፡
ብለው ፡ ስለሚሰጉ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ አካላቱ ፡
ጠንካራ ፡ በመሆኔ ፡ ይሆን? ካለዚያስ ፡ እስ
ካሁን ፡ መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ሴት ፡ ስላላጋጠ
መኝ ፡ ነው?

የራሳቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ ያላቸውን ፡ ሴ
ቶች ፡ በእውነት ፡ ከሆነ ፡ አልወዳቸውም ።
ለእነሱም ፡ ይሆን ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ!..

ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ!.. አዎ! አንድ ፡ ጊዜ ፡
ብቻ ፡ መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ሴት ፡ አፍቅሬ ፤
ልቧን ፡ መግረክ ፡ ተስኖኝ ፡ ነበር ፡ ... ከአ
ነአካቴው ፡ ጠላት ፡ ሆነን ፡ ተለያየን ። ያኔ ፡
የተገናኘነው ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡
ቢሆን ፡ ኖሮ ፤ ግን ፡ መለያየታችን ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡
በያዘ ፡ ነበር ።

ቬራ ፡ ታማለች ። በጣም ፡ ታማለች ። መታመ
ሟን ፡ ግን ፡ ለማመን ፡ አትፈልግም ። በሽታዋ ፡
የሳምባ ፡ ወይም ፡ fièvre lente የተባለው ፡ በሽታ ፡
ሳያሠጋ ፡ አይቀርም ። Fièvre lente የሩሲ
ያ ፡ በሽታ ፡ ስላልሆነ ፡ በሩሲያ ፡ ቋንቋ ፡ ስም ፡
የለውም ።

በጥሻዋ ፡ ውስጥ ፡ ቁሜ ፡ እንዳልን ፡ ጠሮ ፡
ያሠን ፡ አኩል ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ አሰቆየን ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ታማኟ ፡ እንዴሠን ፡ አላስማለ
ችኝም ። ከተለያየንም ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሌላ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ችርችም ፡ ያለ ፡ ከርዳዳ ፡ ነው ። እሳት ፡ የለበሱ ፡ ዓይኖች ፡ አሉኝ ። ደመ ፡ ፍልም ፡ ነኝ ።

ወደቤቴም ፡ ተመልሼ ፡ በፈረሴ ፡ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ያንን ፡ ሜዳ ፡ ተያያዝሁት ። በደፋር ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብሎ ፡ ለረጃጅም ፡ የሳር ፡ ዳዋ ፡ እየጣሉ ፡ በበረሃ ፡ ነፋስ ፡ እያስመቱ ፡ እየሩንም ፡ እየሳቡ ፡ እየቀረቡ ፡ እየቀረቡ ፡ በሄዱ ፡ ቁጥር ፡ ግልጽ ፡ እየሆነ ፡ የሚሄደውን ፡ ደብዛዛ ፡ ነገር ፡ እያዩ ፡ መጋለቡ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሐዘን ፡ ወይም ፡ ልብን ፡ ቢያስጨንቅም ፤ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ መንፈስን ፡ ቢረብሽም ፤ የአካላት ፡ ድክመት ፡ ከደረሰ ፡ በአንጐል ፡ ውስጥ ፡ የተጠራቀመውን ፡ ሐሳብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያሚሚና ፡ ሰላም ፡ ያሰፍንበታል ። ከደቡብ ፡ የሚመጣው ፡ በፀሐይ ፡ ጨረር ፡ የሚያብረቀርቀውን ፡ በዛፍ ፡ የተረበጠውን ፡ ተራራ ፡ ስመለከት ፤ የጠራውን ፡ ሰማይ ፡ ደመና ፡ ሲሸፍነው ፤ ከቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ቋጥኝ ፡ እየዘለለ ፡ የሚወርደውን ፡ የወንዝ ፡ ጩኸት ፡ ስሰማ ፡ የማይረሳኝ ፡ የሴት ፡ ዓይን ፡ የለም ።

በማማ ፡ ላይ ፡ የቆሙት ፡ የካዛክ ፡ ዘበኞች ፡ ያለምንም ፡ ዓላማ ፡ በፈረስ ፡ ሲጋልብ ፡ ሲያዩኝ ፡ ሳይገረሙ ፡ አያቀሩም ። በአለባበሴም ፡ የቹር ኬስ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያገምቱ ፡ ይሆናል ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ የቹርኬስ ፡ ልብስ ፡ ለብሼ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ስወጣ ፡ ቹርኬሰን ፡ በጣም ፡ እንደ

ምመስል ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነግረውኛል ። በውነቱ ፡ ለዚህ ፡ አባባል ፡ ተስማሚ ፡ ነኝ ። ውድነት ፡ ያላቸው ፡ መሣርያዎች ፡ በተራ ፡ ነገር ፡ ተይዘዋል ። የባርኔጣዬ ፡ ፀጉር ፡ እረጅምም ፡ አጭርም ፡ አይደለም ። ከለስላሳ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራው ፡ ቦት ፡ ጫማዬ ፡ ከቢሽሜቴና ፡ ከቼርኬስ ፡ ጥቁር ፡ ቡናማ ፡ ኩቲ ፡ ጋራ ፡ ተስማምቷል ። እንደተራራማ ፡ ሰዎች ፡ ከፈረስ ፡ ላይ ፡ ዘልዬ ፡ ጉብ ፡ ለማለት ፡ ብዙ ፡ ልምምድ ፡ አድርጌያለሁ ። ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ እንደኮከዝ ፡ ሰው ፡ ፈረስ ፡ ትጋልባለህ ፡ የሚል ፡ ሙገሳ ፡ ሳገኝ ፡ ነው ። ለብቻ ፡ መጋለቡ ፡ ስለሚሰለች ፡ ሶስት ፡ ጓደኞቼን ፡ ለግልቢያ ፡ እጋብዛለሁ ። ሆኖም ፡ ጓደኞቼ ፡ ደስታቸው ፡ ፈረሶቼን ፡ መውሰድ ፡ እንጂ ፡ አብረውኝ ፡ ጋልበው ፡ እያውቁም ። የራት ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ብሎኝ ፡ሳስታውስ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ፈረሴ ፡ ፈጽሞ ፡ ደክሞ ፡ ነበር ። ፀጠል፡ተኞች ፡ የሚንሸራሸሩበትን ፡ ከፒቲኮርስነ ፡ መደጀርመን ፡ ስፈር ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ይገር ፡ መደቤቱ ፡ ሐድኩ ። በጐጅታዎች ፡ የተሞመዘመዘ ፡ መንገድ ፡ በረጃጅም ፡ ግሮች ፡ ላይ ፡ እያፏጨ ፡ መደሚሽከላከሉት ፡ ትናንሽ ፡ ጅራቶች ፡ ያደርሳል ። በአካባቢው ፡ የቢሽቱ ፡ የዝሜኢናያ ፡ የገርሌዝናያና ፡ የሊሳያ ፡ ተራሮች ፡ ሰማያዊ ፡ ደልዳላ ፡ ጫፎችሙ ፡ ይታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያል ። ከነዚህ ፡ ትናንሽ ፡ ጅራቶች ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ፈረሴን ፡ ውኃ ፡ ሳጠጣ ፡ ያሸበረቁ ፡ ፈረሰኞች ፡ እየጋለቡ ፡ ሲመጡ ፡ አየሁ ። ከእነሱም ፡ መሐከል ፡ ጥቁርና ፡ ሰማያዊ ፡ ድብልቅልቅ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ወንዶች ፡ ይታያሉ ። ግሩሽኒትስኪይና ፡ ልዕልት ፡ ሚሪም ፡ የፊት ፡ መሪዎች ፡ ሁነው ፡ ወደጅራቱ ፡ ደረሱ ።

የመጡት ፡ ወይዛዝርት ፡ ቼርኪሶች ፡ በቀን ፡ ሴቶችን ፡ ይጠልፋሉ ፡ የሚባለውን ፡ እንጋገር ፡ ከልብ ፡ ያምኑታል ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ በዚያ ፡ በትልቁ ፡ የወታደር ፡ ካፖርት ፡ ላይ ፡ ጐራዴዋንና ፡ ሁለት ፡ ሽጉጡን ፡ የታጠቀው ፡ ለዚህ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ሁኔታ ፡ በጣም ፡ የሚያስቅ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ከእነሱ ፡ ቢደብቀኝም ፡ በቅጠሎች ፡ አሾልኬ ፡ የሚያደርጉትን ፡ በሙሉ ፡ ከማየት ፡ አልተግደደሁም ። በፈታቸው ፡ ላይ ፡ እንዳነበብሁት ፡ የሚያወሩት ፡ ስለፍቅር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ ። በመጨረሻም ፡ ወደቁልቁለቱ ፡ ጠጋ ፡ አሉ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ የልዕልቷን ፡ ፈረስ ፡ ልጓም ፡ ጨብጦ ፡ ይሄዳል ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ የውይይታቸውን ፡ የመጨረሻ ፡ ንግግር ፡ ለመስማት ፡ ቻልሁ ።

«ታድያ ፡ የቀረው ፡ እድሜዎን ፡ በካውካሰስ ፡ ውስጥ ፡ ለማሳለፍ ፡ ይፈልጋሉ ፡ ማለት ፡ ነው?» ስትል ፡ ልዕልቷ ፡ ጠየቀቻው ።

«ለእኔ ፡ ሩሲያ ፡ ምንድናት? ከእኔ ፡ የከበሩ ፡ በሽ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ሰዎች ፡ የማያስጠጉኝ ፡ አገር ፡ እኮ ፡ ናት ። እዚህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ለምሳሌ ፡ የለበስሁት ፡ ወፍራም ፡ የተራ ፡ ወታደር ፡ ካፖርት ፡ ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅ ፡ ምንም ፡ አላገደኝም ...»

«እንዲያውም ...» ብላ ፡ እንደማፈር ፡ አለች ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ የተደሰተ ፡ ይመስላል ። ከዚያም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ።

«በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሕይወቴ ፡ በእነዚህ ፡ አረመኔዎችና ፡ ወንበዴዎች ፡ የንዴት ፡ ፍጪት ፡ ታጥራ ፡ ያለመሰልችት ፡ ሳላስበው ፡ በፍጥነት ፡ ትገባደዳለች ። ፈጣሪዬማ ፡ በየዓመቱ ፡ መልካም ፡ ፈገግታ ፡ የምትጋብዘኝ ፡ ሴት ፡ ቢልክልኝ ፡ ለምሳሌም ፡ እንደ ...»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እየተጠጉ ፡ እኔን ፡ ከሸሸገኝ ፡ ጉድጓድ ፡ ደረሱ ። እኔም ፡ ፈረሴን ፡ ገርፌ ፡ ከነበርሁበት ፡ ቦታ ፡ ፈትለክ ፡ ብዬ ፡ ሔድሁ ።

«Mon dieu, un circassien!..*» ብላ ፡ ልዕልቷ ፡ በድንጋጤ ፡ ባረቀች ።

እኔ ፡ ከድንጋጤዋ ፡ ላረጋጋት ፡ ብዬ ፡ እንጉርን ፡ ያፋ ፡ እድርጌ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መለስሁላት ፡

---

* እግዚኦ! ቼርኪስ ፡ ነሞ!

t.me/OLDBOOKSPDF

«Ne craignez rien, madame, je ne suis pas plus dangereux que votre cavalier.»*

ልዕልቲ ፡ የምትይዘው ፡ የምትጨብጠው ፡ አጣች ። ግን ፡ ለምን ፡ ቢሆን? ስለተሳሳተች ፡ ወይስ ፡ መልሴ ፡ ስላላስደሰታት? ያስቆጣት ፤ ሁለተኛው ፡ ምክንያት ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ቆሞ ፡ ገላመጠኝ ።

ያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከምሽቱ ፡ በአምስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ወደአደባባይ ፡ የሚያመራውን ፡ ዛፎች ፡ የተተከሉበት ፡ መንገድ ፡ ድጅ ፡ መንሸራሸር ፡ ጀመርሁ ። ከተማው ፡ በሙሉ ፡ ድብን ፡ ባለ ፡ እንቅልፍ ፡ ተውጧል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በአንድ ፡ አንድ ፡ መስኮቶች ፡ ላይ ፡ የመብራት ፡ ብርሃን ፡ ይታያል ። በሶስቱ ፡ ማዕዘን ፡ በማ ሹክ ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ደመና ፡ ጥላ ፡ አርፎበታል ። ጨረቃ ፡ በምሥራቅ ፡ ብት ፡ ማለት ፡ ጀምራለች ። ከሩቁ ፡ የበረዶ ፡ ባርኔጣ ፡ የደኑ ፡ ተራራዎች ፡ ብራማ ፡ ብርሃን ፡ ያንፀባርቃሉ ። የዘበኞቹ ፡ ድምፅ ፡ ከተለተቀው ፡ ሞቃታማ ፡ ፀበል ፡ ጋር ፡ ያስተጋባል ። የፈረሶች ፡ ኩቲ ፡ በናጋዮች ፡ ጋራና ፡ በታታር ፡ እንጉርጉሮ ፡ ታጅቦ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይሰማል ።

---

* አይሥጉ ፡ እሜቴ ፡ ከርስም ፡ አጀብ ፡ የበለጠ ፡ አደገኛ ፡ አያደለሁም ።

በአጠገቤ ፡ ባለው ፡ አግድም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ቱሞ ፡ ብዬ ፡ በሐሳብ ፡ ተመሰጥሁ ። የተሰማኝን ፡ ስሜት ፡ የማጋራበት ፡ የወዳጅነት ፡ ውይይት ፡ ቢኖር ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ነበር ... ግን ፡ ከማን ፡ ጋር? ይህን ፡ ጊዜ ፡ ቬራ ፡ ምን ፡ ትሠራለች ፡ ስል ፡ አሰብሁ ። እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡ እጀጀን ፡ ልጨብጥ ፡ ብችል ፡ እንዴት ፡ ጥሩ ፡ ነበር ።

በድንገት ፡ ፈጣንና ፡ ያልተመጣጠነ ፡ ኩቲ ፡ ተሰማኝ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ቢሆን ፡ ይቀላል?.. አዎ ፡ እሱ ፡ ነው ።

«የት ፡ ነበርህ?»

«ልዕልት ፡ ሊጕቭስካያ ፡ ጋ ፡» ብሎ ፡ በኩራት ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ «ሚሪ ፡ ስትዘፍን ፡ እንዴት ፡ ግሩም ፡ ናት!» አለኝ ።

«ስማ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይገባሃል ። ለኔ ፡ መቼም ፡ አንተቲን ፡ እሰጣለሁ ፡ ሚሪ ፡ አንተን ፡ ከማዕረግህ ፡ በትጣት ፡ የወረድህ ፡ እንጂ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ አልመሰልሃትም ።»

«ምናልባት ፡ ታድያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ!» ሲል ፡ በቸልታ ፡ መለሰልኝ ።

«እንዲያው ፡ ነግሩን ፡ እውቀው ፡ ብዬ ፡ ነው ።»

«በጣም ፡ እንዳናደድሃት ፡ ይገባሃል? በእውነቱ ፡ ያደርግኸውን ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ፀያፍ ፡ አድርጋ ፡ ነው ፡ የወሰድችው ፡ አስተዳደግህ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዲያውም ፡ ደስ ፡ እንዲልህ ፡ ከፈለግህ ፡ ልዕልቲን ፡ ይገርት ፡ ለመዞር ፡ እችላለሁ ።»

«ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚሆነው ፡ ገና ፡ ከተናገርህ ፡ አስተድሞ ...»

«በእንተ ፡ እንጋገር ፡ እስክትሰለች ፡ ድረስ ፡ ለጊዜው ፡ እጠብቃለሁ ... ይህና ፡ እሩ ...»

«እኔ ፡ ገና ፡ እዞራለሁ ። እንቅልፍ ፡ እምቢ ፡ ብሎኛል ። ለምን ፡ ወደቡና ፡ ቤት ፡ እንሂድም? ቁማር ፡ ለመጫወትም ፡ ይቻላል ... ዛሬ ፡ የሚያስፈልገኝ ፡ ኃይለኛ ፡ ስሜት ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ነገር ፡ ነው... »

«እንደምትበላ ፡ ፀሎቴ ፡ ነው ...»

ወደቤቴ ፡ ሔድሁ ።

ግንቦት ፡ ፳፩ ።

እነሊጐቭስካያን ፡ ካየኋቸው ፡ እነሆ ፡ ሳምንት ፡ አለፈ ። ከእነሱም ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ አጋጣሚ ፡ በመጠበቅ ፡ ላይ ፡ ነኝ ። ግሩሽኒ ትስኪይ ፡ ልዕልት ፡ ሜሪን ፡ ልክ ፡ እንደጥላ ፡ ይከተላታል ። ንግግራቸውም ፡ ማብቂያ ፡ የለውም ። በእሱ ፡ ንግግር ፡ የምትስለቸው ፡ መቼ ፡ ይሆን ? እናትዮዋም ፡ የሁለቱን ፡ ሁኔታ ፡ ከመጠናቸውም ። ምነኛ ፡ እሙኛዋ ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ። የእናቶች ፡ አስተሳሰብ ፡ ያንዘላላችሁ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ፈገግታ ፡

ጥሩና ፡ ከሰው ፡ ተግባቢ ፡ እንደሆንህ ፡ እሷንም ፡ ለመስደብ ፡ እንዳላደርግህው ፡ ለማስረዳት ፡ ብዙ ፡ ደክሙሁ ። እሷም ፡ ስለራሱ ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ ያለውና ፡ ኩሩ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ታስባለች ።»

«እውነትዋን ፡ ነው ፤ አልተሳሳተችም ። እሷን ፡ ልትከላከላት ፡ ትፈልጋለህ ?»

«ይህንን ፡ መብት ፡ ገና ፡ አላገኘሁም ፤ አዝናለሁ ።»

«አ! ሰውየው ፡ ገና ፡ የወደፊት ፡ ተስፋ ፡ አለው ፡» ብዬ ፡ በልቤ ፡ አሰብሁ ።

«የምትገዳው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ከእንግዲህ ፡ወዲያ ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ በጣም ፡ ያስቸግርሃል ። ያሳዝናል ፤ ያሳዝናል ፤ ካሉት ፡ የጨዋ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነበር ...»

በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ፈገግ ፡ አልሁ ።

«ለእኔ ፡ የጨዋ ፡ ቤት ፡ ብዬ ፡ የምቆጥረው ፡ የራሴን ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡» እያልሁ ፡ እያዛጋሁ ፡ ወደቤቴ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣሁ ።

«ይህም ፡ ሆኖ ፡ ገዳዩ ፡ እንዳሳዘነህ ፡ ማመን ፡ አለብህ ።»

«እሱን ፡ ተወው ። ቁም ፡ ነገር ፡ የለውም ። ከፈለግሁ ፡ ነገ ፡ ማታ ፡ ልዕልታ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ እችላለሁ ...»

«እሱንም ፡ እስቲ ፡ እናያለን ...»

t.me/OLDBOOKSPDF

ልዕልት ፡ ሚሪን ፡ ቅናት ፡ በተሞላበት ፡ በጥ
ላቻ ፡ መልክ ፡ ያይዋት ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡
ጥሩ ፡ አለባበስ ፡ ታውቃለችና! ራሳቸውን ፡
ወይዛዝርት ፡ እድርገው ፡ የሚቆጥሩት ፡ የቀበ
ሌዋ ፡ ሰዎች ፡ ጥላቻቸውን ፡ በልባቸው ፡ እም
ቀው ፡ በአካባቢዋ ፡ ውር ፡ ውር ፡ ሲሉ ፡ ነበር ።
ይህም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ መሆን ፡ የለበትም ።
ሴቶች ፡ ባሉበት ፡ አካባቢ ፡ ሁሉ ፡ የከፍተ
ኛና ፡ የዝቅተኛ ፡ ክፍል ፡ መደብ ፡ ከመቅጽበት ፡
ይለያል ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ውጭ ፡ ከቆሙት ፡
መካከል ፡ ሆኖ ፡ ከመስተዋቱ ፡ ፊቱን ፡ ለጥፎ ፡
ያችን ፡ አምላክዋን ፡ ይመለከታል ። በእጠገ
ቡም ፡ ስታልፍ ፡ እንኳቺን ፡ ሰበር ፡ እድርጋ ፡
ሰላም ፡ ብላው ፡ ሔደች ። እንደጸሐይ ፡ ጮራ ፡
አበራ ... የመጀመሪያው ፡ የፖላንድ ፡ ዳንስ ፡
ነበረ ፡ ከዚያም ፡ እርኪስትራው ፡ የቫልስ ፡
ሙዚቃ ፡ ይጫወት ፡ ገባ ። በመኳንንቶች ፡
በጫማው ፡ ተረከዝ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ብረትም ፡
ከሙዚቃው ፡ ጋር ፡ ያስተጋባ ፡ ጀመር ። እዳራ
ሹም ፡ በዳንስ ፡ ተሽከረከረ ።

ሮዝ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የዶሮ ፡ ላባ ፡ ከሠ
ካች ፡ እንዲት ፡ ረጅም ፡ ሴት ፡ ኋላ ፡ ቆሚያለሁ ።
አለባበሷ ፡ በጀኟኖውና ፡ በጀዠኖው ፡ ከፍለ ፡
ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የሴቶ
ችን ፡ አለባበስ ፡ አስታወሰኝ ። በእንግሊ ፡
ላይ ፡ የወጣው ፡ እጢ ፡ በከፊል ፡ በከፈ ፡

የተሞላበት ፡ አስተያየት ፡ እንድ ፡ ሁለት ፡
ጊዜ ፡ ስትሰነዘርበት ፡ ልብ ፡ ብያለሁ ። ይህም ፡
ሁኔታ ፡ መቀጠል ፡ የለበትም ።

ቬራ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ትላንትና ፡
ወደፀበሉ ፡ ብቅ ፡ አለች ። ከዚያች ፡ ዋሻ ፡
ከተገናኘን ፡ ወዲህ ፡ ከቤት ፡ ወጥታ ፡ አታ
ውቅም ። ከፀበሉ ፡ ወርደን ፡ በብርጭቆአችን ፡
የፀበሉ ፡ ውኃ ፡ እንጎንብሰን ፡ ስንቀዳ ፡ በሹክ
ሹክታ ፡ እንዲህ ፡ አለችኝ ፡

«ወደሊጉቭስካያ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ እት
ሻም ። ልንገናኝ ፡ የምንችልበት ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡
እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ...»

ወቀሳ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ደስ ፡ አይልም ።
ግን ፡ ይገባኛል ።

በነገራችን ፡ ላይ ፡ ነገ ፡ በልዩ ፡ ትዕዛዝ ፡
በሬስቶራንት ፡ ቤት ፡ የዳንስ ፡ ምሽት ፡ ይደረ
ጋል ። እኔም ፡ ከልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ጋራ ፡ ወማዙ
ርካ ፡ ለመደነስ ፡ ሐሳብ ፡ አለኝ ።

ግንቦት ፡ ፳፪ ።

በዚያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ሬስቶራንቱ ፡ የመ
ኳንንት ፡ ክበብ ፡ ሆኖ ፡ አመሸ ። ልክ ፡ ከምሽ
ቱ ፡ በሶስት ፡ ሰዓት ፡ የተጠሩት ፡ እንግዶች ፡
በሙሉ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር ። ልዕልት ፡ ሊንሽ
ስካያና ፡ ልጅዋ ፡ በመጨረሻ ፡ ከሦስት ፡
ሙሰጥ ፡ ናቸው ። ብዙዎቹ ፡ መኮዛዘት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንጋይ ፡ ጌጥ ፡ ተሸፍኗል ። አጠገቧ ፡ ላለው ፡ የፈረሰኛ ፡ ሻምበል ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤

«ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ሊጐብስካያ ፡ እስከዚህም ፡ ጨዋ ፡ ሆና ፡ አላገኘኋትም ። ከገፈጠረችኝ ፡ በኋላ ፡ ይቅርታ ፡ እንኳ ፡ አልጠየቀችኝም ። እንዲያውም ፡ ይብሱን ፡ በእጅ ፡ የሚያዘውን ፡ መነጽሯን ፡ ደንግራ ፡ የጐረጥ ፡ አይታኝ ፡ አለፈች ... C'est impayable!..* እስከዚህ ፡ የሚያኮራት ስ ፡ ምኑ ፡ ነው? መታረም ፡ ይኖርባታል ...»

«ይህን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ይተውት ፡» ብሎ ፡ ሻምበሉ ፡ ከመለሰላት ፡ በኋላ ፡ ወደሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ገባ ።

የማይተዋወቁ ፡ ሰዎች ፡ ለመደነስ ፡ በእካባቢው ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ በመጠቀም ፡ ተቀዳድሚ ፡ ልዕልቷን ፡ ለዳንስ ፡ ጠየቅኋት ።

የደስታ ፡ ፈገግታውን ፡ ለመቆጣጠር ፡ አልቻለችም ። ወዲያው ፡ ግን ፡ መለስ ፡ ብላ ፡ ኮስተር ፡ አለችብኝ ። ላመል ፡ እጅዋን ፡ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጋ ፡ አንገቷን ፡ ወደአንድ ፡ ጐን ፡ ጋደድ ፡ አድርጋ ፡ መሸከርከር ፡ ጀመርን ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ እጥፍ ፡ ዘርጋ ፡ የሚል ፡ ዳሌ ፡ በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ። ያ ፡ ትኩስ ፡ ጣፋጭ ፡ ትንፋሽ ፡ ፊቴን ፡ ገረፈኝ ። ከተጠቀለለው ፡ ወገቧ ፡ መካከል ፡ ተንጥሎ ፡

---

* ይህ ፡ የሚገርም ፡ ነገር ፡ ነው ። (ፈረንሳይኛ ።)

የሚወረወረው ፡ እንዱ ፡ እንደሳት ፡ የጋለውን ፡ ጉንጯን ፡ ይዳስሰዋል ... የቤቱን ፡ ወለል ፡ ሥስት ፡ ጊዜ ፡ ዞርኩት ። (የቫልስ ፡ አደናነሷ ፡ ወደር ፡ የለውም ።) ትንፋሿ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይላል ። ዓይኖቿም ፡ ፍም ፡ መስለዋል ፡ በትንሽ ፡ ከፈት ፡ ያሉ ፡ ከንፈሮቿም ፡ የተለመደውን ፡ «Merci, monsieur»* ለማለት ፡ የተሳናቸው ፡ ይመስላሉ ።

ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ትሁት ፡ ሆኜ ፡ እንዲህ ፡ አልኋት ፤

«ልዕልት ፡ ሆይ! ግና ፡ ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ሳንተዋወቅ ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቅር ፡ እንዳሰኘሁዎት ፡ ሰማሁ ። እርስዎም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ግምት ፡ አድርብዎታል ፡ አሉኝ ። ይህ ፡ እውነት ፡ ነው?»

«ታዲያ ፡ አሁን ፡ ያን ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዳጠነክረው ፡ ነው ፡ የሚፈልጉት?» ይህን ፡ ስትል ፡ ያሳየችውን ፡ ምጸት ፡ የተሞላበት ፡ ገጽ ፡ ከተንቀሳቃሽ ፡ ስውኔ ፡ ጋር ፡ ተጣምሮ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ፈጠረ ።

«ከዚህ ፡ በፊት ፡ እርስዎን ፡ ደፍሬ ፡ አላዝኜምት ፡ እንደሆነ ፡ አውንም ፡ በይበልጥ ፡ ደፍሬ ፡ ይትርጉምን ፡ ልጠይት ። በእውነቱ ፡ ስለእኔ ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክለኛ ፡ እንዳልሆነ ፡ ላረጋግጥልዎ ፡ እሻለሁ ።»

---

* አመሰግናለሁ ፡ ጌተዬ ። (ፈረንሳይኛ ።)

t.me/OLDBOOKSPDF

«ይህ ፡ መቸም ፡ ለእርስዎ ፡ በጣም ፡ አስ
ቸጋሪ ፡ ሥራ ፡ ይመስለኛል ...»

«ለምን?»

«እኛ ፡ ቤት ፡ እይመጡም ። እነዚህም ፡ ምሽ
ቶች ፡ ቢሆኑ ፡ የሚደጋገሙ ፡ አይመስለኝም ።»

ወደእነሱ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ በሩ ፡ የተዘጋ
ብኝ ፡ መሆኑን ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የጠቆመኝ ፡
መሰለኝ ።

ትንሽ ፡ ኩፍተር ፡ ብዬም ፡ እንዲህ ፡ አል
ኋት ፤

«ልዕልት ፡ ሆይ! አንድ ፡ ሰው ፡ ሃሚተኛን ፡
ወንጅሎ ፡ ብቻ ፡ ዝም ፡ አይልም ። ምክንያቱም ፡
ሃሚተኛ ፡ የባሰ ፡ በደል ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላልና ...
ያኔ ...»

ንግግሬን ፡ ሳቅና ፡ ሹክሹክታ ፡ አቋረጠኝ ።
ዞር ፡ ብዬ ፡ መመልከት ፡ ተገደድሁ ። ራቅ ፡
ብሎም ፡ ያ ፡ በልዕልቷ ፡ ላይ ፡ የዛተው ፡ የፈረሰ
ኛ ፡ ሻምበል ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሞ ፡ አየሁ ።
ሻምበሉም ፡ በደስታ ፡ ሁለት ፡ እጆቹን ፡ እያሻ
ሸ ፡ ባጠገቡ ፡ የቆሙትን ፡ ጓደኞቹን ፡ እየጠ
ቃቀሰ ፤ በከፍተኛ ፡ ሣቅ ፡ ይንፈቀፈቃል ። በድ
ንገትም ፡ ረኸም ፡ የእራት ፡ ኮት ፡ የለበሰ ፡
መኳንንት ፡ ከመሃከላቸው ፡ ወጥቶ ፡ እየተን
ገዳገደ ፡ ወደልዕልቷ ፡ መጣ ። ለመስከሩ ፡
ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። የተደናገጠችው ፡
ልዕልት ፡ ፊት ፡ እጆቹን ፡ አጣምሮ ፡ ቆሞ ፡ ማረጫ ፡

ዓይኖቹን ፡ ከልዕልቷ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ እንዲህ ፡
አላት ፤

«Permettez*... ወዲያ!.. ማዙርካ ፡ ለመደነ
ስ ፡ እፈልጋለሁ ።»

«ምንድን ፡ ነው ፡ የሚፈልጉት ፡ ጌታዬ?»
በማለት ፡ በተደናገጠ ፡ ድምፅ ፡ እየጠየቀች ፡
ዙሪያ ፡ ከጉን ፡ በዓይን ፡ የሚረዳት ፡ ሰው ፡
ትፈልግ ፡ ጀመር ። ሆኖም ፡ እናቷ ፡ ለእሱ ፡
ራት ፡ ብላ ፡ ትገኛለች ፤ በአካባቢው ፡ ከሚያን
ጎብቡት ፡ መሃከል ፡ አንዳቸውም ፡ እንኳ ፡
ባጠገብዋ ፡ አልነበሩም ። በቅርብ ፡ የሚያው
ቃት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖርም ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡
ደስ ፡ በማይል ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡
ስላልፈለገ ፡ ራሱን ፡ በሰዎች ፡ መሃከል ፡ ቀብሮ ፡
ዝም ፡ አለ ።

ሰካራሙ ፡ መኳንንት ፡ የሚያበረታታውን ፡
የተረኛ ፡ ሻምበል ፡ እያየ ፤ «ታድያ ፡ እምቢ ፡ ባ
ይሉ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። Pour mazure...
እንደገና ፡ እጋብዝዎታለሁ ... ምናልባትም ፡
የሠከርሁ ፡ መስዬዎት ፡ ይሆናል ። እሱ ፡ ግድ ፡
የለም ። ከሆነም ፡ ይበጃል ። ይመኑኝ »

ልዕልቷ ፡ በድንጋጤ ፡ እራስዋን ፡ ልትስ
ትንሽ ፡ ቀራት ።

መደሰካራሙ ፡ መኳንንት ፡ ጠ[illegible] ፡ ብሎ

*ይፍቀዱልኝ ። (ፈረንሳይኛ ።)

t.me/OLDBOOKSPDF

እጁን ፡ ጨብጨ ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጨ ፡ እያየሁ ፡ ልዕልቲቱ ፡ ማዙርካ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለመደነስ ፡ ቃል ፡ እንደገባችልኝ ፡ ነገርሁት ።

«ነው! እንግዲያውስ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ እጠይ ቃለሁ ፡» በማለት ፡ እየጣቀ ፡ ወደጓደኞቹ ፡ እየተንገዳገደ ፡ ሄደ ። ሲቀላቀል ፡ አጅበው ፡ ይዘውት ፡ ወጡ ።

ለዚህ ፡ ድርጊቱ ፡ ከእሷ ፡ የተሰጠኝ ፡ ሽል ማት ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ አመለካከት ፡ ነበር ።

ልዕልቲቷ ፡ ወደእናቷ ፡ ሄዳ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አወራቻት ። እናትዋም ፡ ለማመስገን ፡ ከሰዎች ፡ መሃከል ፡ ፈልጋ ፡ አገኙችኝ ። በዚህ ም ፡ አጋጣሚ ፡ እናቲን ፡ እንደምታውቅና ፡ ከስድስት ፡ አከስቶቹም ፡ ጋር ፡ ወዳጅ ፡ እን ደሆነች ፡ አወራችኝ ።

«እስካሁን ፡ ድረስ ፡ እንዴት ፡ እንዳልተዋወ ቅን ፡ አይገባኝም ። ለዚህም ፡ ጥፋተኛ ፡ እርስዎ ፡ መሆንዎን ፡ ማመን ፡ አለብዎት ። ራስዎን ፡ በጣም ፡ አግለው ፡ ይኖራሉ ። የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ክፍሌ ፡ ገለልተኛነትዎን ፡ እንደሚያስተዋት ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። ታዲያ ፡ ስለዚህ ፡ ምን ፡ ይላ ሉ?»

ለእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጋጣሚ ፡ ጥያቂ ፡ እያን ዳንዴ ፡ ሰው ፡ ለመልስ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሐረ ጉች ፡ ያገሙሁላት ።

የካድራሉ ፡ ዳንስ ፡ በጣም ፡ ረጅም ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ የማዙርካ ፡ ዳንስ ፡ ተጀምሮ ፡ ከወጣት ፡ ልዕልት ፡ አጠገብ ፡ ሔጂ ፡ ተቀመጥሁ ።

ሰካራሙ ፡ መኩንን ፡ ወይም ፡ በፊት ፡ ስላሳየሁት ፡ ጠባይ ፡ ካለዚያ ፡ ስለግሩሽኒትስ ኪይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ አላነሳሁም ። ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ካሳደረባት ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተላቀቀች ፡ መጣ ፡ ፊቷ ፡ አበራ ። አንጋገሯም ፡ ደስ ፡ አለ ። ንግ ግሯም ፡ ነፃ ፡ ነበር ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ የመ ሰለ ፡ ተጽዕኖ ፡ አይታይባትም ። በአካባቢዋ ፡ ያሉትንም ፡ ነገሮች ፡ የምታጤናቸው ፡ ጠለቅ ፡ ብላ ፡ ነው ። በሚያሻማና ፡ በሚያደናገር ፡ አንጋገር ፡ በእሷ ፡ ላይ ፡ ጥሩ ፡ ስሜት ፡ ካደረ ብኝ ፡ የቆየ ፡ መሆኑን ፡ ስገልጽላት ፡ አንገቷን ፡ ደፋ ፡ አድርጋ ፡ በፈገግታ ፡

«ጠባይዎ ፡ የተለመደ ፡ አይደለም ፡» አለ ችኝ ።

«በብዙ ፡ አድናቂዎችዎ ፡ ታጅበው ፡ ስለማ ይዎና ፡ በነሱም ፡ መካከል ፡ ገብቼ ፡ ተውፊጅ ፡ የምቀር ፡ ስለመሰለኝ ፡ ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ለመተ ዋወቅ ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር ።»

«ምንም ፡ የሚያስፈራዎ ፡ ነገር ፡ አልነበ ረም ። ሁሉም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ስልቹዎች ፡ ናቸው ።»

«ሁሉም? መቼም ፡ ሁሉም ፡ አሥመስለ ኝም ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድ ፡ ነገር ፡ ለማስታወስ ፡ እንዲፈለግች ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ ካየችኝ ፡ በኋላ ፡ አፈር ፡ ብላ ፣ «እኮ! ሁሉም ፡» አለችኝ ።

«ጓደኛዬ ፡ ግሩሽኒትስኪይም ፡ ሞምር?»

«ጓደኛዬ ፡ አሉ ፡ እንዴ?» ስትል ፡ በመጠራጠር ፡ ጠየቀችኝ ።

«አዎ!»

«እሱ ፡ በእውነቱ ፡ ከሰልቹቹ ፡ መካከል ፡ የሚመደብ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።»

«ታድያ ፤ ምድቡ ፡ ከእድለ ፡ ቢሶች ፡ ጋር ፡ ነዋ!» በማለት ፡ ከት ፡ ብዬ ፡ ሳቅሁ ።

«አዎ! ምን ፡ የሚያስቅ ፡ ነገር ፡ አገኙ? እርስዎ ፡ በእሱ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሆኑ ፡ ባየሁ ...»

«ምን ፡ አለ? እኔም ፡ በጊዜዬ ፡ እጨ ፡ መኩንን ፡ ነበርሁ ፤ የሕይወቴ ፡ መልካም ፡ ዘመን ፡ ያሳለፍኩት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።»

«እጨ ፡ መኩንን ፡ ነው?» ብላ ፡ ከጠየቀች ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀጠል ፡ አድርጋ ፤ «እኔማ ፡ የመሰለኝ ...»

«ማን ፡ መስሎዎት ፡ ኑሯል?»

«ማንም ... ማንም ፡ አልመሰለኝ ... እኒያ ፡ ወይዘሮ ፡ ማናቸው?»

ውይይታችን ፡ ሌላ ፡ መስመር ፡ ስለያዘ ፡ በዚህ ፡ አርዕስት ፡ ላይ ፡ ተመልሰን ፡ አልመጣንበትም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግዘተኻም ፡ አልቆ ፡ እንደገና ፡ እስክንገናኝ ፡ ድረስ ፡ ተለያየን ። ወይዛዝርቱም ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። ለራት ፡ ስገባ ፡ ቪርነርን ፡ አገኘሁት ።

«ታድያ ፤ ጉዱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ... ካልዕ ልታ ፡ ጋር ፡ የምተዋወቀው ፡ ከአንድ ፡ የሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ካዳንኳት ፡ በኋላ ፡ ነው' ፡ አላሉኝም?»

«የበለጠ ፡ ነው ፡ የሠራሁት ። ከዳንሱ ፡ ምሽት ፡ ላይ ፡ ሕሊናዋን ፡ ስታ ፡ ከመውደቅ ፡ አድኛታለሁ ።»

«ምን ፡ እንደሆነ ፡ ያውሩኝ!»

«የለም ፤ መግመት ፡ አለብዎት ። በተለይ ፡ እርስዎ ፡ ከፀሐይ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ገምተው ፡ ለመድረስ ፡ ችሎታ ፡ አለዎት!»

ግንቦት ፡ ፳፫ ።

ከምሽቱ ፡ እንድ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ በእደባባይ ፡ አካባቢ ፡ ስንሽራሸር ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከሩት ፡ አይቶኝ ፡ ወደእኔ ፡ መጣ ። አመለካከቱ ፡ አስቲኝ ፡ ነበር ። እጁን ፡ በኃይል ፡ ጨበጥ ፡ አድርጉ ፡ አላዛኝ ፡ በሆነ ፡ ድምፅ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

«እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፤ ፕቾሪን ... ምን ፡ ለማለት ፡ እንደፈለግሁ ፡ ይገባሃል ፤ አይደለም?»

«የለም ፣ እይገባኝም ። ያም ፣ ሆነ ፣ ይህ ፣ ምንም ፣ የሚያስመሰግነኝ ፣ ነገር ፣ የለም ፣» ብዬ ፣ መለስሁለት ።

እንደእውነቱ ፣ ከሆነ ፣ ሕሊናዬን ፣ የሚወቅስ ፣ እንጂ ፣ የሚያስመሰግን ፣ ምንም ፣ ነገር ፣ አልሠራሁም ።

«እንዴታ! ትላንትናውስ? ረሳህው ፣ እንዴ?.. ሜሪ ፣ ሁሉንም ፣ እጫወተችኝ ...»

«እሁን ፣ የምትመሰገኑት ፣ ሁለታችሁ ፣ ናችሁ! ሁሉም ፣ ነገር ፣ የጋራ ፣ ሆኖላችኋል?»

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ግሩሽኒትስኪይ ፣ በቁም ፣ ነገር ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ አወራኝ ፤

«ጓደኛዬ ፣ ሆነህ ፣ ለመኖር ፣ ከፈለግህ ፣ በፍቅሬ ፣ አታሹፍብኝ ። ከልቤ ፣ እንደምወዳት ፣ አይታይህም ፣ እንዴ?.. እኔም ፣ እንደእብድ ፣ የማምነውና ፣ ተስፋ ፣ የማደርገው ፣ እሷም ፣ እንደእኔ ፣ ትወደኛለች ፣ ብዬ ፣ ነው ... አንድ ፣ የምለምንህ ፣ ነገር ፣ አለኝ ። ዛሬ ፣ ማታ ፣ እንግዳነት ፣ እንደምትሄድ ፣ አውቃለሁ ። ማን ኛውንም ፣ ነገር ፣ ልብ ፣ ብለህ ፣ እንደምትመለከት ፣ ታል ፣ ግባልኝ ። በዚህ ፣ ነገር ፣ ጥሩ ፣ ልምምድ ፣ እንዳለህ ፣ አምናለሁ ። የሴቶችንም ፣ ጠባይ ፣ ከኔ ፣ ይበልጥ ፣ ታውቃለህ ። አይ ፣ ሴቶች ... አይ ፣ ሴቶች ! እነሱን ፣ በያንዳ ፣ የሚያውቅ ፣ ማን ፣ ይሆን? ፈገግታቸውና ፣ አስተያየታቸው ፣ አንድ ፣ አይደለም ። ቃላቶ

ችም ፣ ተስፋ ፣ የሚሰጡና ፣ የሚያታልሉ ፣ ናቸው። ድምፃቸው ፣ ግን ፣ የሚያርቅ ፣ ነው ። በአንድ ፣ ጊዜ ፣ ውስጣዊ ፣ ስሜትህን ፣ ገምተው ፣ ሊያውቁት ፣ ያችላሉ ። ወይም ፣ እንድ ፣ እንዴ ፣ ግልጽ ፣ የሆነ ፣ ነገር ፣ እንኳ ፣ ለመገመት ፣ ይሳናቸዋል ... ለምሳሌ ፣ ልዕልቲቷን ፣ ውሰድ ፤ ትላንትና ፣ ዓይኖቿ ፣ በእኔ ፣ ላይ ፣ ሲያርፍ ፣ የነበራቸው ፣ የሩቅር ፣ ስሜት ፣ ሌላ ፣ ውበት ፣ ነበራቸው ። አሁን ፣ ግን ፣ ቀዝቃዛችና ፣ ደብዛዛች ፣ ሆነዋል ።»

«እንደዚህ ፣ ያደረጋት ፣ ፀበሉ ፣ ይሆናል ፣» ብዬ ፣ መለስሁለት ።

«ሁልጊዜ ፣ የምታየው ፣ የእንድ ፣ ነገር ፣ መጥፎ ፣ ወገን ፣ ብቻ ፣ ነው ። ማቴርያሊስት ፣ ነህ ፣» ካለው ፣በኋላ ፣ «እስቲ ፣ ይህን ፣ ወደጉን ፣ ትተን ፣ ወደሌላው ፣ ማተር ፣ (ጉዳይ ፣ ማለት ፣ ነው) እንመለስ ።» በዚህ ፣ ሁለት ፣ ፍች ፣ ባለው ፣ ደካማ ፣ ቀልድ ፣ ተደስቶ ፣ መንፈሱ ፣ ዐና ።

ከምሽቱ ፣ ሶስት ፣ ሰዓት ፣ በፊት ፣ ሲሆን ፣ ወደልዕልቷ ፣ ቤት ፣ አብረን ፣ ሄድን ።

በቪራ ፣ ቤት ፣ በኩል ፣ ስናልፍ ፣ ቪራን ፣ በመስኮት ፣ አየናት ፣ አጭር ፣ የነጠን ፣ ሰላምታ ፣ ተለዋወጠን ፣ አለፍን ። ሊጐቪስካያ ፣ ቤትም ፣ ስንደርስ ፣ ቪራ ፣ ተከታትላን ፣ ገባች ። እናቷ ፣ ልዕልት ፣ ቪራን ፣ ወዘመዴ ፣ ናት ፣»

t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት ፡ አስተዋወቀችኝ ። ሻይ ፡ ቀረበ ። ብዙ ፡ እንግዶች ፡ ተገኝተዋል ። ውይይቱም ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ ነበር ። እኔም ፡ እናቷን ፡ ልዕልት ፡ ለማስደሰት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀልዶች ፡ እያወራሁ ፡ ብዙ ፡ ከልቢ ፡ እንድትስቅ ፡ ገፋፋኋት ። ወጣቷም ፡ ልዕልት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለመሳቅ ፡ ከጅሏት ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የያዘችው ፡ ሚና ፡ ላለመሳት ፡ ስትል ፡ የሳቅ ፡ ፍላጐትዋን ፡ እምቃ ፡ ለመያዝ ፡ ተገድዳለች ። መክሳተሩ ፡ የሚያምርባት ፡ ይመስላታል ። ምናልባትም ፡ እውነቷን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤ የእኔ ፡ ቀልድና ፡ ጨዋታ ፡ በእሷ ፡ ላይ ፡ ተዕዕኖ ፡ ስለሌለው ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ ሳያስደስተው ፡ አልቀረም ።

ሻይ ፡ ከጠጣን ፡ በኋላ ፡ ሁላችንም ፡ ወደ እንግዳ ፡ መቀበያው ፡ ክፍል ፡ ተመልሰን ፡ ሔድን ።

«ትዕዛዝሽን ፡ አክብሬ ፡ ስለመጣሁ ፡ ደስ ፡ አላለሽም?» ብዬ ፡ ሳልፍ ፡ ቬራን ፡ ጠየቅኋት ።

«ፍቅርና ፡ ምስጋና ፡ የተቀላቀለበት ፡ አመለካከት ፡ ለገሰችኝ ። ይህን ፡ ዓይነት ፡ አመለካከት ፡ በእውነቱ ፡ ለእኔ ፡ አዲስ ፡ አይደለም ። ሆኖም ፡ ከልቤ ፡ ያስደሰተኝ ፡ የነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ልዕልት ፡ ሊጐብኟኸያ ፡ ልጅዋን ፡ ከጢያኖው ፡ አጠገብ ፡ ካስቀመጠቻት ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንድትጫወት ፡ ያለምናት ፡ ግባ ። እኔ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ታል ፡ አልተነፈስሁም ።

የነበረውን ፡ ግርግር ፡ ተጠቅሚ ፡ ከቬራ ፡ ጋር ፡ ወደመስኮቱ ፡ ጠጋ ፡ ብለን ፡ ቆምን ። ቬራም ፡ ለሁለታችንም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ የምትነግረኝ ፡ መሆኗን ፡ ገለፀችልኝ ... ነገሩን ፡ በኋላ ፡ ስሰማው ፡ ግን ፡ ዋጋ ፡ የለሽ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ...

በኔ ፡ ግዴለሽነት ፡ ወጣቷን ፡ ልዕልት ፡ እንዳላስደስታት ፡ ግልምጫ ፡ ከተሞላበት ፡ አስተያየቷ ፡ ለመገመት ፡ ቻልሁ ። ይህ ፡ ድዳ ፡ የሆነ ፡ አሮር ፡ ኃይለኛ ፡ የንግግር ፡ ዘይቤ ፡ ሲገባኝ ፡ አያድርስ ፡ ነው!..

ልዕልቷ ፡ መዝፈን ፡ ጀመረች ። ድምጿ ፡ ግሩም ፡ ቢሆንም ፡ አወራረዱ ፡ መጥፎ ፡ ነበር ... እንዲያውም ፡ አልሰማኋትም ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ግን ፡ ክርኑን ፡ ከፒያኖው ፡ ላይ ፡ አሳርፎ ፡ ፍቅር ፡ በተራቡ ፡ ዓይኖቹ ፡ ልዕልቷን ፡ ፈዞ ፡ እያየ ፡ ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፤ «Charmant! delicieux!»* ይላት ፡ ነበር ።

«ስማኝ ፤ ከባሌ ፡ ጋር ፡ እንድትተዋወቅ ፡ አልፈልግም ። ልዕልቷ ፡ ቢወዱህ ፡ ግን ፡ ግሩም ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ በቀላሉ ፡ ልታደርገው ፡ ትችላለህ ። የፈለግኸውን ፡ ለማድረግ ፡ የሚላንህ ፡ ነገር ፡ የለም ። ለመገናኘት ፡ ያለን ፡ እድል ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡» ብላ ፡ ቬራ ፡ ተማጠነችኝ ።

*ግሩም ፤ አስደናቂ ፡ ነው! (ፈረንሳይኛ ።)

t.me/OLDBOOKSPDF

«እዚህ ፡ ብቻ?»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሽራ ፡ ፊቷ ፡ እሳት ፡ መስሎ ፡ ንግግሯን ፡ ቀጠለች ፡

«ባርያህ ፡ እንደሆንሁ ፡ ታውቃለህ ። ሳይህ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ራሴን ፡ ለመቆጣጠር ፡ እትም ፡ ያጥረኛል ። ለዚህም ፡ ዋጋዬን ፡ እንደማገኘው ፡ ይሰማኛል ። ምክንያቱም ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ እኔን ፡ መውደድህን ፡ ታቆማለህ ። ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ስሜን ፡ ማስከበር ፡ እሻለሁ ። ይህንንም ፡ የማደርገው ፡ ለእኔ ፡ ብዬ ፡ እንዳልሆነ ፡ በደንብ ፡ ታውቃለህ ። እባክህን ፡ በእኅል ፡ ጥርጣሬና ፡ በግዴለሽነት ፡ እንደድሮው ፡ አታሰቃየኝ! ከቀን ፡ ወደቀን ፡ እቅም ፡ እየተሳነኝ ፡ ሔጃለሁ ። በቅርቡም ፡ ሳልሞት ፡ አልቀርም ... ይህም ፡ ሲሆን ፤ ስለሕይወት ፡ እርቲ ፡ አበባ ፡ አላውቅም ። የማልመው ፡ ስላንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እናንተ ፡ ወንዶች ፡ እንድ ፡ መልካም ፡ አመለካከታችሁ ፡ ወይም ፡ ዳሰሳችሁ ፡ የመተቃቀፋን ፡ ያህል ፡ ስሜት ፡ እንደሚያሳድርብን ፡ አይገባችሁም ። ድምፅህ ፡ ጥልቅና ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከማያባል ፡ የከንፈር ፡ ጣዕም ፡ በበለጠ ፡ ስሜቴን ፡ እንደማ ቀሰቅሰው ፡ አመነኝ ።»

በዚህ ፡ ወቅት ፡ ልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ዘፈኗን ፡ አቆመች ። በአካባቢዋ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ሙገሳዎች ፡ ቀረቡላት ። እኔም ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡

መጨረሻ ፡ ሄጂ ፡ ስለዘፈኗ ፡ የተለመደ ፡ ተራ ፡ ሙገሳዬን ፡ ሰጠኋት ።

ፊቷን ፡ በማኮሳተር ፡ የታች ፡ ከንፈሯን ፡ እነ ታንቃ ፡ አስቂኝ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ትቁነጠነጥ ፡ ገባች ።

«የርስዎ ፡ ደግሞ ፡ አጉል ፡ የሆነ ፡ ሙገሳ ፡ ነው ። ስጫወት ፡ ፊትዎን ፡ ዞረው ፡ ቆመው ፡ እያዳምጡኝም ፡ ነበር ። ሙዚቃ ፡ አይወዱም ፡ ይሆን?»

«እንዲያውማ ... ከራት ፡ በኋላ ፡ ሙዚቃ ፡ መስማት ፡ በተለይ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።»

«ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ያለዎ ፡ ጣዕም ፡ ከሰው ፡ የማይገጥም ፡ ነው ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ለካስ ፡ እውነቱን ፡ ነው ። ለሙዚቃ ፡ እንኳ ፡ ያለዎ ፡ ጣዕም ፡ በልቶ ፡ የጠገበ ፡ ሰው ፡ ካለው ፡ አይለይም ...»

«አውንም ፡ ተሳሳቱ ። ሆዳም ፡ አይደለሁም ። እንዲያውም ፡ አይበላልኝም ። ሆኖም ፡ ከራት ፡ በኋላ ፡ ሙዚቃ ፡ ያስተኛል ። ከራት ፡ በኋላም ፡ በጊዜ ፡ መተኛት ፡ ጤንነት ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ ሙዚቃን ፡ የምወደው ፡ ከሕክምና ፡ አቅጣጫ ፡ ተመልክቼ ፡ ነው ። ከመሸ ፡ በኋላ ፡ ሙዚቃ ፡ መስማቱ ፡ ግን ፡ እእምሮዬን ፡ ይረብሸዋል ። ይህ ፡ ጊዜ ፡ ለእኔ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የማገኝበት ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የምደሰትበት ፡ ወቅት ፡ ነው ። በእንድ ፡ ስብስባ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ማዘኑ ፡ አስቂኝ ፡ ነው ። ያለመጠን ፡ መደሰቱ ፡ ደግሞ ፡ የተለመደ ፡ አይደለም ...»

ንግግሬን ፡ ሳልጨርስ ፡ ጥላኝ ፡ ሔዳ ፡ ከግሩ ሽኒትስኪይ ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠች ። ሁለቱም ፡ ፍቅር ፡ በተሞላው ፡ ሁኔታ ፡ ጨዋታቸውን ፡ ቀጠሉ ። ፍልስፍና ፡ የሞላቸውን ፡ ሐረጐች ፡ በጥሞና ፡ የምታዳምጥ ፡ ብትመስልም ፡ የልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ሐሳብ ፡ ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ እንዳልነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ከልብ ፡ የምትሰማው ፡ ያስመሰላት ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያልረጉት ፡ ዓይኖቿ ፡ ያያቸው ፡ ግሩሽኒትስኪይም ፡ ከውስጣዊ ፡ ስሜቷ ፡ የተረበሸችበትን ፡ ምክንያት ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጐ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በዓይኖቹ ፡ አትኩሮ ፡ ስለሚያያት ፡ ነው ። ሐሳቧ ፡ ከሌላ ፡ ቦታ ፡ መሆኑን ፡ የመምሰል ፡ ሁኔታ ፡ ሊሸፍነው ፡ አልቻለም ።

ውቢቷ ፡ ልዕልት! ምስጢርዎ ፡ ገብቶኛል ። ስለዚህ ፡ ጠንቀቅ ፡ ይበሉ! ከብራን ፡ ነክተው ፤ እኔ ፡ በአቆሰልሁዎት ፡ ዘዴ ፡ መልሰው ፡ ሊያቆስሉኝ ፡ ይሻሉ ። ሆኖም ፡ መቸም ፡ ሆነ ፡ መች ፡ አይሳካልዎትም ። ጦርነት ፡ ያከፈት ፡ ካሉ ፡ እርስዎን ፡ አያርገኝ ።

ያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ በውይይታቸው ፡ ለመካፈል ፡ ያጋማሚ ፡ ሞከርኩ ። ሆኖም ፡ የምሰጣቸውን ፡ አስተያየቶች ፡ በማድየለሽነት ፡ ትመልሳቸው ፡ ነበር ። ሁኔታው ፡ ያሳዘነኝ ፡ መስዬ ፡

በመጨረሻ ፡ ሙከራዬን ፡ ሁሉ ፡ አቆምኩ ። ልዕልቲቷና ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ የዛሬው ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ሆኑ ። ፈንጥዙ ፡ ወዳጆቼ! ድሉ ፡ የእናንተ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ፈንጠዝያው ፡ የሚዘልቅ ፡ አይደለም ። የሚቀጥለው ፡ ምንድነው? የወደፊቱ ፡ ፍንትው ፡ ብሎ ፡ ይታየኛል ። ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ስተዋወቅ ፡ ያለምንም ፡ ስሕተት ፡ ትወደኝ ፡ እትወደኝ ፡ እንደሆን ፡ የማወቅ ፡ ኃይል ፡ አለኝ ።

የቀረውን ፡ ምሽት ፡ ከቬራ ፡ ጋር ፡ አሳለፍኩት ። ስላለፈው ፡ ታሪካችን ፡ ስናወራ ፡ አመሸን ። በእውነቱ ፡ ለምን ፡ እንደዚህ ፡ እንደምትወደኝ ፡ አላውቅም ። በተለይም ፡ እውነተኛ ፡ ጠባዬን ፤ ማንኛቸውን ፡ ደካማነቴን ፡ ቁምር ፤ አበጥራ ፡ የምታውቅ ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡ ናት ። ታድያ ፡ ደካማነት ፡ እንዲህ ፡ ይወደዳል?

ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ እብረን ፡ ተመለስን ። ከቤቱ ፡ እንደወጣን ፡ ከንዴን ፡ ይዞ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፤

«ታድያስ ፡ ምን ፡ ትላለህ?» ሲል ፡ ጠየቀኝ ።

«ያደብ ፡ ነህ ፡» ልለው ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ ይህን ፡ ስሜቴን ፡ እፍኜ ፡ ይዤ ፡ ትከሻዬን ፡ አነቃንቁ ፡ ዝም ፡ አልኩት ።

ግንቦት ፡ ፳፱ ።

በእነዚህ ፡ ሁለ ፡ ቀናት ፡ ኪየዝሁት ፡ የአቀራረብ ፡ ዘዴ ፡ አልተየርሁም ። ለልዕልቲቱ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ትክር ፡ ብዬ ፡ ከተመለከትኳት ፡ በኋላ ፡ ኮስተር ፡ አልሁ ። የዚያን ፡ ቀንም ፡ ውይይታችን ፡ በዚህ ፡ አከተመ ። ትናንትና ፡ ማታ ፡ በጣም ፡ የምታስብ ፡ ትመስል ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ጧት ፡ ደግሞ ፡ ከወበሉ ፡ እንዳየኋት ፡ ከትናንቱ ፡ በባሰ ፡ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ የተዋጠች ፡ ትመስላለች ። ወደሷ ፡ ስሄድ ፡ ስለተፈጥሮ ፡ ይመስለኛል ፡ የሚያወራትን ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ በግማሽ ፡ ልብ ፡ ስታዳምጠው ፡ አየኋት ። ልክ ፡ እኔን ፡ ስታየኝ ፡ በሳቅ ፡ ትንፈቀፈቅ ፡ ጀመር ። (ሳቁ ፡ ፍፁም ፡ የታደለ ፡ ነው) ፡ እንዳላየችኝም ፡ ለመሆን ፡ ሞከረች ። እሷ ፡ ካለችበት ፡ ወደሌላ ፡ ራቅ ፡ ብዬ ፡ የጐሪጥ ፡ እመለከታት ፡ ገባሁ ። አብሯት ፡ ካለው ፡ አጃቢዋ ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ እንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አዛጋች ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ እንደሰለቻት ፡ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ አልነበረኝም ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ለአንድ ፡ ለሁለት ፡ ቀን ፡ ላላነጋግራት ፡ ወሰንኩ ።

ሰኔ ፡ ፫ ።

ለፍትወተ ፡ ሥጋ ፡ የማልሻትን ፡ ወይም ፡ ለማግባት ፡ የማልፈልጋትን ፡ ሴት ፡ እንድትወደኝ ፡ ለማድረግ ፡ ለምን ፡ እንደምጥር ፡ ለራሴ ፡ ለዘወትር ፡ የማቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ጊዜያዊ ፡ ፍትር ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ የሚጥመኝ፤ ልዕልት ፡ ሚረ ፡ መቸም ፡ ጊዜ ፡ ልትወደኝ ፡ የማትችለውን ፡ ያህል ፡

ንግግሬ ፡ እየጣማት ፡ ሄደ ። በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ካጋጠሙኝ ፡ አስደናቂ ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ እንዳንዶቹን ፡ አወራኋት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እኔን ፡ ያልተለመደ ፡ ሰው ፡ አድርጋ ፡ መመልከት ፡ ጀመረች ። ከወሃይ ፡ በታች ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ በስሜት ፡ ላይ ፡ እቀልድ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ሁኔታ ፡ በመጠኑ ፡ አደናገጣት ። እኔ ፡ ባለሁበት ፡ ጊዜ ፡ ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ ፍትር ፡ የተሞላበት ፡ ውይይት ፡ ማድረጉን ፡ አቋረጠች ። በብዙም ፡ አጋጣሚዎች ፡ ላይ ፡ ፌዝ ፡ የተሞላበት ፡ ፈገግታ ፡ ለግሩሽኒትስኪይ ፡ ታቀርብለት ፡ ጀመር ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ወደሷ ፡ አጠገብ ፡ በመጣ ፡ ቁጥር ፡ ትሁት ፡ መስዬ ፡ ለብቻቸው ፡ ትቻቸው ፡ ገለል ፡ እል ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፡ ይህን ፡ ስሠራ ፡ ደስ ፡ አላት ። ያለዚያም ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ለመምሰል ፡ ሞከረች ። በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ትዕግሥት ፡ አጣች ። በሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በግሩሽኒትስኪይ ፡ ላይ ፡ ተቆጣች ።

ትናንትና ፡ «ምነው ፡ ትንሽ ፡ ኩራት ፡ የለም? ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ መሆኑን ፡ የምመርጥ ፡ ለምን ፡ መሰለም?» ብላ ፡ ጠየቀችኝ ።

እኔም ፡ ለጓደኛዬ ፡ ደስታ ፡ ስል ፡ የራሴን ፡ ደስታ ፡ እንደምሰዋ ፡ መለስኩላት ።

«ታድያ ፡ የእኔንም ፡ ደስታ ፡ ጨምረው ፡ ነው ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ፡ ቪራ ፡ ትወደኛለች ። ሚሪ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የማትበገር ፡ ሴት ፡ ሆና ፡ ነው? ይህ ፡ ከሆነ ፡ አስቸጋሪነቱ ፡ እራሱ ፡ ለማደርገው ፡ ወጣ ፡ ወረድ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ በቻለ ፡ ነበር ።

ሆኖም ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ አይደለም ። ፍቅርን ፡ የተጠማንበት ፡ በልጅነታችን ፡ ዘመን ፡ ተገባዶ ፡ ሁኔታችን ፡ የሚያንገሸግሻት ፡ እስኪ ያጋጥመን ፡ ድረስ ፡ ከአንድ ፡ ሴት ፡ ወደሌላ ፡ ሴት ፡ በምንሯሯጥበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረንም ፡ ስሜት ፡ አይደለም ። በአንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ መርጋትን ፡ የምንጀምረው ፡ ያኔ ፡ ነው ። ይህም ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ፍቅር ፡ በሂሳብ ፡ ሕግ ፡ ይተርጐም ፡ ከተባለ ፡ ከአንድ ፡ ነጥብ ፡ ተነስቶ ፡ ወደጠፈር ፡ የሚያመለክት ፡ መስመር ፡ ይመስላል ። የመስመሩ ፡ ፍጻሜ ፡ አልቦ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈልገውን ፡ ግብ ፡ ስላላገኘ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ታድያ ፡ እኔን ፡ የሚገፋፋኝ ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው? በግሩሽኒትስኪይ ፡ ቀንቼ ፡ ይሆን? ምስኪን! እሱን ፡ ቢሆን ፡ የሚቀርባት ፡ አልነበረም ። ካለዚያስ ፡ በመጥፎ ፡ ስሜት ፡ ተገፋፍቶ ፡ ምንም ፡ ትርጉም ፡ ላይኖረው ፡ የአንድ ፡ የቀረበ ፡ ወዳጅ ፡ ትንሽ ፡ ደስታ ፡ ይምስሸ ፡ በንዘን ፡ ተሰብሮ ፡ ወደእሱም ፡ ሲመጣ ፡ «ወዳጄ» ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በእኔም ፡ ደርሷል ። ግን ፡ እንደምታየኝ ፡ እበላለሁ ፡

በደንብ ፡ እተኛለሁ ። ያለምንም ፡ ሐዘንና ፡ እምባ ፡ እንደምሞት ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡» ለማለት ፡ ይሆን?

ይሁንና ፡ እምቡጥ ፡ ሕይወት ፡ ያላትን ፡ ኮረዳ ፡ መማረኩን ፡ ከፍተኛ ፡ ደስታን ፡ ያጐናጸፋል ። እንደዚህም ፡ ያለች ፡ ቆንጆ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የፀሐይ ፡ ጨረር ፡ ለመቀበል ፡ እንደተዘጋጀች ፡ ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ እንዳላት ፡ አበባ ፡ የፈካች ፡ ናት ። ይህችን ፡ መልካም ፡ ሽታ ፡ ያላት ፡ አበባም ፡ በዚያችው ፡ ደቂቃ ፡ ቀጥፎ ፡ በሽታዋ ፡ ስሜትን ፡ ካረኩ ፡ በኋላ ፡ እንዱ ፡ ያነሳታል ፡ በሚል ፡ ተስፋ ፡ ተመርኩዞ ፡ መወርወር ፡ ያሻል ። በመንገዴ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ለማግበስበስ ፡ እፈልጋለሁ ። የሰዎችን ፡ ኃዘንና ፡ ደስታ ፡ የምመለከተው ፡ ምግብ ፡ ለሥጋዊ ፡ ሕዋሳቴ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ከራሴ ፡ አንፃር ፡ ተነስቼ ፡ ነው ። በፍቅር ፡ የተነሳ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወድያ ፡ ሕሊናዬን ፡ ለመሳት ፡ በፍጹም ፡ አልሻም ። የራስ ፡ ወዳድን ፡ ስሜቴ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ጠፍቷል ። ይሁንና ፡ ይህ ፡ ራስ ፡ ወዳድነት ፡ ስሜቴ ፡ በአዲስ ፡ መልክ ፡ ተቀይሮ ፡ ቀርቧል ። እራስ ፡ ወዳድነት ፡ ማለት ፡ እኩ ፡ ለሥልጣን ፡ የሚደረግ ፡ ጥማት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከፍተኛ ፡ ደስታ ፡ የምጐናጸፈው ፡ በእካባቢዬ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በፈለግሁት ፡ ስመራው ፡ ነው ። ፍቅርን ፡ ታማኝነትን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ንድ ፡ ቦታ ፡ ቱጭ ፡ ካለ ፤ ያብዳል ፤ ከዚያም ፡ ሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል ። በሰውነት ፡ ማጠ ንከርያ ፡ አካሉን ፡ ያዳበረ ፡ ሰው ፡ ጅምናስቲ ኩን ፡ ካቋረጠ ፡ ደሙ ፡ ቱሞ ፡ በድንገተኛ ፡ እንደሚሞት ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

ፍላጐትና ፡ አምሮት ፡ ገና ፡ በመፈጠር ፡ ላይ ፡ ካለ ፤ የመነጨ ፡ ከሐሳብ ፡ ነው ። ፍላ ጐት ፡ አፍላ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ሕይወቴን ፡ በሙ ሉ ፡ ይህ ፡ ስሜት ፡ ይከተለኛል ፡ ብሎ ፡ የሚያ ስብ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ሞኝ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ጅረቶ ች ፡ ሲጀምሩ ፡ ታላላቅ ፡ ፏፏቴዎች ፡ ነበሩ ። ሆኖም ፡ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ እንዳቸውም ፡ ፏፏቴ ፡ ሁኖ ፡ ከውቅያኖስ ፡ አይቀላቅሉም ። እነዚህ ፡ ጸጥተኛ ፡ ጅረቶች ፡ የተሰወረ ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ። ሙላትና ፡ ጥል ቱት ፡ ያለው ፡ ስሜት ፡ ግንፍል ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፡ የለውም ። ምክንያቱም ፡ የኃዘንና ፡ የደስታን ፡ ጊዜ ፡ ልብ ፡ አጠናቆ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ። ያለ ፡ ጠሮ ፡ የዐሐይ ፡ ሙቱት ፡ ብቻውን ፡ ልብን ፡ ሊያቅልጣት ፡ ይችላል ። እናት ፡ የምትወደውን ፡ ልጅዋን ፡ በጉያዋ ፡ አቅፋ ፡ እንደምትይዘው ፡ ሁሉ ፡ ልብዋ ፡ በራሱ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ሕይወት ፡ አላት ። ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ የፈጣሪ ፡ ፍጥረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊፈርደው ፡ የሚችለው ፡ በዚህ ፡ በከፍተኛ ፡ በራስ ፡ ማወቅ ፡ ዘመቻ ፡ ራሱን ፡ ያዳበረ ፡ ለት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ፍርሃትን ፤ በሌሎች ፡ ላይ ፡ ለማሳደር ፡ በሚደረ ገው ፡ ሙከራ ፡ የሚገኘው ፡ ድል ፡ የሥልጣን ፡ የመጀመሪያው ፡ ምልክት ፡ እይደለምን? ያለም ንም ፡ መብት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ እጣ ፡ የሥቃ ይና ፡ የደስታ ፡ ምክንያት ፡ ከመሆን ፡ በበለጠ ፡ እራስ ፡ ወዳድነትን ፡ የሚያረካ ፡ ፍስሃ ፡ አለ ፡ ወይ? ደስታ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው? የረካ ፡ ኩራት ፡ ማለት ፡ ነው ። በዓለም ፡ ካለ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ኃይል ፡ አለኝ ፡ ብዬ ፡ የምገም ተው ፡ ደስተኛ ፡ ሰው ፡ ስሆን ፡ ነው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወዶኝ ፡ በየጊዜውም ፡ አዳዲስ ፡ ፍቅር ፡ ሲያጋጥመኝ ፡ ያኔ ፡ ደስተኛ ፡ ነኝ ፡ ለማለት ፡ እችላለሁ ። ክፋት ፡ ክፋትን ፡ ይወልዳል ። ሌሎችን ፡ ማሰቃየት ፡ ደስታን ፡ የሚሰጠህ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሥቃይ ፡ ከደረሰብህ ፡ በኋላ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ የክፋትን ፡ እውነተኛ ፡ ትር ጉም ፡ ለማወቅ ፡ ከፈለገ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማ ዋል ፡ ፍላጐት ፡ ያሸዋል ። «ሐሳብ ፡ አንድ ፡ ጠባይ ፡ አለው ፡» ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተናግ ሯል ። አንድ ፡ ሐሳብ ፡ ገና ፡ ሲፈጠር ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ ቅርጽ ፡ ይኖረዋል ። ይህም ፡ ቅርጽ ፡ ድርጊት ፡ ነው ። ሚንቅላቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ የሚፈጥር ፡ ሰው ፡ ከሌላው ፡ በይበልጥ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነው ። አንድ ፡ ልዩ ፡ ተሰጥዎ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የበሮ ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ያስቀመጡት ፡ እንደሆነ ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ በአ

t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህን ፡ ገዳዮች ፡ መልሼ ፡ ሳናባቸው ፡ ከሞናው ፡ አርእስት ፡ እንደወጣሁ ፡ ይታወቀኛል ። ይህንን ፡ ማስታወሻ ፡ የምጽፈው ፡ ለራሴ ፡ ስለሆነ ፡ ምን ፡ አለበት ። የማሰፍረው ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ትዝታ ፡ እንደሚያሳድርብኝ ፡ አምናለሁ ።

. . . . . .

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ሲሮጥ ፡ መጥቶ ፡ በእንገቴ ፡ ላይ ፡ ተጠመጠመብኝ ። የመኩንንነት ፡ ማዕረግ ፡ አገኘ ። ለደስደሱ ፡ ሻምፓኝ ፡ ጠጣን ። ዶክተር ፡ ቩርነርም ፡ ተከትሎ ፡ ገብቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ ፡ አልልህም ።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም ፡ አሁን ፡ እዚሁ ፡ እዐበሉ ፡ ተሰፍቶ ፡ ከምትለብሰው ፡ የመኩንን ፡ የመድፈኛ ፡ ኮት ፡ ይልቅ ፡ የድሮ ፡ ትልቁ ፡ የወታደር ፡ ልብስህ ፡ ይበልጥ ፡ ያምርብሀ ፡ ነበርና፤.. አየህ ፤ እስከዛሬ ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ከሌሎቹ ፡ ለየት ፡ ብለህ ፡ ጐልተህ ፡ ትታይ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደማንኛውም ፡ ሁሉ ፡ ልትሆን ፡ ነው ።»

«ዶክተር ፡ የፈለጉትን ፡ ይበሉ ። ከመደሰት ፡ ግን ፡ ሊያቆሙኝ ፡ አይችሉም ፡» ካለ ፡ በኋላ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ወደእኔ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤ «ለዚህ ፡ ማዕረግ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ እንዲጣልበት ፡ ዶክተሩ ፡ አልገባውም ... አይ! ማዕረግ ... አይ! ማዕረግ ... እናንተ ፡ ኮከቦቹ ፡ የወደፊት ፡ እጣዬ ፡ ዋስ ትናዎቹ ፡ ናችሁ ... የለም! በእውነት ፡ በጣም ፡ ተደስቻለሁ ።»

ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለመንሸራሸር ፡ ወደሽለቆው ፡ ትሄዳለህ!» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

«ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አዲሱ ፡ የመኩንን ፡ ልብሴ ፡ ተሰፍቶ ፡ ሳልለብስ ፡ ልዕልቷ ፡ ፊት ፡ አልደርስም ።»

«ስለእገኘኸው ፡ ማዕረግ ፡ ለልዕልቲቷ ፡ የደስደሱን ፡ ልንገራት?»

«በዱብ ፡ ዕዳ ፡ ላስደስታት ፡ ስለምፈልግ ፡ እስቀድመህ ፡ እትንገራት ።»

«ከልዕልቲቷ ፡ ጋር ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ?»

ሰጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደግፈር ፡ ብሎ ፡ ተከዘ ። ጉራ ፡ ለመንዛትና ፡ ለመዋሸት ፡ ፈልጐ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕሊናው ፡ ስለወቀሰው ፡ ዝም ፡ አለ ። በሌላ ፡ አኳያም ፡ እውነቱን ፡ ለመናዘዝ ፡ አልደፈረም ።

«የምትወድህ ፡ ይመስልሃል?»

«ትወድኛለች፣ ጌቾሪን ፡ ስለፈጠረህ ፡ ተመኝ ። ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እስተሳሰብ ፡ ነው ፡ ያለ

t.me/OLDBOOKSPDF

እጇን ፡ ሰጠኋት ። ከዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጀምሮ ፡ እስከመጨረሻው ፡ እጇን ፡ አልለቀቅችውም ።

ንግግራችን ፡ የተጀመረው ፡ በጠብ ፡ ነው ። በውይይታችንም ፡ ላይ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ያሉትንና ፡ የሌሉትን ፡ ሁለታችንም ፡ የምናውቃቸውን ፡ ሰዎች ፡ እያነሳሁ ፡ በመጀመሪያ ፡ የዋህ ፡ ጠባያቸውንና ፡ ኋላ ፡ መጥፎ ፡ ጠባያቸውን ፡ እንድ ፡ ባንድ ፡ እየዘረዘርሁ ፡ ማዋየት ፡ ጀመርሁ ። በቀልድ ፡ የጀመርሁትም ፡ ጨዋታ ፡ መጥፎ ፡ ጠባዬን ፡ ስለቀሰቀስብኝ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ አንቋሸሻቸው ፡ ገባሁ ። እነጋገሬ ፡ በመጀመሪያ ፡ አስቂት ፡ ነበር ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ደነገጠች ።

«እደግኛ ፡ ሰው ፡ ነዎት ፡» ካለችኝ ፡ በኋላ ፡ ንግግሯን ፡ በመቀጠል ፤ «በእርስዎ ፡ ምላስ ፡ ከምወድቅ ፡ እዚሁ ፡ በጩቤ ፡ መወጋቴን ፡ እመርጣለሁ ። ከልቤ ፡ ነው ፡ የምለምንዎ ፤ ስለእኔ ፡ መጥፎ ፡ ከሚናገሩ ፡ በጩቤ ፡ ቢወጉኝ ፡ ይሰ ፡ ይለኛል ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚሳንምት ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ እይመስለኝም ፡» ብላ ፡ ለመነችኝ ።

«ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ እመስላለሁ?»

«ያብሳሉ ...»

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደማሰብ ፡ አልሁና ፡ በጣም ፡ ያዘነ ፡ ሰው ፡ መስዬ ፡ እንዲህ ፡ አልኋት ፡

«አዎ ፡ ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡ የነበረኝ ፡ ዕጣ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ሁሉ ፡

ሀ? በእጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ይህንን ፡ ትጠብቃለህ? ከዚያም ፡ ሌላ ፡ እንደሷ ፡ ያለች ፡ የተከበረች ፡ ሴት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እወድሃለሁ ፡ አትልም ...»

«ጉድ ፡ ነው! የተከበረም ፡ ወንድ ፡ ስሜቱን ፡ መደበቅ ፡ አለበት ፡ ብለህ ፡ ታምናለህ ፡ ማለት ፡ ነዋ!»

«ወዳጄ ፡ ሆይ! አንድን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ ዘዴ ፡ ያሻዋል ። ሳይነገሩ ፡ በግምት ፡ የሚታወቁ ፡ ብዙም ፡ ነገሮች ፡ አሉ ...»

«እሱስ ፡ እርግጥ ፡ ነው ... በሴቶች ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የሚነበብ ፡ ፍቅር ፡ ሐቀኛን ፡ የሚያስተማምን ፡ አይደለም ። ግን ፡ ታላት ... ግሩ ሽኒትስኪይ ፡ ተጠንቀቅ! እያታለለችህ ፡ ናት...»

«እሷ?» ብሎ ፡ ዓይኖቹን ፡ ወደሰማይ ፡ ቀስሮ ፤ «ፔቾሪን ፡ ታሳዝነኝለህ!» ብሎኝ ፡ ወጣ ።

ሲመሻሽ ፡ ወደሸለቆው ፡ ለመንሸራሸር ፡ የወጡት ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ። በአካባቢው ፡ ሊታውንት ፡ በዚህ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ እንደነበረበት ፡ ይናገራሉ ። ይህም ፡ ሸለቆ ፡ የሚገኘው ፡ ከማሹክ ፡ ተራራ ፡ ዳገት ፡ ከከተማው ፡ እንድ ፡ ቨርስታ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ነው ። ወደሸለቆው ፡ የሚወስደው ፡ ጠመዝማዛ ፡ መንገድ ፡ ቱጥቧጠዎችንና ፡ የቁም ፡ ድንጋይ ፡ ሰንጥቆችን ፡ ያልፋል ። ተራራውን ፡ መውጣት ፡ ሰንጀምር ፡ ለልዕልታ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

መናገር ፡ ጀመርሁ ። የሕብረተ ፡ ሰብንም ፡ ሕግ ፡ ላውት ፡ የእናኳርን ፡ ዘዴ ፡ ተማርሁ ። ሌሎች ፡ ግን ፡ እንዲያ ፡ እንዳለት ፡ የነበርሁትን ፡ የኑሮ ፡ ዘዴ ፡ ያለምንም ፡ ጥበብ ፡ ሲመግቡት ፡ እየሁ ። በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ሐዘን ፡ ያደረብኝ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሐዘን ፡ በእን ዲት ፡ የሽጉጥ ፡ ጥይት ፡ የሚጠፋ ፡ ሳይሆን ፤ በመልካም ፡ ፈገግታና ፡ በጨዋነት ፡ የተሸፈነ ፡ ተዝታዛ ፤ ኃይል ፡ የሌለው ፡ እሮሮ ፡ ነው ። የመንፈስ ፡ ሽባ ፡ ሆነውኝ ። ግማሹ ፡ ልቤ ፡ የለም ። ደርቋል ። ሞቷል ። ቆርጡም ፡ እው ጥቼ ፡ ጥየዋለሁ ። የቀረው ፡ ግማሹ ፡ ግን ፡ ይን ቀሳቀሳል ። ይኖራልም ። እያንዳንዱንም ፡ ሰው ፡ ለማገልገል ፡ ዝግጁ ፡ ነው ። ሌላ ፡ የልቤ ፡ ግማሽ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ የሚያስብ ፡ ስለሌለ ፡ ይህን ፡ ማንም ፡ ሊያስበው ፡ አልቻለም ። እርስዎ ፡ የሞተውን ፡ ልቤን ፡ ትዝታ ፡ ስለቀሰቀሱት ፡ በመታብሩ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ እንበብሁ ልዎ ። ሰዎች ፡ በመታብር ፡ ላይ ፡ የሚጻፈውን ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ያደርጉታል ። እኔ ፡ ግን ፡ በተለይም ፡ በዚያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥር ፡ የተኙትን ፡ ሙታን ፡ ሳስታውስ ፡ ይህንን ፡ ሐሳብ ፡ አልቀበ ለውም ። በሐሳቡ ፡ እንዲስማሙ ፡ አልጠይቅ ዎትም ። የተናገርሁት ፡ አስቂኝ ፡ ከመስለዎት ፡ ይንፈትፈቱ ። እኔን ፡ ግን ፡ በፍፁም ፡ እንደማ ያናድደኝ ፡ ይወቁ ።»

ክፈቴ ፡ ላይ ፡ የሌለ ፡ መጥፎ ፡ ምልክቶችን ፡ ያያሉ ። እንዲህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለሚያስቡ ፡ መጥፎ ፡ ሐሳቦች ፡ በእንጮሌ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጠ ሩ ። ሁለመናዬም ፡ ቁጥብ ፡ ስለሆነ ፡ ብልጣ ፡ ብልጥ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይሰድቡኛል ። ስለዚህ ም ፡ ከሰው ፡ እርቄ ፡ ለመኖር ፡ ተገደድሁ ። ክፉና ፡ ደግን ፡ በደንብ ፡ ለይቼ ፡ በማወቄ ፡ መንከባከብ ፡ ሲገባኝ ፤ እሰደብና ፡ ዓይንህ ፡ ካፈር ፡ ስለምባል ፡ ጭንቅላቴ ፡ የክፋት ፡ ነገር ፡ መጠራቀሚያ ፡ ለመሆን ፡ ቻለ ። ሌሎች ፡ ሕፃ ናት ፡ በሙሉ ፡ ደስተኞችና ፡ ፍንድቅድቆች ፡ ሲሆኑ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ እንገተ ፡ ሰባራ ፡ ሆኜ ፡ እደግሁ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በግሌ ፡ ከእነሱ ፡ የበላይነት ፡ ስሜት ፡ ቢያድርብኝም ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ዝቅተኛ ፡ ተብዬ ፡ መቆጠሬ ፡ አልቀ ረም ። ስለሆነም ፡ ከፍተኛ ፡ ጥላቻ ፡ እደረብ ኝ ። ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ ለመውደድ ፡ ዝግጁ ፡ ነበርሁ ። ግን ፡ የተረዳኝ ፡ ሰው ፡ ማን ም ፡ ስላልነበረ ፡ ጥላቻን ፡ ተማርሁ ። የደስ ፡ ደስ ፡ የሌለው ፡ የሕፃንነት ፡ ዘመኔ ፡ ከራሴና ፡ ከሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ጋር ፡ ትልቅ ፡ ቅራ ኔን ፡ ፈጠረ ። ሽሙጥና ፡ ፈዝን ፡ በመናራት ፡ የነበሩኝን ፡ መልካም ፡ ስሜቶች ፡ በልቤ ፡ ው ስጥ ፡ አፍኜ ፡ ያዝኋቸው ። በዚያውም ፡ ሞተው ፡ ተቀብረው ፡ ቀሩ ። እውነትን ፡ እያናገር ፡ ነበር ። ግን ፡ የሚያምነኝ ፡ ስለማላገኝ ፡ ውሸት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ፡ ለመናገር ፡ እንደፈለገች ፡ ከሁኔታዋ ፡ ያስታውታል ። ጡቶቿም ፡ ተርበደበዱ ... የለበሰችው ፡ ስስ ፡ ጨርቅ ፡ እጁዋን ፡ ለአመ ል ፡ ሸፍኖታል ። ከአካላቷ ፡ የመጣው ፡ የኤ ለክትሪክ ፡ ኃይል ፡ ከእጁ ፡ ወደእጅዋ ፡ ሲ ተላለፍ ፡ ተሰማኝ ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ፍቅ ር ፡ የሚጀምረው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሴት ፡ በእቅማችን ፡ ወይም ፡ በምላሳችን ፡ ትወደ ናለች ፡ ብሎ ፡ ማሰቡ ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። በእርግጥ ፡ ልቧ ፡ ያን ፡ ታላቅ ፡ የፍ ቅር ፡ እሳት ፡ ለመቀበል ፡ እንዲችል ፡ መንገዱን ፡ ይጠርግለታል ። ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ወሳኙ ፡ ግን ፡ የመጀመርያው ፡ አቀራረብ ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ መቼም ፡ ደግ ፡ ሆኜ ፡ ነው ፡ የዋል ሁት?» በማለት ፡ ልዕልቷ ፡ ከፍላጐቷ ፡ ውጭ ፡ ራሷን ፡ አስገድዳ ፡ ጠየቀችኝ ።

ተለያየን ።

በራሷ ፡ አልተደሰተችም ። ቀዝቃዛ ፡ ብላም ፡ በመዋሷ ፡ እራሷን ፡ ጥፋተኛ ፡ አድርጋ ፡ ቆጥራ ዋለች ። ይህም ፡ የመጀመሪያውና ፡ ትልቁ ፡ ድል ፡ ነው ። ነገ ፡ ልታስደስተኝ ፡ እንደምትፈ ልግ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ይህን ፡ ሁሉም ፡ በቃሌ ፡ አውቀዋለሁ ። ስልቹም ፡ የሚሆነው ፡ ለዚህ ፡ ነው ።

ሰኔ ፡ ፩ ።

ቪራን ፡ አሁን ፡ አገኘኋት ። ከአደረባት ም ፡ ቅናት ፡ የተነሳ ፡ ሞቼ ፡ ብቀብርላት ፡

በዚህ ፡ ወቅት ፡ ዓይኖቻችን ፡ ሲገናኙ ፡ የሷ ፡ ዓይኖች ፡ እንባ ፡ አቅረው ፡ አየሁ ። በ ክንዴ ፡ ላይ ፡ ያንተራሰችው ፡ እጅዋ ፡ ይንቀጠ ቀጣል ። ጉንጮቿ ፡ ፍም ፡ መስለዋል ። አዝ ናልኛለች ። ማንኛዋንም ፡ ሴት ፡ የሚማርከ ው ፡ የሐዘኔታ ፡ ፍቅርም ፡ በዚች ፡ ልምምድ ፡ በሌላት ፡ ሴትም ፡ ልብ ፡ ሰርጾ ፡ ገባ ። በሽር ሽሩ ፡ ወቅት ፡ ሁሉ ፡ ከማንም ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ሳትዳራ ፡ ተከዛ ፡ ዋለች — ይህም ፡ ትልቅ ፡ ምልክት ፡ ነው!

ሸለቆው ፡ ጋ ፡ ደረስን ፡ ሌሎች ፡ ወይዛዝርት ፡ ተላቀው ፡ ለየብቻቸው ፡ ሲሄዱ ፡ እሷ ፡ ግን ፡ እጄን ፡ አልለቀቀችውም ። የአካባቢው ፡ ውካ ታና ፡ ጨዋታ ፡ ከትካዜዋ ፡ ፈጽሞ ፡ አልቀሰቀ ሳትም ። የቆመችበት ፡ የገደል ፡ ጥልቀት ፡ ም ንም ፡ ያህል ፡ አላስደነገጣትም ። ሌሎች ፡ ወይዛ ዝርት ፡ ግን ፡ በፍርሃት ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ በእጆ ቻቸው ፡ መዳፎች ፡ ይከልሉና ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ።

ወደቤት ፡ ስንመለስ ፡ ያን ፡ አሳዛኝ ፡ ጨዋታ ዩን ፡ አልጀመርሁም ። ዋጋ ፡ ቢስ ፡ የሆኑትን ፡ ፍሬ ፡ ከርሲኪ ፡ ጥያቄዎችን ፡ በአጭርና ፡በግዴ ለሽ ፡ መልሶች ፡ ተጨቻቸው ።

በመጨረሻም ፡ ወሳኙ ፡ ይዘምት ፡ ያው ታል?» ብዬ ፡ ጠየቅኋት ።

ትኩር ፡ ብላ ፡ ነየችኝ ፡ በኋላ ፡ አንገቷን ፡ ወዝውዛ ፡ ተመልሳ ፡ ትከዝ ፡ አለች ። አንድ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ደስ ፡ ባላት ። ልዕልቷ ፡ የልቧን ፡ ምስጢር ፡ ለማ
ካፈል ፡ ቬራን ፡ እንደመረጠች ፡ አምናለሁ ።
«ይህ ፡ ሁሉ ፡ ወዴት ፡ እንደሚያመራ ፡
ለመገመት ፡ ለእኔ ፡ አይሳነኝም ። ይልቅስ ፡
ልዕልቷን ፡ እወዳታለሁ ፡ ብለህ ፡ ብትነግረኝ ፡
ይሻላል ፡» ብላ ፡ ቬራ ፡ ጠየቀችን ።
«ምናልባትም ፡ ባልወዳትስ?»
«ካልወደድሃት ፡ ታድያ ፡ ለምን ፡ ትከታተላ
ታለህ? ለምን ፡ ትረብሻታለህ? ለምንስ ፡ ሐሳ
ቧን ፡ ታጨናግፍባታለህ? አንተን ፡ መቼም ፡
በቅርብ ፡ አውቅሃለሁ ። እኔ ፡ እንዳምንህ ፡
ከፈለግህ ፡ ከሳምንት ፡ በኋላ ፡ ወደኪስሎቮ
ድስክ ፡ ና ። እኛም ፡ ነገ ፡ ወደዚያው ፡ እን
ሔዳለን ፤ ልዕልት ፡ ሊጐብስካያ ፡ እዚሁ ፡
ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ይቆያሉ ። እኛም ፡ ቤት ፡ የ
ምንከራየው ፡ ከምንጩ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡
ትልቅ ፡ ቤት ፡ የማዛኒ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ ቅር
ብ ፡ ያለውን ፡ ቤት ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ተከራየው ።
ልዕልት ፡ ሊጐብስካያ ፡ የታችኛውን ፡ ክፍል ፡
ይይዙታል ። በአጠገቡም ፡ የዚሁ ፡ ባለቤት ፡
ሐብት ፡ የሆነ ፡ ያልተያዘ ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ አለ ...
ትመጣለህ?..»
ታል ፡ ገባሁላት ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ቤቱን ፡
እንዲከራይልኝ ፡ ሰው ፡ ላክሁ ።
ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከምሽቱ ፡ በሰድስት ፡
ሰዓት ፡ ወደእኔ ፡ መጥቶ ፡ አዲሱ ፡ የመኰንን ፡

ልብሱ ፡ ተሰፍቶ ፡ አልቆ ፡ ለነገው ፡ የዳንስ ፡
ምሽት ፡ እንደሚያርስለት ፡ ነገረኝ ።
«ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ ከእሷ ፡ ጋር ፡ የምደ
ንስበት ... በልቤም ፡ ውስጥ ፡ ያመቅሁት ፡
የማወራላት ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ደረሰ!» አለኝ ።
«የዳንስ ፡ ምሽቱ ፡ መቼ ፡ ነው?»
«ነገ ። አላወቅህም? ታላቅ ፡ በዓል ፡ ነው ።
የሚያዘጋጁት ፡ የቀበሌዋ ፡ ባለሥልጣኖች ፡
ናቸው ።»
«ወደአደባባይ ፡ እንውጣ ።»
«በፈጠረህ ፡ ተወኝ ። ይህን ፡ አስቀያሚ ፡
ኮት ፡ ለብሼ ፡ አልወጣም ።»
«በምን ፡ ጊዜው ፡ ጠላኸው?»
በመጨረሻም ፡ ብቻዬን ፡ ሔጄ ፡ ከልዕልት ፡
ሜሪ ፡ ጋር ፡ ተገናኘሁ ። ከዚያም ፡ ማዙርካ ፡
እንድንደንስ ፡ ጋበዝኋት ።
በአድናቆትና ፡ ደስታ ፡ በተቀላቀለበት ፡ ዓይን ፡
አየችኝ ፤ «የሚደንሱት ፡ እንዳለፈው ፡ ጊዜ ፡
አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ መስሎኝ ፡
ነበር ፡» በማለት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ፈገግታ ፡
ቁላትላ ፡ ጠየቀችኝ ።
የግሩሽኒትስኪይን ፡ መኖር ፡ አለመኖር ፡
ልብ ፡ ያለችው ፡ አይመስልም ።
«ነገ ፡ እንድ ፡ የሚያስደስት ፡ ነገር ፡ ያጋጥመ
ዎታል ፡» አልኋት ።
«ምንድ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ምስጢር ፡ ነው ... ከምሽቱ ፡ ዳንስ ፡ ሲመጡ ፡ ያዩታል ።»

ምሽቱን ፡ በልዕልት ፡ ሊገ-ቭስካያ ፡ ቤት ፡ አሳለፍኩ ። ከቪራና ፡ ከአንድ ፡ አስቂኝ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ በስተቀር ፡ ሌሎች ፡ እንግዶች ፡ አልነበሩም ። ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ስለነበረ ፡ የመጣልኝን ፡ ሁሉ ፡ ሳወራ ፡ አመሸሁ ። ልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ በፍቅር ፡ ትመለከተኝና ፡ ንግግሬን ፡ በጥንቃቄ ፡ ተከታትላው ፡ ስለነበር ፡ አሳፈረኝ ። ያ ፡ ሁሉ ፡ ጉራዋ ፤ ኩራትዋ ፤ ንቀቷ ፤ ያ ፡ ሁሉ ፡ ውካታዋ ፡ ንዝንዟ ፤ የውሸት ፡ ፈገግታዋ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ግዴለሽነቷ ፡ የት ፡ ገባ?

ቪራ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በጥሞና ፡ ስለተመለከተች ፡ በዚያ ፡ ሕመምተኛ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ሐዘን ፡ ይታይበት ፡ ነበር ። የመስኮቱ ፡ ጥላ ፡ በአረፈበት ፡ ሰፊ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላለች ። በጣም ፡ አሳዘነችኝ ...

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በእኔና ፡ በቪራ ፡ መካከል ፡ ስለነበረው ፡ አስገራሚ ፡ ወዳጅነትና ፡ ፍቅር ፡ በውሸት ፡ ስም ፡ ለሜሪ ፡ አወራላት ፡ ጀመር ።

ስለነበረኝ ፡ ከፍተኛ ፡ ስሜትና ፡ ፍቅር ፡ ስናገር ፡ ቪራን ፡ በሚመለከተው ፡ በኩል ፡ በጥሩ ፡ ሥዕላዊ ፡ ድርሰት ፡ አሸሞንሙኜ ፡ ለልዕልቷ ፡ ስላወራሁት ፡ ከሜሪ ፡ ጋር ፡ ስለማደርገው ፡ መሽኮርመም ፡ ቪራ ፡ ይቅርታ ፡ አደረገችልኝ ።

ከነበረችበት ፡ ወንበር ፡ ተነስታ ፡ ካጠገባችን ፡ መጥታ ፡ ተቀመጠች ። ስሜቷ ፡ ተመልሶ ፡ ከፍ ፡ አለ ... ሐኪሞች ፡ ለጤንነት ፡ በአምስት ፡ ሰዓት ፡ መተኛት ፡ ይበጃል ፡ ያሉት ፡ ትዝ ፡ ያለን ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ሰኔ ፡ ፩ ።

ዳንሱ ፡ ከመጀመሩ ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ በዚያ ፡ ሙሉ ፡ የመኰንን ፡ የመድፈኛ ፡ ልብስ ፡ አሽብርቆ ፡ ብቅ ፡ አለ ። የእጅ ፡ መነጽሩ ፡ የተያያዘበት ፡ የመዳብ ፡ ሰንሰለት ፡ ከሶስተኛው ፡ የኩቱ ፡ ቁልፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሏል ። በትከሻው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጐፈር ፡ የኩፒድን ፡ ክንፍ ፡ ያክላል ። ጫማው ፡ ሲጥ ፡ ሲጥ ፡ ይላል ። በግራ ፡ እጁ ፡ ቡናማ ፡ የሆነ ፡ የእጅ ፡ ሹራብና ፡ ባርኔጣውን ፡ ይዟል ። በቀኝ ፡ እጁ ፡ አጭር ፡ ቁጥጥር ፡ ጸጉሩን ፡ እያፍተለተለ ፡ ይብሱን ፡ ይኮማተራል ። ፍራቻና ፡ በራስ ፡ መተማመን ፡ የተደባለቀበት ፡ ስሜት ፡ በሁኔታው ፡ ይታይበታል ። በዓላዊ ፡ አለባበሱና ፡ የኩራት ፡ አረማመዱ ፡ ከወጣ ንፁት ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ የማይቃረን ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በሳቅ ፡ በተንከተከትው ፡ ነበር ።

ባርኔጣውንና ፡ የእጁን ፡ ሹራብ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ወርውሮ ፡ የኩቱን ፡ ሜፍ ፡ ወደታች ፡ ሳብ ፡ ሳብ ፡ አድርጉ ፡ ከመስተዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሄዶ ፡ ቆመ ። ከክራቫት ፡ ማሠርያው ፡ ወደላይ ፡ እንድ ፡ ጥቁር ፡ ሻሽ ፡ መሐረብ ፡ ከሸሚዙ ፡ እንገት ፡ ላመል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ተጠምጥሟል ። በመስተዋቱ ፡ ከተመ ለከተ ፡ በኋላ ፡ እንሶ ፡ ስላየው ፡ ስቦ ፡ ጅሮ ፡ ግንዱን ፡ አለበሰው ። የዩኒፎርሙ ፡ የሸሚዝ ፡ እንገት ፡ ጠባብ ፡ ስለነበር ፡ ለማስተካከል ፡ የሚያደርገው ፡ ትግል ፡ መላ ፡ ፊቱ ፡ ደም ፡ ለበሰ ።

«በነዚህ ፡ ቁናት ፡ ውስጥ ፡ ልዕልቴን ፡ ፋታ ፡ አ ሳጥተሃት ፡ ነበር ፡ ሲባል?» ሲል ፡ እኔን ፡ ሳይ መለከት ፡ በቀዘቀዘ ፡ ድምጽ ፡ ጠየቀኝ ።

በፑሽኪን ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊውን ፡ ተወዳጅ ፡ ተረት ፡ ተጠቅሜም ፡ «ለእኛ ፡ ለምስኪኖች ፡ ለሻይ ፡ መጠጫ ፡ ምን ፡ ቦታ ፡ አለን!» አልሁት ።

«ስማ ፡ የለበስሁት ፡ ዩኒፎርም ፡ አላማረብኝ ም?.. የማይረባ ፡ አይሁድ ... ብብቴ ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ይዞኛል ... ሽቶ ፡ ቢጤ ፡ የለህም!»

«ስለፈጠረህ ... ሌላስ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ!.. የተለቀለቅኸው ፡ ፓውደር ፡ እንኳ ፡ ይቀረ ናል!»

«ግድ ፡ የለም ፡ ትንሽ ፡ ስጠኝ ።»

እንድ ፡ ብልቃጥ ፡ ሽቶ ፡ በእንገቱና ፡ በሸ ሚዙ ፡ ላይ ፡ አርከፈከፈበት ።

«ወደዳንሱ ፡ ምሽት ፡ ትሄዳለህ?» ሲል ፡ ጠየቀኝ ።

«አልመሰለኝም ።»

«ከልዕልቲቱ ፡ ጋር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ማዙርካ ፡ መደነሱ ፡ ሳይኖርብኝ ፡ አይቀርም ። ውዝዋዜውን ፡ እንኳ ፡ በደንብ ፡ አጣርቼ ፡ አላውቅም ።»

«ማዙርካ ፡ ለመደነስ ፡ ልዕልቷን ፡ ጠይቀሃ ታል?»

«የለም ፡ ገና ፡ አልነገርኋትም ... »

«ተጠንቀቅ ፡ ያልጠበቅኸው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሊያጋጥምህ ፡ ይችላል ...»

«እውነትህን ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ ግንባሩን ፡ በመዳፉ ፡ ከመታ ፡ በኋላ ፡ «ደህና ፡ ሁን ። በሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆሜ ፡ ልጠብቃት ፡ » በማለት ፡ ባር ኔጣውን ፡ ይዞ ፡ ወጣ ።

ከእኩል ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ እኔም ፡ ከቤቴ ፡ ተነሳሁ ። ከክበብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በምግብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ (የፈለጋችሁትን ፡ ስም ፡ ስጡት ፡) ሕዝቡ ፡ በመሰብሰብ ፡ ላይ ፡ ነው ። መስኩቶቹ ፡ በርተዋል ። የፈረሰኞቹን ፡ የሙዚቃ ፡ ዜማ ፡ የምሽቱ ፡ ነፋስ ፡ እያመጣ ፡ ያሰማኛል ። ቀስ ፡ እያልሁ ፡ በሐዘን ፡ እየተለመድሁ ፡ ወደክበቡ ፡ ተጠጋሁ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ያለኝ ፡ እቢያ ፡ ተግባር ፡ የሌሎችን ፡ ተስፋ ፡ ማጨ ናገፍ ፡ መሆን ፡ አለበት? በሚል ፡ ባሕረ ፡ ሐሳብ ፡ ተዋጥሁ ። ያለእኔ ፡ ጣልቄ ፡ ገብነት ፡ የሰዎች ፡ ዕጣ ፡ የማይሰበርና ፡ የማይሞት ፡ ይመስል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ዕድሉ ፡ በሰዎች ፡ ሐዘን ፡ ላይ ፡ እየወሰደ ፡ ይኖለኛል ።ሳልወድ ፡ በግድም ፡ የጓዳይዋ ፡ የክዳተኛ ፡ ባሕርይ ፡ መስጂ ፡ የአም ስተኛን ፡ ክፍል ፡ ሚና ፡ ደጅ ፡ ስጫወት ፡ ኑርያ ለሁ ። ዕድሉ ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ ያገኝችው ፡ ዋጋ ፡ አለ? ምናልባትም ፡ የእኔ ፡ እጣ ፡ የተመደበው ፡ ለመካከለኛው ፡ ክፍል ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ለመ ጻፍ ፡ ቢሆን ፡ ወይስ ፡ ለቤተሰብ ፡ የፍቅር ፡ ድርሰት ፡ ለመድረስ? ፡ ካለዚያስ ፡ ለአንባብያን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚሆኑ ፡ ድርሰቶችን ፡ ለማቅረብ? ማን ፡ ያውቃል? የሕይወታችን ፡ ፍጻሜ ፡ እንደትልቁ ፡ አሌክሳንድር ፡ እንደሎርድ ፡ ባይሮን ፡ ይሆናል ፡ እያሉ ፡ በተስፋ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ዕድሜያቸውን ፡ በሙሉ ፡ ተራ ፡ የመ ንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሆነው ፡ ቀርተው ፡ የለ ምን?

ከምሽቱ ፡ አዳራሽ ፡ ገብቼ ፡ ከሰዎች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅዬ ፡ እካባቢውን ፡ ማጤን ፡ ጀመርሁ ። ግራሽኒትስኪይ ፡ ከልዕልታ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ በታላት ፡ ስሚት ፡ ሲያወራት ፡ እየሁ ። እሷዋ ፡ የማይለሽነት ፡ ጆሮዋን ፡ ለእሱ ፡ ሰጥታ ፡ ማርገ ቢያዋን ፡ ከከንፈሮቿ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አደርጋ ፡ ዓይኖቿ ፡ ከወዲያ ፡ መዲህ ፡ ሲትበለበሉ ፡ ታዩ ኝ ። ንግግራቸውን ፡ ለማዳመጥ ፡ እኔም ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ ጠጋ ፡ አልኋቸው ።

«ልዕልት! የሚያሰታዩኝ ፡ በጣም ፡ ነው ።

ከአለፈው ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ አሁን ፡ በጣም ፡ ተቀ ያረው ፡ አየሁዎት ፡ » ሲላት ፡ ሰማሁ ።

ግራሽኒትስኪይ ፡ እራሱ ፡ ባልገባው ፡ ምፀ ታዊ ፡ በሆነ ፡ ገረፍታ ፡ ተመልከታ ፡

«እርስዎም ፡ ተቀያረዋል ፡» አሰችው ።

«እኔ ፡ ልቀየር ፡ በፍጹም? በፍጹም ፡ ይህ ፡ እንደማይሆን ፡ በደንብ ፡ ያውቃሉ ። በሕይወቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የእርስዎን ፡ ገጽ ፡ የተመለከተ ፡ ሁሉ ፡ ሥዕልዎ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀረፅ ፡ ወደመቃብር ፡ ይወርዳል ።»

«ቢቱም ፡ ... »

«እስከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በደስታ ፡ ያዳም ጡት ፡ የነበረው ፡ ንግግሬ ፡ ምነው ፡ ዛሬ ፡ ዘገነነዎ?»

«ምክንያቱም ፡ ነገር ፡ ሲደጋገም ፡ አልወድ ምና ፡» ብላ ፡ ሳቀች ።

«እቤቱ ፡ ፈጣሪ! እንዴት ፡ ያለ ፡ ስህተት ፡ እደ ረግሁ? ምንኛ ፡ ሞኝ ፡ ነኝ? በጫንቃዬ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጉፈሮች ፡ ለምኞቱ ፡ መሳካት ፡ ምክንያት ፡ ይሆናሉ ፡ ብዬ ፡ እስቤ ፡ ነበር ፡ ... የቀረውን ፡ ዘመኔን ፡ በሙሉ ፡ ዓይኖችዎ ፡ ያረፉበትን ፡ ያን ፡ የወታደር ፡ ወፍራም ፡ ካፖርት ፡ ለብሼ ፡ ባሳል ፈው ፡ በተሻለኝ ።»

«ከሆነስ ፡ ያ! ትልት ፡ ካፖርት ፡ ይበልጥ ፡ ይስ ማማዎ ፡ ነበር ።»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከተደበቅሁበት ፡ ወጥቼ ፡ ልዕልቲቷን ፡ እጅ ፡ ነሳሁ ። እሷም ፡ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማፈር ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀች ፡

«ሙሴ ፡ ፔቾሪን! ለሙሴ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ያ ፡ አረጅም ፡ ካፖርት ፡ ይበልጥ ፡ አያስማማቸውም?»

«አያመስለኝም ። ይህ ፡ አዲስ ፡ ዩኒፎርም ፡ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ ወጣት ፡ አድርጐታል ።»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ይህን ፡ ስድብ ፡ በቀላሉ ፡ ሊቀበለው ፡ አልቻለም ። እንደማንኛውም ፡ ጐረምሳ ፡ ሽማግሌ ፡ መባል ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ይሰማዋል ። ከዛም ፡ ሌላ ፡ በፍቅር ፡ የተኮፋተሩት ፡ የግንባሩ ፡ ሽንትሮች ፡ በሽምግልና ፡ የመጡ ፡ አድርጐ ፡ ሰው ፡ እንዲወስድለት ፡ ይፈልጋል ። ከግር ፡ እስከራሴም ፡ ከገላመጠኝ ፡ በኋላ ፡ በእግሩ ፡ ምድሩን ፡ ረግጦ ፡ በቆምንበት ፡ ጥሎን ፡ ሄደ ።

«ምንም ፡ እንኳ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ነገረ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ አስቂኝ ፡ ቢሆንም ፡ እስከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከዛ ፡ ትልቅ ፡ ካፖርቱ ፡ ጋር ፡ ያስደስትዎ ፡ እንደነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡» አልኋት ።

በዓይኗ ፡ ብቻ ፡ አተኩራ ፡ ተመልከታኝ ፡ ዝም ፡ አለች ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ ልዕልቷን ፡ ሲከታተል ፡ አመሸ ። ወይ ፡ አብሯት ፡ ይደንሳል ፡ ካለዚያም ፡ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ሆኖ ፡ ይጫወታል ። በዓይኑም ፡ ሊበላት ፡ ያርሳል ።

ንዝንዙና ፡ መጓተቷ ፡ አናጋገሩ ፡ እጅ ፡ እጅ ፡ አላት ። በሶስተኛው ፡ ዙሪያ ፡ ዳንስ ፡ ላይ ፡ ከልቧ ፡ ጠላችው ።

ወደኔም ፡ መጥቶ ፡ እጁን ፡ አለፍ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ «ይህን ፡ ካንተ ፡ አልጠበቅሁም ፡ ነበር ፡» አለኝ ።

«ስለምንድነው ፡ የምታወራ?»

«ከእሷ ፡ ጋር ፡ ማዙርካ ፡ ልትደንስ ፡ ነው? እራሷም ፡ ነግራኛለች ፡ ...» ሲል ፡ በለሆሳስ ፡ ድምጽ ፡ ጠየቀኝ ።

«ታዲያ ፡ ይህ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ እንዴ?»

«እንዴታ! ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ የምጠብቀው ፡ ከሌሎች ፡ ልጃገረዶች ፡ እንጂ ፡ ከእሷ ፡ አልነበረም ... ግዴለም ፤ ቂሜን ፡ እበቀላለሁ ።»

«ያንን ፡ ትልቅ ፡ ካፖርትህን ፡ ወይም ፡ የትከሻህን ፡ ጐፈር ፡ ተቀየምበት ፡ እንጂ ፤ እሷን ፡ ምን ፡ አርጊ ፡ ትላታለህ ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አልወድህም ፡ በማለቷ ፡ ጥፋተኛ ፡ ናት ፡ ትላለህ?»

«ለምን ፡ ተስፋ ፡ ሰጠችኝ?»

«እንተ ፡ ማን ፡ ተስፋ ፡ አድርግ ፡ አለህ? አንድን ፡ ነገር ፡ መፈለግና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ያባት ፡ ነው ። ግን ፡ በዚያ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ተስፋ ፡ መጣል ...»

«ዛሬ ፡ ጊዜያዊ ፡ ድል ፡ አግኝተሃል ፡» በማለት ፡ የማሾፍ ፡ ፈገግታውን ፡ አሳየኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማዙርካው ፡ ተጀመረ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከልዕልቷ ፡ አልፎ ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ አላስነሳም ። የቀሩትም ፡ በምሽቱ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ በየደ ቂቃው ፡ ተሽቀዳድመው ፡ ለዳንስ ፡ የሚጋብዝ ዋት ፡ እሷን ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉም ፡በኔ ፡ ላይ ፡ የተዶለተ ፡ ሸር ፡ እንደሆነ ፡ ገባኝ ። ይህም ፡ ዓይነት ፡ ድርጊት ፡ እኔን ፡ ይጠቅመኛል ፡ እን ጂ ፡ አይጐዳኝም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ ትፈልጋለች ። ሆኖም ፡ ሁኔታው ፡ አልፈቀደ ላትም ። ይህም ፡ ያለመቻል ፡ አጋጣሚ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለመወያየት ፡ ያላትን ፡ ፍላጐት ፡ ይበልጥ ፡ እያበረታው ፡ ይሄዳል ።

አንዴ ፡ ሁለቴ ፡ እጅዋን ፡ ጨበጥ ፡ አድርጌ ፡ ያዝኋት ። በሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳት ናገር ፡ እጅዋን ፡ አስለቅቃ ፡ ወሰደችው ።

ማዙርካው ፡ እንዳለቀ ፤ «ዛሬ ፡ ማታ ፡ እንቅልፍ ፡ አያወስደኝም ፡» አለችኝ ።

«የግሩሽኒትስኪይ ፡ ጥፋት ፡ ነዋ ።»

«አይደለም ።» በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ በሐዘ ንና ፡ በሐሳብ ፡ የተለዋወጠውን ፡ ገጿን ፡ ሳይ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ እጆቿን ፡ እንደምስማቸው ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረግኩ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደየቤቱ ፡ መሄድ ፡ ጀመረ ። እኔም ፡ ልዕልቲቷን ፡ ወደሠረገላው ፡ ገድፌ ፡ ካስገባሁ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ታል ፡ ሳልተነፍስ ፡ እነዚያን ፡ ትናንሽ ፡ ጣቶችዋን ፡ ወሰጀ ፡ ከከንፈ

ሮቿ ፡ አላጠፍኋቸው ። በጣም ፡ ጨለማ ፡ ስለ ነበር ፡ ማንም ፡ አላየኝም ።

ያለመጠንም ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ወደአዳራሹ ፡ ተመለሽ ፡ ገባሁ ።

ጉበዛዝት ፡ አንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ከበው ፡ ቁጭ ፡ ብለዋል ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከመሃላቸው ፡ ገብ ፡ ብሏል ። እኔ ፡ ስገባ ፡ ወዲያውኑ ፡ ጨዋታቸውን ፡ አቆሙ ። የሚነጋገሩበት ፡ አርእስት ፡ እኔ ፡ ሳልሆን ፡ አልቀርም ። በዚያን ፡ ሰሞን ፡ ከተደ ረገው ፡ የዳንስ ፡ ምሽት ፡ በኋላ ፡ ብዙዎች ፤ በተለይም ፡ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፤ ከፍተኛ ፡ ጠላቱ ፡ ሆኗል ። በአሁኑም ፡ ጊዜ ፡ በግሩሽ ኒትስኪይ ፡ የሚመራ ፡ አንድ ፡ የኔ ፡ ተቃዋሚ ፡ ቡድን ፡ ተቋቁሟል ። የግሩሽኒትስኪይም ፡ ኩራ ትና ፡ ድፍረት ፡ አይወራ ።

ሁኔታው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። ጠላቶ ቼን ፡እወዳለሁ ። ያ ፡ ፍቅር ፤ ግን ፡ ከርስትያኖች ፡ ካላቸው ፡ መውደድ ፡ የተለየ ፡ ነው ። ያስቁ ኛል ። ንቁም ፡ እንድሆን ፡ ይገፋፉኛል ። እኔ ፡ የሕይወቴ ፡ ትርጉም ፡ የምለው ፡ ጥንቁቅ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፤ የያንዳንዱን ፡ እስተያየትና ፡ የያን ዳንዱን ፡ ታል ፡ ትርጉም ፡ ማጤን ፤ የያንዳ ንዱን ፡ ሰው ፡ ውስጣዊ ፡ እስተሳሰብ ፡ ገምቶ ፡ መረዳት ፤ የተዶለተን ፡ ነገር ፡ ማክሸፍ ፤ የተ ታለሉ ፡ መስሎ ፡ ቀርቦ ፡ ብዙ ፡ የተለፋበትን ፡ የሴራ ፡ ቦምብ ፡ በእንድ ፡ ቡጢ ፡ ማፍረሱ ፡ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በእራት ፡ ሰዓት ፡ በሙሉ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከዚያ ፡ የፈረሰኛ ፡ ሻምበል ፡ ጋር ፡ ሲንሾካ ሾክ ፡ አመሸ ።

ሰኔ ፡ ፮ ።

ዛሬ ፡ ጥዋት ፡ ቬራ ፡ ከባልዋ ፡ ጋር ፡ ኪስሎቮድስክ ፡ ሄደች ። ወደልዕልት ፡ ሊጐቭስካያ ፡ ቤት ፡ ስሄድ ፡ በመንገድ ፡ ተገናኘን ። በሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለች ፡ ቅሬታ ፡ በተሞላበት ፡ ዓይን ፡ ተመልከታኝ ፡ ሰላም ፡ ብላኝ ፡ አለፈች ።

ጥፋተኛው ፡ ማን ፡ ነው? ለብቻዋ ፡ እንዳገኛት ፡ ለምን ፡ ዕድል ፡ አልሰጠችኝም? ፍቅርዋ ፡ እንደእሳት ፡ ያለነዳጅ ፡ ጠፋ ፡ ነው ። ምናልባትም ፡ በልመና ፡ ያልተሳካልኝ ፡ በቅናት ፡ ይሳካ ፡ ይሆን?

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ልዕልቲቷ ፡ ቤት ፡ ቁጭ ፡ አልሁ ። ሚሪ ፡ ታማ ፡ ስለነበረ ፡ ብቅ ፡ አላለችም ። አመሻሽም ፡ ወደአደባባይ ፡ አልወጣችም ። ብቅ ፡ አላለችም ። በቅርቡ ፡ በተፈጠረው ፡ የበቀል ፡ ተወዛ ፡ ቡድን ፡ አባሎችም ፡ በእጅ ፡ የሚያዝ ፡ መነጽራቸውን ፡ ደንቅረው ፡ ተሰብስበው ፡ ያረታቸውን ፡ ነሳቱው ፡ ቆመዋል ። ልዕልቲቷም ፡ በመታመሟ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ። ቤት ፡ ባትውል ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ቡድን ፡ አንድ ፡ አስፀያፊ ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ አይመለስም ፡ ነበር ። የግሩሽኒትስኪ ፡ ወጉር ፡ ተንጨፍሯል ። እጅግ ፡ በጣም ፡ ተናደደ ።

ክብሩ ፡ ስለተነካበት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ ወደኋላ ፡ አይልም ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ሐዘንና ፡ ቆራጥነት ፡ እንኳ ፡ ወሯቸው ፡ አስቂኝ ፡ ናቸው ።

ወደቤቱ ፡ ስመለስ ፡ በዛ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የጐደለ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ተሰማኝ ። ይኸውም ፡ እሷን ፡ አላየኋትም! ታማለች! ፍቅር ፡ ነው?.. እያሠኝም!

ሰኔ ፡ ፯ ።

ልዕልት ፡ ሊጐቭስካያ ፡ ዘወትር ፡ ጥዋት ፡ ወደየርሞሎቭ ፡ ፀበል ፡ በምትሄድበት ፡ ወቅት ፡ በቤቷ ፡ ደጃፍ ፡ አለፍኩ ። ልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ከመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ በሐሳብ ፡ ተውጣ ፡ ቁጭ ፡ ብላለች ። ገና ፡ ስታየኝ ፡ ከመቀመጫዋ ፡ ብድግ ፡ አለች ።

ወደክፍሉ ፡ ዘው ፡ ብዬ ፡ ገባሁ ። የእካባቢውን ፡ ባሕል ፡ በመጠቀም ፡ «ግባ ፡» ሳልባል ፡ ወደእንግዳ ፡ ቤት ፡ አመራሁ ።

የልዕልቷ ፡ ያ ፡ ውብ ፡ መልኳ ፡ ገርጥቷል ። ከወንበሩ ፡ መደገፊያ ፡ ክንዷን ፡ አሳርፋ ፡ ከፒያኖው ፡ አጠገብ ፡ ቁማለች ። እጅዋ ፡ ላመል ፡ ይንተጠቀጠል ። ቀስ ፡ ብዬ ፡ ተጠግቼ ፡ እንዲህ ፡ አልኋት ፡

«በኔ ፡ ላይ ፡ ተናደዋል?»

አንገቷን ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ በጠለቁ ፡ ዓይኖቿ ፡ ከተመለከተችኝ ፡ በኋላ ፡ ራሷን ፡ ነቀነቀች ።

t.me/OLDBOOKSPDF





ከንፈሮቿ ፡ ለመናገር ፡ ይሻሉ ። ግን ፡ አልቻለችም ። ዓይኖቿ ፡ በእንባ ፡ ተሞሉ ። ተመልሳም ፡ ከወንበሯ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ ፊቷን ፡ በመዳፎቿ ፡ ጋረደችው ። እጆቿዋንም ፡ ያዝ ፡ አድርጌ ፤

«ምን ፡ ሆነዋል ?» ብዬ ፡ ጠየቅኋት ።

«እባክዎ ፡ ይተውኝ! እርስዎ ፡ ለኔ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ አክብሮት ፡ የለዎትም!»

ጥቂት ፡ እርምጃዎች ፡ ወደኋላዬ ፡ አፈገፈግሁ ። ተመልሳም ፡ ድፍት ፡ ብላ ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ወንበር ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ በድንጋጤ ፡ አፍጣ ፡ እየችኝ ...

በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የመዝጊያውን ፡ እጀታ ፡ በእጄ ፡ ይዤ ፡ እንዲህ ፡ አልኋት ፤

«ልዕልት ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ! እንዳበደ ፡ ሰው ፡ መሆኔ ፡ ይገባኛል ... ሁለተኛ ፡ ግን ፡ እንደማይደግመኝ ፡ አረጋግጥልዎታለሁ ። በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ መቼም ፡ አያውቁ ፤ መደፈትም ፡ ሊያውቁት ፡ አይችሉም ። ለርስዎ ፡ ይህ ፡ ላይሻልዎ ፡ አይቀርም ። ይህና ፡ ይሁኑ ።»

ከክፍልዋም ፡ ወጥቼ ፡ ሰሄድ ፡ የለቅሶ ፡ ስቅስቅታ ፡ የሰማሁ ፡ መሰለኝ ።

አመሻሹን ፡ በሙሉ ፡ የማሽነ ፡ ተራራ ፡ አካባቢ ፡ ሲዞር ፡ ያክሞኝ ፡ ለሰንበር ፡ መያቤቱ ፡ ተመልሼ ፡ በቁመናዬ ፡ ባልጋው ፡ ላይ ፡ ተዘረርሁ ።

ወዲያውም ፡ ቪርነር ፡ ሊጐበኘኝ ፡ መጣ ።

«ልዕልት ፡ ሊጐብኝህያን ፡ ሊያገቡ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ እውነት ፡ ነው?»

«ለምን ፡ ያጠያቁኛል?»

«ከተማው ፡ በሙሉ ፡ የሚያወራው ፡ ስለዚሁ ፡ ነው ። የበሽተኞቹም ፡ አበዶ ፡ ዜና ፡ ይህ ፡ ነው ። ከወበልተኞች ፡ የሚያመልጥ ፡ ወሬ ፡ መቼም ፡ የለም ።»

ይቺ ፡ የግሩሽኒትስኪይ ፡ ቀልድ ፡ እንደሆነች ፡ ገባኝ ።

«የዚህን ፡ ሐሜት ፡ ሐሰተኛነት ፡ ለርስዎ ፡ በምስጢር ፡ ያህል ፡ ነገ ፡ ወደኪስሎቮድስክ ፡ መሄዴን ፡ ይወቁ ።»

«ልዕልት ፡ ሜሪም ፡ ይሄዳሉ?»

«የለም ፤ እሷ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ትቆያለች ...»

«ታዲያ ፡ ሊያገቧት ፡ እያስቡም ፡ ማለት ፡ ነዋ?»

«ዶክተር! ዶክተር! እስቲ ፡ በጥሞና ፡ ይመልከቱኝ ፡ እሁን ፡ እኔ ፡ የማገባ ፡ ሰው ፡ እመስላለሁ?»

«ያሁን ፡ ማለቱ ፡ እንኳ ፡ አይደለም ... ሆኖም ፡ እኮ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያጋጥማል ።» ካለ ፡ በኋላ ፡ ለመግ ፡ ያህል ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ። «ጨዋ ፡ ሰው ፡ በግድ ፡ ባለትዳር ፡ መሆን ፡ አለበት ። በዚህም ፡ ሌላ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አጋጣሚ ፡ እንዳለ ፡ አስቀድመው ፡ የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰኔ ፤ ፲ ።

ኪስሎቮድስክ ፤ ከገባው ፤ ሶስት ፤ ቀን ፤ ሆነ ኝ ። ከዐበሉ ፤ ወይም ፤ በሽርሽር ፤ ቦታ ፤ ላይ ፤ ሼራን ፤ ሁልጊዜ ፤ እገኛታለሁ ። ጥዋት ፤ ተነ ስቼ ፤ ከመስኮቱ ፤ ጥግ ፤ ቁጭ ፤ እልና ፤ ያን ፤ መያዣ ፤ ያለውን ፤ መነጽር ፤ ደንቅሬ ፤ ወደሷ ፤ ቤት ፤ መስኮት ፤ መመልከት ፤ እጀምራለሁ ። እሷም ፤ በተስማማነው ፤ መሰረት ፤ አስቀድማ ፤ ለብሳ ፤ ስለምትጠብቀኝ ፤ ከቤታችን ፤ ወረድ ፤ ብሎ ፤ ወደዐበሉ ፤ ከሚያመራው ፤ ቁልቁለት ፤ አለው ፤ አትክልት ፤ ውስጥ ፤ በድንገት ፤ የተገ ናኘን ፤ እንመስላለን ። በመጋቢው ፤ ንጹህ ፤ የተራራ ፤ አየር ፤ ወሏ ፤ ተመልሷል ፤ ጉልበትም ፤ አግኝታለች ። ናርዛን ፤ የኃያላን ፤ ምንጭ ፤ ተብሎ ፤ የሚጠራው ፤ እንዲሁ ፤ አይደለም ። የቀበሌው ፤ አካባቢ ፤ ነዋሪዎች ፤ የኪስሎቮድስክ ፤ አየር ፤ ፍትርን ፤ ያጠነክራል ፤ ብለው ፤ ያምናሉ ። በማሹክ ፤ ተራራም ፤ የተጀመረ ፤ የፍቅር ፤ አበባ ፤ የሚፈነድቀው ፤ በዚሁ ፤ ቦታ ፤ ነው ። በጠባብ ፤ መንገድ ፤ ዳርና ፤ ዳር ፤ ችምችም ፤ ብለው ፤ የበቀሉት ፤ የዛፎች ፤ ጥላ ፤ በፏፏቴው ፤ ሞጋግ ፤ ጢስ ፤ ለብሶ ፤ ግብስባሽ ፤ ቅጠላ ት ፤ ከጋማት ፤ ጋማት ፤ እያጋጨ ፤ ሰማያዊ ፤ ተራራዎችና ፤ በየቦታው ፤ ተንጠልጥለው ፤ የሚታዩትን ፤ በሀዘን ፤ ፀጥታ ፤ የተዋጡትን ፤ ሸለቆች ፤ በርግዶ ፤ በሚፈሰው ፤ ወንዝ ፤ ላይ ፤

ያስጠነቅቁም ፤ እናቶች ፤ አይጠፉም ። ስለዚ ህም ፤ እኔ ፤ እንደወዳጂ ፤ የምመክርዎት ፤ ይበ ልጥ ፤ እንዲያስቡበት ፤ ነው ። ይህ ፤ የፀበል ፤ ቦታ ፤ አደገኛ ፤ ነው ። ስንት ፤ ወጣት ፤ ወንዶች ፤ የተሻለ ፤ ሕይወት ፤ መኖር ፤ ሲችሉ ፤ ተቻኩ ለው ፤ ለተከሊል ፤ ቱርባን ፤ ወደቤተ ፤ ክርስት ያን ፤ እምርተዋል ። ቢያምኑም ፤ ባያምኑም ፤ እኔን ፤ እንኳ ፤ ሊድሩኝ ፤ ፈልገው ፤ ነበር! ይህም ፤ የእንድ ፤ በቀበሌው ፤ የሚገኙ ፤ የገረ ጣች ፤ ልጃገረድ ፤ እናት ፤ ሥራ ፤ ነው ። የልጃ ቸው ፤ የገረጣው ፤ መልክ ፤ ሊመለስ ፤ የሚች ለው ፤ ካገባች ፤ በኋላ ፤ መሆኑን ፤ አስረዳኋቸው ። በዚህም ፤ ጊዜ ፤ ምስጋና ፤ የተሞላባቸውን ፤ ዓይኖች ፤ በእንባ ፤ እንጠርበው ፤ ልጃቸውን ፤ እንዳገባና ፤ ያላቸውን ፤ ሀብት ፤ በሙሉ ፤ (አምላ ፤ ገበሬዎች) አብረው ፤ ሸለሙኝ ። እኔም ፤ ለትዳር ፤ ያልተዘጋጀሁ ፤ መሆኔን ፤ ገለጽሁላቸው ።»

ቬርነር ፤ በጊዜው ፤ አስፈላጊውን ፤ ማስጠን ቀቅያ ፤ እንደሰጠኝ ፤ አምኖ ፤ ወደቤቱ ፤ ተመ ለሰ ።

ከቬርነር ፤ አንጋገር ፤ የተረዳሁት ፤ ነገር ፤ ቢኖር ፤ ስለእና ፤ ስለልዕልቲቱ ፤ የሚያስተጋ ባው ፤ ወሬ ፤ ከተሣውን ፤ እንዳጥለቀለቀው ፤ ነው ። ግሩሽኒትስኪ ፤ ለዚህ ፤ ሥራው ፤ ተገቢ፣ ዋጋ ፤ ማግኘት ፤ አለበት!

t.me/OLDBOOKSPDF

በተለያየ ፡ ቀንድ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ገብቶ ፡ ራሱን ፡ አስደሳች ፡ መቼ ፡ ጠፋ ፡ ሞልቶ፣ ይህን ፡ መሳይ ፡ ዋዛ ፡ እኔ ፡ አልሻም ፡ ከቶ ።

ግሩሽኒትስኪያና ፡ ቡድኑ ፡ በየለቱ ፡ በዚያ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲፈነጥዙ ፡ ይውላሉ ። ሰላምም ፡ የሚለኝ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ። የመጣው ፡ ግና ፡ ትላንትና ፡ ሲሆን ፡ ያለ ፡ ተራው ፡ ፀበል ፡ መነከር ፡ አለብኝ ፡ በማለት ፡ ከሶስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ተሟግቷል ፤ ያጋጠመውም ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ተነጫናጭ ፡ ጠባይ ፡ አውርሶታል ።

ሰኔ ፡ ፲፩ ።

በመጨረሻም ፡ ደረሱ ። የሠረገላቸውን ፡ ድምጽ ፡ የሰማሁት ፡ ከመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ነው ። የልቤም ፡ ትርታ ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ ። ይህስ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው? ፍቅር ፡ ያዘኝ ፡ ማለት ፡ ነው? ተፈጥሮዬ ፡ ልዩ ፡ ስለሆነ ፡ ከኔ ፡ ሁሉንም ፡ መጠበቅ ፡ ይቻላል ።

ምሳ ፡ የበላሁት ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ነበር ። ልዕልት ፡ ሊጉቭስካያ ፡ በፍቅር ፡ ዓይን ፡ ሲመለከቱኝ ፡ አመሸ ። ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ ከልጃቸው ፡ ጐን ፡ ሠር ፡ አላሉም ... እም! መጥፎ ፡ ምልክት ፡ ነው! ቬራ ፡ በልዕልት ፡ ሚሪ ፡ በጣም ፡ ቀንታለች ። ይህም ፡ በመጨረሻ ፡

አርፏል ። ያየሩ ፡ መዓዛ ፡ ከረጃጅም ፡ የደቡብ ፡ ሳሮችና ፡ ነጫጭ ፡ ቁጥቋጦዎች ፡ ጋር ፡ ተቀ ሀዶ ፡ ላካባቢው ፡ ልዩ ፡ ሽታ ፡ ሰጥቶታል ። ከሸለቆው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ወርደው ፡ ከፖ ድኩሞክ ፡ ወንዝ ፡ የሚቀላቀሉት ፡ የጅረቶች ፡ ድምጽ ፡ ለጆሮ ፡ ልዩ ፡ የሙዚቃን ፡ ድምጽ ፡ ያሰማል ። ከወዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ሰፈሙ ፡ ሸለቆ ፡ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ከማሸብረቁም ፡ በላይ ፡ አቋርጣው ፡ የምታልፍ ፡ አንድ ፡ አቧራማ ፡ መንገድ ፡ ትታያለች ። ይኸን ፡ መንገድ ፡ ባየሁ ፡ ቁጥር ፡ አንዲት ፡ ጉንጮቿ ፡ የሮዝ ፡ ቀለም ፡ የለበሱ ፡ አንገቷን ፡ በመስኮቱ ፡ ብቅ ፡ ያደረገች ፡ ቆንጆ ፡ ሴት ፡ የተቀመጠችበት ፡ ሠረገላ ፡ ውልብ ፡ ብሎ ፡ ያለፈ ፡ ይመስለኛል ። እስካሁን ፡ ብዙ ፡ ሠረገላዎች ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ አልፈዋል ። እኔ ፡ የማስባት ፡ ሴት ፡ ያለችባት ፡ ሠረገላ ፡ ግን ፡ ብቅ ፡ አላለም ። ከሠፈሩ ፡ ውጭ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰፍረውበታል ። ከኔም ፡ መኝታ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የሚገኘው ፡ ሆቴል ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የመብራት ፡ ብርሃን ፡ ይታየኛል ። እስከውድትት ፡ ድረስ ፡ የመለኪያዎቹ ፡ ግፊት ፡ ያስተጋባል ።

በዚህ ፡ አካባቢ ፡ እንዳለው ፡ የካኽቲያን ፡ ቪኖና ፡ ፀበል ፡ ያለ ፡ በየትም ፡ ቦታ ፡ አይገኝም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ፡ ማስታወሻ ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ ባንዲት ፡ ሴት ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፡ ምን ፡ ትል ፡ ይሆን? «ውሸት!» ብላ ፡ በኩራት ፡ መደን ፋታ ፡ አይቀርም ።

ገጣሚዎች ፡ ግጥም ፡ መደርደርና ፡ ሴቶችም ፡ ግጥማቸውን ፡ ማንበብ ፡ ከጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ (ለዚህም ፡ ይመሰገናሉ) በየጊዜው ፡ ተደጋግሞ ፡ መላእክት ፡ ተብለው ፡ የተወደሱ በትን ፡ ከዚያ ፡ ጋር ፡ ልባቸው ፡ እምነው ፡ ተቀብ ለውታል ። የረሱት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ ገጣ ሚዎች ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጣቸው ፡ ኔሮን ፡ ግማሽ ፡ እምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሊያሞግሱት ፡ ችለ ዋል ።

ከፀሐይ ፡ በታች ፡ ከሴቶች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወዳጅ ፡ የማላውቅና ፡ ለነሱም ፡ ስል ፡ አእም ሮዬን ፣ የወደፊት ፡ ዕድሌን ፡ ሕይወቴን ፡ ለመሰ ዋት ፡ የተዘጋጀሁ ፡ እኔ ፣ እንዲህ ፡ አድርጌ ፡ ሳንቋሸሻቸው ፡ ለጆሮ ፡ ይከብዳል ። ይህን ፡ የማደርገው ፡ ለበቀል ፣ ወይም ፡ ራስ ፡ ወዳድ ፡ ሆኜ ፡ አይደለም ። በዚህም ፡ ተገፋፍቼ ፡ ግን ኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ የጣ ለውን ፡ ታምራዊ ፡ ሻሸ ፡ ገልጾ ፡ እውነተኛ ፡ ጠባያቸውን ፡ ለማየት ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ዘዴ ፡ ለመውሰድ ፡ ፈልጌም ፡ እንዳልሆን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የለም ፣ ስለነሱ ፡ የምናገረው ፡ በሙሉ ፡ የተገኘው ፣

በሷ ፡ ላይ ፡ ያገኘሁት ፡ ትልቅ ፡ ድል ፡ ነው ። ሴት ፡ ጠላትዋን ፡ ለማጥቃት ፡ የማትሞክ ረው ፡ ሥራ ፡ የለም ። አንዲት ፡ ሴት ፡ ሌላዋን ፡ ስለወደድሁ ፡ ብቻ ፡ የወደደችኝ ፡ ሴት ፡ እንደ ነበረች ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። እንደሴት ፡ ሞን ቅላትና ፡ አስተሳሰብ ፡ ግራ ፡ የሚያጋባ ፡ ነገር ፡ የለም ። ሴቶችን ፡ እራሳቸው ፡ ለማሳመን ፡ ከሚችሉበት ፡ ደረጃ ፡ ሳይደርሱ ፡ እነሱን ፡ በአንድ ፡ ነገር ፡ ለማሳመን ፡ በጣም ፡ አስቸ ጋሪ ፡ ነው ። ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ የማይቀበ ሉበት ፡ እምነታቸው ፡ ከሁሉ ፡ የተለየ ፡ ነው ። የነሱን ፡ ፍልስፍና ፡ ለመረዳት ፡ በሞንቅላታ ቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ የተጠ ይቅ ፡ (የሎጂክ) አስተሳሰብ ፡ እውጥተን ፡ መወ ርወር ፡ ይኖርብናል ።

«ይህ ፡ ሰው ፡ ይወደኛል ፤ ግን ፡ ትዳር ፡ ያለኝ ፡ ሴት ፡ ነኝ ። ስለሆነም ፡ እሱን ፡ መው ደድ ፡ የለብኝም ።»

የሴቶች ፡ ተጠይቅ ፡ (ሎጂክ) ግን ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ይቀርባል ፤ «ባለትዳር ፡ ስለሆንሁ ፡ እሱን ፡ መውደድ ፡ የለብኝም ። ግን ፡ ልቡ ፡ ስለሚወደኝ ...»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያሉትን ፡ ነጠብጣቦች ፡ ለመሙላት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መጠየቅ ፡ አያስፈ ልግም ። አእምሮ ፡ ምንም ፡ አይነግረም ። ዓይ ንና ፡ ምላስ ፡ ካለ ፡ ልብ ፡ ይገልጻቸዋልና ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በተራጋ ፡ መንፈስ ፡ ባንጉሉ ፡ አበጥሬ ፡ የልብን ፡ ፍላጐት ፡ በጠለቅ ፡ መርምሬ ፣*

እኔ ፡ የማውቃቸው ፡ ያህል ፡ ወንዶች ፡ በሙሉ ፡ እንዲያውቋቸው ፡ የሴቶች ፡ ፍላጐት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ምክንያቱም ፡ እኔ ፡ ሴቶችን ፡ መፍራት ፡ ካቆምሁበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮና ፡ ደካማ ፡ ባሕሪያቸውን ፡ ማወቅ ፡ ከቻልሁ ፡ ወዲህ ፡ ከበፊቱ ፡ የበለጠ ፡ ይበልጥ ፡ እየወደድኋቸው ፡ ሄጃለሁ ።

በነገራችን ፡ ላይ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ቪርነር ፡ ሴቶችን ፡ «ነፃዋ ፡ እየሩሳሊም» በሚለው ፡ በታሰ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከተገለጸው ፡ ደን ፡ ጋር ፡ ሲያወዳድራቸው ፡ ነበር ። «ጠጋ ፡ በለው ። አካባቢህ ፡ በሙሉ ፡ በተግባር ፤ በኩራት ፤ በክብር ፤ ባካባቢ ፡ አስተያየት ፤ በፈዝ ፤ በጥላቻ ... ፍራቻ ፡ ተወሯል ። ግን ፡ ዞር ፡ ብለህ ፡ አትመልከተው ፤ መንገድህን ፡ ቀጥል ። እስ ደንጋጭ ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ በሙሉ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይጠፋሉ ። ብርሃናማ ፡ ከሆነ ፡ ባረን ጓደ ፡ ቅጠላት ፡ ከተለወጠ ፡ ገላጣማ ፡ ቦታ ፡ ትደርሳለህ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልብህ ፡ ተደናግጦ ፡

* በተራጋ ፡ መንፈስ ፡ ባንጉሉ ፡ አበጥሬ ፡ ይህ ፡ ኤቭጌኒይ ፡ ኦኔጊን ፡ ከተባለው ፡ ከፑሽኪን ፡ ድርሰት ፡ ከመጨረሻዎቹ ፡ መስመሮች ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ከመጀመሪያው ፡ አርምጃ ፡ ወደኋላ ፡ ዞር ፡ ካልህ ፡ አንተን ፡ አያርገኝ!» ይላል ፡ ታስ ።

ሰኔ ፡ ፲፪ ።

የባሬው ፡ ምሽት ፡ በብዙ ፡ አጋጣሚዎች ፡ የተሞላ ፡ ነበር ። ከኪስሎቮድስክ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቨርስታ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የፖድኩሞክ ፡ ወደሚፈስበት ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ቀለበት ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ አንድ ፡ ስንጥር ፡ ቋጥኝ ፡ ይገኛል ። ይኸም ፡ የተፈጥሮ ፡ ስንጥር ፡ ቋጥኝ ፡ በጀርባው ፡ ተንጣሎ ፡ ለሚገኘው ፡ ሸለቆ ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ነው ። ያመሻሽ ፡ ፀሐይ ፡ ለዓለም ፡ የመጨረሻ ፡ የብርሃን ፡ ፊትዋን ፡ የምታሳየው ፡ በዚህ ፡ የቋጥኝ ፡ ስንጥር ፡ መስኩት ፡ ነው ። ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ መስኩት ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ የምታየውን ፡ ፀሐይ ፡ ለመመልከት ፡ ከብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ተሰብስበዋል ። እውነት ፡ እንኳንገር ፡ ከተባለ ፡ ካሉት ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ግሩም ፡ ተፈጥሮ ፡ ለማየት ፡ ማንም ፡ የለ ። እኔ ፡ ወደዚህ ፡ ቦታ ፡ የሄድኩት ፡ ከልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ጉን ፡ ቋሞ ፡ ብዬ ፡ ነው ። ወደቤታችን ፡ ስንመለስ ፡ ፖድኩሞክን ፡ መሻገር ፡ ነበረብን ። በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ የሚሰርፁ ፡ ምንጮች ፡ ላይቀሩ ፡ በጣም ፡ እደገኞች ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ እንደማዕበሎች ፡ ኃይል ፡ ጥልቀታቸውም ፡ በየጊዜው ፡ ይቀየ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራል ። ትላንትና ፡ ድንጋያማ ፡ የነበረው ፡ ወንዝ ፡ አሁን ፡ የውኃ ፡ ተሞልቶ ፡ ጥልቅ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የልዕልቷን ፡ የፈረስ ፡ ልጓም ፡ እየጐተተው ፡ እስከጉልበት ፡ የሚደርሰውን ፡ ወንዝ ፡ ማቋረጥ ፡ ጀመርሁ ። ወንዙን ፡ እየተጋፋን ፡ አግድም ፡ ለማቋረጥ ፡ ተያያዝነው ። ወንዙን ፡ ሲሻገሩ ፡ ውኃ ፡ ውኃውን ፡ ማየት ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ያዞራልና! ይህንንም ፡ ለልዕልት ፡ ሚሪ ፡ ረስቼው ፡ ሳልነግራት ፡ ቀረሁ ።

ከወንዙም ፡ መሃል ፡ ስንደርስ ፡ በድንገት ፡ ልዕልቲቷ ፡ እየተወዛወዘች ፡ «አዞረኝ» እያለች ፡ ትጮኽ ፡ ጀመር ። እኔም ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደሷ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ በእጆቼ ፡ ለስላሳ ፡ ዳሌዋን ፡ አቀፍኋት ።

በሹክሹክታ ፣ «ቀና ፡ ይበሉ! አይፍሩ ፣ግድ ፡ የለዎትም ። ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፡» አልኋት ።

ትንሽም ፡ እንደተሻላት ፡ እጅዋን ፡ ከሽንጯ ፡ ለማላቀቅ ፡ ስትሞክር ፡ ይብሱን ፡ አጥብቄ ፡ ያዝኋት ። ጉንጮቿና ፡ ጉንጮቼ ፡ ተጠጋጉ ። ከሷም ፡ ጉንጮች ፡ የሚተነው ፡ እሳት ፡ ተሰማኝ ።

«ምን ፡ መሆንዎ ፡ ነው? እግዚኦ!..»

በፅ ፡ መያናገር ፡ ሳልሽበር ፡ ያን ፡ ለስላሳ ፡ ጉንጯን ፡ ሳም ፡ አደረግሁት ፡ ተያናገጠች ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ አልተናገረችም ። ጉዞዋችን ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ መጨረሻ ፡ ስለነበር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አላየንም ። ዳርቻውን ፡ እንደያዝን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሩት ፡ ሁሉ ፡ ግልቢያቸውን ፡ ጀመሩ ። ልዕልቷ ፡ ግን ፡ የፈረሷን ፡ ልጓም ፡ ይዛ ፡ ቀጥ ፡ አለች ። እኔም ፡ አብርያት ፡ ቆምሁ ። በዝምታዬ ፡ የተጨነቀች ፡ ትመስላለች ። እኔም ፡ አውቂ ፡ ምንም ፡ ላለመናገር ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ወሰንሁ ። ይህን ፡ ከመሰለ ፡ አስጨናቂ ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ ለመውጣት ፡ እንደምትችል ፡ ለማወቅ ፡ ጓጓሁ ።

በመጨረሻም ፡ በለቅሶ ፡ በሚንሰቀሰቀው ፡ ድምጿ ፤ «ወይም ፡ ይጠሉኛል ፤ ካለዚያም ፡ በጣም ፡ ይወዱኛል ። ወይም ፡ ሊቀልዱብኝ ፡ ፈልገዋል ። በስሜቱ ፡ ከተጫወቱ ፡ በኋላ ፡ ሊተውኝ ፡ አስበው ፡ ይሆናል ... ይህንንም ፡ በጣም ፡ ወራዳ ፤ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሳስበው ፡ እንኳ ... የለም ፡ በውነቱ ...» ካለች ፡ በኋላ ፡ ሐቅ ፡ በተሞላው ፡ አነጋገር ፡ እንዲህ ፡ አለችኝ ፤ «እኔን ፡ እንዳልከበር ፡ የሚያደርገኝ ፡ ጠባይ ፡ የለብኝም ። የርስዎ ፡ ጠባይ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ግራ ፡ የሚያጋባ ፡ ነው ... ይህም ፡ ሆኖ ፡ ይቅርታ ፡ ለማድረግ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። ምክንያቱም ፡ እራሴን ... እስቲ ፡ እኮ ፡ ይመልሱልኝ ። ቢናገሩ ፡ ድምጽዎን ፡ መስማት ፡ እፈልጋለሁ!..»

ይህ ፡ አነጋገሯ ፡ ቶሎ ፡ መልስ ፡ እንደምትጠብቅ ፡ እንደማንኛውም ፡ ሴት ፡ ስለነበረ ፡ ሳልወድ ፡ በግድ ፡ ፈገግ ፡ አልሁ ። ደግነቱ ፡ ጨለምለም ፡ ብሎ ፡ ነበር ። መልስ ፡ አልሰጠኋትም ።

«ምንም ፡ ዓይነት ፡ መልስ ፡ ለሰጡኝ ፡ አይፈልጉም?» በሚል ፡ ጥያቄ ፡ ንግግሯን ፡ በመቀጠል ፤ «ምናልባትም ፡ 'እወድዎታለሁ' ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በመጀመሪያ ፡ ከኔ ፡ ይፈል ጋሉ ፡ ልበል?»

አሁንም ፡ ቢሆን ፡ መልስ ፡ አልሰጠኋትም ።

በድንገት ፡ እራስዋን ፡ ወደኔ ፡ ዞር ፡ አድርጋ ፤

«ይህን ፡ እንዳደርግ ፡ ይፈልጋሉ?» ብላ ፡ ጠየቀችኝ ። ያ ፡ ሐቀኛ ፡ አስተያየቷና ፡ ለስላሳ ፡ ድምጿ ፡ በውነትም ፡ ማራኪ ፡ ነበር ።

«ለምን ፡ ብዬ ፡» በማለት ፡ ትከሻዬን ፡ ነቀነቅሁ ።

ፈረስዋን ፡ በልጓሟ ፡ ገጨት ፡ አድርጋ ፡ በዚያ ፡ ጠባብ ፡ አደገኛ ፡ መንገድ ፡ ግልቢያዋን ፡ ጀመረች ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚሆነው ፡ በድንገት ፡ ስለነበረ ፡ ጋልቤ ፡ ልደርስባት ፡ በፍጹም ፡ አልቻልሁም ። ብደርስባትም ፡ ከሉሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከተቀላቀለች ፡ በኋላ ፡ ነው ። ቤት ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ታወካና ፡ ታወራ ፡ ነበር ። ሁኔታዋ ፡ በሙሉ ፡ ጢናማ ፡ አልነበረም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አላየችኝም ። ይህም ፡ ዓይነት ፡ ያልተለመደ ፡ ሁኔታዋ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ልዕልት ፡ ሊንቬስካያ ፡ ልጇቸውን ፡ ሲያያት ፡ በውስጣቸው ፡ መሃሰታቸው ፡ ያስታውቃል ።

ሆኖም ፡ እንደውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የልጃቸው ፡ መጥነክነክ ፡ የመነጨው ፡ ከጭንቀት ፡ ነው ። ሉሊቱንም ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ እንደምታነጋው ፡ ገብቶኛል ። ይህን ፡ ማሰቡ ፡ እንኳ ፡ እራሱ ፡ ከፍተኛ ፡ ደስታን ፡ ያጐናጽፈኛል ። የቫምፒር* ፡ ስሜት ፡ አንዳንዴ ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ይገባኛል ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ስሜት ፡ ስለማጥፋት ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ እጥራለሁ ።

ወይዛዝርቱ ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ ከወረዱ ፡ በኋላ ፡ ወደልዕልት ፡ ሊንቬስካያ ፡ ቤት ፡ ገቡ ። እኔ ፡ ግን ፡ በጭንቅላቴ ፡ የሞላው ፡ ጭንቀቴ ፡ ስላቋነጠነጠኝ ፤ ይህን ፡ ሐሳብ ፡ ለማውረድ ፡ ስል ፡ ወደተራራው ፡ ግልቢያዬን ፡ ቀጠልሁ ። በጭጋግ ፡ የተሞላው ፡ ምሽት ፡ ለስላሳ ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ነበረው ። ጨረቃዋ ፡ በጨለማ ፡ ከተዋጠው ፡ ተራራ ፡ ጀርባ ፡ ገና ፡ ብቅ ፡ አለች ። ፈረሴ ፡ የሚያደርገው ፡ የያንዳንዱ ፡ እርምጃ ፡ ኩቴ ፡ በዚያ ፡ ፀጥ ፡ ባለ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ያስተጋባል ። ፈረሴን ፡ ውኃ ፡ አጠጥቼ ፡ የራሴንም ፡ ጥማት ፡ በንዲህ ፡ የቀዘቀዛ ፡ የምሽት ፡ አየር ፡ እርክቼ ፡ ወደቤቴ ፡

---

* ቫምፒር ፡ በ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. በወጣው ፡ በእንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ የሥቃይን ፡ ሚና ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ያ ፡ የኩራት ፡ ፈጣሪታው ፡ ያሞ ፡ ... እምን ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ፈሪ ፡ ነው ። አዎ ፤ ፈሪ ፡ ነው ።»

«እኔም ፡ እንዲያ ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ ፤ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ወደቀልድ ፡ ይቀለብሰዋል ። እንዴ ፡ ትገ ፡ ይለኛል ፡ ሙልሞ ፡ እድርጌ ፡ ስደብሁት ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ባለሁበት ፡ በጐራዴ ፡ ባረደኝ ። ፔቾሪን ፡ ግን ፡ ጉዳዩን ፡ በሳቅ ፡ አሳለፈው ። እኔም ፡ ጠቡን ፡ አላጠነከርሁትም ፤ በርግጥ ፡ መገፋፋቱ ፡ የራሱ ፡ ፋንታ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ መያያዙን ፡ አልፈለግሁትም ...» በማለት ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ድንፋታውን ፡ አስተጋባ።

«ግሩሽኒትስኪይ ፡ እንዲህ ፡ የሚናደደው ፡ ፔቾሪን ፡ ልዕልቷን ፡ ስለነጠቀው ፡ ነው ፡» ሲል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተናገረ ።

«ምን ፡ በማለት ፡ ነው? በርግጥ ፡ ከልዕልቷ ፡ ጋር ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አብሬ ፡ ቆይቻለሁ ። ግን ፡ በጠባይ ፡ ከማትስማማኝ ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ መጋባት ፡ ከዓላማዬ ፡ ውጭ ፡ ስለሆነ ፤ ጉዳዩን ፡ ወዲያውኑ ፡ ተውሁት ።»

«በመጨረሻ ፡ ፈረንቱን ፡ ላረጋግጥላችሁ ፡ እሻለሁ ። ይህንንም ፡ ስለፔቾሪን ፡ ማለቱ ፤ እንጂ ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ አለመሆኑን ፡ እንድታውቁልኝ ፡ እሻለሁ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ እውነተኛ ፡ መጻጂ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው ። ክቡራን! ከመሐከላችን ፡ ፔቾሪ

አመራሁ ። ከዚያም ፡ ከነፈረሴ ፡ ወደመንደሩ ፡ ገባሁ ። በየመስኮቶቹ ፡ የሚታዩት ፡ መብራቶች ፡ በመጥፋት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ባካባቢው ፡ ማማ ዎች ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ዘበኞች ፡ የካሣክ ፡ ወታደሮች ፡ ድምጻቸውን ፡ ባሻገር ፡ ይቀባበላሉ ።

መንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ባንዲ ፡ በሸለቆው ፡ አፋፍ ፡ በምትገኝዋ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ከወትሮው ፡ ይበልጥ ፡ ደመቅ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ በርቶበት ፡ አየሁ ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በዚያች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በወታደሮች ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ የሚሰማ ፡ ጩኸትና ፡ ጫጫታ ፡ ያስተጋባል ። ከፈረሴ ፡ ወርጄ ፡ ወደመስኮቱ ፡ ጠጋ ፡ አልኩኝ ፤ አንዲ ፡ የመስኮት ፡ ክንፍ ፡ በደንብ ፡ ሳትዘጋ ፡ ገርበብ ፡ ብላ ፡ ስለነበር ፤ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ለማየትና ፡ የሚነጋገሩትን ፡ ለመስማት ፡ ቻልሁ ። ወሬው ፡ ስለኔ ፡ ነበር ።

በቪኖው ፡ መጠጥ ፡ ሞቅ ፡ ያለው ፡ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ ፀጥታ ፡ ለማስከበር ፡ ጠረጴዛውን ፡ በጡጫ ፡ ይደበድባል ።

«ክቡራን! የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ መቀጠል ፡ የለበትም ። ፔቾሪንን ፡ ማስተማር ፡ አለብን ፡ እንዚህ ፡ የፔቱርቡርግ ፡ ሬሌዎች ፡ በሚገባ ፡ ካልተመቱ ፡ ቲን ፡ ቲን ፡ ማለታቸው ፡ አይቀርም ። ንጹህ ፡ የጅ ፡ ሹራብና ፡ የተወለወለ ፡ ጫማ ፡ ለሳያረገ ፡ ከሱ ፡ የተሻለ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አልመሰለውም ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ንን ፡ የሚደግፍ ፡ አለ? ማንም ፡ የለም? እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ መልካም ፡ ነው ። ያለውን ፡ ድፍረት ፡ ለመሞከር ፡ የሚፈልግ ፡ ማን ፡ አለ? በጣም ፡ አስቂኝ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ...» በማለት ፡ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ ተናገረ ።

«እንፈልጋለን ፤ ግን ፡ እንዴት?»

«እንግዲህ ፡ ይህና ፡ አድርጋችሁ ፡ አዳም ጡኝ ። በፔቾሪን ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ የተናደደው ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ስለሆነ ፡ የግንባር ፡ ቀደምነት ፡ ሚና ፡ የሚይዘው ፡ እሱ ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ቆስቁሶ ፡ በማጋነን ፡ ፔቾሪንን ፡ ለፍልምያ ፡ ይጋብዘው ... ቆይ ፡ እኮ! ታግሱ ፡ እንጂ! ዋናው ፡ ነጥብ ፡ ያለው ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ... ፔቾሪንን ፡ ለጠብ ፡ ይቀሰቅሰዋል ። እስካሁን ፡ ጥሩ ፡ መጥተናል ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ የጠቡ ፡ ትስቀሳ ፤ ዝግጅቱና ፡ በጠቡ ፡ በሚኖረው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓታዊ ፡ በጣም ፡ የከረረ ፡ ይሆናል ። የዚህንም ፡ ኃላፊነት ፡ እኔ ፡ እወስዳለሁ! የሩልምያውም ፡ አዋጊ ፡ ካንተ ፡ ወገን ፡ እኔ ፡ እሆንልሃለሁ ፡ ወዳጄ! በጣም ፡ ጥሩ! የሚተጥለው ፡ ጥላኔ ፡ ያሞ ፡ ይህ ፡ ነው ። ሽጉጡን ፡ ጥይት ፡ አያጉርሳቸውም ፡ እመኑኝ! ፔቾሪን ፡ በሩቢኮት ፡ ያረበሃበዳል ። እኔ ፡ ያሞ ፡ ፈጣሪ ፡ ያውቃል ፡ በሰይስት ፡ እርምጃ ፡ ነው ፡ የም ወስነው ። ከቡራን ፡ ሐሳቡ ፡ ያስማማችኋል?»

«ማሩም! ድንት!» የሚሉ ፡ ቃላት ፡ ከየቦታው ፡ ይሰማሉ ።

«እንተስ ፡ ግሩሽኒትስኪይ?»

የግሩሽኒትስኪይንም ፡ መልስ ፡ ለመስማት ፡ ጓጓሁ ። የነዚህ ፡ ቂሎች ፡ መጫወቻ ፡ ከመሆን ፡ ዕድሉ ፡ እንዳወጣችኝ ፡ ሳስበው ፡ ሰውነቴን ፡ እንድ ፡ ነገር ፡ ወረረኝ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ በነገሩ ፡ ባይስማማበት ፡ ኖሮ ፡ ዘልዬ ፡ ባንገቱ ፡ ላይ ፡ በተጠመጠምሁ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ጥቂት ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ከመቀመጫው ፡ ተነስቶ ፡ በታላቅ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፤ «እስማማለሁ ፤ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡» አለ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ክቡራን ፡ የተሰማቸውን ፡ ደስታ ፡ ለመግለጽ ፡ ቃላት ፡ ያጥሩኛል ።

ቤቱ ፡ እንደተመለስኩ ፡ ሰውነቴ ፡ በሁለት ፡ ሐሳብ ፡ ተወረረ ። የመጀመሪያው ፡ ሐዘን ፡ ነው ፤ ለምንድነው ፡ ሁሉም ፡ የሚጠሉኝ ... ለምን? ማንንስ ፡ በደልሁ? የለም ። ገና ፡ ገጽ ቸው ፡ ሲታይ ፤ በሰው ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ ከሚያሳድሩ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ እንዱ ፡ ነኝ! እያልሁ ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ቆየሁ ። እንዳች ፡ መርዘኛ ፡ ስሜት ፡ ሰውነቴን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየወረረኝ ፡ ሲሄድ ፡ ይሰማኛል ። በዚያች ፡ በቢቱ ፡ ነፍስ ፡ ወለል ፡ እየተንጐራደድሁ ፤ «እትኾልም ፤ ነበር ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፤ ይጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንቀቱ ። በኔ ፡ ላይ ፡ ለመቀለድ ፡ አይችሉም ። በነዚህ ፡ ቂል ፡ ጓደኞችዎ ፡ ምክንያት ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ ሳይኖርብዎት ፡ አይቀርም ። አሻንጉሊትዎ ፡ አይደለሁም!..» እያልሁ ፡ በሐሳቤ ፡ እናገር ፡ ጀመር ።

ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሳልተኛ ፡ አደርሁ ። ጠየት ፡ ስነሳ ፡ ልክ ፡ እንደብርቱካን ፡ ገርጥቼ ፡ ነበር ።

ማለዳ ፡ ልዕልት ፡ ሚሪን ፡ ከፀበሉ ፡ አጠገብ ፡ አገኘኋት ።

በጥሞና ፡ ከተመለከተችኝ ፡ በኋላም ፤ «ታመዋል ፡ እንዴ?» ብላ ፡ ጠየቀችኝ ።

«ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ባይኔ ፡ ሳይዞር ፡ አደረ ።»

«እኔም ፡ እንደርስዎ ፡ አልተኛሁም ፤ ለዚሁም ፡ ጥሩተኛ ፡ እርስዎ ፡ ነዎ ። ምናልባትም ፡ አያስፈልግም ፡ ነበር ... ግን ፡ እኮ ፤ ምክንያቱን ፡ በያስረዱኝ ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ይቅርታ ፡ አያርግልዎ ፡ ነበር ።»

«ለጥሩተኞቼ ፡ በሙሉ?»

«አዎ ፡ በሙሉ ... ግን ፡ እውነቱን ፡ ይንገሩኝ ፡ ቶሎ ፡ ይንገሩኝ ። እሰካሁን ፡ ድረስ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ ማስተባበያ ፡ ለማግኘት ፡ ያማሚ ፡ ያጋማሚ ፡ ሰዋር ፡ ቆይቻለሁ ። ምናልባትም ፡ የወላጆቼን ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ያፈራሉ ፡ ልበል? ስለዚህ ፡ ምንም ፡ የሚያሳስብዎት ፡

ጉዳይ ፡ የለም ። ነገሩን ፡ የሰሙት ፡ ለት ፡ (እንደበቷ ፡ ይተሳሰራል) እለምናቸዋለሁ ። ወይስ ፡ እርስዎ ፡ ሌላ ፡ አቋም ፡ አለዎት? ለምወያው ፡ ሰው ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ መቻሌን ፡ እንዲያውቁልኝ ፡ እፈልጋለሁ ። እባክዎ ፤ ቶሎ ፡ መልስ ፡ ይስጡኝ ። አላሳገዝንዎትም? መቼም ፡ አይጠሉኝም? እውነት ፤ አይደለም? መቼም ፡ አይጠሉኝም ።»

እጇን ፡ ያዝ ፡ አደረገችው ።

ልዕልት ፡ ሊጐብስካያ ፡ ከቬራ ፡ ባለቤት ፡ ጋር ፡ ከፊት ፡ ፊት ፡ ስለሚሄዱ ፡ እኛን ፡ አላዩንም ። ባካባቢው ፡ ያሉት ፡ ፀበልተኞች ፡ ግን ፡ ያዩናል ። ፀበልተኞቹ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ አሉባልተኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ያን ፡ ፍቅር ፡ ያዘለ ፡ እጅዋ ፡ ከእጇ ፡ አላቀቅሁት ።

«እውነቱን ፡ በሙሉ ፡ እነግርዎታለሁ ። ለሁኔታዬ ፡ ማስተባበያ ፡ ምክንያት ፡ አልሻም ። አልወድምትም ፡» አልኋት ።

ከንፈሮቿ ፡ ለአመል ፡ ወዲያው ፡ ገረጡ ። በዝትተኛ ፡ ድምጽ ፤ «ብቻዬን ፡ ይተውኝ ፡» አለችኝ ።

እኔም ፡ ትከሻዬን ፡ ነቅንቄ ፡ ፊቴን ፡ አዙሬ ፡ መንገዴን ፡ ቀጠልኩ ።

ሰኔ ፡ ፲፭ ።

እንዳንዴ ፡ ራሴን ፡ እጠላለሁ ፤ ሌሎችን ፡ የምጠላው ፡ ለዚህ ፡ ይሆን? ለከፍተኛ ፡ ሥራ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ለች ፡ እንደሷ ፡ አንጋገር ፡ የመሞቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነው ፡ ካንዲት ፡ መጥፎ ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ በማደርገው ፡ ጋብቻ ፡ ሳቢያ ፡ ነው ። ይህ ፡ አባባል ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ተፅዕኖን ፡ ከማሳየቱም ፡ ሌላ ፡ ለጋብቻ ፡ ያለኝን ፡ ጥላቻ ፡ አብሮኝ ፡ እንዲያድግ ፡ አድርጐታል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ትንቢት ፡ እውነተኝነት ፡ ይኖረዋል ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ አሳድሮብኛል ። እስከም ችለውም ፡ ድረስ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ እጋተረዋለሁ ።

ሰኔ ፡ ፲፩ ።

አፕፈልባውም ፡ የተባለው ፡ ምታተኛ ፡ ትላንትና ፡ ደረሰ ። በምግብ ፡ ቤቱ ፡ በር ፡ ላይ ፡ የተለጠፈው ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። «ጅምናስቲክ ፡ አዋቂው ፤ መድሐኒት ፡ ቀማሚው ፤ ዝነኛው ፡ ምታተኛ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ በምሽቱ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ በመኳንንት ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ (የምግብ ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ መሆኑ ፡ ነው) አንድ ፡ ትርኢት ፡ ያሳያል ። የመግቢያ ፡ ዋጋ ፡ ሁለት ፡ ሩብል ፡ ተኩል ።»

ይህን ፡ ዝነኛ ፡ ምታተኛ ፡ ለማየት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተዘጋጅቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ልጃቸው ፡ ብትታመሙም ፤ ልዕልት ፡ ሊጉቭስካያ ፡ ቲኬት ፡ ገዝተዋል ።

ከራት ፡ በኋላ ፡ በቬራ ፡ መስኮት ፡ በኩል ፡ ሳልፍ ፡ ከበረንዳው ፡ ላይ ፡ ብቻዋን ፡ ቁጭ ፡

ከእንግዲህ ፡ ተገቢ ፡ አይደለሁም ። ራሴ ፡ እንኳ ፡ አስቂኝ ፡ ፍጡር ፡ እንዳልሆን ፡ እሠጋለሁ ። በኔ ፡ ቦታ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለልዕልቲቱ ፡ son cœur et sa fortune* በሰጣት ፡ ነበር ። ለኔ ፡ ጋብቻ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ልዩ ፡ ፍች ፡ ነው ፡ ያለው ። እንዲትን ፡ ሴት ፡ በጣም ፡ ልወዳት ፡ እችላለሁ ። ግን ፡ ጋብቻ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንዴ ፡ እንኳ ፡ ካነሳችው ፡ ፍቅርን ፡ እሰናበተዋለሁ ። ልቤ ፡ ድንጋይ ፡ ይሆናል ። እንደገናም ፡ ሕይወት ፡ ሊዘራበት ፡ የሚችል ፡ ምንም ፡ ኃይል ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። «አግባ ፡» በሚሉኝ ፡ «ማንኛውንም ፡ መስዋእትነት ፡ ተቀበል» ቢሉኝ ፡ ይቀለኛል ። ሕይወቴንና ፡ ክብሬን ፡ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ ባጣቸው ፡ ይሻለኛል ። ሆኖም ፡ ነፃነቱን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ አልሸጥም ። ለምንድነው ፡ ለነፃነቴ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ የምሰጠው? በውስጡ ፡ ምን ፡ አገኝበታለሁ? የወደፊት ፡ ግቤ ፡ ምንድነው? ከወደፊትስ ፡ ሕይወት ፡ ምን ፡ እጠብቃለሁ? ምንም ፡ አልጠብቅም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ልገልጻቸው ፡ የማልችለው ፡ የውስጣዊ ፡ ፍራቻዬ ፡ ነው ... አዎ! አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ያለምንም ፡ ምክንያት ፡ ሽረራትን ፡ አይጥን ፡ ይፈራሉ ። ልናዘዝ? ገና ፡ በሕፃንነቴ ፡ ዘመን ፡ እንዲት ፡ አሮጊት ፡ ስለወደፈረሱ ፡ ዕድሉ ፡ ለናቴ ፡ እጫወታታ

* ልቡንና ፡ እድሉን ፡ ማለት ፡ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ብላ ፡ እየኋት ። አንድ ፡ ትንሽ ፡ ማስታወሻ ፡ ከግሬ ፡ ሥር ፡ ዱብ ፡ አለች ።

ዛሬ ፡ ማታ ፡ ከምሽቱ ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ በዋናው ፡ በር ፡ በኩል ፡ እጠብቅሃለሁ ። ባለ ቤቱ ፡ ወደጢቲጉርስክ ፡ ስለሄደ ፡ እስከነገ ፡ ጠዋት ፡ አይመለስም ። እሽክሮቹና ፡ ገረዶቹም ፡ አይኖሩም ። ለነሱና ፡ ለልዕልቷ ፡ እሽክሮች ፡ ምትሃቱን ፡ እንዲያዩ ፡ የመግቢያ ፡ ቲኬት ፡ ገዝቼ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ። ማንም ፡ የለም ፡ እጠብቅ ሃለሁ ፡ እንዳትቀር ፡» የሚል ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ።

ዉሺ! የፈለግሁት ፡ ሁሉ ፡ ተሳካልኝ ፤ አይደለም?» ብዬ ፡ አሰብሁ ። ከምሽቱ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደትርኢት ፡ ቤቱ ፡ ዘው ፡ አልሁ ። ሕዝቡ ፡ የተሰበሰበውና ፡ ትርኢቱም ፡ የተጀመረው ፡ ከምሽቱ ፡ ሶስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። የመጨረሻው ፡ ወንዘሮች ፡ ላይ ፡ የልዕልቲቱንና ፡ የቪራን ፡ እሽክሮች ፡ አየሁ ። ሁሉም ፡ እዚያው ፡ ነበሩ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ በመጀመሪያ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ያን ፡ በእጅ ፡ የሚያዝ ፡ መነጽሩን ፡ ደንቆሮ ፡ ቱሜ ፡ ብሏል ። አስማተኛው ፡ መሐረብ ፡ ሰዓት ፡ ቀለበት ... የመሳሰሉት ፡ ነገሮች ፡ ባስፈለጉት ፡ ቁጥር ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ ይጠያቀዋል ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ እኔን ፡ ሰላም ፡ ማለቱን ፡ ካቆመ ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ፡ ሆኖታል ። በተለይ ፡ ዛሬ ፡ በጥላቻ ፡ ዓይን ፡ አንድ ፡ ሁለቱ ፡ ግላመ

ጠኝ ። ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራው ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ ይኖርበታል ።

አራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ሲሆን ፡ ወጣሁ ። ውጪም ፡ በጣም ፡ ጨልሟል ። ባካባቢው ፡ ባሉት ፡ ተራራዎች ፡ ቁንጮው ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ የክረምት ፡ ደመናዎች ፡ ጉብ ፡ ብለው ፡ ይታ ያሉ ። የነበረው ፡ ነፋስ ፡ ከደካማነቱ ፡ የተ ነሳ ፡ በምግብ ፡ ቤቱ ፡ አጠገብ ፡ የበቀሉትን ፡ የዛ ፎች ፡ ቅጠላት ፡ የሚያወዛውዘው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ። ቁልቁለቱን ፡ ከወረድሁ ፡ በኋላ ፡ ወደበሩ ፡ ዘው ፡ ብዬ ፡ በፈጣን ፡ እርምጃ ፡ ወደፊት ፡ ገሰገስሁ ። በድንገትም ፡ ሰው ፡ እንደ ሚከተለኝ ፡ ተሰማኝ ። ቆም ፡ ብዬም ፡ ዙርያዬን ፡ ተመለከትሁ ። በጣም ፡ ጨለማ ፡ ስለነበር ፡ ምንም ፡ ለማየት ፡ አልቻልሁም ። ለጥንቃቄም ፡ ስል ፡ የምንሸራሸር ፡ መስዬ ፡ ቤቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዞርሁት ። የልዕልት ፡ ሜሪን ፡ መስኮት ፡ ላልፍ ፡ ደግሞ ፡ ከኋላዬ ፡ የሰው ፡ ኩቴ ፡ ተሰማኝ ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ካፖርት ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ አልፎኝ ፡ እሮጠ ፡ ሄደ ። ይህም ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ አላስበኝ ፡ እኔም ፡ ጨለማ ፡ ወደለበሰው ፡ በረንዳ ፡ ጥግ ፡ አፈግፍጌ ፡ ደጅ ፡ ቆምሁ ። ቤቱም ፡ ተከፍቶ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ እጅ ፡ በጂ ፡ ላይ ፡ አረፈ ።

«ማንም ፡ አላየን» ብላ ፡ ቪራ ፡ በሹክሹክታ ፡ እጁን ፡ እንደጨበጠች ፡ ጠየቀችኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ማንም ።»

«አሁንስ ፡ እንደምወድህ ፡ ታምናለህ ? አቤቱ ፣ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እወላወልሁ! ስንቴ ፡ ተሰቃየሁ፣ አንተ ፡ ግን ፡ እንደፈለግክ ፡ ትጫወትብኛለህ ።»

ልቧ ፡ በኃይል ፡ ይመታል ። እጆቿ ፡ እንደ በረዶ ፡ ቀዝቅዘዋል ። ቁጥላም ፡ የቅናቱን ፤ የውንጀላውን ፡ መዓት ፡ ታወርድብኝ ፡ ጀመር ። የሷ ፡ ፍላጐት ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ ሳይሆን ፡ ያደረግሁትን ፡ ሁሉ ፡ እንድዘረዝርላት ፡ ጠየቀችኝ ። ለመቀበል ፡ ዝግጁ ፡ መሆንዋን ፡ ገለጸችልኝ ። ሆኖም ፡ አንጋገርዋን ፡ አላመንሁትም ፤ ያም ፡ ሆኖ ፡ የኋላውንና ፡ የወደፊቱን ፡ ተስፋ ፡ ከላይ ፡ እስከታች ፡ አወረድሁላት ።

ፀታድያ ፤ ልዕልት ፡ ሜሪን ፡ ላታግባ ፤ አይደለማ! አትወዳትም?.. እሷማ ፡ የመሰላት ... ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንደወደደችህ ፡ ታውቃለህ ። ምስኪኗ!..

. . . . . .

. . . . . .

ከምሽቱ ፡ ሰምንት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ መስኮቱን ፡ ከፍቼ ፡ ሁለት ፡ መያረብያ ፡ ሻሾች ፡ አሥሬ ፡ ከላይኛው ፡ በረንዳ ፡ ወደታችኛው ፡ የቤቱን ፡ የውጭ ፡ ምሰሶ ፡ እየተያገዙ፡ መሬድሁ ። የልዕልት ፡ ሜሪ ፡ ቤት ፡ መብራት ፡ እስካሁን ፡ አልጠፋም ። አንዳች ፡ የሙስጥ ፡ ኃይል ፡ ወደላይ መስኮት ፡ እንድሄድ ፡ ገፋፋኝ ።

መጋረጃው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተዘግቶ ፡ ስላልነበረ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ለማየት ፡ ቻልሁ ። ሜሪ ፡ በእጆቿ ፡ ጉልበቶቿን ፡ ይዛ ፡ በአልጋዋ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብላለች ። ያ ፡ ረጅም ፡ ወጉሯ ፡ በማታ ፡ የመኝታ ፡ ቆብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ተሸፍኗል ። ያም ፡ አበባ ፡ የመሰለው ፡ ትከሻዋ ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ቀይ ፡ መደረብያ ፡ ሻሽ ፡ ተከድኗል ። እነዚያ ፡ ትንንሽ ፡ እግሮቿም ፡ በሚያንፀባርቁ ፡ ፔርሽያ ፡ የቤት ፡ ጫማዎች ፡ ተውጠዋል ። ከተቀመጠችበት ፡ እንቅስቃሴ ፡ አታደርግም ። ጭንቅላቷን ፡ ያለመጠን ፡ ደፍታዋለች ። ፊቷ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ጠረጴዛ ፡ አንድ ፡ የተገለጠ ፡ መጽሐፍ ፡ ይታያል ። በእንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያተኮረች ፡ እስተያየቷ ፡ ሲታይ ፡ ያን ፡ መጽሐፍ ፡ ደግማ ፡ ደጋግማ ፡ እንዳነበበችው ፡ ያስታውቃል ። ሆኖም ፡ ሐሳብዋ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ...

በዚህ ፡ ወቅት ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ በቅጠሎቹ ፡ መካከል ፡ ውልብ ፡ ሲል ፡ አየሁ ። እኔም ፡ ወዲያውኑ ፡ ከበረንዳው ፡ ዘልዬ ፡ ወደመሬቱ ፡ ዱብ ፡ አልሁ ። እንድ ፡ የማይታይ ፡ እጅም ፡ ከትከሻዬ ፡ ላይ ፡ አረፈ ።

ቁጥሉም ፡ በጉሮና ፡ ድምጽ ፤ «እሃ! ያዝሁህ ፤ አይደለም? በየሴሊቱ ፡ በየልዕልቶቹ ፡ ቤት ፡ በመልከስከስህ ፡ ተገቢ ፡ ዋጋህን ፡ ታገኛለህ ።» አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መስጠቱ ፡ አጠፋው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ጩኸትና ፡ ጫጫታ ፡ አስተጋባ ። አንድ ፡ ካህክ ፡ ከጦር ፡ ሠፈሩ ፡ እየጋለበ ፡ መጣ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ መንደሩ ፡ ድብልቅልቁ ፡ ወጣ ። ቹርከሶችም ፡ በያንዳንዱ ፡ ቱጥ ቂጦ ፡ ሥር ፡ ይፈለጉ ፡ ጀመር ። ግን ፡ ማንም ፡ ስላልነበረ ፡ የተያዘ ፡ ቹርከስ ፡ የለም ። «ዘበኞቹ ፡ ቅልጥፍናና ፡ ድፍረት ፡ ባይኖራቸው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ሃያ ፡ ወራሪዎች ፡ ሳይያዙ ፡ አይቀሩም ፡ ነበር ፡» ብለው ፤ ከሠፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ ሳያስቡ ፡ አልቀሩም ።

ሰኔ ፡ ፲፮ ።

የቹርከሶቹ ፡ ወራሪ ፡ በማግሥቱ ፡ በፀበሉ ፡ ላይ ፡ አቢይ ፡ ዜና ፡ ሆኖ ፡ ዋለ ። የታዘዘውን ፡ ያህል ፡ የናርዛንን ፡ ፀበል ፡ ጠጥቼ ፡ አንድ ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ በዛፍ ፡ በተከበበው ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ከተመላለስሁ ፡ በኋላ ፡ ከፒቲጐርስክ ፡ ወዲያውኑ ፡ የተመለሰውን ፡ የቬራን ፡ ባል ፡ አገኘሁት ። እጂን ፡ ይዞኝ ፡ ወደቡና ፡ ቤቱ ፡ ለቁርስ ፡ ገባን ። ስለሚሰቱ ፡ በጣም ፡ ተጨንቋል ። «ትላንትና ፡ ማታ ፡ በጣም ፡ ተሸብራ ፡ ነበር ። የሚገርመው ፡ እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ያጋጠማት ፡ ልክ ፡ እኔ ፡ ስሄድ ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ አወራኝ ። ወደሚቀጥለው ፡ ነፍስ ፡ በሚያስገባው ፡ በር ፡ እጠገብ ፡

ሌላውም ፡ ከጥግ ፡ ፈትለክ ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፤ «በደንብ ፡ ያዘው!» ብሎ ፡ ጮኸ ።

ሰዎቹም ፡ ግሩሽኒትስኪይና ፡ ያ ፡ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ ነበሩ ።

የሻምበሉን ፡ በቡጢ ፡ ከግንባሩ ፡ ላይ ፡ ወግሬ ፡ ጥዬ ፡ ወደጫካው ፡ ገባሁ ። ካት-ክልቶች ፡ ተነስቶ ፡ እቤቴ ፡ አፋፍ ፡ ድረስ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ በደንብ ፡ አውቀዋለሁ ።

«ሌባ! ሌባ! ያዘው!..» እያሉ ፡ ይጮሁ ፡ ገቡ ። ጥይት ፡ ተተኮሰ ፤ የተተኮሰውም ፡ ጥይት ፡ ከግሬ ፡ አጠገብ ፡ አረፈ ።

ደቂቃ ፡ ሳይሞላ ፡ እቤቴ ፡ ደርሼ ፤ ልብሴን ፡ አወላልቄ ፡ አንሶላዬ ፡ ውስጥ ፡ ገብቻለሁ ። አሽከሬ ፡ በሩን ፡ ልክ ፡ ዘግቶ ፡ እንደጨረሰ ፡ ግሩሽኒትስኪይና ፡ የሻምበሉ ፡ በሩን ፡ ይደበድቡ ፡ ገቡ ።

«ፔቾሪን ፡ ተኝተዋል ፤ እንዴ?» እያለ ፡ የሻምበሉ ፡ ይጮህ ፡ ጀመር ።

«ተኝቻለሁ ፡» ብዬ ፡ ቁጣ ፡ ባለው ፡ ድምጽ ፡ መለስሁላቸው ።

«ይነሱ ። የቹርከስ ፡ ሌቦች ፡ መጥተዋል ...»

«ገንዘብ ፡ ይዞኛል ፤ ከተነሳሁ ፡ ይብስብኛል ፡» ብዬ ፡ መለስሁላቸው ።

ሁለቱም ፡ ተመልሰው ፡ ሄዱ ። መልስ ፡ ባልሰጣቸው ፡ ኖሮ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ባትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ይፈልጉኝ ፡ ነበር ። መልስ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በቁርስ ፡ ቢያዝም ፡ ግራሽኒትስኪይ ፡ የነበርሁ
በት ፡ ቦታ ፡ በጥርጣሬ ፡ ሲናገር ፡ ይኼ ፡ ሰው ፡
ይሰማዋል ፡ የሚል ፡ ስጋት ፡ ያዘኝ ። ሆኖም ፡
ግራሽኒትስኪይ ፡ በቅናት ፡ ታፍኖ ፡ ስለነበረ ፡
ሌላ ፡ ቦታ ፡ ይሄዳል ፡ ብሎ ፡ ፈጽሞ ፡ አልጠረ
ጠረኝም ።

«እና ፡ በኋላ ፡ በውሸት ፡ ጥይት ፡ ጠመንጃ
ችንን ፡ አጉርሰን ፡ ሰውየውን ፡ ለማስደንገጥ ፡
ተያይዘን ፡ ሄድን ። እስከሌሊቱ ፡ ስምንት ፡
ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ባትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ አደፈጥን ፤
በመጨረሻም ፡ የምንጠብቀው ፡ ሰው ፡ ብቅ ፡
አለ ። ከየት ፡ በኩል ፡ እንደወጣ ፡ ግን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ይወቀው ። መስኮቱ ፡ ስላልተከ
ፈተ ፡ ከመስኮቱ ፡ እንዳልወጣ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።
ከምሰሶው ፡ በስተጀርባ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡
በመስተዋት ፡ በር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡
የወጣው ... ወዲያውም ፡ ወደበረንዳው ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ሲወጣ ፡ አየን ። ታድያ ፡ ስለልዕ
ልታ ፡ ምን ፡ ታስባላችሁ? እነዚህ ፡ የሞስኮ ፡
ወይዛዝርት ፡ ለኔ ፡ በፍጹም ፡ አይሆኑም ። ይህ
ንስ ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ ማንን ፡ ያምናሉ? ልንይዘው ፡
ሞክርን ፡ ግን ፡ ከጃችን ፡ አፈትልኮ ፡ ሮጦ ፤
እንደጥንቸል ፡ ጫካ ፡ ገባ ። የተኮሰሁበትም ፡
ያኔ ፡ ነው ።»

ግራሽኒትስኪይ ፡ በተናገረው ፡ ላይ ፡ ባካባ
ቢው ፡ የጥርጣሬ ፡ ጉርምርምታ ፡ ተሰማ ።

ካለው ፡ ወንበር ፡ ቁጭ ፡ አልን ። በሚቀጥለው ፡
ጓዳ ፡ አንድ ፡ አሥር ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተቀምጠ
ዋል ። ከነዚህም ፡ መካከል ፡ ግራሽኒትስኪይ ፡
ይገኝበታል ። የሱ ፡ እጣ ፡ በሚወሰንበት ፡ ውይ
ይት ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ባጋጣሚ ፡ ለማዳመጥ ፡
እድል ፡ አገኘሁ ። አላየኝም ። ስለሆነም ፡
አነጋገሩ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ከሰዎቹ ፡ እንድጠነ
ቀቅ ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ አይደለም ። ይህም ፡
እኔ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያለኝን ፡ ጥላቻ ፡ አበረታብኝ ።

«በእውነት ፡ ቼርከሶች ፡ ናቸው? ያያቸው ፡
ሰው ፡ አለ?» ሲል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጠየቀ ።

«ያለውን ፡ እውነት ፡ በሙሉ ፡ አወራችኋ
ለሁ ። ግን ፡ አሳልፋችሁ ፡ እንዳትሰጡኝ ፤
እደራ ፡ እላችኋለሁ ። የሆነው ፡ እንደዚህ ፡
ነው ። ትላንትና ፡ ማታ ፡ ስሙን ፡ ልጠቅሰው ፡
የማልፈልገው ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ከሃ
ሽቱ ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ወደልዕልት ፡
ሊገ-ቭስካያ ፡ ቤት ፡ ሾልኮ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡
እንዳለ ፡ ነገረኝ ። ላስታውሳችሁ ፡ የምፈልገው ፤
በዛ ፡ ሰዓት ፡ ልዕልት ፡ ሊገ-ቭስካያ ፡ በትርኢቱ ፡
አዳራሽ ፡ እዚህ ፡ ነበሩ ፤ ሚሪ ፡ ግን ፡ ብቻዋን ፡
እዚያው ፡ ቤት ፡ ቀርታ ፡ ነበር ። እኔም ፡ ወደዚያ ፡
ሄጄ ፡ ከመስኮቱ ፡ የሚወርደውን ፡ እድለኛ ፡
ሰው ፡ ስጠብቅ ፡ አመሸሁ ፡» በማለት ፡ ግራሽ
ኒትስኪይ ፡ ወሬውን ፡ በሰፈው ፡ ተያያዘው ።

አብሮኝ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ዓይኑን ፡ በንዴት ፡ ደፍቶ ፤ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ቆሚል ። በእውነትና ፡ በሐሰቱ ፡ መሐከል ፡ ያለው ፡ ትግል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፈ ጀም ። የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ እንዲናገር ፡ በትከሻው ፡ ይገፋው ፡ ነበር ። ግሩ ሽኒትስኪይ ፡ ለጊዜው ፡ ቢደናገጥም ፡ እንገቱን ፡ እንደያዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ ።

«ጌታዬ! አንድ ፡ ነገር ፡ ካልሁ ፡ በኋላ ፡ ያንኑ ፡ ለመድገም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ... የርስዎ ፡ ዛቻ ፡ ደግ ም ፡ አያስደነግጠኝም ። ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። ምንም ፡ የምፈራው ፡ ነገር ፡ የለ ኝም ። ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ፡» አለኝ ።

«አዎ! ይህንን ፡ የመጨረሻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ምን ፡ ደጋግሙት ፡» ብዬ ፡ በዝግታ ፡ ድምጽ ፡ ከመለስሁለት ፡ በኋላ ፡ የፈረሰኛውን ፡ ሻምበል ፡ እጅ ፡ ያዝ ፡ አድርጌ ፡ ከክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ ወጣን ።

«ከእኔ ፡ የሚፈልጉት ፡ ምንድነው?» ብሎ ፡ የሻምበሉ ፡ ጠየቀኝ ።

«የግሩሽኒትስኪይ ፡ ጓደኛ ፡ ነዎት? ምናል ባትም ፡ ለፍልሚያው ፡ አዋጊ ፡ ከሱ ፡ ወገን ፡ የሚተርቡ ፡ ሁለተኛ ፡ ሰው ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀ ሩም ።»

የሻምበሉ ፡ በኩራት ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

«ይህና ፡ ገምተዋል ። እኔም ፡ ከግሩሽኒ ትስኪይ ፡ ወገን ፡ ሁለተኛ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡

«አታምኑኝም ፡ እንዴ? የተናገርሁት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ እምልላችኋለሁ ። ለማረጋ ገጥም ፡ ከፈለጋችሁ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ለመጥራት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ።»

«ማነው? ማነው?» የሚል ፡ ድምጽ ፡ ከሁሉም ፡ ቦታ ፡ አስተጋባ ።

«ፔቾሪን ፡» ብሎ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ መለሰ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ቀና ፡ ቢል ፤ ከበሩ ፡ አጠገብ ፡ ከፊት ፡ ለፊቱ ፡ ተገትሬ ፡ አየኝ ። በድንጋጤ ፡ ፊቱ ፡ ቀላ ። እኔም ፡ ወደሱ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ በቀስታ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፤

«በፍጹም ፡ ሊታመን ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ተናግረው ፡ ከማሉ ፡ በኋላ ፡ በመድረሴ ፡ በጣም ፡ አዘንሁ ። የኔ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ መገኘት ፡ ወደ ባሰ ፡ ውሸት ፡ እንዳይገቡ ፡ ያግዘዎታል ።»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ በንዴት ፡ ተናዶ ፡ ከወንበሩ ፡ ብድግ ፡ አለ ። ያንኑ ፡ የለሆሳስ ፡ ድምጼን ፡ በመቀጠል ፤ «የተናገሩት ፡ በሙሉ ፡ ሐሰት ፡ እንደሆነ ፡ ያውቃሉ ፤ መልሰው ፡ እንዲያነሱት ፡ እጠይቅዎታለሁ ። ያለዎትን ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ እንዲት ፡ ሴት ፡ ባትተበለው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የውርደት ፡ ማቅ ፡ መልበስ ፡ አይገባትም ። እንደገና ፡ ያለቡበት ፤ በተናገሩት ፡ ውሸት ፡ ላይ ፡ የሚወጉ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ነብሪዎንና ፡ ሕይወትዎን ፡ ያሰጋዋል ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ግዴታ ፡ አለብኝ ፤ ምክንያቱም ፡ ትላንትና ፡ ማታ ፡ አብሬው ፡ ስለነበርሁ ፡ ስድቡ ፡ እኔንም ፡ ይመለከተኛል ።»

«በቡጢ ፡ ጭንቅላትዎን ፡ የወገርሁዎት ፡ እርስዎን ፡ ነው?»

በገጹ ፡ ላይ ፡ ብጫና ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለማት ፡ ተለዋወጡበት ፤ ንዴቱንም ፡ አምቆ ፡ እንደያዘው ፡ ግልጽ ፡ ነበር ።

«እኔም ፡ በበኩሌ ፡ በኔ ፡ ወገን ፡ አዋጊ ፤ አጋገርን ፡ ዛሬውኑ ፡ እልክልዎታለሁ ፡» በማለት ፡ ንዴቱ ፡ እንዳልታየኝ ፡ አድርጌ ፡ በጨዋ ፡ መልክ ፡ ነገርሁት ።

ከምግብ ፡ ቤቱ ፡ በረንዳ ፡ ላይ ፡ የቪራ ፡ ባል ፡ ሲጠብቀኝ ፡ ቆየ ።

አድናቆት ፡ በተሞላበት ፡ ስሜት ፡ ክንዴን ፡ ጨበጥ ፡ አደረገኝ ።

ዓይኖቹም ፡ በእንባ ፡ ተንጠርገዘው ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤ «የተከበሩ ፡ ወጣቱ ፡ ሆይ! ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ሰምቻለሁ ። ይህ ፡ መናጢ ፡ እርካሽ ... ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የጨዋን ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ይጀፍ ፡ ያዩታል? የእግዚአብሔር ፡ ክብሩ ፡ ይስፋ ፡ ሲቶች ፡ ልጆች ፡ የሉኝም ። ለዓ. ፡ ሲሉ ፡ ሕይወትዎን ፡ የሚያሳልፉላት ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ተገቢውን ፡ ዋጋ ፡ ትከፍል ዎታለች ። ለጊዜው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ተአምር ፡ በምሥጢር ፡ እንደምይዘው ፡ ይመኑኝ ። እኔም ፡

በጊዜዬ ፡ ወጣት ፡ ነበርሁ ። በውትድርናም ፡ አገልግያለሁ ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ እንደማያስፈልግ ፡ አውቃለሁ ። ይህና ፡ ይሁኑ ።»

ምስኪን! ሲቶች ፡ ልጆች ፡ ስለሌሉት ፡ ደስ ፡ ብሎታል ...

ከዛም ፡ በቀጥታ ፡ ወደቪርነር ፡ ቤት ፡ አመራሁ ። ቪርነርንም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አገኘሁት ። ስለማንኛውም ፡ ነገር ፡ አጫወትሁት ። ስለቬራና ፡ ስለልዕልቷ ፡ የነበሩኝን ፡ ስሜቶች ፡ አወራሁት ። እነዚህ ፡ መኳንንት ፡ ጥይት ፡ በሌለው ፡ ሽጉጥ ፡ አታኩሰው ፡ ሊያዋክቡኝ ፡ ሲሞክሩ ፡ እንደሰማሁ ፡ አወጋሁት ። ይሁንናም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጉዳይ ፡ ከቀልድ ፡ አልፏል ። አፈጻጸሙም ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ያልቃል ፡ ብለው ፡ አይገምቱም ።

ዶክተሩ ፡ በኔ ፡ ወገን ፡ ያለ ፡ ረዳት ፡ አዋጊ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስማማ ። ስለፍልሚያው ፡ ሁኔታ ፡ አንዳንድ ፡ መመርያዎችን ፡ አስረዳሁት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ካስፈለገ ፡ ሕይወቴን ፡ ለመሰዋት ፡ ዝግጁ ፡ ብሆንም ፡ ግን ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ላጠፋት ፡ ስለማልፈልግ ፡ ዶክተሩ ፡ በታላቅ ፡ ምስጢር ፡ እንዲይዘው ፡ አስጠናቀቅሁት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደቤቱ ፡ ተመለስሁ ። ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላም ፡ ዶክተሩ ፡ ከተላከበት ፡ ቦታ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዓት ፡ ላይ ፡ እነሱ ፡ እቦታው ፡ ይደርሳሉ ። እኛም ፡ ከእኩል ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ከቤት ፡ እንነሳለን ። የምትታኮሱት ፡ ከስድስት ፡ እርምጃ ፡ እርቀት ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ነው ። ስድስት ፡ እርምጃ ፡ እንዲሆን ፡ የፈለገው ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ነው ። የሚቹ ፡ ሬሳ ፡ በቸርከሶች ፡ እንዲተው ፡ ተዋውለናል ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እኔ ፡ የጠረጠርኩት ፡ ልንገርዎት ። የግሩሽኒትስኪይ ፡ ዳኞች ፡ በፊት ፡ የተስማሙበትን ፡ ቀይረው ፡ በግሩሽኒትስኪይ ፡ ሽጉጥ ፡ ጥይት ፡ ሊያወርሱት ፡ ተስማምተዋል ። ሁኔታውን ፡ ሲያዩት ፡ ፍልምያ ፡ ሳይሆን ፡ ለነፍስ ፡ ግድያ ፡ የሚዘጋጁ ፡ ይመስላል ፤ በርግጥ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፤ በተለይም ፡ በእዚያቲኮች ፡ ጦርነት ፡ ማንኛውም ፡ ብልጠት ፡ መደረጉን ፡ እናውቃለን ። በእውነቱ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከጓደኞቹ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እደፍራለሁ ። ምን ፡ ይመስልዎታል? ተንኮላቸውን ፡ እንዳወቅንባቸው ፡ እንንገራቸው?»

«ዶክተር ፤ በፍጹም ፡ መንገር ፡ አያስፈልግም ፤ በነሱ ፡ ወጥመድ ፡ እንደማልገባ ፡ ይመኑኝ ።»

«ምን ፡ ሊያደርጉ ፡ ፈልገዋል!»

«እሱ ፡ ለኔ ፡ የግል ፡ ምስጢር ፡ ነው ።»

«ከወጥመዱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገቡ ፡ ይጠንቀቁ ... እርቀቱ ፡ ስድስት ፡ እርምጃ ፡ መሆኑን ፡ ያስታውሱ ።»

«በውነቱ ፡ በርስዎ ፡ ላይ ፡ የተጠነሰሰ ፡ ታላቅ ፡ ሴራ ፡ ይታየኛል ፤ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ና ፡ እንድ ፡ ስሙን ፡ የማላስታውሰው ፡ ሌላ ፡ መኮንን ፡ በግሩሽኒትስኪይ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ። በመግቢያው ፡ ላይ ፡ ጫማዬን ፡ ለማውለቅ ፡ ቆም ፡ ስል ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሚጫታና ፡ ውካታ ፡ ተሰማኝ ። «እኔ ፡ በዚህ ፡ በፍጹም ፡ አልስማማም» እያለም ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ይከራከራል ። «በርግጥ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ባደባባይ ፡ ሰድቦኛል ። ያ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ...» ሲል ፡ የሻምበሉ ፤ «ምን ፡ ችገረህ ፤ ማንኛውን ፡ ኃላፊነት ፡ የምወስደው ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለአምስት ፡ ፍልሚያዎች ፡ ዳኛ ፡ ሁኜ ፡ አታኩሻለሁ ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እንዲት ፡ መካሄድ ፡ እንዳለበት ፡ በሚገባ ፡ አውቃለሁ ። እያንዳንዱም ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ አዘጋጅቻለሁ ። ብቻ ፡ እንተ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባህ ፡ አትረብሸኝ ። ፒቾሪንን ፡ ትንሽ ፡ ማስደንገጥ ፡ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ሊቀር ፡ ሲችል ፡ ሕይወትህን ፡ ለምን ፡ ባደጋ ፡ ላይ ፡ ትጥለዋለህ?» በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወደክፍሉ ፡ ዘው ፡ ብዬ ፡ ስገባ ፡ ተናጋሪዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ወጥ ፡ አሉ ። ውይይታችን ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ ። ሆኖም ፡ በመጨረሻ ፡ ወደስምምነት ፡ መጣን ። እኛ ፡ ካለንበት ፡ አንድ ፡ አምስት ፡ ቨርስታ ፡ ራት ፡ ብሉ ፡ አንድ ፡ ወጥ ፡ ያለ ፡ ሽለቆ ፡ አለ ። ነገ ፡ ከሌሊቱ ፡ ባሥር ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ታድያ ፣ ምን ፣ አለ? መሞት ፣ ካለብኝ ፣ እሞታለሁ! በኔ ፣ መሞት ፣ ዓለም ፣ የምታጣው ፣ ነገር ፣ የለም ። ለኔም ፣ ዓለም ፣ ስልችታኛለች ። ራሴንም ፣ የዳንስ ፣ ምሽት ፣ ላይ ፣ በድካም ፣ ተውጨ ፣ እየገባሁ ፣ ወደቤቱ ፣ የሚወስደውን ፣ ሠረገላ ፣ የሚጠብቅ ፣ ሰው ፣ አድርጌ ፣ ቆጠርሁ ። እነሆ ፣ ሠረገላው ፣ ደረሰ ... ደህና ፣ ሁኑ!

ያለፈውን ፣ ሕይወቴን ፣ ሳልወድ ፣ ማሰላሰል ፣ ጀመርሁ ። ለምንድነው ፣ የኖርሁት? ለምንስ ፣ ተወለድሁ? ምክንያት ፣ አለው ፣ ለማለት ፣ እደፍራለሁ ። እጣዬ ፣ ሴላ ፣ የከበረ ፣ ነገር ፣ እዘጋጅ ታልኛለች ፣ ብዬም ፣ እገምታለሁ ። ገናም ፣ ያልተሞከረ ፣ ጉልበትና ፣ ችሎታ ፣ በውስጤ ፣ እንዳለ ፣ ይሰማኛል ... እጣዬ ፣ ግን ፣ አልተገለጸልኝም ። ምስጋና ፣ በሌለው ፣ በባዶ ፣ ፍቅር ፣ ስንገዋለል ፣ ቆይቻለሁ ። ይህን ፣ ሁሉም ፣ ፈተና ፣ አልፈ ፣ ልክ ፣ ቀዝቃዛ ፣ ብረት ፣ ሆኛለሁ ። ስለሆንም ፣ የከበረ ፣ ስሜትና ፣ የሕይወት ፣ እንቡጥ ፣ አበባ ፣ ከኔ ፣ ተለይተው ፣ ይኖራሉ ። ከዚያን ፣ ጊዜ ፣ ጀምሮ ፣ በሕይወት ፣ ላይ ፣ የተሰነዘረ ፣ የመጥረቢያ ፣ ባሕርይ ፣ ሚና ፣ ይገፍ ፣ ፕራያለሁ ፤ እንደማረጃም ፣ ሰይፍ ፣ እድል ፣ በፈረደችላቸው ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ ስጨፍር ፣ ናፈ ያለሁ ። ይህንንም ፣ ሳደርግ ፣ ያላንዳች ፣ ሐዘንና ፣ ቅሬታ ፣ ነው ... የኔ ፣ ፍትር ፣ ማንንም ፣ አስያስቶ ፣ አያውትም ። ምክንያቱም ፣ ለምወ

«ዶክተር ፤ ነገ ፣ በተባለው ፣ ባሥር ፣ ሰዓት ፣ እጠብቅዎታለሁ ። ፈረሶቹም ፣ ተጭነው ፣ ይቆያሉ ። ደህና ፣ ይሁኑ ።»

ማታውኑ ፣ ከፍሉን ፣ ዘግቼ ፣ ቤቴ ፣ ቁጭ ፣ ብዬ ፣ አመሸሁ ። ከልዕልት ፣ ሊጐብኝስካያ ፣ ሲጠራኝ ፣ የመጣውን ፣ መልእክተኛ ፤ «ታምሚ ያለሁ» ብዬ ፣ መለስሁት ።

. . . . . .

ከሌሊቱ ፣ ስምንት ፣ ሰዓት ፣ ሁኖአል ... እኔን ፣ ግን ፣ እንቅልፍ ፣ አልወሰደኝም ... ነገ ፣ እጅ ፣ እንዳይንቀጠቀጥ ፣ ማረፍ ፣ እንዳለብኝ ፣ ይገባኛል ። ሆኖም ፣ ስድስት ፣ እርምጃ ፣ እርቀት ፣ ካለው ፣ ተኩሱን ፣ መሳት ፣ በጣም ፣ ያጠራጥራል ። አይ! ክቡር ፣ ግሩሽኒትስኪይ ፣ ውጥንዎ ፣ በፍጹም ፣ አይሳካልዎትም ። ሚናችንን ፣ እንቀያየራለን ። በዚያ ፣ በገረጣ ፣ ፊትዎ ፣ ላይ ፣ የተደበቀ ፣ የፍርሃት ፣ ስሜት ፣ መፈለጉም ፣ የኔ ፣ ሩንታ ፣ ይሆናል ። ስድስት ፣ እርምጃዎች ፣ ካልሆነ ፣ ብለው ፣ የተከራከሩት ፣ ለምን ፣ ይሆን? ፔቾሪን ፣ ለኢላማ ፣ ግንባሩን ፣ አናጥጦ ፣ ይሰጣል ፣ ብለው ፣ አስበው ፣ ይሆን? እስቲ ፣ እኮ ፣ ለሁሉም ፣ እጣችን ፣ ይፈርደናል ። ያኔ ... ያኔ ... ግን ፣ የእጣው ፣ እድል ፣ ፊቱን ፣ ወደሱ ፣ ያዞረ ፣ እንደሁ ፣ ምን ፣ ይበጀኛል? ይህም ፣ ቢሆን ፣ አይገርመኝም ፣ እስከዛሬ ፣ እድለኛ ፣ ሆኜ ፣ ቆይቻለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳቸው ፡ መስዋእት ፡ ለመሆን ፡ ገማጁ ፡ የሆንኩ በት ፡ ጊዜ ፡ አልነበረምና!.. የምወደው ፡ ለራሴ ፡ ደስታና ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካት ፡ ብቻ ፡ ነው ። የምወ ዳቸውንም ፡ ሴቶች ፡ ስሜት ፡ ለስላሳ ፡ ጠባይ ፡ ደስታና ፡ ጭንቀት ፡ እንደተራበ ፡ ሰው ፡ እመገ በዋለሁ ። ሆኖም ፡ መቼም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ጠግቤው ፡ አላውቅም ። ከድካምና ፡ ከረሐብ ፡ የተነሳ ፡ አእምሮው ፡ ተነክቶ ፡ ሥጋና ፡ ቪኖ ፡ እንደሚያልም ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ ቁጭ ፡ አልሁ ። በዚህ ፡ እራሱ ፡ በፈጠረው ፡ በምኞት ፡ ምግብ ፡ ጠግቦ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። ግን ፡ ከነበረበት ፡ የረ ሐብ ፡ እንቅልፍ ፡ ነቅቶ ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ ሲያጣ ፤ እረሐቡና ፡ ችግሩ ፡ ይብስበታል!

ምናልባት ፡ ነገ ፡ እሞት ፡ ይሆናል ። የኔን ፡ ጠባይ ፡ በደንብ ፡ የተረዳ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ፍ ጡር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የለም ። ግማሹ ፡ ከሚ ገባኝ ፡ የበለጠ ፡ አጋኖ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ሲለኝ ፤ ገሚሱ ፡ ግን ፡ ካለኝም ፡ አሳንሶ ፡ ይጠ ላኛል ። አንዱ ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ሲለኝ ፡ ሌ ላው ፡ መጥፎ ፡ ነበር ፡ ያለኛል ። ሆኖም ፡ ሁለቱ ፡ አስተያየት ፡ ትክክል ፡ አልነበረም ። ከእንግ ዲህ ፡ ወዲህ ፡ መኖር ፡ ትርጉም ፡ አለው፣ ያም ፡ ሆን ፡ ይህ ፡ ትኖራለህ ። አዳዲስ ፡ ነገር ፡ መያዝ ፡ እየጠበቅህ ፡ በዚያም ፡ እየተገፋፋህ ፡ ትኖ ራለህ ። ይህም ፡ አስቴኛና ፡ አብሻቂ ፡ ነው፤

«እን» ሠፈር ፡ ከመጣሁ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ተኩል ፡ ሆነኝ ። ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ መደእደን ፡ ሄደ ። ብቻዬን ፡ ነኝ ፤ ከመስኩቱ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብያለሁ ። በሩቅ ፡ የሚታዩ ፡ ተራራዎች ፡ በከባድ ፡ ደመና ፡ ተሸፍነዋል ። ፀሐይዋ ፡ በጭጋግ ፡ ውስጥ ፡ ልክ ፡ እንደቢጫ ፡ ነጥብ ፡ ሁና ፡ ትታያለች ። ይበርዳል ። ነፋሱ ፡ የመስኩቱን ፡ መሸንጐርያ ፡ ያወዛውዛል ... ይሰለቻል! በብዙ ፡ አጋጣሚዎች ፡ የተቋረጠብኝን ፡ ማስታወሻ ፡ መጻፌን ፡ እቀጥላለሁ ።

የመጨረሻውን ፡ ገጽ ፡ ሳነብ ፡ ያስቀኛል ። የሞ ሞት ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ። ግን ፡ አልተቻለም ። የሥ ቃዬን ፡ የመጨረሻ ፡ ጽዋ ፡ ገና ፡ አልጨበጥሁም ። አሁን ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የምኖር ፡ ይመስለኛል! ያለፈው ፡ ሁሉ ፡ በጉልህ ፡ ተቀርጾ ፡ ከአእምሮዬ ፡ ሳይወጣ ፡ እንዳለ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተረሳኝ ፡ ነገር ፡ የለም ።

የፍልምያው ፡ ዋዜማ ፡ ምንም ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳልወሰደኝም ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። አንድ ፡ ልገልጸው ፡ የማልችለው ፡ ስሜት ፡ አካ ላቴን ፡ ወሮት ፡ ስለነበረ ፡ ብዙም ፡ ለመጻፍ ፡ አልቻልሁም ። ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ስንጐራደድ ፡ ቆየሁ ። ከዚያም ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ በጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሞልቶር ፡ ስኩትን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ጀመርሁ ። መጽሐፉም ፡ ፈጥንቃዊ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

አሚሚት» ተብሎ ፡ ይጠራል ። በመጀመሪያ ፡ መጽሐፉን ፡ ለማንበብ ፡ ራሴን ፡ ማስገደድ ፡ ነበረብኝ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በመጽሐፉ ፡ አስደናቂ ፡ ታሪክ ፡ ተማርኬ ፡ ተሳብሁ ። ለዚሁ ፡ አስደናቂ ፡ ባለቅኔ ፡ አንባቢው ፡ በመጽሐፉ ፡ ስለሚ ደሰትበት ፡ በዚያኛው ፡ ዓለም ፡ ዋጋውን ፡ እይከ ፈልለትምን ፡ በማለት ፡ አሰብኩ ።

በመጨረሻም ፡ ነጋ ፤ ተዝናንቻለሁ ። ፊቴን ፡ በመስተዋት ፡ ስመለከት ፡ አለመተኛቴን ፡ የሚ መሰክርብኝ ፡ የገረጣ ፡ ፊት ፡ ታየኝ ። ዓይኖቼ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጥላሸት ፡ ቢመስሉም ፡ በኩራ ት ፡ ያበሩ ፡ ነበር ። በራሴ ፡ ተደሰትሁ ።

ፈረሶቼ ፡ እንዲጫኑ ፡ ትዕዛዝ ፡ ከሰጠሁ ፡ በኋ ላ ፡ ለባብሼ ፡ ወደፀበሉ ፡ በፍጥነት ፡ አመራሁ ። በናርዛንም ፡ ፀበል ፡ ውስጥ ፡ ስንከር ፡ የመንፈ ስና ፡ የአካል ፡ ብርታት ፡ አገኘሁ ። ከፀበሉም ፡ ስመለስ ፡ ልክ ፡ ወደጎንስ ፡ ምሽት ፡ የምጓዝ ፡ መሰለኝ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሰውነት ፡ አካል ፡ ብርታት ፡ በውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አያሳድርም ፡ ቢሉኝ ፡ አላምንም ።

ቤቴ ፡ ስደርስ ፡ ዶክተሩን ፡ አገኘሁት ። ግራጫ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የፈረሰኛ ፡ ሱሪ ፡ ታጥቋል ። የቼርኬስ ፡ ባርኔጣና ፡ ባለመቀነት ፡ ረጅም ፡ ኮት ፡ ያደባል ። በዚያ ፡ ትልቅ ፡ ባርኔጣ ፡ ሥር ፡ ያቺን ፡ ትንሽ ፡ ረዘን ፡ ሳያ ፡ በሳት ፡ ተንፈቀፈቅሁ ። ባጠቃላይ ፡ ሠላ ፡ ሁኔታው ፡

ለጦርነት ፡ የተፈጠረ ፡ አይመስልም ። በዛሬ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ያብሱን ፡ ለውግያ ፡ የተሰለፈ ፡ አይመስልም ።

«ምነው ፡ እንደዚህ ፡ አዝነዋል ፡ ዶክተር? ለምች ፡ ያለምንም ፡ ማጉረምረም ፡ ወደዚያኛው ፡ ዓለም ፡ ሲሸጋገሩ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ አላዩምና ፡ ነው? አንድ ፡ ጽኑ ፡ በሽታ ፡ ይዞኛል ፡ እንበል ። የመዳንም ፡ የመሞትም ፡ እኩል ፡ ዕድል ፡ አለኝ ፤ ሁለቱም ፡ ለዓለማችን ፡ የተለመዱ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። ነና ፡ በሽታው ፡ ያልታወቀ ፡ ሕመምተኛ ፡ እድርገው ፡ ይቁጠሩኝ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የርስዎ ፡ ጥርጣሬ ፡ ከፍተኛ ፡ ይሆናል ። ለማወቅም ፡ ያለዎ ፡ ጉጉት ፡ የበለጠ ፡ ይጠነክራል ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ከፍተኛ ፡ የአካል ፡ ምርመራ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈልጋሉ ... ሞትን ፡ በግድ ፡ መፈለግ ፡ ራሱ ፡ ከፍተኛ ፡ በሽታ ፡ አይደለም ፡ ይላሉ!»

ይህ ፡ አነጋገሬ ፡ ዶክተሩን ፡ ከነበረበት ፡ ሐዘን ፡ አላቀቀው ።

ፈረሶቻችን ፡ ላይ ፡ ወጣን ። ቬርነር ፡ የፈረሱን ፡ ልጓም ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ጨብጦ ፡ ይዟል ፤ በእንድ ፡ እጅም ፡ መንደሩንና ፡ የጦር ፡ ሠፈሩን ፡ ጋልበን ፡ አለፍን ። እንድ ፡ ጠመዝማዛ ፡ መንገድ ፡ ተከትለን ፡ ወደሸለቆ ፡ ገባን ። መንገዱ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ድምጽ ፡ ባላቸው ፡ ጅረቶች ፡ በሚ ቋረጡ ፡ በረጃጅም ፡ ሳሮች ፡ ሸለቆው ፡ ተከቧል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መንገዱ ፡ እየጠበበ ፡ ሰማያዊ ፡ እየሆነና ፡ እያ
ስፈራ ፡ ሄደ ፡ በመጨረሻም ፡ ካንድ ፡ ጠቅጣቃ ፡
ጠንካራ ፡ ግድግዳ ፡ የተላጠቀ ፡ ይመስላል ።እኛም ፡
ድምጻችንን ፡ እጥሩተን ፡ መንገዳችንን ፡ ቀጠልን ።
«ኑግዘውን ፡ ጽፈዋል?» ሲል ፡ ቩርነር ፡ በድ
ንገት ፡ ጠየቀኝ ።
«የለም ።»
«ቢገደሉስ?»
«ወራሾች ፡ እራሳቸው ፡ ፈልገው ፡ ያገኙ
ታል ።»
«የመጨረሻ ፡ የስንብት ፡ ቃልዎን ፡ የሚልኩ
ለት ፡ ዓደኛ ፡ አውነት ፡ የለዎትምን?»
እራሴን ፡ ነቀነቅሁ ።
«ማስታወሻ ፡ የሚተውላት ፡ ሴት ፡ እንኳ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የለችም?»
«የልቤን ፡ ምስጢር ፡ ገልጬ ፡ እንዳወራዎ ፡
ይፈልጋሉ ፡ ዶክተር?» ካልሁት ፡ በኋላ ፡
ውይይቴን ፡ ቀጠልሁ ።
«እንደሚያዩኝ ፡ የምኖረው ፡ ሰዎች ፡ ሲሞቱ ፡
በመጨረሻ ፡ እስትንፋሳቸው ፡ የፍቅራቸውን ፡
ስም ፡ ጠርተው ፡ የተሠራ ፡ ወይም ፡ ያልተሠራ ፡
ዑደር ፡ የሚያመርሱበትን ፡ ዘመን ፡ አልፈ ፡
ነው ። ስለሞት ፡ ትርብነትና ፡ መቻል ፡ ሳስብ ፡
ስለራሴ ፡ ነው ፡ የማስበው ፡ ሴሎች ፡ እንኳ ፡
ያዘንን ፡ እያሠሩትም ፡ ብዙ ፡ በግሌ ፡ አሰ
ላስላለሁ ። ነገ ፡ ጠዋት ፡ የሚረሱኝ ፡ ዓደኞቼ ፡

የዶክተሩ ፡ ፈረስ ፡ በያንዳንዱ ፡ ፈላሽ ፡ ውኃ ፡
ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ይቆም ፡ ስለነበር ፡ በጣም ፡ ተቸ
ግሮ ፡ ነበር ።
እንደዚያን ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ የጠራ ፡ ሰማይና ፡
ንጹህ ፡ አየር ፡ መቼም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ አይቼ ፡
አላውቅም ። በነዚያ ፡ ሰማያዊ ፡ አድማስ ፡
በለበሱ ፡ ተራሮች ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ፀሐይዋ ፡
ጋር ፡ ብቅ ፡ ማለትዋ ፡ ነው ። የመጀመርያዋ ፡
የጮራዋ ፡ ሙቀት ፡ ከጠዋት ፡ ብርድ ፡ ጋር ፡
ሲቀላቀል ፡ የሚሰጠው ፡ ጣፋጭ ፡ መዓዛ ፡
ልዩ ፡ ስሜት ፡ ይሰጣል ። የዚያ ፡ የወጣት ፡
ቀን ፡ የፀሐይ ፡ ጮራ ፡ እኛ ፡ ባለንበት ፡
ሸለቆ ፡ ገና ፡ አልደረሰም ። ከበላያችን ፡ ያሉት ፡
የስንጥር ፡ ቋጥኞች ፡ እናቶች ፡ ግን ፡ ብርሃኑ ፡
ደርሷቸዋል ። በቋጥኞቹ ፡ ስንጥቅ ፡ ላይ ፡ ከበቀ
ሉት ፡ ጥቅጥቅ ፡ ካሉት ፡ ጉጭታዎች ፡ የተንጠለጠ
ሉት ፡ እንደአልማዝ ፡ የሚያንፀባርቁት ፡ ጤዛ
ዎች ፡ በትንሽ ፡ የነፋስ ፡ ሽውታ ፡ ከላይ ፡ እየረ
ገፉ ፡ አረጠቡን ። ባዝንለት ፡ ከመቼውም ፡ ይበል
ጥ ፡ ተፈጥሮን ፡ እንደወደድሁና ፡ እንዳከበርሁ ፡
ትዝ ፡ ይለኛል ። ከሰፈው ፡ የወይን ፡ ቅጠል ፡ ላይ ፡
እየተንጠባጠበ ፡ የሚለያን ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡
ቀለም ፡ የምታንፀባርቀውን ፡ የያንዳንዷን ፡
ጤዛ ፡ ጠብታ ፡ መመልከት ፡ ምንኛ ፡ ደስታን ፡
ይሰጣል! ዓይኖቼ ፡ ከሩት ፡ ያንን ፡ ሚስጥግ ፡
ሰንጥቀው ፡ ለመግባት ፡ ይሻሉ ፡ አልጠገቡም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ብለው ፡ እን
ደሚያስወሩ ፡ አምላክ ፡ ይወቅ ፤ ሴቶች ፡ በሌ
ሎች ፡ ጉያ ፡ ሥር ፡ ገብተው ፡ መዳጀቻቸው ፡
ነገ ፡ በማልኖረው ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ቅናት ፡ እንዳያ
ድርባቸው ፡ እያፈዙብኝ ፡ የሚያንሾካሹኩት ፡
ይታዩኛል ። ታድያ ፤ እኔ ፡ ለነሱ ፡ ግድ ፡ አለኝ?
ከሕይወት ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ሐሳብ ፡
ጨልፈያለሁ ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ ስሜት ፡ በል
ቤ ፡ አላስቀረሁም ፤ ለብዙም ፡ ጊዜ ፡ የኖርሁት ፡
በስሜት ፡ ሳይሆን ፡ ባንጐሌ ፡ ነው ። ስሜቴንና ፡
ድርጊቴን ፡ ከፍላጐቴ ፡ ጋር ፡ ካመሳዘንሁና ፡
ካሰላሰልሁ ፡ በኋላ ፡ ያለምንም ፡ ርህራሄ ፡ ኖሬ
ያለሁ ። የሁለት ፡ ሰው ፡ አካላት ፡ በራሴ ፡
ውስጥ ፡ ይኖራሉ ። አንደኛው ፡ ሰው ፡ የሚለው ፡
የቃል ፡ ትርጉም ፡ የወከለ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡
ግን ፡ እያሰላሰለና ፡ እያውጠነጠነ ፡ በአንደኛው ፡
ላይ ፡ ይፈርዳል ። የመጀመርያው ፡ አካሌ ፡ ምናል
ባት ፡ ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ከርስዎና ፡ ከዚህ ፡
ዓለም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይለያል ። ሁለተኛው ፡
ግን ... ሁለተኛው ... ዶክተር! ያያሉ? እዛ ፡ ማ
ዶ ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ ሶስት ፡ ሰዎች ፡ ይታ
ይዎታል? ጠላቶቻችን ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ።»

ፈረሶቻችንን ፡ ሬጠን ፡ እያልን ፡ እንጋልብ ፡
ጀመር ።

ተራራው ፡ ሥር ፡ ካሉት ፡ ቱጉዝጠች ፡
አጠገብ ፡ ሶስት ፡ ፈረሶች ፡ ታሰረዋል ። እኛም ፡

ከዚያው ፡ ቦታ ፡ ፈረሶቻችንን ፡ አሰርን ፤ ግሩ
ሽኒትስኪይ ፡ ከፈረሰኛው ፡ ሻምበልና ፡ ከአ.
ሻን ፡ አግናቲች ፡ (የዘር ፡ ግንድ ፡ መጠርያ ፡
ስሙን ፡ አላውቅም) ጋር ፡ ሆነው ፡ ወደማ
ጠቁን ፡ የሚመራውን ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡
ይዘን ፡ በእግራችን ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልን ።

የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ በማሾፍ ፡ ፈገግ ፡
ብሎ ፡ «ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ጠበቅናችሁ» አለን ።

ሰዓቴን ፡ አውጥቼ ፡ አሳየሁት ።

«እንግዲያውስ ፡ የኔ ፡ ሰዓት ፡ ፈጥኖ ፡ ነው»
በማለት ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀኝ ።

ለብዙ ፡ ደቂቃዎች ፡ ያህል ፡ እካባቢው ፡
በፀጥታ ፡ ተዋጠ ። ያህም ፡ ፀጥታ ፡ በመጨረሻ ፡
የደፈረሰው ፡ ዶክተሩ ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ ሲ
ያነጋግር ፡ ነው ።

«ከቡራን! ሁለታችሁም ፡ ለፍልምያ ፡ እዚህ ፡
ድረስ ፡ በመምጣታችሁ ፡ ከብራችሁን ፡ ለማስ
ከበር ፡ ዝግጁ ፡ መሆናችሁን ፡ አስመሰክራች
ኋል ። ከእንግዲህ ፡ በኋላ ፡ ከቡራን ፤ ሁለ
ታችሁ ፡ ተነጋግራችሁ ፡ ከእንድ ፡ ስምምነት ፡
ላይ ፡ ደርሳችሁ ፡ ፍልምያው ፡ ብትተውት ፡
ምን ፡ አለ?»

«በበኩሌ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ» አልኩ ።

የሻምበሉ ፡ የጠቀሰው ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡
የተናገርኩት ፡ ከፍርኃት ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡ በማ
ለት ፡ ኩራት ፡ ታየበት ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ፡ ደህና ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ሁኔታው ፡ እናያያኝ ።

ዶክተሩ ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ በተረበሸ ፡ ድምጽ ፤ «ምክክር ፡ እንዳላቸው ፡ እረሱት ፡ እንዴ? እኔ ፡ እንደሆነ ፡ ሽንጥ ፡ እንዴት ፡ እንደሚጐርስ ፡ አላወቅም ። ታድያ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ... በጣም ፡ የሚገርሙ ፡ ሰው ፡ ነዎት ። የጠነሰሱትን ፡ ሴራ ፡ እንደነቁባቸው ፡ ይንገርዋቸው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ አይደፍሩም ... ምን ፡ እንደሚሠሩ ፡ አይገባኝም ። እንደወፍ ፡ ከመቅጽበት ፡ ያወርድ ብዎታል ...» አለኝ ።

«እባክዎ ፡ ዶክተር ፤ አይደንግጡ ፡ ትንሽ ፡ ይቆዩ ... ጉዳዩን ፡ የማቀርበው ፡ እነሱ ፡ እንዳይጠ ቀሙበት ፡ መፈናፈኛ ፡ አሳጥቼ ፡ ነው ። ተዋቸው ፤ ይንሾካሹኩ ...»

ከዚያም ፡ ድምጼን ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፤ «ከቡራ ን! አሁንስ ፡ ሥራችሁ ፡ ሁሉ ፡ አድካሚ ፡ ሆነ ፤ የምንፋለም ፡ ከሆነ ፡ እንፋለም ፤ ለመመካከሩ ፡ እንደሆነ ፡ ትላንት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ነበረላችሁ...»

«ተዘጋጅትናል ፤ ቦታችሁን ፡ ያዙ ፡ ከቡራን! ዶክተር ፡ እባክዎ ፡ ስድስት ፡ እርምጃ ፡ ቢለኩ!» ሲል ፡ የሻምበሉ ፡ ተናገረ ።

ኢሻን ፡ ኢማናቲም ፡ በዛ ፡ በቀጭን ፡ ድምጹ ፡ ተደገመ ፤ «ቦታችሁን ፡ ያዙ» አለ ።

«ይቅርታ ፡ አድርጉልኝና ፡ እንድ ፡ ሌላ ፡ የተ ረሳ ፡ ነገር ፡ አለ ። ፍልምያው ፡ የሞትና ፡ የሽ

እስከዚህ ፡ ደቂቃ ፡ ድረስ ፡ በጣም ፡ ገርጥቶ ፡ ነበር ። ከመጣሁ ፡ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አየኝ ። በውስጡ ፡ ቅራኔዎች ፡ እንደሚገ ጩበት ፡ አስተያየቱ ፡ ያስታውቃል ።

«ፍልሚያው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንዲሆን ፡ ይፈልጋሉ? የሚቻለኝን ፡ በሙሉ ፡ ለማድረግ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ...» በማለት ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ጠየቀኝ ።

«የኔ ፡ ፍላጐት ፡ አሁንም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ላደረጉት ፡ ዘለፋ ፡ ባደባባይ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲ ጠይቁኝ ፡ ነው ።»

«አይ! ጌታዬ! እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ በማቅረብዎ ፡ ይገርመኛል ።»

«ታድያ ፤ ሌላ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ ላቀርብልዎ?»

«እንግዲያውስ ፡ እንፋለም ።»

ትከሻዬን ፡ ወዝውዤ ፤ «መልካም ፤ ግን ፡ ከሁለት ፡ አንዳችን ፡ እንደምንሞት ፡ ያስታ ውሱ» አልሁት ።

«እርስዎ ፡ እንደሚሆኑ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።»

«እኔ ፡ ደግሞ ፡ እርስዎ ፡ ነዎት ፡ እላለሁ ።»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ተቆጥቶ ፡ ፊቱ ፡ ቀላ ፤ ቱቦሎም ፡ እራሱን ፡ አሰገድዶ ፡ የግዴታ ፡ ሳቁን ፡ ፈገግ ፡ አለ ። የሻምበሉ ፡ እጅን ፡ ወደጐን ፡ ጐት ቶ ፡ ወስዶ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሰንሾካሾኩ ፡ ቆዩ ። ወደዚህ ፡ ስመጣ ፡ መንፈሴም ፡ ሆነ ፡ ስሜቴ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ረት ፡ ስለሆነ ፡ ማንኛውንም ፡ ጥንቃቄ ፡ መው
ሰድ ፡ ይኖርብናል ። ይዝውም ፡ ይህ ፡ ጠባችን ፡
ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ መያዝ ፡ እንዳለበትና ፡ ዳኞቻች
ንም ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጎላፈነት ፡ እንደሌለ
ባቸው ፡ መስማማት ፡ አለብን ። በዚህ ፡ ትስማማ
ላችሁ?» በዱ ፡ ጠየቅኋቸው ።

«በሙሉ ፡ እንስማማለን ።»

«እኔ ፡ ያስብሁት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ከዚያ ፡
ቋጥኝ ፡ ድንጋይ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ በስተቀኝ ፡
ያለችዋ ፡ ጠባብ ፡ ቦታ ፡ ትታያችኋለች? በቋ
ጥኝ ፡ አፋፍ ፡ እስከመሬት ፡ ድረስ ፡ ቢኖንስ ፡
ቢያንስ ፡ ሠላሳ ፡ ሜትር ፡ ይሆናል ፡ ከዚታቹ ፡
የሾሉ ፡ ድንጋዮች ፡ እሩቸውን ፡ ከፍተው ፡ ይጠ
ብቃሉ ። ትንሽ ፡ የቆሰለ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡
ከወደቀ ፡ አይተርፍም ። እያንዳንዳችንም ፡ ከገ
ማቱ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ እንቆማለን ፤ የርስዎንም ፡ የስ
ድስት ፡ እርምጃ ፡ እርቀት ፡ ያሚላል ። ከሁሰታ
ችን ፡ እንዳችን ፡ ከቆሰልን ፡ መደገደሉ ፡ መድ
ቀን ፡ መንከታከት ፡ አይቀርልንም ። ከዚያም ፡
ይከተር ፡ የገባችውን ፡ ጥይት ፡ ቀይው ፡ ነወጡ ፡
በኋላ ፡ አሚሚቱ ፡ በደንገት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡
ያስችላል ። ማናችንም ፡ በመጀመርያ ፡ እንዲ
ምንተኩሰ ፡ እጣ ፡ እናወጣለን ። በመጨረሻም ፡
ለማለት ፡ የምፈልገው ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ፍል
ምያ ፡ የሚልፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።»

መለማተን ፡ ሚንቅላተን ፡ አወጣውሠ ፡ የገ
ለፀውን ፡ ግራቪኒትስኪን ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡

ከየው ፡ በኋላ ፡ «ደሁን» ሲል ፡ የሻምበሉ ፡
ተናገረ ። የግራቪኒትስኪይ ፡ ፊት ፡ በየደቂቃ
ው ፡ ይተያየራል ። አስቸጋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡
እስገብቸሞለሁ ። ሁኔታ ፡ ገፋፍቶኝ ፡ ባላስገባ
ው ፡ ኖሮ ፡ በተላሉ ፡ እግሬን ፡ አቁስሎ ፡ ንዴቱ
ን ፡ ተወጥቶ ፡ የሕሊናው ፡ ውቅሳም ፡ ይቀልለት ፡
ነበር ። እሁን ፡ ግን ፡ ወደሰማይ ፡ መተኮስ ፡
አለበት ፡ ካለበለዚያም ፡ ገዳይ ፡ መሆን ...
ወይም ፡ ዘደውን ፡ ሁሉ ፡ ቀይሮ ፡ እኔ ፡ የወሰድ
ሁትን ፡ አስጊ ፡ ምርጫ ፡ መውሰድ ፡ ይኖርበ
ታል ። በዚች ፡ ደቂቃ ፡ በግራቪኒትስኪይ ፡ ቦታ ፡
ላይ ፡ መሆንን ፡ አልፈልግም ። የሻምበሉን ፡
ወደጉን ፡ እድርጉ ፡ በጣም ፡ በተረበሸ ፡ ሁኔታ ፡
ያነጋግረው ፡ ነበር ። እነዚያም ፡ ሰማያዊ ፡ የመ
ሰሉ ፡ ከንፈሮቹ ፡ ሲርበደበዱ ፡ አየሁ ። የሻ
በሉ ፡ ግን ፡ በማሾፍ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ፊቱን ፡
አዞረበት ። ድምፁንም ፡ ከፍ ፡ እድርጉ ፡ ግሩቪ
ኒትስኪይን ፡ «ደደብ ፡ ነህ ፤ ምንም ፡ አይገባ
ህም» ካለው ፡ በኋላ ፡ «እንሂድ ፡ ከቡራን» አለን ።

በቴጥቋጠዎቹ ፡ መካከል ፡ እየተጠማዘዘ ፡
የሚሄደውን ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ተከትለን ፡
መደላይ ፡ ወጣን ። የአለቱ ፡ ድንጋይ ፡ በተፈ
ጥሮ ፡ ተበርበሮ ፡ መወጣጫ ፡ መሠላል ፡ ሠር
ቷል ። የቴጥቋጠዎችን ፡ ቅርንጫፍ ፡ እየቧጠ
ጥን ፡ ወደላይ ፡ መውጣት ፡ ጀመርን ። ግሩቪኒ
ትስኪይ ፡ ከፈት ፡ ለፈት ፡ ቀድሞ ፡ ድኮያል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኞችና ፡ ዶክተሩ ፡ ከኋላው ፡ ሲከተሉት ፡ እኔ ፡ መጨረሻ ፡ ነበርሁ ።

ዶክተሩ ፡ እጁን ፡ በኃይል ፡ ጨበጥ ፡ አድርጐ ፡ ከያዘኝ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ። «በእውነቱ ፡ የሚገርሙ ፡ ሰው ፡ ነዎት ። እስቲ ፡ የደም ፡ ስርዎን ፡ ላዳምጠው ። የተረበሹ ፡ ይመስላሉ ። ግን ፡ ፊትዎ ፡ ምስጢርዎን ፡ አያወጣም ። እንዲያውም ፡ ዓይናችዎ ፡ ከወትሮው ፡ ዛሬ ፡ የበለጠ ፡ ያበራሉ ።»

በድንገት ፡ ኮረት ፡ ድንጋዮች ፡ እየተንኳኩ ፡ ከእግራችን ፡ ሥር ፡ ይወድቁ ፡ ጀመር ።

ምን ፡ ሆነ? ምን ፡ መጣ? ብዬ ፡ ስመለከት ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ በያዘው ፡ ቁጥቋጦ ፡ ተንተሎበት ፡ ሊወድቅ ፡ ሲል ፡ ከኋላው ፡ ያሉት ፡ ዳኞች ፡ ደግፈው ፡ አዳኑት ።

«ተጠንቀቁ!.. ያለጊዜው ፡ አይውደቁ! መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ነው ። ጁለስ ፡ ሲዘርን ፡ ያስታውሱ» በማለት ፡ ጮህ ፡ ብዬ ፡ ተናገርሁት ።

በመጨረሻም ፡ ከኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ደረስን ። የነበረችዋም ፡ ትንሽ ፡ ቦታ ፤ ሆን ፡ ብላ ፡ ለፍልምያ ፡ እንያተዘጋጀች ፤ በአሸዋ ፡ ተደልድላለች ። ቢጫማ ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ የጠዋት ፡ ሜጋማ ፡ በአካባቢው ፡ ተሰብጧል ። የተራሮችም ፡ ቁንጮች ፡ ከራቅ ፡ ሲታዩ ፡ ሰፍረው ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ያመሰላሉ ። በስተደቡብ ፡ የኢልብራስ ፡ ተራራ ፡ ነጭ ፡ በረዶ ፡

ለብሶ ፡ ቆሟል ። በነዚያ ፡ ነጭ ፡ ባርኔጣ ፡ በደፉ ፡ ጫፎችም ፡ ዙርያ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡ ፡ ክንፍ ፡ ያላቸው ፡ የሚመስሉ ፡ ያመናዎች ፡ ያንጃብቡ ፡ ይታል ። ከቆምንበት ፡ ጠባብ ፡ ደልዳላ ፡ ቦታ ፡ ወደገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ቁልቁል ፡ ተመለከትሁ ። አዘቅት ፡ አዙሮ ፡ ሊጥለኝ ፡ ነበር ። በገደሉ ፡ አዘቅት ፡ ልክ ፡ እንደመቃብር ፡ ቀዝቃዛና ፡ ጥልመት ፡ ነው ። በአውሎ ፡ ነፋስና ፡ በእርጅና ፡ የተቀረፀው ፡ አለት ፡ ድንጋይም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ከላይ ፡ ቀለቡን ፡ ይጠብቃል ።

ለፍልምያ ፡ የቆምንበት ፡ ቦታ ፡ ባለሶስት ፡ ማዕዘን ፡ ናት ፤ ስድስቱ ፡ እርምጃ ፡ ተለካ ። የሚተኮስበት ፡ ሰው ፡ ጀርባውን ፡ ወደገደሉ ፡ አድርጐ ፡ እንዲቆም ፡ ተስማማን ። ካልሞተም ፡ ቦታቸውን ፡ ይቀያየራሉ ።

ግሩሽኒትስኪይን ፡ ለመሞከር ፡ ስለፈለግኩ ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ እድል ፡ ሰጠሁት ። ምናልባት ፡ እርሀራሄ ፡ በልቡ ፡ ገብቶ ፡ ይሆን? እንዲያማ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የማንኛውም ፡ ጉዳይ ፡ በሰላም ፡ ባለቀ ፡ ነበር ። ግን ፡ ያ ፡ ደካማ ፡ ጠባይና ፡ እራስ ፡ መዳድነት ፡ ላያሸንፈው ፡ አይቀርም ... ይህንንም ፡ የማያረገው ፡ እድለኛ ፡ ሆኜ ፡ ካልሞትኩ ፡ ከቀረሁ ፡ ብገለው ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሕሊና ፡ ወቀሳ ፡ እንዳይደርስብኝ ፡ ነው ። ከራሱ ፡ ሕሊና ፡ ጋር ፡ ያልታገለ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ አለ?

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሰዓቱ ፡ ደርሷል» በማለት ፡ ዶክተሩ ፡ ልብሴን ፡ ሳብ ፡ አድርጉ ፡ ነገረኝ ፤ ከዚያም ፤ «አሁን ፡ እነሱ ፡ የተበተቡትን ፡ ሴራ ፡ እንደ ሚያውቁ ፡ ካልነገርዋቸው ፡ አበቃ ። አያዩም ፤ ሽጉጦቻቸውን ፡ እያጐራሱ ፡ ናቸው ፤ እርስዎ ፡ ካልተናገሩ ፡ እኔ ፡ እናገራለሁ ...» አለኝ ።

እጇን ፡ ያዝ ፡ አድርጌም ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ።

«በፍጹም ፡ አያስፈልግም ፤ ዶክተር! ጉዳዩን ፡ ያበላሹብኛል ፤ ጣልቃ ፡ ላይገቡ ፡ ቃል ፡ ገብተው ልኝ ፡ ነበር ። በቃልዎ ፡ ቢፀኑ ፤ ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ያገባዎታል? ለመሞት ፡ እፈልግስ ፡ እን ደሁ ፡ በምን ፡ ያውቃሉ?»

ዶክተሩ ፡ በአድናቆት ፡ ተመለከተኝ ።

«አዩ! ደግ ፤ ይህ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ከወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ሄደው ፡ ግን ፡ በኔ ፡ እን ዳያዝኑ ።»

በዚህ ፡ ወቅት ፡ የሻምበሉ ፡ ሽጉጥን ፡ አጉርሷል ። እንዱን ፡ ለግሩሽኒትስኪይ ፡ ፈገ ግታ ፡ በተመላበት ፡ ሹክሹክታ ፡ ሲሰጠው ፡ ሁለተኛውን ፡ ለኔ ፡ አደለኝ ።

እቦታዬ ፡ ሄጄ ፡ ከቆምሁ ፡ በኋላ ፤ ምናልባት ፡ ከቆሰልሁ ፡ ወደገደሉ ፡ እንዳልወድቅ ፡ በማ ለት ፤ የግራ ፡ እግሬን ፡ ከእንድ ፡ ድንጋይ ፡ ጋራ ፡ አስጠግቼ ፡ ወደፊት ፡ ጉብደድ ፡ ብዬ ፡ ቆምሁ ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከኔ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፡

«ዶክተር ፡ እጣዋን ፡ ያውጡ?» ብሎ ፡ የሻም በሉ ፡ ተናገረ ።

ዶክተሩ ፡ ከኪሱ ፡ እንድ ፡ ሳንቲም ፡ አ ውጥቶ ፡ ወደሰማይ ፡ አሽቀነጠረ ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ በድንገት ፡ ከእንቅልፉ ፡ በወዳጅ ፡ እንደተቀሰቀሰ ፡ ሰው ፤ «አንበሳ» ብሎ ፡ ጮኸ ።

«ጐፈር» ብዬ ፡ እኔም ፡ በተራዬ ፡ ተናገርሁ ።

ሳንቲምም ፡ በአየር ፡ ከተሽከረከረች ፡ በኋላ ፡ ቅጭል ፡ ብላ ፡ ወደመሬት ፡ አረፈች ። ሁላች ንም ፡ እየሮጥን ፡ ሄደን ፡ ተመለከትናት ።

«ግሩሽኒትስኪይ ፤ እድለኛ ፡ ነዎት ፤ የመ ጀመርያ ፡ ተኳሽ ፡ ሆነዋል ፤ ግን ፡ ልብ ፡ ይበሉ! ካልገደሉኝ ፡ እንደማልምርዎ ፡ እምልልዎታ ለሁ ።»

ግሩሽኒትስኪይ ፡ ፊቱ ፡ ደም ፡ ለበሰ ፤ መሣ ርያ ፡ ያልያዘውን ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ በጣም ፡ አሳፍሮታል ። ልብ ፡ ብዬ ፡ ተመለከትሁት ፤ ካሁን ፡ አሁን ፡ ከጫማዬ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ይቅ ርታ ፡ ይጠይቅኛል ፡ ብዬ ፡ ያሰብሁበትም ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ። ሆኖም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አሰቃቂ ፡ ሽር ፡ ለማናዘዝ ፡ ድፍረት ፡ ያንሰዋል ። የቀረው ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ወደ ሰማይ ፡ መተኮስ ፡ ነው! ዒላማን ፡ ሌላ ፡ ፍል ምያ ፡ ይጠይቃል ፡ የሚለው ፡ ግሙቱ ፡ ይህን ፡ ከማድረግ ፡ ሳያግደው ፡ አይተኮም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ተናገረው ፡ በኋላ ፡ ወደቦታው ፡ ተመለሰ ።
ዓይኖቹ ፡ እምባ ፡ ያቀረሩት ፡ ኢቫን ፡ ኢግናቲ
ችም ፡ ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ ተሳስሞ ፡
ተሰናበተው ። በመጨረሻም ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡
ብቻውን ፡ ከፊት ፡ ለፊቴ ፡ መጥቶ ፡ ተገተረ ።
እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ የነበረኝን ፡
ስሜት ፡ ለራሴ ፡ ለማስረዳት ፡ እሞክራለሁ ።
ይህም ፡ ስሜት ፡ የከብሬ ፡ መነካት ፡ ከመሆ
ኑም ፡ ሌላ ፤ እሁን ፡ ከፊቴ ፡ ቀዝቅዞ ፡ በዝምታ ፡
የቆመው ፡ ሰው ፡ ከሁለት ፡ ደቂቃ ፡ በፊት ፡
ያለምንም ፡ እርጎራሄ ፡ እንደውሻ ፡ ሊገድ
ለኝ ፡ ቆርጦ ፡ እንደነበረ ፡ መሆኑን ፡ እያሰብኩ ፡
የነበረኝ ፡ ብሽቀት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ የበለጠም ፡
ቆስሎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከኋላዬ ፡ ካለው ፡ ገደል ፡
ተሰባብሬ ፡ ቀርቼ ፡ ነበር ።

ለጥቂት ፡ ደቂቃዎችም ፡ ያህል ፡ ምናልባት ፡
የፀፀት ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ ትኩር ፡ ብዬ ፡
ተመለከትሁት ። በፀፀትም ፡ ፈንታ ፡ ያየሁት ፡
ሳቁን ፡ ለማፈን ፡ ሲጨነቅ ፡ ነው ።

«ከመሞትዎ ፡ በፊት ፡ የመጨረሻ ፡ ጸሎት
ዎን ፡ እንዲያደርጉ ፡ ጊዜ ፡ እሰጥዎታለሁ»
አልሁት ።

«ከራስዎ ፡ ነፍስ ፡ አብልጠው ፡ ለእኔ ፡ ነፍስ ፡
የሚያስቡ ፡ መስለው ፡ አይቅረቡ ። የምለም
ንም ፡ እንድ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ይተኩሱ!»

«ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተናገሩትን ፡ አስበው ፡

ቦታ ፡ ያዘ ። ምልክቱም ፡ ሲሰጥ ፡ ሽጉጡን ፡
ወደላይ ፡ አነሳው ። ጉልበቶቹ ፡ ተርበደበዱ ፡
በቁጥጥም ፡ ከግንባሬ ፡ ላይ ፡ አንጣጠረብኝ ...

ያልተጣራ ፡ ንዴት ፡ ሰውነቴን ፡ በሙሉ ፡
ወረረው ።

በድንገትም ፡ የሽጉጡን ፡ አፈሙዝ ፡ ወደምድ
ር ፡ አወረደው ። እንደአንሶላም ፡ የገረጣውን ፡
ፊቴን ፡ ወደዳሞቹ ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ባረቀ ።

«አልቻልሁም ።»

«አንተ ፡ ፈሪ!» ብሎ ፡ የሻምበሉ ፡ ጮኸበት ።

ተተኮሰ ፤ ጉልበቴም ፡ በመጠኑ ፡ በጥይት ፡
ተጨረፈ ። ከወደኋላዬ ፡ ወዳለው ፡ ገደል ፡ እን
ዳልገባ ፡ በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ተንደርድሬ ፡
ወደፊት ፡ ትንሽ ፡ እርምጃዎችን ፡ ተጓዝሁ ።

«አይ ፡ ወንድም ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ መሳትህ ፡
ያሳዝናል! በል ፡ እንግዲህ ፡ በተራህ ፡ ቦታህን ፡
ተረከብ ፤ ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ስመኝ ፡
ከንግዲህ ፡ አንገናኝም ።» ካለው ፡ በኋላ ፡ የሻ
ምበሉ ፡ ሳቁን ፡ ውጦ ፡ ተሳሳመ ፤ ቀጥሎም ፡
ግሩሽኒትስኪይን ፡ በመሸኮርመም ፡ ዓይን ፡
ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡ «አትፍሪ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ምንም ፡ የረባ ፡ ነገር ፡ የለም ። ተፈጥሮ ፤
እድል ፤ ሕይወት ፡ እራሱ ፡ ምንም ፡ ጠቃሚ ፡
ነገሮች ፡ አይደሉም ፡» ይለው ፡ ገባ ።

የሻምበሉ ፡ ይህን ፡ አሳዛኝ ፡ አንጋገር ፡ ከ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይቅር፡ ፡ አይጠይቁኝም? ሕሊናዎ ፡ እንዳይወ
ቅስዎትም? እስቲ ፡ በጥሞና ፡ ያስቡት?»

«ከቡር ፡ ፔቾሪን ፡ ሆይ! እዚህ ፡ የመጡት ፡ ሊሰብኩ ፡ አይደለም ። ቶሎ ፡ ጨርሰን ፡ ሰው ፡ ሳያየን ፡ ወደቤታችን ፡ እንመለስ ፡» በማለት ፡ የፈረሰኛው ፡ ሻምበል ፡ በቁጣ ፡ ተናገረ ።

«ጥሩ ፤ ዶክተር ፡ እስቲ ፡ እባክዎ ፤ ወደኔ ፡ ይምጡ ።»

ዶክተሩ ፡ እንደታዘዘው ፡ ወደኔ ፡ መጣ ። ግሩሽኒትስኪይ ፡ ከአሥር ፡ ደቂቃ ፡ በፊት ፡ ከገረጣው ፡ ይበልጥ ፡ አመድ ፡ ለብሷል ። ምስኪን ፡ ዶክተር!

የሚከተሉት ፡ ቃላት ፡ ልክ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሲነገር ፡ እንደሚነበብ ፡ ሁሉ ፡ አውቄ ፡ ጮኽ ፡ ብዬ ፡ እናገራቸው ፡ ጀመር ።

«ዶክተር! እነዚህ ፡ ከቡራን ፡ የኔን ፡ ሽጉጥ ፡ ጥይት ፡ ሳያጐርሱ ፡ የረሱት ፡ ይመስለኛል ። እባክዎ ፤ ጥይቱን ፡ ያጉርሱልኝ ፡ እና ...»

«አይሆንም! አይደረግም! ሁለቱንም ፡ ሽጉጦች ፡ ጥይት ፡ አጉርሻቸዋለሁ ። ከሽጉጥዎ ፡ ጥይቱ ፡ ወድቆ ፡ ከሆነ ፡ ጥሩቱ ፡ የኔ ፡ አይደለም ። እንደገና ፡ ለማጉረስ ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የለዎትም ... በምንም ፡ ዓይነት ፡ አይችሉም ፤ የፍልምያን ፡ ሕግ ፡ መሣሪ ፡ ነው ። እኔ ፡ በፍጹም ፡ አላውቅም ...» በማለት ፡ የሻምበሉ ፡ ያጉራ ፡ ጀመር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ደግ ፤ ጉዳዩ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነም ፡ እኔና ፡ እርስዎ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እንፋለማለን ፡» አልሁት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሻምበሉ ፡ የሚናገረው ፡ አጣ ።

ግሩሽኒትስኪይ ፡ እንጉቱን ፡ በሐዘንና ፡ በኃፍረት ፡ ከደረቱ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ቆሞአል ።

በመጨረሻም ፡ ከዶክተሩ ፡ እጅ ፡ ሽጉጡን ፡ ለመንጠቅ ፡ የሚታገለውን ፡ የሻምበል ፤ ግሩሽኒትስኪይ ፤

«ሽጉጡን ፡ ቢለቁላቸው! እንደፈለጉ ፡ ያድርጉ ፤ ልክ ፡ እንዳልነበርን ፡ እርስዎም ፡ ያውቃሉ» አለው ።

የሻምበሉ ፡ ግሩሽኒትስኪይን ፡ በጥቅሻ ፡ ያዋከበው ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ቀናም ፡ ብሎ ፡ አላየውም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዶክተሩ ፡ ሽጉጡን ፡ እጉርሶ ፡ አቀበለኝ ። የሻምበሉም ፡ ምድሩን ፡ በሚማው ፡ ወግሮ ፡ ምራቁን ፡ ከተፋ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ «ወዳጄ ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፤ ቂል ፡ ነህ ፤ የመጨረሻ ፡ ሞኝ ፡ ነህ! እንዴ ፡ እምነሽኝ ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ እምነት ፡ እስከመጨረሻው ፡ ማድረስ ፡ ነበረብህ ። በል ፡ እንግዲህ ፡ እንደዝንብ ፡ መጨፍለትህ ፡ ነው» ብሎ ፡ በግሩሽኒትስኪይ ፡ ከደንፋ ፡ በኋላ ፡ በማጉረምረም ፤ «ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ ነው» ብሎ ፡ የሻምበሉ ፡ ዞር ፡ አለ ።

ጣሎ ፡ እየሁ ። ሳልወድ ፡ በግድ ፡ ዓይኔን ፡ ከድ
ኘ ፡ አለፍሁ ...

በፈረሴም ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ በሰው ፡ እርምጃ ፡
ፍጥነት ፡ ወደቤቴ ፡ እመራሁ ። ልቤን ፡ ከብ
ዶታል ። ፀሐይም ፡ የምታበራ ፡ አይመስለኝም ።
ሙቀቱም ፡ አይሰማኝም ።

ወደሠፈሩ ፡ ከመድረሴ ፡ በፊት ፡ በስተቀኝ ፡
ወደሚገኘው ፡ ሽለቆ ፡ ገባ ፡ አልሁኝ ። በዚያን ፡
ሰዓት ፡ ማንንም ፡ ለማየት ፡ አልሻም ፤ ብቻዬ
ን ፡ ለመሆን ፡ ፈለግሁ ። የፈረሱን ፡ ልጓም ፡
ለቅቄ ፡ እንገቴን ፡ ወደምድር ፡ ቀብሬ ፡ ጥቂት ፡
ከተጓዝሁ ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ ከማላውቀው ፡
መንደር ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ ። ወደኋላም ፡ ተመልሼ ፡
መንገዴን ፡ መፈለግ ፡ ጀመርሁ ። እየተደከምሁ ፡
ኪስሎቮድስክ ፡ ስደርስ ፡ ፀሐይዋ ፡ ጠልቃ ፡ ቆ
የችኝ ። ሥቃይተኛ ፡ በተሠቃየው ፡ ፈረስ ፡ ላ
ይ ...

እቤት ፡ ስደርስ ፡ እሽከሬ ፡ ዶክተሩ ፡ መጥቶ
እንደነበረ ፡ ነገረኝ ። ሁለት ፡ ማስታወሻዎች ፡
ከቪራና ፡ ከራሱ ፡ ትቶልኝ ፡ የሔደውንም ፡
ሰጠኝ ።

የመጀመርያውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከፈትሁኝ ።
የሚለውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

«ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በተጋለ ፡ መጠን ፡
በደንብ ፡ ተዘጋጅቷል ። ሬሳውም ፡ መጥቷል ። ጥ
ይቱም ፡ ከሥራቱ ፡ ወጥቷል ። የግሩሽኒትስኪይ ፡

«ግሩሽኒትስኪይ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ጊዜ ፡
አለም ፤ የተናገሩትን ፡ ወያፍ ፡ ቃል ፡ ከሳቡት ፡ ይ
ቅርታ ፡ ላደርግልም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። በኔ ፡ ላይ ፡
ለመላለቅ ፡ የጠነሰሱት ፡ ሴራ ፡ ከሽፎብዎታል ።
በበኩሌ ፡ የምፈልገውን ፡ አግኝቻለሁ ። ከዚህ ፡
ቀድሞ ፡ ወዳጆች ፡ እንደነበርን ፡ ያስታውሱ ...»

የግሩሽኒትስኪይ ፡ ፊት ፡ ጉበት ፡ መሰለ ፡
ዓይኑም ፡ ተጉረጠረጠ ።

«ይተኩሱ! እራሴን ፡ ንቄአለሁ ፤ እርስ
ዎንም ፡ እጠላዎታለሁ ። ዛሬ ፡ ካልገደሉኝ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ጀርባዎን ፡ በጩቤ ፡ ተር
ትሬ ፡ እገልዎታለሁ ። ይህች ፡ ዓለም ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ለሁለታችንም ፡ ቦታ ፡ የላትም ... »

ተኮሰሁ ።

የባሩዱ ፡ ጪስ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ብመለከ
ት ፡ ግሩሽኒትስኪይ ፡ በቦታው ፡ አልነበረም ። ከ
ገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አፀራ ፡ ሲበን ፡ ታየኝ ።
ወዲያውኑ ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የድንጋጤ ፡
ድምጽ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ አሰተጋባ ። ወደዶክ
ተሩም ፡ ዞር ፡ ብዬ ፡«Finita la comedia» አልሁ
ት ። ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠኝም ። በጣም ፡
ተረብሾ ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ ሄደ ።

እኔም ፡ በግዴለሽነት ፡ ትከሻዬን ፡ ነቀነቅሁ
ወገዛሁ ፡ በኋላ ፡ የግሩሽኒትስኪይን ፡ ዱሾች ፡
እጅ ፡ ነሳሁ ።

መንገዴን ፡ ይዣ ፡ ወደታች ፡ ሰወርድ ፡ የ
ግሩሽኒትስኪይ ፡ ፈሳ ፡ በደንጋዮች ፡ ላይ ፡ ተን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕታህ ፡ ነው ። የደስታ ፡ የፍርሃት ፡ የሐዘን ፡ ም
ንጭ ፡ አድርገህ ፡ ትቆጥረኝ ፡ ነበር ። ያለእነሱ ፡
ደግሞ ፡ ሕይወት ፡ የሚሰለች ፡ ነው ፡ ይህን ፡
የተረዳሁት ፡ ገና ፡ ከመጀመርያ ፡ ነው ...
ግን ፡ ደስተኛ ፡ ስላልነበርህ ፡ ምናልባት ፡ አ
ንድ ፡ ቀን ፡ ለኔ ፡ ሥጦታ ፡ ዋጋ ፡ ትሰጠዋለህ ፡
በሚል ፡ ተስፋና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ውስጣ
ዊ ፡ ርህሩህነቱን ፡ ትረዳልኛለህ ፡ በማለት ፡
እስካሁን ፡ ጠበቅሁ ፡ ከዚያን ፡ ጀምሮ ፡ እስ
ካሁን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፏል ። የልብህን ፡
ውስጣዊ ፡ ምስጢር ፡ በሙሉ ፡ ለማንበብ ፡
ችያለሁ ... በመጨረሻም ፡ የኔ ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡
ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ። ሀዘኔም ፡ በጣም ፡
ከፍተኛ ፡ ሆነ ። ፍቅሬና ፡ ልቤ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡
ቀለጠ ፤ ሆኖም ፡ እሳታቸው ፡ ደበዘዘ ፡ እንጂ ፡
ጨርሶ ፡ አልጠፋም ።

የምንለያየው ፡ ለዘላለም ፡ ነው ። መቼም ፡
ቢሆን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንደማልወድ ፡ እመነኝ ።
ልቤ ፡ ያለውን ፡ ሐብት ፡ በሙሉ ፡ እምባውን ፤
ተስፋውን ፡ ያራገፈው ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነው ።
እንተን ፡ የወደድኽ ፡ ሴት ፡ ያለንቁት ፡ በሙሉ ፡
ዓይን ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ልታይ ፡ እትችልም ።
ደኽ ፡ የሚሆነው ፡ ግን ፡ እንተ ፡ ከነሱ ፡ ተሻ
ለህ ፡ እያደለም ። በፍጹም ፡ እትሻልም ፤ ሆ
ኖም ፡ ተፈጥሮህ ፡ ልዩ ፡ ነው ። ለብቻህ ፡ የታ
ደለ ፡ ምስጢራዊና ፡ ዙሩ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ አለ

አሚሚት ፡ ድንገተኛ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሁሉም ፡
እምነዋል ። ስለጠባችሁ ፡ የሚያውቀው ፡ የሠፈ
ሩ ፡ አዛኟ ፡ ብቻ ፡ እራሱን ፡ ነቀነቀ ። እሱም ፡
ቢሆን ፡ ምንም ፡ አላለ ። እርስዎን ፡ የሚያስ
ከሰስ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ምስክር ፡ የለም ።
ኪቻሉ ፡ በሰላም ፡ ይተኙ ፤ ደህና ፡ ይሁኑ ።።

የሁለተኛውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከፍቼ ፡ ከማንበ
ቤ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ አመነታሁ ። ለእኔ ፡ ምን ፡
ልትጽፍልኝ ፡ ትችላለች? የደብዳቤውን ፡ ይዘት ፡
በመገመት ፡ ብቻ ፡ በጣም ፡ ተጨነቅሁ ።

ለዘለዓለም ፡ በአእምሮዬ ፡ ተቀርጾ ፡ የቀ
ረው ፡ የደብዳቤዋ ፡ ይዘት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

«ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ የምጽፍልህ ፡ ሁለተኛ ፡
እንደማንገናኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኜ ፡ ነው ።
ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ስንለያይ ፡ ልክ ፡
እንደዚህ ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ግን ፡ ያምላክ ፡
ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ እንደገና ፡ ተገናኘን ። ይኸማው ፡
ልቤ ፡ ፈተናውን ፡ ሊያልፈው ፡ አልቻለም ።
በዚያ ፡ በማውቀው ፡ ድምጽህ ፡ እንደገና ፡
ተማረክሁ ። በዚህ ፡ መቼም ፡ አትጠላኝምን?
ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የስንብትና ፡ የኑዛዜ ፡ ነው ።
ልቤ ፡ አንተን ፡ ከወደደበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያጠራ
ቀመውን ፡ በሙሉ ፡ ልዘከዝክልህ ፡ እሻለሁ ።
አልወነጅልህም ። ባንተ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሌላም ፡
ወንድ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ልክ ፡ እንዳንተው ፡ ባይ
ረግ ፡ ነበር ። ትወደኝም ፡ የነበረው ፡ ልክ ፡ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ህ ፤ አንደበትህ ፡ ምንም ፡ ብትናገር ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ድምጽ ፡ አለው ። ለረኽቦም ፡ ጊዜ ፡ የመወደድ ፡ ኃይል ፡ የተሰጠህ ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ክፋት ፡ የተሞላበት ፡ ጠባይም ፡ ባንተ ፡ እንደሚስማማ ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፡ አያምርም ። ተስፋ ፡ የሚሰጡ ፡ እረፍት ፡ የሌላቸው ፡ ዓይኖች ፡ ካንተ ፡ ሌላ ፡ የማንም ፡ የለው ። እንዳን ተም ፡ ያሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በደንብ ፡ የሚጠ ቅምባቸው ፡ ወንድ ፡ አንድም ፡ የለም ፤ እራስ ህን ፡ ዘወትር ፡ ደስተኛ ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ ስለምት ቆጥር ፡ እንዳንተ ፡ ዓይነት ፡ እውነተኛ ፡ ሐዘን ተኛ ፡ ማንም ፡ የለም ።

በድንገት ፡ ለምን ፡ ተነስቼ ፡ እንደምሄድ ፡ ማስረዳት ፡ ይኖርበኛል ። ጉዳዩ ፡ የሚመለከተ ውኝ ፡ እኔን ፡ ስለሆነ ፡ ላንተ ፡ ምናልባት ፡ ምን ም ፡ ፍች ፡ አይሰጥህ ፡ ይሆናል ።

ዛሬ ፡ ጠዋት ፡ ባሌ ፡ መጥቶ ፡ ከግሩሽኒትስ ኪይ ፡ ጋር ፡ ስለነበረህ ፡ ጠብ ፡ አወራኝ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የፊቴ ፡ ገጽ ፡ ስለተለዋወጠ ፡ ዓይን ፡ ዓይኔን ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ይመለከተኝ ፡ ገባ ። ለናልምያ ፡ መሄድህንና ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክን ያት ፡ እኔ ፡ መሆኔ ፡ ሲገባኝ ፡ ሕሊናዬን ፡ ልስት ፡ ትንሽ ፡ ቀረኝ ... አሁን ፡ ግን ፡ ሳስብ ፡ አንተ ፡ በሕይወት ፡ እንደምትኖር ፡ እርግጠኛ ፡ ሆንሁ ። ያለኔ ፡ ብቻህን ፡ ትሞታለህ ፡ ብዬ ፡ በፍጹም ፡ አላምንም! ባለቤቴ ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለረኽቦም ፡

ጊዜ ፡ ሲንጐራደድ ፡ ቆየ ። ምን ፡ እንዳለኝ ፡ አላውቅም ። ምንም ፡ እንደመለስሁለት ፡ ትዝ ፡ አይለኝ ... ምናልባት ፡ አንተን ፡ እንደምወድ ህ ፡ ሳልነግረው ፡ የቀረሁ ፡ አይመስለኝም ... ትዝ ፡ የሚለኝ ፡ ከንግግራችን ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መጥፎ ፡ ቃል ፡ ሰድቦኝ ፡ እንደ ወጣ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ሠረገላው ፡ እንዲጮን ፡ አዘዘ ... ከሃድህበት ፡ ትመለሳለህ ፡ ብዬ ፡ እስ ከሶስት ፡ ሰዓት ፡ ከመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ጠበቅሁህ ... ግን ፡ ለምኑ ፡ ነው? በሕ ይወት ፡ እንዳለህ ፡ እምናለሁ ። አንተ ፡ ልት ሞት ፡ አትችልም! ሠረገላው ፡ ተዘጋጅቷል ... ደህና ፡ ሁን ... ደህና ፡ ሁን ... ሞቻለሁ ... አንተ ፡ ግን ፡ ለዘወትር ፡ እንደምታስታውሰኝ ፡ እርግጠኛም ፡ ብሆን ፤ ውደደኝ ፡ ለማለት ፡ አይደለም ፤ አስታውሰኝ ፡ እንጂ ... ደህና ፡ ሁን ... መጡ ብኝ ... ደብዳቤውን ፡ መደበቅ ፡ አለብኝ ።

ሚሪን ፡ መቼም ፡ እትወዳትም? አታገባትምም? እኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለኝን ፡ በሙሉ ፡ ላንተ ፡ ስል ፡ መስዋዕት ፡ እንዳደረግሁ ፡ ሁሉ ፡ አንተም ፡ ለኔ ፡ ስትል ፡ አድርግልኝ ...»

ልክ ፡ እንደእብድ ፡ ሰው ፡ ከቤቴ ፡ ወጥቼ ፡ ወደ፡ነር ፡ በምትመስደው ፡ ፈረሴ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብዬ ፡ ወደ፡ቲቱር፡ስክ ፡ የሚያመራውን ፡ መንገ ድ ፡ ያዝ ፡ ጋለብሁ ። ያን ፡ በዚያ ፡ ድንጋ ያማ ፡ መንገድ ፡ የሚያንከሰውን ፡ በድካም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ፡ የተዋጠጠውን ፡ ፈረስ ፡ ያለ ፡ እርጎራሄ ፡ እገርፈው ፡ ጀመር ።

በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ ተራራዎች ፡ ጀርባ ፡ ፀሐይዋ ፡ በጥቁር ፡ ደመናዎች ፡ ታክልላለች ። ሸለቆው ፡ ፍጹም ፡ ጨላልሟል ። የፖድክ ሞክ ፡ ወንዝ ፡ በጨኸት ፡ ቋጥኞቹን ፡ እየሰነጣጠቀ ፡ ያልፋል ። በትዕግሥት ፡ እጠት ፡ ከላይ ፡ ከላዩ ፡ እየተነፈስሁ ፡ ግልቢያዬን ፡ ቀጠልሁ ። ፒቲጐርስክ ፡ ባላገኛትስ? የሚለው ፡ ሐሳብ ፡ ሲመጣብኝ ፡ ልቤ ፡ በመዶሻ ፡ እንደተመታ ፡ ያመኛል ። ምነው ፡ ላንዲት ፡ ደቂቃ ፡ እንኳ ፡ ባየኋት? ምነው ፡ ላንድ ፡ ደቂቃ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ለማለት ፡ እጆችዋን ፡ ለመጨበጥ ፡ እድል ፡ ባገኘሁ ፡ ፀለይሁ ፡ ተሳደብሁ ፤ አለቀስሁ ፤ ሳትሁ ... ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረኝ ፡ ስሜትና ፡ ሐዘን ፡ የምገልጽበት ፡ ቃላት ፡ የሉኝም ። አሁን ፡ ቪራን ፡ ለዘላለም ፡ እንደማላየት ፡ ሳውቅ ፡ በዓለም ፡ ካሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፤ ከሕይወት ፤ ከክብርና ፡ ከደስታ ፡ አብልጬ ፡ ወደድኋት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሚንቀላቱ ፡ ያልመጣ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አለ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፇረሴን ፡ ያለምንም ፡ ርኅራሔ ፡ እየገረፍሁ ፡ ግልቢያዬን ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ነኝ ። በመጨረሻም ፡ ፈረሱ ፡ በኃይል ፡ ሰያደናቅ ፡ እየሁት ። ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሊወድቅም ፡ ሞከሮት ፡ ነበር ። ከሚቀጥለው ፡ አሲንቡክ ፡ ወደሚባለው ፡

የካሣክ ፡ መንደር ፡ ፈረስ ፡ ለማግኘት ፡ ከምችልበት ፡ ለመድረስ ፡ አምስት ፡ ቬርስታ ፡ ያህል ፡ ቀርቶኛል ።

ፈረሴ ፡ ለአሥር ፡ ደቂቃ ፡ የሚሆን ፡ ጉልበት ፡ በያገኝ ፡ ኖሮ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ጥሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ይኖረው ፡ ነበር ። ከቁልቁለቱም ፡ ወረድ ፡ ብለን ፡ ከመዞርያው ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ ፈረሴ ፡ ወድቆ ፡ ተዘረረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከኮርቻው ፡ ዘልዬ ፡ ወረድሁ ። ለማስነሳት ፡ ልጓሙን ፡ እየጐተትሁ ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ ሞከርሁ ፤ ግን ፡ አልቻልሁም ። በመጨረሻም ፡ ልጓም ፡ በገባበት ፡ አፍ ፡ የጭንቀት ፡ ድምጹን ፡ ካሰማ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ። እኔም ፡ ብቻዬን ፡ በዚያ ፡ ሚዳ ፡ ላይ ፡ ቀረሁ ። ተስፋዬም ፡ ሁሉ ፡ አብሮ ፡ ጠፋ ። መንገዱን ፡ በግሬ ፡ ለመቀጠል ፡ ሞከርሁ ፤ ግን ፡ ጉልበቴ ፡ ተንቀጠቀጠ ። የለቱ ፡ ጭንቀትና ፡ የትላንቱ ፡ ሌሊት ፡ የእንቅልፍ ፡ እጦት ፡ ስለተጫጫኑኝ ፤ ፍጹም ፡ ለመንቀሳቀስ ፡ አልቻልሁም ። እዛም ፡ እርጥብ ፡ ሣር ፡ ላይ ፡ ድፍት ፡ ብዬ ፡ እንደሕፃን ፡ ልጅ ፡ ስቅስቅ ፡ ብዬ ፡ አለቀስሁ ።

ባለሁበት ፡ እያለቀስሁ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ ቦታ ፡ ቆየሁ ። እንባዬንም ፡ ለማቆም ፡ እኔም ፡ አልሞከርሁም ። ደረቴም ፡ በሐዘን ፡ የሚፈነዳ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ። ያ ፡ የነበረኝ ፡ ሁሉም ፡ ድፍረት ፡ ልበ ፡ ሙሉነት ፡ እንደእፈር ፡ ቡን ፡ ብሎ ፡ ጠፋ ። መንፈስ ፡ ደካማ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆንሁ ። ማሰብ ፡ አቃተኝ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢያይኝ ፡ ኖሮ ፡ በንቀት ፡ ፊቱን ፡ ባዞረ ብኝ ፡ ነበር ።

የምሽቱ ፡ ጨዛና ፡ የተራራው ፡ ነፋስ ፡ ካቀዘ ቀዘኝ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ማሰብ ፡ ጀመርሁ ። የጠፋውን ፡ ደስታ ፡ ማሳደድ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ተረዳሁ ። ሌላ ፡ ምን ፡ እፈልጋ ለሁ ። እሷን ፡ ለማየት? ለምን? በመካከላችን ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ አላለቀም? አንድ ፡ የመጨረሻ ፡ የስንብት ፡ መሳሳም ፡ ያለፉትን ፡ ትዝታዎቼን ፡ አድሶ ፡ አያቀርብልኝ? እንዲያውም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ መለያየቱ ፡ ይበልጥ ፡ ይቸግራል ።

ይህም ፡ ሆኖ ፡ እራሴ ፡ ማልቀስ ፡ መቻሌን ፡ ማወቁ ፡ ደስ ፡ ይላል ። የልቅሶዬ ፡ አቢይ ፡ ምክ ንያቶች ፡ ጭንቀቴ ፤ የእንቅልፍ ፡ እጦቴ ፤ የ ሽንጥ ፡ አፈ ፡ ሙዝ ፡ እያየሁ ፡ የቆየሁባቸው ፡ ቀውጢ ፡ ደቂቃዎችና ፡ እረሃቡ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ።

እንዲያውም ፡ ያሁኑ ፡ ይበልጥ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ ። ይህ ፡ አዲሱ ፡ ስሜት ፡ በወታ ደሮች ፡ አጠራር ፡ ወደሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ይመራ ኛል ፡ ብዬ ፡ አስባለሁ ። ግልቀስ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ ፊደሲን ፡ በያካም ፡ ገደዱ ፡ በግሬ ፡ አሥራም ስት ፡ ቪርስታ ፡ ወደከተማው ፡ ባልንዝ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬንም ፡ ሌሊት ፡ ያለእንቅልፍ ፡ ባንጋሁት ፡ ነበር ።

ኪስሎቮድስክ ፡ የደረስኩት ፡ ከጠዋቱ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ነው ። እንደደረስሁም ፡ በአልጋዬ ፡ ላይ ፡ ናፖልዮን ፡ ከዋተርሎ ፡ መልሶ ፡ እንደተኛ ፡ እኔም ፡ ተዘረርሁ ።

ስነሳ ፡ ጨላልሞ ፡ ነበር ። የካፖርቴን ፡ ቁልፎች ፡ ፈትቼ ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ አልሁ ። በዚህ ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ድካሙ ፡ ያላለፈለትን ፡ ደረቴን ፡ ከተራራው ፡ በሚመ ጣው ፡ አየር ፡ አስመታው ፡ ጀመር ። ከወንዙቹ ፡ ማዶ ፡ ያለው ፡ የወታደር ፡ ሠፈር ፡ ብርሃን ፡ በጫካው ፡ መካከል ፡ ቦግ ፡ ድርግም ፡ ይል ፡ ነበር ። ሠፈሩ ፡ በሙሉ ፡ በፀጥታ ፡ ተውጧል ፡ የልዕልቲቷም ፡ ቤት ፡ በጨለማ ፡ ተጋርዷል ።

ዶክተሩ ፡ ወደቤቴ ፡ ገባ ፤ ፊቱ ፡ ተከፋትሯል ። የእጁም ፡ ሰላምታ ፡ ያለወትሮው ፡ ገታው ።

«ዶክተር ፤ የት ፡ ነበሩ?»

«ከልዕልት ፡ ሊጐቭስካያ ፡ ቤት ፡ መምጣ ቴ ፡ ነው ። ልጃቸው ፡ ታመዋል ። የአንጐል ፡ መናወጽ ፡ ደርሶባቸዋል ። የመጣሁት ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ አይደለም ። ባለሥልጣኖች ፡ መጠርጠር ፡ ጀምረዋል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ለክስ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ማስረጃ ፡ ባይኖራቸውም ፡ እንዲጠና ቅቁ ፡ ለመንገር ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ልዕልቲቷ ፡ በልጃቸው ፡ ምክንያት ፡ መታከስዎን ፡ ነግረው ኛል ። እኒያ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰውዬ ... ስማቸው ፡ ጠፋኝ ... እሳቸው ፡ ናቸው ፡ የነገርዋቸው ፤ በም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሰናበት ፡ መምጣቴን ፡ ስነግራቸው ፡ በጣም ፡ ደንገጡ ።

«ቢሆንም ፤ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ የማወራው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡» አሉኝ ። ምንም ፡ ቃል ፡ ሳልናገር ፡ ቁሜ ፡ አልሁ ።

ከየት ፡ ለመጀመር ፡ እንደጠፋቸው ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ፊታቸው ፡ ቀላ ፤ የሚርበደበዱትን ፡ ጣቶቻቸው ፡ በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ይንቀጣቀጣሉ ። በመጨረሻም ፡ ንግግራቸውን ፡ ጀምረው ፡ እንዲህ ፡ አሉኝ ።

«ክቡር ፡ ፔቾሪን! የተከበሩ ፡ ለመሆንዎ ፡ ጥርጥር ፡ የለኝም ...» ሲሉኝ ፤ እጅ ፡ ነሳሁ ።

ከዚያም ፡ ንግግራቸውን ፡ ቀጥለው ፡ «በዚህ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ በፍጹም ፡ አልጠራጠርም ። ቢሆንም ፡ ጠባይዎ ፡ በመጠኑ ፡ ግራ ፡ የሚያጋባና ፡ የሚያስጠይቅ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ለኔ ፡ ላይገባኝ ፡ ይችላል ። ግን ፡ ለምን ፡ አይነግሩኝምና ፡ አብረን ፡ እንወያይበትም ። ልጄን ፡ ከሐሜት ፡ አድነዋታል ። ለሷም ፡ ሲሉ ፡ ፍልምያ ፡ ገጥመዋል ፤ ሕይወትዎንም ፡ ለሞት ፡ እሳ ልፈው ፡ ሰጥተዋል ... ግድ ፡ የለም ፤ መልስ ፡ አልፈልግም ፤ ግሩሽኒትስኪይ ፡ ስለሞተ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እንደሚሉኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። (ያማትባሉ ፡) ፈጣሪ ፡ ይቅር ፡ ይበለው ። እርስዎም ፡ ይቅር ፡ ይበልዎ፤ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡

ግብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከግሩሽኒትስኪይ ፡ ጋር ፡ የነበራችሁን ፡ ጠብ ፡ አሜው ተዋቸዋል ። ስለዚህም ፡ አሁን ፡ የመጣሁት ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ነው ። ደህና ፡ ይሁኑ ... ምናልባትም ፡ ከእንግዲህ ፡ ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ እንገናኝ ፡ ይሆናል ። ወደሌላ ፡ ቦታ ፡ ሳይዘዋወሩ ፡ አይቀሩም ።»

ይህን ፡ ካሉኝ ፡ በኋላ ፡ የበሩን ፡ መዝጊያ ፡ ይዘው ፡ ቆም ፡ አሉ ። እጄን ፡ ሊጨብጡኝ ፡ ይፈልጋሉ ። ትንሽ ፡ ፊት ፡ ባሳያቸው ፤ መጥተው ፡ ባንገቴ ፡ ላይ ፡ ይጠመጠሙ ፡ ነበር ። ግን ፡ እኔ ፡ እንደድንጋይ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ዝም ፡ ስላልሁ ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ጥለውኝ ፡ ወጡ ።

ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ። ሁሉም ፡ ይመሳሰላሉ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ያንድን ፡ ድርጊት ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ቢያውቁም ፡ መውጫ ፡ ነገር ፡ ሲያጡ ፡ ይመክራሉ ፤ ያጽናናሉ ፤ ድጋፋቸውንም ፡ ይሰጣሉ ። ከዚያም ፡ ሙሉ ፡ ኃላፊነት ፡ የወሰደውን ፡ ሰው ፡ ትተው ፡ ከያሙ ፡ ንጹህ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ዞር ፡ ይላሉ ። ሁሉም ፡ ያው ፡ ናቸው ። ከሁሉም ፡ እሩሀሩህና ፡ አዋቂ ፡ የተባሉት ፡ ሳይቀሩ ፡ አንድ ፡ ናቸው ።

በማግሥቱ ፡ ጠዋት ፡ ካለቱቺ ፡ ወደ N ፡ ሠፈር ፡ እንደሄድ ፡ ትዕዛዝ ፡ ያረሰኝ ። ለስንብትም ፡ ወደልዕልት ፡ ቤት ፡ ዘው ፡ አልሁ ።

ለሳቸው ፡ የምንግራቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ ያለኝ ፡ የመሰላቸው ፡ ልዕልት ፡ ሊጉሽስካያ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ጌ ፣ ነው ። ያስታውሱ ፤ ያለችኝ ፣ እንዲት ፣ ልጅ ፣ ብቻ ፣ ናት ። እንዲት ፣ ብቻ ...»

ይህን ፣ ካሉ ፣ በኋላ ፣ ስቅስቅ ፣ ብለው ፣ አለቀሱ ።

«ልዕልት ፣ ሆይ! ለዚህ ፣ ጥያቄዎ ፣ እኔ ፣ መልስ ፣ መስጠት ፣ አልሻም ፤ ከልጅዎ ፣ ጋር ፣ ለብቻ ፣ እንድንወያይ ፣ ይፍቀዱልኝ ፡» አልኋቸው ።

በዚህ ፣ እንጋገር ፣ በጣም ፣ ተቆጥተው ፤ «በፍጹም ፣ አይቻልም ፡» ብለው ፣ ከወንበራቸው ፣ አፈፍ ፣ አሉ ።

እኔም ፣ ለመሔድ ፣ ተነስቼ ፣ «እንደወደዱ ፡» አልኋቸው ።

ትንሽ ፣ ካሰቡም ፣ በኋላ ፣ እንድቆይ ፣ በእጃቸው ፣ ምልክት ፣ ሰጥተው ፣ ከፍሉን ፣ ተለውልኝ ፣ ወጡ ።

አንድ ፣ አምስት ፣ ደቂቃ ፣ አለፈ ። ልቤ ፣ በኃይል ፣ ምቱን ፣ አሰማ ። አስቀሳሰቤ ፣ ግን ፣ የረጋ ፣ ነበር ። በሚቻለኝ ፣ ሁሉ ፣ ያቺን ፣ ውብ ፣ ሚሪን ፣ እወዳት ፣ እንደሆነ ፣ በሚል ፣ ጥርጣሬ ፣ ልቤን ፣ ፈተሽሁት ። ግን ፣ ምንም ፣ የማልወዳት ፣ ሆኜ ፣ ተገኘሁ ።

በሩ ፣ ተከፍቶ ፣ ሚሪ ፣ ገባች ። ያንት ፣ ያለህ ፣ ባለፈው ፣ ጊዜ ፣ ካየኋት ፣ ምንኛ ፣ ተለውጣለች ። ጊዜው ፣ እንኳ ፣ እስከዚህ ፣ እሩቅ ፣ አልነበረም ።

ከነሩሉ ፣ መለል ፣ መሃል ፣ ስትደርስ ፣ ተን

የኔ ፣ ተግባር ፣ አይደለም ... እርስዎን ፣ ለመ ወንጀል ፣ ምንም ፣ መብት ፣ የለኝም ። የሷ ፣ ጥፋትም ፣ ባይሆን ፣ ለዚህ ፣ ሁሉ ፣ ምክንያት ፣ የሆነችው ፣ የኔ ፣ ልጅ ፣ ናት ። ግንኛውንም ፣ ነገር ፣ እሚውታኛለች ... ግንኛውንም ... እርግጠኛም ፣ ነኝ ። እንደሚወዷት ፣ ገልጸ ውላታል ፤ እርሷም ፣ እንደምትወድዎት ፣ ነግራ ዎታለች ፣ (ከዚህ ፣ ላይ ፣ ልዕልቲቷ ፣ በኃይል ፣ ተነፈሱ) አሁን ፣ ታማለች ። በሽታዋ ፣ የተለመደ ፣ አይደለም ። እንድ ፣ ከፍተኛ ፣ ሐዘን ፣ አመንምኖ ፣ ሊገላት ፣ ነው ። እሷ ፣ እት ናገረውም ። እኔ ፣ ግን ፣ የዚህ ፣ ሁሉ ፣ ምክንያት ፣ እርስዎ ፣ እንደሆኑ ፣ አምናለሁ ... ይስሙኝ ፤ ምናልባትም ፣ እኔን ፣ ከፍተኛ ፣ ማዕረ ግንና ፣ ሐብትን ፣ የምፈልግ ፣ አድርገው ፣ ይገም ቱኝ ፣ ይሆናል ። እንደዚህ ፣ ካሰቡ ፣ ግን ፣ ስተ ተኛ ፣ ነዎት ። እኔ ፣ የምፈልገው ፣ የልጇን ፣ ደስ ታ ፣ ብቻ ፣ ነው ። አሁን ፣ ያለዎት ፣ ቦታ ፣ እስከ ዚህ ፣ የሚያኮራ ፣ ቦታ ፣ አይደለም ፤ ከፍ ፣ ሊል ፣ ግን ፣ ይችላል ። ሐብት ፣ አለዎት ። ልጇም ፣ ትወድዎታለች ። አሰተዳደጓም ፣ ባልዋን ፣ ለማ ስደሰት ፣ የሚያስችላት ፣ ነው ። እኔ ፣ ጌታ ፣ ነኝ ። ያለችኝ ፣ ልጅ ፣ አንድ ፣ እሷ ፣ ብቻ ፣ ናት ... ወደኋላ ፣ የሚጐተትዎት ፣ ምንድነው? ይህን ፣ ሁሉ ፣ ስንግረዎት ፣ ባልተገባ ፣ ነበር ። ያወጋ ውዎት ፣ በክብርዎና ፣ በፍቅርዎ ፣ ተሰፋ ፣ አድር

t.me/OLDBOOKSPDF

በተቻለኝም ፡ መጠን ፡ ድምጼን ፡ በቁጥር ፡ ሥር ፡ አግብቼ ፡ ሳቅ ፡ እንደማለት ፡ ብዬ ፤

«እንደሚያዩት ፡ እነሆ ፡ እርስዎን ፡ ሳገባ ፡ አልችልም ። እርስዎ ፡ እንኳ ፡ ቢፈልጉ ፡ ውሳኔዎ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ያሳዝነዎታል ። ከናትዎ ፡ ጋር ፡ ያደረግሁት ፡ ውይይት ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ በግልጽ ፡ እንድናገር ፡ ያስገድደኛል ። እናትዎም ፡ እንደ ተሳሳቱ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፤ ሆኖም ፡ ከፈለጉ ፡ ቶሎ ፡ ሊመልሷቸው ፡ ይችላሉ ። እንደሚያዩት ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ እንኳ ፡ ከፊትዎ ፡ ቆሜ ፡ አሳዛኝና ፡ አስቀያሚ ፡ የሆነ ፡ ሚና ፡ እየተጫወትሁ ፡ ነኝ ። ይህንም ፡ አምናለሁ ። ለርስዎ ፡ አደርግልዎት ፡ የምችለው ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ነው ። አፍቅረውኝ ፡ እንኳ ፡ ከሆነ ፡ ከዚች ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ሊጠሉኝ ፡ ይገባል ፤ አይጠሉኝም?»

ያሳየችኝ ፡ መልክ ፡ እንደእብነ ፡ በረድ ፡ የደረቀ ፡ ነው ። ዓይኖቿ ፡ ግን ፡ ያብረቀርቃሉ ።

«ፈትዎን ፡ ማየት ፡ አስጠላኝ ፡ » አለችኝ ። አመስግኛት ፤ እጅ ፡ ነስቻት ፡ ወጣሁ ።

ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሠረገላው ፡ ከኪስሎቮድስክ ፡ በፍጥነት ፡ ይዞኝ ፡ ሄደ ። ኢሲንቱኪ ፡ ትንሽ ፡ ቪርስታዎች ፡ ሲቀረኝ ፡ የፈረሴ ፡ ሬሳ ፡ ከተኛበት ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ አወጣሁት ። እቦታውም ፡ ስደርስ ፡ ኮርቻው ፡ ተንሸራቶ ፡ አገኘሁት ። በዚያ ፡ የሚያልፉ ፡ ካዛኮች ፡

ገዳገደች ። እኔም ፡ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ እጇን ፡ ሰጥቻት ፡ ወደመደገፍያው ፡ መንበር ፡ መሰድኋት ።

ፊት ፡ ለፊቷ ፡ ቆሜያለሁ ። ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ሁለታችንም ፡ ዝም ፡ አልን ፤ እነዚያ ፡ ሐዘን ፡ የተሞላባቸው ፡ ትልልቅ ፡ ዓይኖቿ ፡ ዓይኖቼ ፡ ውስጥ ፡ ተስፋን ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። እነዚያ ፡ የገረጡ ፡ ከንፈሮቿ ፡ ፈገግ ፡ ለማለት ፡ ሞክረው ፡ ሳይቻላቸው ፡ ቀሩ ። ከጉልበቶቿ ፡ ላይ ፡ ያረፉት ፡ እጆቿ ፡ ከመከለፍለፋቸው ፡ ሌላ ፡ አጥንታቸው ፡ ፈጠ ፡ ይታያል ፤ በጣም ፡ አሳዘነችኝ ።

«ልዕልት ፡ ሆይ ፤ በእውነቱ ፡ በጣም ፡ ቀልጀብዎታለሁ ። ይህንንም ፡ በደንብ ፡ ያውቃሉ ። አያደለም? ሊጠሉኝ ፡ ይገባዎታል ።»

ይህን ፡ ስትሰማ ፡ ይበልጡን ፡ አመድ ፡ ለበሰች ።

«ስለሆነም ፡ እኔን ፡ ሊወዱኝ ፡ አይችሉም ፡» አልኩ ።

ዘወር ፡ ብላ ፤ በእጆቿ ፡ ክርኖች ፡ ጠረጴዛውን ፡ ተደግፋ ፡ በመዳፎቿ ፡ ፊቷን ፡ ዘጋችው ። በጆቿም ፡ መካከል ፡ እንባ ፡ የታየኝ ፡ መሰለኝ ።

በቀስታም ፡ ድምጿ ፡ «ወይ! አንተ ፡ ፈጣሪ!» አለች ።

የነበረው ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ደቂቃ ፡ ቀጥሎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በእግሯ ፡ ላይ ፡ እጠመጠም ፡ ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

፫

ባለዕጣ ሰው።

አንድ ፡ ጊዜ ፤ ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ካንዲት ፡ ካዛክ ፡ መንደር ፡ በስተግራ ፡ ባለ ችው ፡ ሠፈር ፡ ውስጥ ፡ ኖሬያለሁ ፤ የመድፈኛ ፡ ባታልዮን ፡ በዚያው ፡ ሠፈር ፡ አርፎ ፡ ስለነበር ፡ መኮንኖቹ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ በየተራ ፡ በየጓደኞ ቻቸው ፡ ቤት ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ካርታ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ በሻለቃ ፡ C ፡ ቤት ፡ የምንጫወተው ፡ የቦስተን ፡ ጨዋታ ፡ ስለሰለ ቸን ፡ እስኪመሽ ፡ ድረስ ፡ ወሬ ፡ ቀጠልን ። በመጀመርያም ፡ ጨዋታችን ፡ ደስ ፡ ይል ፡ ነበር ፡ ውይይታችንም ፡ የያንዳንዱ ፡ ነፍስ ፡ እጣ ፡ እስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ ስለሚለው ፡ የእስልምና ፡ ኃይማኖት ፡ እምነት ፡ ነበር ። ከመካከላችን ፡ ይህን ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚደግፉ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። እያንዳንዳችንም ፡ በዚህ ፡ እርእ ሰት ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚና ፡ ደጋፊ ፡ ሆነን ፡ ሐሳባ ችንን ፡ ሰነዘርን ።

ሳያሆኑ ፡ አይቀሩም ። በኮርቻውም ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ ጥምብ ፡ አንሳ ፡ አሞሮች ፡ ጉብ ፡ ብለው በት ፡ አየሁ ። በሐዘን ፡ ፊቴን ፡ አዙሬ ፡ መንገ ዴን ፡ ቀጠልሁ ።

በዚህ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ባለ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ያለፈ ውን ፡ ሕይወቴን ፡ ባስታወስኩ ፡ ቁጥር ፡ እራሴ ፡ እንደዚህ ፡ እያልኩ ፡ እጠይቃለሁ ። ቋሚ ፡ ደስታና ፡ የአእምሮ ፡ እረፍት ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ ሕይወት ፡ እያሳየኝ ፡ እምቢ ፡ ያልሁት ፡ ለምን ድነው? የለም ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኑሮስ ፡ ለመኖ ር ፡ አልችልም ፡ ነበር ። ሕይወቴ ፡ ኑሮው ፡ በሙ ሉ ፡ ከማዕበል ፡ ጋር ፡ እንደተያዘ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ እንደተወለደ ፡ መርከበኛ ፤ ማዕበል ፡ እንኳ ፡ ወደዳርቻ ፡ ቢተፋው ፤ ደስ ፡ ከሚለው ፡ የፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ሸሽቶ ፡ ወደባሕሩ ፡ ለመመለ ስ ፡ የሚፈልገውን ፡ ይመስላል ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በባሕሩ ፡ አሸዋማ ፡ ወደብ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ እየተ ንጐራደደ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ድምጽ ፡ ያለ ውን ፡ የባሕር ፡ ማዕበል ፡ ሲያጸምጥ ፡ ከመዋ ሉም ፡ ሌላ ፡ ከባሕሩ ፡ ባሻገር ፡ ባለው ፡ ደመና ፡ ለበስ ፡ አድማስ ፡ ላይ ፡ አትኩሮ ፡ መጀመርያ ፡ ከሩቁ ፡ የባሕር ፡ ወሩ ፡ ከዚያም ፡ እየቀረበ ፡ ሲ ሄድ ፡ በጉልህ ፡ የሚታየውን ፡ መርከብ ፡ ይጠ ብቃል ...

t.me/OLDBOOKSPDF

ለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተጠራቅሞ ፡ የሚያ
ላየው ፡ ዕድል ፡ መልምላ ፡ ከሰጠችው ፡ ጓደ
ኞቹ ፡ ጋር ፡ ሐሳቡንና ፡ ስሜቱን ፡ ለመጋራት ፡
አለመቻሉ ፡ ነው ።

ጉበዝ ፡ ነው ። የሚናገረው ፡ አጭርና ፡ ቁርጥ ፡
ያለ ፡ ነው ። የቢተሰቡንና ፡ የውስጥ ፡ ምስጢ
ሩን ፡ ለማንም ፡ ለማካፈል ፡ አይፈልግም ። ቪኖ ፡
አይጠጣም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ውብ ፡ ከሆኑም ፡
የካዛክ ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ ተጠግቶ ፡ አያውቅም ።
የኮሎኔሉ ፡ ሚስት ፡ በነዚያ ፡ ውብ ፡ ዓይናቹ ፡
ተማርካለች ፡ ይባላል ። እሱ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡
በውስጠዘ ፡ እንኳ ፡ ቢነገር ፡ ይቆጣል ።

ከጠባዮቹ ፡ የማይደብቀው ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡
ነው ። ይኸውም ፡ ቁማር ፡ ነው ። እዛ ፡ አረን
ጓዴ ፡ የቁማር ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ማንኛ
ውንም ፡ ነገር ፡ ይረሳል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡
የሚመለሰው ፡ ተበልቶ ፡ ነው ። በየጊዜውም ፡
ስለሚበላ ፡ ይብሱን ፡ ቁማርተኛ ፡ እየሆነ ፡
ሄደ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ለሥራ ፡ ጉብኝት ፡
ወደውጭ ፡ በሔደበት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አግኝቶ ፡
ነበር ። ከዚያም ፡ በድንገት ፡ የጥይት ፡ ድምጽ ፡
ተሰማ ። ቀጥሎም ፡ የማስጠንቀቅያው ፡ ደውል ፡
ተደወለ ፡ ሁሉም ፡ ወደየመሣርያው ፡ ሮጠ ።
በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዩሊች ፡ እንዱን ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡
«በለው ፡ በሙሉ ፡ እንጫወት» ሲል ፡ ጋበዘው ።
ተጠያቂውም ፡ እየሸሸ ፡ «ስባት» አለ ።

በመጨረሻም ፡ ሽማግሌው ፡ ሻለቃ ፡ እንዲህ ፡
አሉን ። «ክቡራን! እስካሁን ፡ ትናገሩት ፡ የነበረ
ው ፡ በሙሉ ፡ ምንም ፡ የሚያረጋግጠው ፡ ነገር ፡
የለም ። እናንተ ፡ የምትደግፉትን ፡ አስገራሚ ፡
ታምሮች ፡ ያየ ፡ ማንም ፡ የለ ። አይደለም!»

«አዎ ፡ ይህ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ግን ፡ ውይይ
ታችን ፡ የተመሠረተው ፡ በታመነ ፡ ምንጭ ፡
ነው» በማለት ፡ ብዙዎቹ ፡ መለሱ ።

«ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነው» በማለት ፡ አንዱ ፡ ከመ
ሐል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ። ከዚያ ፡ ተከታትሎ ፡ የም
ንሞትበትን ፡ ሰዓት ፡ ሥር ፡ ሥሩን ፡ ያየ ፡ ሰው ፡
የት ፡ አለ? ደግሞስ ፡ የምንሞትበት ፡ ጊዜ ፡ አስ
ቀድሞ ፡ የሚታወቅ ፡ ከሆነ ፡ የራሳችን ፡ አስተሳ
ሰብና ፡ ፍላጐት ፡ ለምን ፡ ይኖረናል? ላደረግ
ነው ፡ ሥራስ ፡ ሁሉ ፡ ለምን ፡ እንጠየቃለን?»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከጥግ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ የነበረ ፡
መኮንን ፡ ወዳለንበት ፡ ቀርቦ ፡ እያንዳንዳችንን ፡
በጥሞና ፡ ይመለከተን ፡ ጀመር ። ዘሩ ፡ ሴርቢ
ያን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ስሙም ፡ ያስታው
ቃል ።

የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዩሊች ፡ መልክ ፡ ከጠባዩ ፡
ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ረጅም ፡ ጠይም ፡ ወጣ ፡
ጥቁር ፡ ትኩር ፡ ብለው ፡ የሚያዩ ፡ ጭልፋ ፡ ዓይ
ኖችና ፡ ከዚያ ፡ የመጣ ፡ ቁጣ ፡ ያለ ፡ ሰንዳዳ ፡
አፍንጫ ፡ ዘወትር ፡ ከከንፈሩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡
ቀዝቃዛና ፡ አሳዛኝ ፡ ፈገግታ ፡ የሚታዩበት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ቩሊች ፡ በተኩሱ ፡ ሳይረበሽ ፡ እስከመጨረ
ሻው ፡ ድረስ ፡ ለመጫወት ፡ ተዘጋጀ ። ካርታ
ውም ፡ ታደለ ።

ከቦታው ፡ ሲደርስ ፡ ተኩሱ ፡ በጣም ፡ ኃይ
ለኛ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ፡ ቩሊች ፡ ስለጥይትም ፡
ሆነ ፡ ስለቸቸን ፡ ጐራዴ ፡ ምንም ፡ ደንታ ፡ አል
ነበረውም ። እሱ ፡ ያሳድድ ፡ የነበረው ፡ ያን ፡
እድለኛ ፡ የካርታ ፡ ቁጥር ፡ ነበር ።

የወጣው ፡ ቁጥር ፡ አሁንም ፡ «ሰባት» ሆነ ።
ቩሊች ፡ አሸናፊውን ፡ ሲያይ ፡ ጮኸ ። በዚህም ፡
ወቅት ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡
እየገሠቱ ፡ ያወጡ ፡ ነበር ። ቩሊች ፡ ለእድለ
ኛው ፡ ሰው ፡ የገንዘቡን ፡ ከረጢት ፡ ያሸናፊውን ፡
ቅዋሜ ፡ ሳይመለከት ፡ አስረከበ ። ይህን ፡ ደስ ፡
የማይል ፡ ተግባሩን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ቩሊች ፡
በፊት ፡ ለፊት ፡ እየተጓዘ ፡ የቸርከስ ፡ ጠላቶ
ችን ፡ በድፍረት ፡ ሲዋጋ ፡ ውልዋል ።

የመቶ ፡ አለቃ ፡ ቩሊች ፡ ገና ፡ መደጠረጁ
ሣው ፡ ሲመጣ ፡ እንደተለመደው ፡ አንድ ፡ አዲ
ስ ፡ ነገር ፡ ይሠራል ፡ በማለት ፡ የተሰበሰበት ፡
በሙሉ ፡ ፀጥ ፡ ብለው ፡ ጠበቁት ።

«ነበራን! (ድምጹ ፡ የረጋ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ከሱ
ላው ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ አጉሮንቶታል) ነበ
ራን! ይህ ፡ የማይረባ ፡ ውይይት ፡ ምን ፡ ያደ
ርጋል? የምትፈልጉት ፡ ማሰሪጀም ፡ አይደል?
አንድ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ሕይወት ፡ ማዘዝ ፡

ይችል ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የሚሞትበትን ፡
ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ያውቅ ፡ እንደሆነ ፡ ለመረዳት ፡
እናረጋግጥ ። ለመሞከር ፡ የሚፈልግ ፡ ማን ፡
አለ?» ሲል ፡ ተናገረ ።

«እኔ ፡ አልፈልግም ...! እኔ ፡ አልፈልግም ...!
ምን ፡ ግራ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ነው? ካለ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ይህን ፡ እንዴት ፡ ያስባል?» የሚል ፡
ድምጽ ፡ ከየአቅጣጫው ፡ አስተጋባ ።

«እኔ ፡ አንድ ፡ ውርርድ ፡ አቀርባለሁ»
በማለት ፡ በፈገ ፡ ተናገርሁ ።

«ምን ፡ ዓይነት ፡ ውርርድ?»

ያለችኝ ፡ ሐያ ፡ የወርቅ ፡ መሐለቅ ፡ ከቦር
ሳዬ ፡ አውጥቼ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ካስቀመጥሁ ፡
በኋላ ፡ «የሰው ፡ ልጅ ፡ የመጨረሻ ፡ እጣው ፡
አስቀድሞ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ አስተ
ሳሰብ ፡ አልቀበለውም» አልሁ ።

«መልካም ፡ እንወራረድ» በማለት ፡ ቩሊች ፡
በከፍታ ፡ ድምጽ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ «የሻለቃ!
እርስዎ ፡ ዳኛ ፡ ይሁኑ ፤ አሥራ ፡ አምስት ፡ የወ
ርቅ ፡ መሐለቅ ፡ እነሆ ፡ ይያዙ ። የተረጣውን ፡
እምሥት ፡ ካለብዎ ፡ ከኔ ፡ ዕዳ ፡ ይሙሉልኝ»
አላቸው ።

«በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው» ካለ ፡ በኋላ ፡ የሻለ
ቃው ፡ «ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆነና ፡ ውርርዱን ፡
በምን ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ልታደርጉት ፡ እንደ
ምትፈልጉ ፡ አላውቅም» አለ ። ምንም ፡ ቃል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የገረጡ ፡ ከንፈሮቹ ፡ ፈገግ ፡ አሉ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በሁኔታው ፡ ደንጋጤ ፡ ባላይም ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ያነበብሁት ፡ ሞትን ፡ ነበር ። እኔ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ልብ ፡ ያልሁትን ፡ ጥንታዊ ፡ ወታደሮ ችም ፡ የሚያረጋግጡት ፡ የሚሞትን ፡ ሰው ፡ በማወቅ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ዓይን ፡ አይስተ ውም ።

«ዛሬ ፡ ይሞታሉ» አልሁት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በድንጉት ፡ ወደኔ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ አውንም ፡ ሳይደና ገጥ ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ ።

«ልሞትም ፡ ላልሞትም ፡ እችላለሁ ...»

ወዲያውም ፡ ወደሻለቃው ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ሽጉጡ ፡ ጥይት ፡ እንዳለው ፡ ጠየቀ ። የተደናገጠው ፡ የሻ ለቃ ፡ ሽጉጡ ፡ ይጉረስ ፡ አይጉረስ ፡ ለማስታ ወስ ፡ አልቻለም ።

«እንግዲህ ፡ በቃዎት ፡ ቩሊች! ጥይት ፡ የሌ ለው ፡ ሽጉጥ ፡ ባልጋው ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ አይን ጠለጠልም ። ምን ፡ ዓይነት ፡ ቀልድ ፡ ነው ፡ የያዙት ፡» ሲል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከመካከል ፡ ባረቀበት ።

«የማይረባ ፡ ቀልድ ፡ ነዋ!» ብሎ ፡ ሌላኛው ፡ አከለበት ።

ሌላው ፡ ሶስተኛ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ በተራው ፡ ተነስቶ ፤ «ሽጉጡ ፡ ጥይት ፡ የለውም ። እምስት ፡ ሩብል ፡ ለሃምሳ ፡ ሩብል ፡ እንወራረድ ፡» አለ ።

በዚህም ፡ አዲስ ፡ ውርርድ ፡ ተደረገ ።

ሳይተነፍስ ፡ ወደሻለቃው ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ሲመራ ፡ ተከትለነው ፡ ሄድን ። ከዚያም ፡ መሣ ርያዎቹ ፡ ወደተንጠለጠሉበት ፡ ግድግዳ ፡ እገ ግሞ ፡ ከተደረደሩት ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ አወ ረደ ። በመጀመርያ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፈለገ ፡ በደንብ ፡ አልገባንም ፡ ነበረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ሽጉጡን ፡ መሠ ፡ ሲያነዳዕር ፡ ስላየነው ፡ ብዙዎቻችን ፡ ሳንወድ ፡ በግድ ፡ እየጮሀን ፡ ሄደን ፡ እጁን ፡ ያዝነው ።

«ምን ፡ ማድረግዎ ፡ ነው? አብደዋል ፡ እንዴ?» እያልን ፡ እንጮህበት ፡ ጀመር ።

እጁን ፡ ከሽጉጡ ፡ እያነቃነቀ ፡ በዝግታ ፡ ድምጽ ፤ «ከቡራን ፡ ሆይ! ከናንተ ፡ መሃከል ፡ ሃያ ፡ መሐለቅ ፡ ወርቅ ፡ የሚከፍለኝ ፡ ማነው?» ሲል ፡ ጠየቀ ።

ሁሉም ፡ ተደናግጠው ፡ ወደኋላ ፡ አፈገፈጉ ። ቩሊች ፡ ወደሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ገብቶ ፡ ጠረጴዛው ፡ አጠገብ ፡ ቁሜ ፡ አለ ። ሌሎቻ ችንም ፡ ተከትለነው ፡ ገባን ። የጠረጴዛውን ፡ ዙርያ ፡ ከበን ፡ እንደንቀመጥ ፡ ምልክት ፡ ሰጠን ። እኛም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንዳች ፡ ምስጢራዊ ፡ ኃይል ፡ በላያችን ፡ ሰለሰፈረብን ፡ ምንም ፡ ሳናጉረመርም ፡ ትዕዛዙን ፡ ፈጸምንለት ። በበኩሌ ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ በአንክሮ ፡ ስመለከ ተው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳያደናግጥ ፡ በልብ ፡ በራድነት ፡ አፀፋውን ፡ መለሰልኝ ። እነዛም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በተንጠለጠለ ፣ ባርኔጣ ፣ ላይ ፣ ተኮሰ ። ሽጉጡ ፣ ተተኮሰ ፤ በሞሱም ፣ ቤቱ ፣ ተሞላ ። ጭሱ ፣ ካለፈም ፣ በኋላ ፣ ባርኔጣው ፣ መውደቁን ፣ አየን ። ልክ ፣ የባርኔጣው ፣ መካከል ፣ በጥይት ፣ ተበስቶ ፣ አየን ፤ አልፎም ፣ ግድግዳው ፣ በጥይት ፣ ተቦርቡሯል ።

ለሶስት ፣ ደቂቃ ፣ ያህል ፣ ግንም ፣ ከመካከላችን ፣ የተነፈሰ ፣ የለም ። ቩሊችም ፣ በኩራት ፣ ገንዘቤን ፣ ከቦርሳው ፣ ውስጥ ፣ አስገባ ።

በመጀመሪያ ፣ ጊዜ ፣ ጥይቱ ፣ ለምን ፣ እንደ ከሸፈ ፣ ብዙ ፣ ምክንያቶች ፣ ተደረደሩ ። እንዳንዶቹ ፣ ጥይት ፣ ያልተተኮሰው ፣ በመጠቀሚያው ፣ ተይዞ ፣ ስለነበረ ፣ ነው ፣ ይላሉ ። ሌሎቹ ፣ በሹክሹክታ ፣ የመጀመሪያው ፣ ጥይት ፣ የከሸፈው ፣ ባሩዱ ፣ እርጥብ ፣ ስለነበረ ፣ ነው ፣ ይላሉ ። በኋላ ፣ ግን ፣ የተተኮሰው ፣ ቩሊች ፣ እዲስ ፣ ዱረቅ ፣ ባሩድ ፣ ስለጨመረበት ፣ ነው ፣ ይላሉ ። እኔ ፣ ግን ፣ ዓይኔን ፣ ከመጀመሪያው ፣ ጀምሬ ፣ ከግንባሩ ፣ ከተደቀነው ፣ ሽጉጥ ፣ ላይ ፣ ስላላነሳሁት ፣ የሁለተኛው ፣ ግምት ፣ ስህተት ፣ መሆኑን ፣ አረጋግጥሁላቸው ።

«በእውነቱ ፣ የቁማርተኛ ፣ እድል ፣ አለዎት ፡» ስል ፣ ቩሊችን ፣ ነገርሁት ።

«ይህ ፣ መቼም ፣ በሕይወቴ ፣ ሙሉ ፣ ለመጀመሪያ ፣ ጊዜ ፣ ያጋጠመኝ ፣ እድል ፣ ነው ። ከግ

ይህ ፣ ግለቂያ ፣ የሌለው ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ እጅ ፣ እጅ ፣ ብሎኝ ፣

«ይስሙኝ! ወይ ፣ ይተኩሱ ፣ ካለዚያም ፣ ሽጉጡን ፣ ከቦታው ፣ ያንሩት ፣ ሄደን ፣ እንተኛበት ፡» አልሁት ።

«እውነት ፣ ነው ፣ ሄደን ፣ እንተኛ ፡» በማለት ፣ አብዛኞቹ ፣ ሐሳቤን ፣ ደገፉት ።

ቩሊች ፣ የሽጉጡን ፣ አፈ ፣ ሙዝ ፣ በግንባሩ ፣ ደቅኖ ፣ «ከቡራን! ከወንበሮቻችሁ ፣ እንዳት ነቃነቁ ፡» አለን ። ሁላችንም ፣ ተደናገጥን ።

ቩሊች ፣ ንግግሩን ፣ በመቀጠል ፣ «ክቡር ፣ ፔቾሪን ፣ እንድ ፣ ካርታ ፣ ያንሱና ፣ ወደላይ ፣ ይወርውሩት ፡» አለኝ ።

አሁን ፣ ላስታውሰው ፣ ያገኘሁት ፣ ካርታ ፣ ባለልብ ፣ ሲሆን ፣ ከጠረጴዛው ፣ እንስቼ ፣ ወደላይ ፣ ወረወርሁት ። በድንጋጤ ፣ ትንፋሻችን ፣ ቁርጥ ፣ ቁርጥ ፣ እያለ ፣ ውጤቱን ፣ ለማወቅ ፣ በዓይናችን ፣ ከሽጉጡ ፣ እንስተን ፣ ወደታች ፣ የምትወርድዋን ፣ ካርታ ፣ መመልከት ፣ ጀመርን ። ካርታዋ ፣ ልክ ፣ የጠረጴዛውን ፣ ክፈፍ ፣ ስትነካ ፣ ቩሊች ፣ የሽጉጡን ፣ ምላጭ ፣ ሳበው ፣ ሆኖም ፣ ከሸፈ ።

«የፈጣሪ ፣ ክብሩ ፣ ይሰፋ ፣ ጥይት ፣ የለውም ፣ ናሯል ፡» የሚሉ ፣ ብዙ ፣ ድምጾች ፣ አስተጋቡ ።

«እስቲ ፣ እኮ ፣ ያግሙን ፣ እናያለን ፣ በማለት ፣ ሽጉጡን ፣ ሌላ ፣ ጥይት ፣ አንተርሶ ፣ ከመሰኩቱ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ንኛውም ፡ የካርታ ፡ እድል ፡ ይህ ፡ በብዙ ፡ ይሻላል ።»

«እያጋውስ?»

«የእንድ ፡ ሰው ፡ እድል ፡ አስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ ፍልስፍና ፡ ማመን ፡ ጀመሩ ፡ እንዴ?»

«አምናለሁ ፡ ለምን ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አላውቅም ፡ ወደዚች ፡ ዓለም ፡ የመጡት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ለመሞት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ቀድሞ ፡ አስቤ ፡ ነበር ...»

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ በማይለሽነት ፡ ሽጉጥ ፡ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ደቅኖ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ባሁኑ ፡ አነጋገሩ ፡ አለመደሰቱን ፡ ለማየት ፡ ቻልሁ ።

«እንግዲህ ፡ በቃዎት ። ውርርዱ ፡ ቀድሞ ፡ አልፏል ። ያሁኑ ፡ አነጋገር ፡ ቦታውን ፡ የጠበቀ ፡ አያደለም ።» ካለኝ ፡ በኋላ ፡ ባርኔጣውን ፡ ይዞ ፡ ወጣ ። ለእኔ ፡ በእውነት ፡ ልዩ ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ ታየኝ ። ይህም ፡ እውነተኛ ፡ ማንት ፡ ነው ።

ትንሽ ፡ እንደቆየን ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደቤታቸው ፡ ተበታተኑ ። ስለ ቩሊችም ፡ ግራ ፡ የገባ ፡ ተማባር ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ የግል ፡ አስተያየታቸውን ፡ ከመሰንዘር ፡ አልተቆጠቡም ። ያለኔ ፡ እርዳታ ፡ ሌላ ፡ አጋጣሚ ፡ የማያገኝ ፡ ያመለከ ፡ ሕያውነቱን ፡ ለማጥፋት ፡ ከሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በመወራረዴ ፡ ሁሉም ፡

ባንድ ፡ ድምጽ ፡ «እራስ ፡ ወዳድ ፡» በማለት ፡ ሳያወግዙኝ ፡ አልቀሩም ።

በነዚያ ፡ የሰው ፡ ዱካ ፡ በሌለባቸው ፡ መንገዶች ፡ አገሪሚ ፡ ወደቤቱ ፡ ሄድኩ ። ወደፍም ፡ እሳት ፡ የተሳችዋ ፡ ጨረቃ ፡ በወጣ ፡ ገቡ ፡ የቤት ፡ ጣራ ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ ጀምራለች ። ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ የጠራ ፡ ጨለማ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ከዋክብቱ ፡ በፀጥታ ፡ አሸብር ቀው ፡ ይታያሉ ። የድሮ ፡ ጠቢባን ፡ የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ በምናደርገው ፡ የመሬት ፡ ግጭት ም ፡ ሆነ ፡ ለሰብአዊ ፡ መብት ፡ በሚደረገው ፡ ትግል ፡ ላይ ፡ ተሳታፊዎች ፡ ይሆናሉ ፡ የሚሉትን ፡ እንጋገር ፡ ሳስታውስ ፡ በሳቅ ፡ ፈነዳሁ ። በጠቢባን ፡ አነጋገር ፡ የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ለጦርነታቸውና ፡ ለድል ፡ እድራጊነታቸው ፡ ብቻ ፡ ያበራሉ ፡ ብለው ፡ የሚያስቧቸው ፡ ከነሱ ፡ ሞት ፡ ጋር ፡ ፍቅራቸውና ፡ ተስፋቸው ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ተንከባካቢ ፡ እጥቶ ፡ እንደቀረ ፡ እሳት ፡ አብሮ ፡ ቢጠፋም ፡ እነሆ ፡ ዛሬም ፡ ብርሃናቸውን ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ይለግሳሉ ። ይህም ፡ ሆኖ ፡ እኛ ፡ ቁጥር ፡ ሥፍር ፡ የሌላቸው ፡ የሰማይ ፡ ዓለማት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባይናገሩ ፡ ለዘላለም ፡ በቅፍር ፡ ዓይን ፡ ያዩናል ፡ ብለው ፡ ስለሚያምኑ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ የመንፈስ ፡ ጥንካሬ ፡ ይሰማቸዋል ። የተረገምን ፡ የነሱ ፡ ተከታዮች ፡ የሆንን ፡ ነው ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እኛ ፡ ግን ፡ ዓለምን ፡ ያለእምነት ፤ ያለኩራት ፤ ያለደስታ ፤ ያለሐዘን ፤ የምንዞር ፤ የማይቀረውን ፡ ፍጻሜ ፡ ስናስብ ፡ ልባችንን ፡ ከሚያሸማቅቀው ፡ ፍርሃት ፡ በስተቀር ፡ ለትልቅ ፡ መስዋእትነት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ደህንነት ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ደስታ ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ የግል ፡ ፍላጐታችንን ፡ ለማርካት ፡ አንችልም ። አያቶቻችን ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ያልተጨበጠ ፡ ተስፋ ፡ እንኳ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ከአንዱ ፡ የተሳሳተ ፡ ሐሳብ ፡ ወደሌላው ፡ እንደሚያመሩ ፡ ሁሉ ፡ እኛም ፡ በማይለወጥ ፡ ከአንድ ፡ ጥርጣሬ ፡ ወደሌላ ፡ ስንሸጋገር ፡ አለን ።

ይሁንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ብዙ ፡ ሐሳቦች ፡ በጭንቅላቴ ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ቆየሁ ። ላልተጨበጡ ፡ እሙን ፡ ላልሆኑ ፡ ሐሳቦች ፡ ግድ ፡ ስለሌለኝ ፡ ችላ ፡ ብዬ ፡ ተውኋቸው ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሐሳቦች ፡ የት ፡ ያመራሉ? በወጣትነት ፡ ዘመኔ ፡ አላሚ ፡ ነበርሁ ። እረፍት ፡ የሌለው ፡ ሕልሜን ፡ የሚሥላቸውን ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ እንደ ፡ ብራህ ፡ የሆነትን ፡ ሥዕሎች ፡ መጸበስ ፡ እወድ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ እገኛሁ ፤ ያተረፍሁት ፡ ከሌሊት ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ የሚገኘውን ፡ ሐዘንና ፡ ድካም ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓለ ፡ በረሃ ፡ ትግል ፡ ውስጥ ፡ ለጥሩ ፡ ሕይወት ፡ አሰራሳር ፡ የሆነውን ፡ ውስ

ጣዊ ፡ ሞታት ፡ ስሜቴንና ፡ ቋሚ ፡ ፍላጐቴን ፡ አጠፋሁ ። በሐሳቤ ፡ የኖርሁትን ፡ ኑሮ ፡ በእውን ፡ መኖር ፡ ስጀምር ፤ ልክ ፡ እንደማያረካ ፡ ትልት ፡ መጽሐፍ ፡ ሰልቺና ፡ አስቀያሚ ፡ ሆኖ ፡ ታየኝ ።

የምሽቱ ፡ ድርጊት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ስሜት ፡ ከማሳደሩም ፡ በላይ ፡ አድክሞኛል ። የአንድ ፡ ሰው ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ አስቀድሞ ፡ ስለመወሰኑ ፡ ጉዳይ ፡ ወላዋይ ፡ እቋም ፡ ነበረኝ ። ያን ፡ ቀን ፡ ግን ፡ በደንብ ፡ አመንሁበት ። ማስረጃው ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የጥንት ፡ አባቶቻችን ፡ ምርምር ፡ ቀደም ፡ ስል ፡ ብሳለቀበትም ፡ በዚያኑ ፡ ለት ፡ የነሱን ፡ እስተሳሰብ ፡ ወርሼ ፡ ዋልሁ ። በጊዜውም ፡ እራሴን ፡ በመግታት ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አደገኛ ፡ መንገድ ፡ የጀመርሁበትን ፡ ጉዞ ፡ እቁሜ ፤ አንድን ፡ ነገር ፡ በጭፍን ፡ ወዶ ፡ በሙሉ ፡ መቀበል ፤ ካለዚያም ፡ በሙሉ ፡ ማውገዝ ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ መቀበሌን ፡ አቆምሁ ። የሚታፈዚክስን ፡ ሕግ ፡ እሽቀንጥራ ፡ ጥዬ ፡ ከእግሬ ፡ ሥር ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ ማየት ፡ ጀመርሁ ። በወፍራምና ፡ በለስላሳ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ልቆም ፡ ስል ፡ ልወድቅ ፡ ነበር ፤ ጥንቅቁም ፡ ጊዜ ያዊ ፡ ነበር ። ጉንበስ ፡ አልሁ ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ አብርቷል ። ከፊት ፡ ለፊቱም ፡ አንድ ፡ አሣማ ፡ በጉራዴ ፡ ከሁለት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ ፡ ስለነበር ፡ «ደህና ፡ እደሪ ፡ ናስትያ ፡» ብያት ፡ ባጠገብዋ ፡ አለፍሁ ። መልስ ፡ ልትሰ ጠኝ ፡ ፈለጋ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ በከባዱ ፡ ተን ፍሳ ፡ ዋጠችው ።

የክፍሉን ፡ በር ፡ ዘግቼ ፡ ሻማዬን ፡ አብርቼ ፤ ባልጋዬ ፡ ላይ ፡ ተዘረርሁ ። እንቅልፍ ፡ ከድ ሮው ፡ ዘግየት ፡ ብሎ ፡ ወሰደኝ ። በእንቅል ፍ ፡ ዓይኖቼም ፡ ሲከደኑ ፡ ነጋግቶ ፡ ነበር ። ግን ፡ ያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ እንቅልፍ ፡ አልተኛ ፡ ሲለኝ ፡ አሥር ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ሁለት ፡ ጡንቻ ዎች ፡ መስኩቴን ፡ ሲደበድቡ ፡ ነቃሁ ። ዘልዬ ፡ ብድግ ፡ አልሁና ፡ «ምን ፡ ነገር ፡ ሆነ?» ብዬ ፡ ጠየቅሁ ። «ተነስ! ልበስ!» የሚሉ ፡ ድምጾች ፡ ተሰሙኝ ። እኔም ፡ በፍጥነት ፡ ለብሼ ፡ ወጣሁ ። ሊቀስቅሱኝ ፡ የመጡት ፡ ሶስት ፡ መኮንኖች ፡ «ምን ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃለህ?» አሉኝ ። ሶስ ቱም ፡ እንደሞት ፡ እንደራሱ ፡ ገርጥተው ፡ ነበር ።

«ምን?»

«ቭሊች ፡ ተገደለ ።»

በድን ፡ ሆነሁ ።

«እም! ተገድሎአል ፤ ቶሎ ፡ እንሂድ ፡» አሉኝ ።

«ወዴት?»

«መንገድ ፡ ላይ ፡ እንነግርሃለን ።»

ተያይዘን ፡ ሄድን ። የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ አጫወቱኝ ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ እያይ

ተሠንጥቃ ፡ አየሁ ። ልክ ፡ ግና ፡ አሣማውንም ፡ እንዳየሁ ፡ ሁለት ፡ ካዛኮች ፡ ከመንገዱ ፡ ገን ፡ እየሮጡ ፡ ወደኔ ፡ መጡ ። አንደኛው ፡ ወደኔ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፤ አንድ ፡ የሠከረ ፡ አሣማ ፡ የሚያ ሳድድ ፡ ካዛክ ፡ አይቼ ፡ እንደሆነ ፡ ጠየቀኝ ። እኔም ፡ ካዛኩን ፡ ያላየሁ ፡ መሆኔን ፡ ከገለጽኩላ ቸው ፡ በኋላ ፡ የውንብድናው ፡ ውጤት ፡ የሆነች ውን ፡ ያችን ፡ የሞተች ፡ አሣማ ፡ አሳየኋቸው ።

«ወሮበላ! ያንን ፡ አረቂውን ፡ ሲጠጣ ፡ ባጠ ገቡ ፡ ቆሞ ፡ የቆየውን ፡ እየቆራረጠ ፡ ያል ፋል ። ዬሬሜኢች! እንከተለው ፡ ፈልገን ፡ ማሰር ፡ አለብን ። ያለበለዚያ ...» በማለት ፡ ሁለተኛው ፡ ካዛክ ፡ ተናገረ ።

ይህን ፡ ተባብለው ፡ ካዛኮቹ ፡ ሄዱ ፤ እኔም ፡ በጥንቃቄ ፡ መንገዴን ፡ ቀጥዬ ፡ በሰላም ፡ ከቤቱ ፡ ገባሁ ።

የምኖረው ፡ ገና ፡ ማዕረገን ፡ ካላገኘው ፡ ሽማግሌ ፡ ዕጩ ፡ መኩንን ፡ ጋር ፡ ነው ። ለጥ ሩ ፡ ጠባዩና ፡ ለቆንጆ ፡ ልጁ ፡ ለናስትያ ፡ ስል ፡ አፈቀርሁት ።

ናስትያ ፡ እንደወትሮዋ ፡ እስክመጣ ፡ ያንን ፡ ወፍራም ፡ ካፖርትዋን ፡ ያርባ ፡ ከበር ፡ ቁሜ ፡ ብላ ፡ ትጠብቀኝ ፡ ነበር ። በብርድ ፡ ሰማያዊ ፡ በሆኑ ፡ ሽጋ ፡ ከንፈሮቿ ፡ ላይ ፡ የፈጠረቻዋ ፡ ብርሃን ፡ አርፎበታል ። እኔን ፡ ስታያ ፡ ፈገግ ፡ አለች ፤ ግን ፡ ጭንትላቱ ፡ በሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ተመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘው ፡ ከመሞቱ ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ከሞ
ት ፡ አፋፍ ፡ የዳነበትን ፡ ታምር ፡ ሞምር ፡ እያወ
ሩኝ ፡ መንገዳችንን ፡ ቀጠልን ። ቩሊች ፡ በዚያ ፡
ጥቅጥቅ ፡ ባለ ፡ ጨለማ ፡ ለብቻ ፡ በሚንሸራ
ሸርበት ፡ ወቅት ፡ ያ ፡ አሣማውን ፡ ያረዳት ፡
ካዛክ ፡ አጋጠመው ። ቩሊች ፡ ድንገት ፡ ቆሞ ፤
ዉማንን ፡ ነው ፡ የምትፈልገው ፡ ወንድምህ
በማለት ፡ ካዛኩን ፡ ባይጠይቀው ፡ ኖሮ ፡ ካዛኩ ፡
ዝም ፡ ብሎ ፡ ባለፈው ፡ ነበር ። ካዛኩም ፡ መልሶ ፤
«የምፈልገው ፡ አንተን ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ ከትክ
ሻው ፡ እስከልቡ ፡ ሰነጠቀው ። ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡
ያሳድዱ ፡ የነበሩት ፡ ሁለት ፡ ካዛኮች ፡ ከቦታው ፡
ደርሰው ፡ የቆሰለውን ፡ ቩሊችን ፡ እነሱት ።
ቁስለኛውም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሞት ፡ አፋፍ ፡
ላይ ፡ ሆኖ ፡ የመጨረሻ ፡ ቃላቱን ፡ ዉእውነቱን ፡
ነው ፡» ሲል ፡ ተንፈሰ ። የዚህ ፡ ቃሳት ፡ ፍች ፡
የሚገባኝ ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የተሰነዘረውም ፡
ለኔ ፡ ነው ፡ ሳልወድ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ እጣ ፡ ላይ ፡
ተንብቼበት ፡ ነበር ። አልተሳሳትሁም ፤ በው
ነትም ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ የሞትን ፡ ማኅተም ፡ በግ
ልጽ ፡ አንብቤ ፡ ነበር ።

ገዳዩም ፡ ከሠፈሩ ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ ባንዲት ፡
ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ዘግቶ ፡ ቁጭ ፡ ብሏል ።
ሁላችንም ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ መድጐጃዋ ፡ እመ
ራን ። ብዙም ፡ ሴቶች ፡ እያለቀሱ ፡ መጀዚህ ፡
አድራሻ ፡ ያገኙናል ። አንዳንድ ፡ የዘገዩ ፡ ካዛ

ኮች ፡ ከቢታቸው ፡ ወጥተው ፡ ጐራዴአች
ውን ፡ መዘው ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተወናጭ
ፈው ፡ ያሮጣሉ ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ አስደ
ንጋጭ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ስንደርስ ፡
በርዋና ፡ መስኩትዋ ፡ በተዘጋው ፡ በዛች ፡
ጐጆ ፡ ዙሪያ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡
ነበር ። መኩንኖችና ፡ ካዛኮች ፡ የጋለ ፡ ክርክር ፡
ይዘው ፡ ነበር ። ሴቶች ፡ በሐዘን ፡ ተውጠው ፡
ቁመዋል ። ከመካከላቸው ፡ ሐዘን ፡ ይበልጥ ፡
በስበራት ፡ በእንዲት ፡ አሮጊት ፡ ላይ ፡ ዓይኔ ፡
አረፈ ። በአንድ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፤ ክርኖቿን ፡
በጉልበቶቿ ፡ ላይ ፡ ጥላ ፤ በእጆቿ ፡ መዳፎች ፡
ላይ ፡ አገጯን ፡ አስደግፋ ፡ ዙርምት ፡ ብላ ፡
ተቀምጣለች ። የገዳዩ ፡ እናት ፡ መሆንዋ ፡ ነው ።
ከንፈሮቿ ፡ በየጊዜው ፡ ይነቃነቃሉ ። ፀሎት ፡
ይሁን ፡ እርግማን ፤ ማን ፡ ያውቀዋል?

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ አድርጐ ፡
ገዳዩን ፡ መያዝ ፡ ያስፈልጋል ። ሆኖም ፡ በመጀ
መሪያ ፡ ማን ፡ ይግባ?

ወደመስኩቱ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ በቀዳዳ ፡ መመ
ልከት ፡ ጀመርሁ ። ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በቀኝ ፡
እጁ ፡ ሽጉጡን ፡ ይዞ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተም
በልብሎ ፡ ተኝቷል ። በደም ፡ የተነከረውም ፡
ጐራዴው ፡ ካጠገቡ ፡ ተዘርግቷል ። ፊቱ ፡ አ
መድ ፡ መስሏል ። እነዚያም ፡ ዓይኖቹ ፡ በፍ
ርሃት ፡ ይቅበዘበዛሉ ። እንዳንዴ ፡ የትላንት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባትም ፡ እርስዎን ፡ ይሰማዎት ፡ ይሆናል ።
እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ድርጊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቆጣ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ መኳንንት ፡ ከቆሙ ፡ እነሆ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሆናቸው ፡» አሳት ።

አሮጊቷ ፡ እናት ፡ የሻምበሉን ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ ካየች ፡ በኋላ ፡ በአምቢታ ፡ እራስዋን ፡ ነቀነቀች ።

ወዲያውኑ ፡ የካዛኩ ፡ የሻምበል ፡ ወደሻለቃው ፡ ሂዶ ፡ «ቫሲል ፡ ፔትሮቪች! ይህ ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ በሰላም ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ፤ አውቀዋለሁ ። በሩን ፡ የሰበርንበት ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይፈጅብናል ። እንዲገደል ፡ ትዕዛዝ ፡ ቢያስተላልፉ ፡ አይሻልም? በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቀዳዳ ፡ አለ ፡» አለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሐሳብ ፡ ጭንቅላቴን ፡ መታኝ ፤ እንደቭሊች ፡ እኔም ፡ እጣዬን ፡ ለመፈተን ፡ ፈለግሁ ።

«ይቆዩ! እኔ ፡ ከንሕይወቱ ፡ እይዝልዎታለሁ ፡» ብዬ ፡ የሻለቃውን ፡ ጠየቅሁት ። ከዚያም ፡ ወደ ሻምበሉ ፡ ዞር ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ምልክት ፡ ስሰጣቸው ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ገብተው ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩን ፡ የሚይዙ ፡ ሶስት ፡ መታደሮች ፡ እንዲያዘጋጅልኝ ፡ ከጠየቅሁት ፡ በኋላ ፡ ልቤ ፡ ሲፈራ ፡ ሲቸር ፡ በጉጅሞ ፡ ዙርያ ፡ ሄጂ ፡ ከመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ቆምሁ ።

ድርጊቱን ፡ እንዳስታወስ ፡ ሁሉ ፡ በሐዘን ፡ እራሱን ፡ በጅቹ ፡ ይይዛል ። ሁኔቱውን ፡ ሳየው ፡ ቆራጥነት ፡ ስላጣሁበት ፡ የሻለቃውን ፡ ሄጂ ፡ ከስካሩ ፡ ሳይነቃ ፡ አሁኑኑ ፡ መያዙ ፤ ከኋላው ፡ የበለጠ ፡ ስለሚቀል ፡ ካዛኮቹ ፡ በሩን ፡ ሰብረው ፡ እንዲይዙት ፡ እንዲያደርግ ፡ ነገርሁት ።
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የካዛክ ፡ የሻምበል ፡ ወደ በሩ ፡ ተጠግቶ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩን ፡ ተጣራ ። ከውስጡ ፡ ያለው ፡ ካዛክም ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።

«ወንድሜ ፡ ዬፊሚች! ታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተሃል ፡ ከእንግዲህ ፡ የምታደርገው ፡ ነገር ፡ የለህም ። እጅህን ፡ ስጥ ፡» ሲል ፡ የካዛኩ ፡ ሻምበል ፡ ጠየቀው ።

«እጄን ፡ አልሰጥም ፤ አሻፈረኝ ፡» በማለት ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ መለሰ ።

«ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይያረብህ ፤ አንተ ፡ አረመኔ ፡ ቸርኬስ ፡ አይደለህም ፤ ያመንህና ፡ የተጠመቅህ ፡ ክርስትያን ፡ ነህ ። እንዴ ፡ ተላስ ተሃል ። ከእድልህ ፡ አምልጠህ ፡ ልትሮጥ ፡ አትችልም ።»

«እጄን ፡ አልሰጥም ፡» ብሎ ፡ ካዛኩ ፡ በጩኸት ፡ ከመለሰ ፡ በኋላ ፡ ሽጉጡን ፡ ሲያቀባበል ፡ ተሰማ ።

ካዛኩ ፡ ወደነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ አሮጊት ፡ እናቱ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡

«ያለሙ ፡ እናት! ልጅዎን ፡ ያነጋግሩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ስማ! እንተ ፡ ወሮበላ ፡ ትቀልድብናለህ? እንተን ፡ መያዝ ፡ እቅቶን ፡ መሰለህ?» በማለት ፡ የሻምበሉ ፡ በከፍተኛ ፡ ድምጽ ፡ በሩን ፡ ይደበድብ ፡ ገባ ። በቀጸጸ ፡ እሾልኬ ፡ ካዛኩን ፡ ስመለከተው ፡ ከጉን ፡ አጠቃለሁ ፡ የሚል ፡ ስጋት ፡ እንደሌለው ፡ ተረዳሁ ። ከዚያም ፡ በድንገት ፡ መስኮቱን ፡ በርግጂ ፡ ከፍቼ ፡ ጭንቅላቴን ፡ አስቀድሜ ፡ ወደሱ ፡ ተወረወርሁ ። የተኮሰው ፡ ሽጉጥ ፡ በጆሮ ፡ ግንዴ ፡ አልፎ ፡ የትከሻዬን ፡ ጉፈር ፡ ሠርፎት ፡ ሄደ ። የሽጉጡ ፡ ጪስ ፡ ከጠላቴ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጐራዴ ፡ እንዳያይ ፡ ረዳኝ ። እጆቹን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጌ ፡ ከመያዜ ፡ ወታደሮች ፡ በሩን ፡ ሰብረው ፡ ገቡ ። ሶስት ፡ ደቂቃም ፡ ባልሞላ ፡ ውስጥ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ እጁን ፡ የፊጥኝ ፡ ታስሮ ፡ በዘበኞች ፡ ተጓዘ ። ወዲያውም ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ወደየቤቱ ፡ ተበታተነ ። መኩንኖቹም ፡ አመሰገኑኝ ፡ በእውነትም ፡ መመስገን ፡ ይገባኛል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ በአጣው ፡ ላያምን ፡ ይችላል? ይህስ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ነገር ፡ ያምን ፡ አያምን ፡ እንደሆነ ፡ በምን ፡ ያውቃል? ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስህተትን ፡ ወይንም ፡ ሰሚታችንን ፡ የሚመስለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እምነት ፡ አድርገን ፡ እንቆጥረዋለን ። እኔ ፡ በዘኩሉ ፡ ግንኛውንም ፡ ነገር ፡

መጠራጠሩ ፡ ይሻለኛል ። ይሀንም ፡ የመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ ቆራጥ ፡ ከመሆን ፡ አያግደኝም ። እንዲያውም ፡ ከፊቱ ፡ የሚጠብቀኝን ፡ ነገር ፡ ሳላውቅ ፡ ሳላወላውል ፡ ወደፊት ፡ እንድራመድ ፡ ያደርገኛል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በመጨረሻ ፡ ከሞት ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ ሊያጋጥመህ ፡ አይችልም ። ከሞት ፡ የሚያመልጥ ፡ ደግሞ ፡ ማንም ፡ የለም ።

ወደሠፈሩ ፡ ስመለስ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪችን ፡ አግኝቸው ፡ ስላየሁትና ፡ ስለሰማሁት ፡ በሙሉ ፡ አወጋሁት ። የአንድ ፡ ሰው ፡ የወደፊት ፡ እጣ ፡ እስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ ስለሚለው ፡ ፍልስፍናም ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ጠየቅሁት ። በመጀመሪያ ፡ ማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ አነጋገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አልገባውም ። እኔም ፡ የሚቻለኝ ፡ የአነጋገሩን ፡ ምንነት ፡ ለማስረዳት ፡ ሞከርሁኝ ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ራሱን ፡ ነቅንቆ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

«እምነ ቁም ፡ ነገር ፡ ያዘለ ፡ ቀልድ ፡ ነው ። በነገራችን ፡ ላይ ፡ የነዚህ ፡ የአዚያቲኮች ፡ ሽጉጥ ፡ ዘይት ፡ ከሌለው ፡ ይዝጋል ። ምላጩም ፡ በጎይል ፡ ካልተሳበ ፡ ይከሽፋል ። የቼርከሶችም ፡ ጠመንጃ ፡ ደስ ፡ አይለኝም ። ለኛም ፡ አይሆንም ፤ ሰደፉ ፡ አሞር ፡ ስለሆነ ፡ ካልተጠነቀቅህ ፡ ተመልሶ ፡ አፍንጫህን ፡ ይወግርሃል ። ጐራዴአችው ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ናቸውነ»

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ካሰበ ፡ በኋላ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«አምላ ያ ፡ ምስኪን ፡ ሰውዬ ፡ ያሳዝነኛል ። ያን ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከዚያ ፡ ሠካራም ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ለምንድነው ፡ ለመነጋገር ፡ የቆመው?.. የእጣ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ነው ።»

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ከማክሲም ፡ ማክሲሞቪች ፡ ምንም ፡ ልሰማ ፡ አልቻልሁም ፡ ለሚታፈዚክስ ፡ ክርክሮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ያንታ ፡ የለውም ።

ተፈጸመ ።

እ. ኤ. አ. ፲፰፻፴፯ — ፲፰፻፴፱ ዓ. ም.

መዝጊያ ።

ፑሽኪንና ፡ ሌርሞንቶቭ ፡ በሩሲያ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እኩል ፡ የሚጠሩ ፡ ስሞች ፡ ናቸው ። ሁለቱም ፡ የተለየ ፡ ተሰጥዎ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ፡ ሁለቱም ፡ የ፲፱ ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ የሩሲያን ፡ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ሕይወት ፡ ጥልቅ ፡ በሆኑ ፡ በጽሑፎቻቸው ፡ የገለጹ ፡ ዝነኛ ፡ ደራሲዎች ፡ ናቸው ። ፑሽኪን ፡ የተወለዱት ፡ በ፲፯፻፺፱ ዓ. ም. ነው ። ሥነ ፡ ጽሑፋቸው ፡ መሠረቱን ፡ የጣለው ፡ በአገራቸው ፡ ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ በገነነበት ፤ የሩሲያ ፡ ሕዝብ ፡ በ፲፰፻፲፪ ዓ. ም. የናፖሊዮንን ፡ ወረራ ፡ ድል ፡ መቶ ፡ በመለሰበት ፤ የሕዝቡ ፡ የጀግንነት ፡ ወኔው ፡ በይበልጥ ፡ በተፋፋመበት ፤ ሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ የዲሞክራቲክ ፡ ለውጥ ፡ በተጠማበት ፡ ወቅት ፡ ነው ።

ሌርሞንቶቭ ፡ የተወለዱት ፡ ፲፭ ዓመት ፡ ከፑሽኪን ፡ በኋላ ፡ ነው ። (በ፲፰፻፲፬ ዓ. ም. እ. አ. አ.) በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ያሉበት ፡ ዘመን ፡ ሌላ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ በሕዝቡ ፡ ውስጥ ፡ የተያያዘው ፡ የለውጥ ፡ ስሜት ፡ ተዝቅዞ ፡ ከባርነት ፡ ቀንበር ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሳቆ ፡ የነጻነት ፡ ሜሶላንሜዶል ፡ ለማየት ፡ የነበረ
ው ፡ ፍላጐት ፡ ሁሉ ፡ ተስፋ ፡ ቢስ ፡ ሆኖ ፡
ነበር ። ሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ያገኘው ፡
ክብሩና ፡ ነጻነቱ ፡ ተነካበት ። የቀሰቀሰውም ፡
የሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ንቅናቄ ፡ መደቀ ።

እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ምስቅልቅል ፡ ጊዜ ፡ የሴር
ሞንቶቭ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ብቅ ፡ አለ ። የመጽ
ሐፉ ፡ እርእስት ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ እንባቢውን ፡
የመማረክ ፡ ኃይል ፡ ነበረው ። «የዘመናችን ፡
ሰው ፡ » መቼም ፡ እንደሚታወቀው ፡ ከዘመ
ናችን ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ የሚወሰዱ ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ
ዎች ፡ ይኖራሉ ። ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የዘመ
ናችን ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው?

ስሙ ፡ ፔቾሪን ፡ ይባላል ። የተማረ ፡ ብልህ ፡
ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ወጣ
ት ፡ ሐብታም ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጓደኝ
ነቱንና ፡ ፍቅሩን ፡ ይፈልጉታል ። ይህም ፡ ሆኖ ፡
እድል ፡ ከፔቾሪን ፡ ጋር ፡ ያጋጠመቻቸው ፡
ሰዎች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ ይሠቃያሉ ፡ ነለዚያም ፡
ይሞታሉ ። ብዙውን ፡ ዘመኑንን ፡ ያሳለፈው ፡
ያላንዳች ፡ ዓላማና ፡ ፍላጐት ፡ ነው ። ልቡ ፡
እርሀራሄ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አያውቅም ። ብቸ
ኛና ፡ እድለ ፡ ቢስ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ከቀልድ ፡ አልፎ ፡ እንዴት ፡ የዘመና
ችን ፡ ሰው ፡ ይሆናል? ተልዕ ፡ አያደለም ።
ጸሐፈው ፡ ያለፈበት ፡ የራሱ ፡ የመራራ ፡ ዘመን ፡

ውጤት ፡ ነው ፡ እንጂ ። ለዚህም ፡ ሴርሞንቶቭ ፡ በ
መጽሐፉ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ መልስ ፡ ሰጥቷል ። «የዘ
መናችን ፡ ሰው ፡ የአንድን ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡
አይመክለም ። ያንድ ፡ ትውልድ ፡ መጥፎ ፡
ጠባዮች ፡ በሙሉ ፡ ተጠቃለው ፡ የቀረቡበት ፡
ባሕርይ ፡ ነው ።» በእርግጥ ፡ የደራሲውን ፡
ገለጻ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ መውሰድ ፡ አያስፈልግም ።
እ. ኤ. አ. በ፲፱፻ው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በ፴ኛው ፡
ዓመታት ፡ የነበረው ፡ ክብር ቴ ፡ በሙሉም ፡
እንደፔቾሪን ፡ ነው ፡ ማለትም ፡ ልክ ፡ አይሆ
ንም ። ሴርሞንቶቭ ፡ ግን ፡ በጽሑፋቸው ፡ ላይ ፡
ቁልጭ ፡ አድርገው ፡ ለማሳየት ፡ የፈለጉት ፡
የዘመናቸው ፡ ትውልድ ፡ ካፈራቸው ፡ ውስጥ ፡
እንዳንድ ፡ እቢይ ፡ ጠባዮችን ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡
በሚገባ ፡ ተገልጿል ። ዋናው ፡ ተዋናይ ፡
ፔቾሪን ፡ በዘመኑ ፡ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡
በሐዘን ፡ የተዋጠ ፡ ሰው ፡ ነው ። በምንም ፡
እንዳያምንና ፡ ተስፋ ፡ እንዳያደርግ ፡ እራሱን ፡
በራሱ ፡ አስተምሮታል ። ማንኛውንም ፡ ነገር ፡
በልበ ፡ በራድነት ፡ ለመመልከት ፡ እንዲችል ፡
አድርጐ ፡ እራሱን ፡ ገርቶታል ። በራሱም ፡ እን
ጋገር ፡ «የሞራል ፡ ሽባ ፡» ሆኗል ። ይህ ፡ ሁሉም ፡
ችግር ፡ የፔቾሪን ፡ የራሱ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡
ሳይሆን ፡ ከአካባቢው ፡ የወረሰው ፡ ነው ።
የሩሲያ ፡ ደሞክራት ፡ ሒስ ፡ እቅራቢ ፡ ቤሊንስ
ኪይ ፡ ስለፔቾሪን ፡ ለእንባቢያን ፡ ሲገልጹ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ ፡ ይላሉ ፣ «የሞራል ፡ ሰዎች ፡ ፔቾሪን ፤ ራስ ፡ ወዳድ ፡ የተረገመ ፡ ጨካኝ ፡ በረ ፡ ሞራል ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይቦርቱ ፡ ይሆናል ። እውነታችሁን ፡ ነው ፣ ክቡራን! ታዲያ ፡ ይህ ፡ ምን ፡ ያስገርማል? ምንስ ፡ ያስቆጣችኋል? የጠላችሁት ፡ ስለኃጢአቶቹ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ እናንተ ፡ ከሱ ፡ ይበልጥ ፡ የጠቆረና ፡ አሳፋሪ ፡ የሆነ ፡ ኃጢአት ፡ ተከናንባችኋልና!.. የጠላችሁት ፡ እነዚህን ፡ ኃጢአቶቻችሁን ፡ በታላቅ ፡ ድፍረት ፤ ማንንም ፡ ሳይፈራ ፡ በመናገሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ...» በእርግጥም ፡ የፔቾሪን ፡ ብሔራዊ ፡ ወንድነቱና ፡ ኃይሉ ፡ የሚታየው ፡ «በድፍረት ፤ ሳይፈራ ፡» መናገሩ ፡ ነው ። የኑሮን ፡ አቋም ፡ ለመለወጥ ፡ በሚደረገው ፡ ግምት ፡ ፔቾሪን ፡ በድፍረት ፡ ገብቶ ፡ ይካፈላል ። ባጼ ውንና ፡ የተንኮታኮተውን ፡ የመኳንንት ፡ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ለማየት ፡ እንኳ ፡ ይቀፈዋል ። ዘወትር ፡ በሞራል ፡ ከሱ ፡ በታች ፡ ካሉም ፡ ሰዎች ፡ መለየትን ፡ ይወዳል ። ሕብረተ ፡ ሰቡን ፡ ለመንቀፍ ፡ ሌርሞንቶቭ ፡ የዘመናችን ፡ ሰው ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ ተዋናይ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ዓላማና ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ራቱቱን ፡ በመቅረቱ ፡ ብዙ ፡ ከርከርን ፡ በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓለም ፡ ፈጥሯል ።

አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነቀፋ ፡ ሕብረተ ፡ ሰቡን ፡ በሐሳብ ፡ የሚያናውበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። የሌርሞንቶቭ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ «የዘመናችን ፡ ሰው ፡» በዚያን ፡ ዘመን ፡ ለንበረው ፡ ትውልድ ፡ የሰጠው ፡ አስተዋጽኦ ፡ የሐሳብ ፡ ንቀት ፡ ነበር ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በታተመበት ፡ ወቅት ፡ የጀግኑ ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ሌርሞንቶቭ ፡ የረዥም ፡ ዘመን ፡ ጦርነት ፡ ወደሚካሔድበት ፡ ወደካውካሱስ ፡ በግዞት ፡ ተልከው ፡ ነበር ። የደራሲው ፡ እድል ፡ ከዚህ ፡ የግዞት ፡ ቦታ ፡ ለመመለስ ፡ ሳትችል ፡ ቀረች ። እንደጥሽኪን ፡ ሌርሞንቶቭም ፡ የሞቱት ፡ በፍልሚያ ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፰፻፵ ፯ ዓ. ም. በጀግ ዓመታቸው ፡ ነው ። እንደጥሽኪንም ፡ በዛች ፡ ባጭር ፤ ሐዘን ፡ ጠቅ ፡ ባለበት ፡ የሕይወት ፡ ዘመናቸው ፡ ውስጥ ፡ ለዘመናዊዋና ፡ ለዚያን ፡ ጊዜዋ ፡ የሩሲያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ አስተዋጽኦ ፡ ለማድረግ ፡ ችለዋል ። ሌርሞንቶቭ ፡ እውብ ፡ ድንቅ ፡ የሆኑ ፡ ረጃጂ ምና ፡ አጫጭር ፡ ግጥሞችን ፡ የያዙ ፡ ብዙ ፡ እትሞች ፤ የትያትር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎችንና ፡ ግሩም ፡ የሆኑ ፡ ድርሰቶችን ፡ አበርክተውልን ፡ አልፈዋል ። «መትሲሪ ፡» «ሰይጣን ፡» የተባሉ ፡ ረጃጂም ፡ ግጥሞቻቸው ፡ «ማስካራድ ፡» የተባለው ፡ ድራማቸውና ፡ ይህ ፡ ራሱ ፡ «የዘመናችን ፡ ሰው ፡» የሚለው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰታቸው ፤ በሩሲያ ፡ የጥንታዊ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግራስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጀና ፡ ማሳ
ሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም
ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና
አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል
አድራሻው ፤

21. Zubovsky Boulevard,
Moscow, U.S.S.R.

t.me/OLDBOOKSPDF